Language: Amharic

Book: Genesis

Genesis

Chapter 1

1 እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። 2 ምድርም ቅርፅ የሌላትና ባዶ ነበረች። ጥልቅ የሆነው ስፍራዋም በጨለማ ተውጦ ነበር።
የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃው ላይ ሰፍፎ ነበር። 3 እግዚአብሔርም፦ “ብርሃን ይሁን” አለ፤ ብርሃንም ሆነ። 4 እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ
አየ፤ ብርሃንኑም ከጨለማ ለየው። 5 እግዚአብሔርም ብርሃኑን ‘ቀን’ ጨለማውን ደግሞ ‘ሌሊት’ ብሎ ጠራው። ቀኑ መሸ ሌሊቱም ነጋ አንድ ቀን ሆነ። 6
እግዚአብሔርም፦ “በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን፣ ውሆችንም ይለያዩ” አለ። 7 እግዚአብሔር ጠፈርን አደረገና ከጠፈር በላይና ከጠፈር በታች ያሉትን
ውሆች ለየ። እንደዚያም ሆነ። 8 እግዚአብሔር ጠፈሩን ‘ሰማይ’ብሎ ጠራው። ቀኑ መሸ ሌሊቱም ነጋ ሁለተኛ ቀን። 9 እግዚአብሔር፦ “ከሰማይ በታች ያለው
ውሃ ወደ አንድ ስፍራ ይሰብሰብ፣ ምድሩም ይገለጥ” አለ። እንደዚያም ሆነ። 10 እግዚአብሔርም ምድሩን ‘የብስ’፣ ወደአንድ ስፍራ የተሰበሰበውንም ውሃ
‘ባሕር’ ብሎ ጠራው። ይህም መልካም መሆኑን ተመለከተ። 11 እግዚአብሔር፦ እንደ ዓይነታቸው ዘርን የሚያፈሩ ተክሎችን፣ በውስጣቸው ዘርን ያዘሉ የፍራፍሬ
ዛፎችን እንደዓይነታቸው የሚያፈሩ አዝርዕትን ታብቅል” አለ። እንደዚያም ሆነ። 12 ምድር እንደአይነታቸው የሚያፈሩ አዝርዕትን አበቀለች። ይህም መልካም
እንደሆነ እግዚአብሔር ተመለከተ። 13 ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ ሶስተኛ ቀን ሆነ። 14 እግዚአብሔር፦ “ቀኑን ከሌሊቱ ይለዩ ዘንድ በሰማይ ብርሃናት ይሁኑ።
እነዚህ ብርሃናት የዓመት ወቅቶችን፣ ቀናትንና ዓመታትን የሚለዩ ምልክቶች ይሁኑ። 15 ለምድርም ብርሃን ይሰጡ ዘንድ በሰማይ ላይ የሚገኙ ብርሃናት ይሁኑ”
አለ። እንደዚያም ሆነ። 16 እግዚአብሔር ታላቁ ብርሃን በቀን፣ ታናሹ ብርሃን በሌሊት ይሠለጥኑ ዘንድ ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ። ከዋክብትንም ደግሞ
አደረገ። 17 ለምድርም ብርሃን ይሰጡ ዘንድና 18 በቀንና በሌሊት ላይ እንዲሠለጥኑ እንደዚሁም ብርሃንን ከጨለማ እንዲለዩ በሰማይ አኖራቸው።
እግዚአብሔር ይህ መልካም እንደሆነ ተመለከተ። 19 ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ አራተኛ ቀን ሆነ። 20 እግዚአብሔር፦ “ውሆች በሕያዋን ፍጡራን የተሞሉ ይሁኑ፣
ወፎችም ከምድር በላይ ባለው በሰማይ ጠፈር ይብረሩ” አለ። 21 እግዚአብሔር ታላላቅ የባሕር ፍጥረታትን እንደዚሁም በምድር የሚንቀሳቀሱ፣ በውሆች
ውስጥ የሚርመሰመሱና በክንፎቻቸው የሚበሩ ወፎችን እንደዓይነታቸው ፈጠረ። እግዚአብሔር ይህ መልካም እንደሆነ ተመለከተ። 22 እግዚአብሔርም፦
“ብዙ ተባዙ የባሕርን ውሆች ሙሉአቸው፣ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ” ብሎ ባረካቸው። 23 ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ አምስተኛ ቀን ሆነ። 24
እግዚአብሔርም፦ “ምድር እንደወገናቸው ሕያው ፍጥረታትን ማለትም ከብቶችን፣ በምድር ላይ የሚሳቡትንና የምድር አራዊትን ታስገኝ” አለ። እንደዚያም ሆነ።
25 እግዚአብሔር በየዓይነታቸው የምድር አራዊትን፣ በየዓይነታቸው ማናቸውንም በምድር የሚሳቡትን ፈጠረ። 26 እግዚአብሔርም፦ “ሰውን በመልካችን እንደ
አምሳላችን እንፍጠር፣ ሰዎችም በባሕር ዓሣዎች፣ በሰማይ በሚበሩ ወፎችና በምድር ላይ በሚሳቡ ማናቸውም ተሳቢ ፍጥረቶች ላይ ሥልጣን ይኑራቸው” አለ።
27 እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ፣ በራሱም አምሳል ፈጠረው። ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። 28 እግዚአብሔር ባረካቸው እንደዚህም አላቸው፦ “ብዙ
ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት ግዟትም። በባሕር ውስጥ ባሉት ዓሣዎች፣ በሰማይ ላይ በሚበሩት ወፎችና በምድር ላይ በሚንቀሳቀሱት ማናቸውም ሕያዋን
ፍጥረቶች ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራችሁ” 29 እግዚአብሔርም፦ “እነሆ፣ ምግብ ይሆኑላችሁ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ በውስጣቸው ዘርን ያዘሉ ማናቸውንም
ተክሎችና በውስጣቸው ፍሬ ያላቸውን ማናቸውንም የፍራፍሬ ዛፎች ሰጥቻችኋለሁ። 30 በምድር ላይ ለሚገኙ እንስሳት ሁሉ፣ በሰማይ ለሚበሩ ወፎች ሁሉ፣
እንዲሁም በምድር ላይ ለሚሳቡ ፍጥረታት ሁሉ ማለትም የሕይወት እስትንፋስ ላለበት ማንኛውም ፍጡር ማንኛውም ለምለም ተክል ምግብ እንዲሆናቸው
ሰጥቻለሁ። እንደዚሁም ሆነ። 31 እግዚአብሔር የፈጠረውን ማንኛውንም ነገር ተመለከተ። እነሆ፣ እጅግ መልካም ነበረ። ቀኑ መሸ፣ ሌሊቱም ነጋ ስድስተኛ ቀን
ሆነ።

---

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 2

1 የምድር በውስጣቸው ያሉትም ሕያዋን ፍጡራን አፈጣጠር በዚህ ሁኔታ ተከናወነ። 2 እግዚአብሔር ይሠራ የነበረውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጽሞ በዚሁ ቀን
ከሥራው ሁሉ አረፈ። 3 እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ሁሉ ፈጽሞ ያረፈው በዚህ ቀን ስለሆነ ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም። 4 እግዚአብሔር አምላክ
ሰማይንና ምድርን በፈጠረበት ወቅት የሰማይና የምድር የአፈጣጠራቸው ታሪክ እንደዚህ ነበር። 5 እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ ዝናብ እንዲዘንብ
ስላደረገና ምድርንም የሚያለማ ሰው ባለመኖሩ በምድር ላይ ምንም ቡቃያ አልነበረም፣ በምድር ላይ የሚበቅል ተክልም ገና አልበቀለም። 6 ነገር ግን ውሃ
ከመሬት እየመነጨ የምድርን ገጽ ያረሰርስ ነበር። 7 እግዚአብሔር አምላክም ከምድር አፈር ሰውን አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤
ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። 8 እግዚአብሔር አምላክም በስተምሥራቅ በኩል በዔደን የአትክልት ስፍራ አዘጋጀ፣ የአበጀውንም ሰው በዚያ አኖረው። 9
ከምድር ውስጥም እግዚአብሔር አምላክ ለዓይን የሚያስደስቱና ለምግብነት የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ዛፎች እንዲበቅሉ አደረገ። በአትክልት ስፍራው መካከልም
የሕይወት ዛፍ ነበር፣ መልካሙንና ክፉውን የሚያሳውቀውም ዛፍ በዚያ ነበር። 10 የአትክልት ስፍራውንም የሚያጠጣ ወንዝ ከኤደን ይፈስ ነበር። ወንዙም
ከኤደን ከወጣ በኋላ አራት ወንዞች ሆኖ ይከፋፈል ነበር። 11 የመጀመሪያው ፊሶን የተባለው ወንዝ ነበር፣ ይህም ወርቅ ይገኝበት የነበረውን መላውን የሐዊላ
ምድር አቋርጦ የሚፈስው ወንዝ ነበር። 12 የዚያ አገር ወርቅ የጠራ ወርቅ ነበር፤ በተጨማሪም በዚያ አገር ሽቶና የከበሩ ድንጋዮች ነበሩ። 13 የሁለተኛው ወንዝ
ስም ግዮን ይባል ነበር፣ እርሱም መላውን የኢትዮጵያ ምድር አቋርጦ ይፈስ ነበር። 14 የሶስተኛው ወንዝ ስም ጤግሮስ ይባል ነበር፣ እርሱም በአሦር
በስተምሥራቅ ይፈሳል። አራተኛው ወንዝ ኤፍራጥስ ነበር። 15 እግዚአብሔር አምላክም የኤደንን የአትክልት ስፍራ ያለማና ይንከባከብ ዘንድ ሰውን ወስዶ በዚያ
አኖረው። 16 እግዚአብሔር አምላክም እንዲህ በማለት አዘዘው፣ “በአትክልቱ ስፍራ ካለው ከማንኛውም የፍሬ ዛፍ መብላት ትችላለህ። 17 ነገር ግን
መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፣ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ።” 18 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ፦ “ሰው
ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። ስለዚህ የምትመቸውን ረዳት እፈጥርለታለሁ” አለ። 19 እግዚአብሔር አምላክም ከምድር አፈር የምድር እንስሶችንና
የሰማይ ወፎችን አበጀ። ምን ስም እንደሚያወጣላቸው ይመለከት ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው። ለእያንዳንዱ ሕያው ፍጡር አዳም ያወጣለት ስም ያ ስሙ ሆነ።
20 አዳም ለሁሉም ከብቶች፣ ለሁሉም የሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው። ነገር ግን ለአዳም ለራሱ የምትመች ረዳት አልተገኘለትም። 21
እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገ፣ ስለሆነም አዳም አንቀላፋ። እግዚአብሔር አምላክ አዳም አንቀላፍቶ ሳለ ከጎድን
አጥንቶቹ አንዱን ወስዶ አጥንቱን የወሰደበትን ስፍራ በሥጋ ዘጋው። 22 እግዚአብሔር አምላክ ከአዳም ከወሰደው የጎድን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት። ወደ
አዳምም አመጣት። 23 አዳምም፦ “አሁን ይህቺ ከአጥንቴ የተገኘች አጥንት ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋ ናት። ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል” አለ። 24 ስለዚህ
ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። 25 አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ
አይተፋፈሩም ነበር።

---

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 3

1 እግዚአብሔር በምድር ላይ ከፈጠራቸው ማናቸውም ሌሎች አራዊቶች ሁሉ ይልቅ እባብ ተንኮለኛ ነበር። እርሱም ሴቲቱን፦ “በእርግጥ እግዚአብሔር
‘በአትክልቱ ስፍራ ካለው ከማንኛውም ዛፍ አትብሉ’ ብሎአልን?” ብሎ ጠየቃት። 2 ሴቲቱም ለእባቡ፦ “በአትክልቱ ስፍራ ካሉት የዛፎች ፍሬዎች መብላት
እንችላለን፤ 3 ነገር ግን በአትክልቱ ስፍራ መካከል ስለሚገኘው ዛፍ እግዚአብሔር “እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም” ብሎአል። 4 እባብም ለሴቲቱ፦
“በፍጹም አትሞቱም። 5 ከእርሱ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንደሚከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካሙንና ክፉውን የምታውቁ እንደምትሆኑ እግዚአብሔር
ስለሚያውቅ ነው አላት።” 6 ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት መልካም፣ ሲያዩት ደስ የሚያሰኝና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ተመልክታ ከፍሬው ወስዳ
በላች፤ ከእርሷ ጋር ለነበረውም ለባሏ ከፍሬው ሰጠችው፣ እርሱም በላ። 7 የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፣ ራቁታቸውን እንደነበሩም አወቁ። የበለስ ቅጠሎችንም
በማጋጠም ከሰፉ በኋላ ለራሳቸው መሸፈኛ ግልድም ሠሩ። 8 ቀኑ ወደ ምሽት ሲቃረብ በአትክልት ስፍራው ሲመላለስ የእግዚአብሔር አምላክን ድምፅ ሰሙ፤
ስለዚህ አዳምና ሚስቱ ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በመሸሽ በአትክልቱ ስፍራ በነበሩት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። 9 እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ጠራውና፣
“የት ነህ?” አለው። 10 አዳምም፣ “በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ ድምፅህን ሰማሁና ራቁቴን ስለነበርሁ ፈራሁ፤ በዚህም ምክንያት ተሸሸግሁ።” 11
እግዚአብሔርም፦ “ራቁትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ብዬ ካዘዝኩህ ከዛፉ ፍሬ በላህን?” አለው። 12 አዳምም፦ “አብራኝ እንድትሆን
የሰጠኸኝ ሴት ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝ፣ እኔም በላሁት” አለ። 13 እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን፦ “ምንድነው ያደረግሽው?” አላት። ሴቲቱም፦ “እባቡ አታለለኝና
በላሁ” አለች። 14 እግዚአብሔር አምላክም ለእባቡ፦ “ይህንን በማድረግህ ከእንስሳት ሁሉና ከምድር አራዊት ሁሉ ተለይተህ የተረገምህ ትሆናለህ። በደረትህ
እየተሳብክ ትሄዳለህ፣ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ አፈር ትበላለህ። 15 በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ መካካል ጠላትነትን አደርጋለሁ። የእርሷ ዘር ራስህን
ይቀጠቅጣል፣ አንተም ተረከዙን ትነክሳለህ” አለው። 16 ለሴቲቱም እንዲህ አላት፦ “በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤ በስቃይም ትወልጃለሽ። ፈቃድሽ ወደ
ባልሽ ይሆናል፣ እርሱም ገዢሽ ይሆናል።” 17 ለአዳምም እንደዚህ አለው፦ “የሚስትህን ቃል ሰምተህ ‘ከእርሱ እንዳትበላ’ ብዬ ካዘዝሁህ ከዛፉ ፍሬ ስለበላህ
ከአንተ የተነሳ ምድር የተረገመች ትሁን፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ በከባድ ድካም ምግብህን ከእርሷ ታገኛለህ። 18 ምድር እሾህና አሜኬላ ታበቅልብሃለች፤
የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። 19 ከተገኘህበት አፈር እስክትመለስ ድረስ በላብህ እንጀራን ትበላለህ። አፈር ነህና ወደ አፈር ተመልሰህ ትሄዳለህ”። 20 የሕያዋን
ሁሉ እናት በመሆኗ አዳም ለሚስቱ ‘ሔዋን’ የሚል ስም አወጣላት። 21 እግዚአብሔር አምላክ ከቆዳ ልብስ አዘጋጅቶ አዳምንና ሚስቱን አለበሳቸው። 22
እግዚአብሔር አምላክ፦ “መልካምንና ክፉውን ለይቶ በማውቅ ረገድ አሁን ሰው ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖአል። ስለዚህ አሁን እጁን ዘርግቶ ከሕይወት ዛፍ ፍሬ
ቀጥፎ እንዳይበላ ለዘላለምም እንዳይኖር ሊፈቀድለት አይገባም” አለ። 23 በዚህም ምክንያት የተገኘባትን ምድር እንዲያለማ እግዚአብሔር አዳምን ከኤደን
የአትክልት ስፍራ አስወጣው። 24 ስለዚህ እግዚአብሔር አዳምን ከአትክልት ስፍራው አባረረው፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ይጠብቁ ዘንድ
ከኤደን የአትክልት ስፍራ በስተቀኝ በኩል ኪሩቤልን እንደዚሁም በየአቅጣጫው የምትገለባበጥ ነበልባላዊ ሰይፍ አኖረ።

Chapter 4

1 አዳምም ከሚስቱ ከሔዋን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ። እርሷም ፀነሰች። ቃየንንም ወለደች። “በእግዚአብሔር ዕርዳታ ወንድ ልጅ ወለድሁ” አለች። 2
ከዚያ በኋላም ወንድሙን አቤልን ወለደች። አቤል የበግ እረኛ ሲሆን ቃየን ግን ገበሬ ሆነ። 3 ከዕለታት አንድ ቀን ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መባ
አቀረበ። 4 አቤል ደግሞ መጀመሪያ ከተወለዱ በጎች መካከል ስባቸውን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። እግዚአብሔር በአቤልና በመሥዋዕቱ ደስ ተሰኘ፣ 5
በቃየንና በመሥዋዕቱ ግን ደስ አልተሰኘም። ስለዚህ ቃየን በጣም ተቆጣ፣ ፊቱም ተኮሳተረ። 6 እግዚአብሔር አምላክ ቃየንን፦ “ለምን ተቆጣህ፣ ፊትህስ ለምን
ተኮሳተረ? 7 መልካም ብታደርግ ፊትህ ያበራ አልነበረምን? ያደረግኸው መልካም ካልሆነ ግን ኃጢአት በደጅህ እያደባች ናት፣ ልትቆጣጠርህም ትፈልጋለች፣
አንተ ግን በቁጥጥርህ ሥር አድርጋት” አለው። 8 ቃየን ወንድሙን አቤልን፦ “ወደ ሜዳ እንውጣ” አለው፣ በዚያም ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ በቁጣ
ተነሳበት፣ ገደለውም። 9 ከዚያ በኋላም እግዚአብሔር ቃየንን፦ “ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?” አለው። እርሱም፦ “አላውቅም፣ እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?”
አለ። 10 እግዚአብሔርም፦ “ያደረግኸው ምንድን ነው? የወንድምህ ደም ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል” አለው። 11 “አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ
ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። 12 ምድርንም በምታርስበት ጊዜ ፍሬዋን በሙላት አትሰጥህም። በምድር ላይ ኮብላይና
ተንከራታች ትሆናለህ” አለው። 13 ቃየንም ለእግዚአብሔር፦ ቅጣቴ ከምችለው በላይ ነው። 14 በእርግጥም ዛሬ ከምድሪቱ አባርረኸኛል፣ እኔም ከፊትህ
እሸሸጋለሁ። በምድር ላይ ኮብላይና ተንከራታች እሆናለሁ፣ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል” አለው። 15 እግዚአብሔርም፦ “ቃየንን የሚገድል ማንኛውም ሰው
ሰባት እጥፍ የበቀል እርምጃ ይወሰድበታል” አለ። ከዚያ በኋላም የሚያገኘው ማንኛውም ሰው እንዳይገድለው እግዚአብሔር በቃየን ላይ ምልክት አደረገበት።
16 ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ፣ ከኤደን በስተምሥራቅ በነበረው ኖድ በተባለው ምድር ኖረ። 17 ቃየንም ከሚስቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት
ፈጸመ፣ እርሷም ፀነሰች፣ ሄኖክንም ወለደች። ቃየን ከተማን መሠረተ፣ የመሠረታትንም ከተማ በልጁ ስም ሄኖክ ብሎ ጠራት። 18 ሄኖክም አራድን ወለደ።
አራድም መሑያኤልን ወለደ። መሑያኤልም መቱሳኤልን ወለደ። መቱሳኤልም ላሜክን ወለደ። 19 ላሜክም ዓዳና ጺላ የተባሉ ሁለት ሚስቶችን አገባ። 20 ዓዳ
ያባልን ወለደች፣ እርሱም በድንኳን ለሚኖሩ ለከብት አርቢዎች አባት ነበር። 21 የእርሱ ወንድም ዩባልም የበገና ደርዳሪዎችና የዋሽንት ነፊዎች አባት ነበር። 22
ጺላም ከነሐስና ከብረት መሣሪያዎችን የሚሠራውን ቱባልቃይንን ወለደች። የቱባልቃይንም እህት ናዕማ ትባል ነበር። 23 ላሜክ ለሚስቶቹ፦ “አዳና ጺላ ስሙኝ፣
እናንተ የላሜክ ሚስቶች የምላችሁን ስሙኝ ስለጎዳኝና ስላቆሰለኝ አንድ ሰው ገድያለሁ። 24 ቃየንን የሚገድል ሰባት እጥፍ የበቀል እርምጃ የሚወሰድበት ከሆነ
የላሜክ ገዳይማ ሰባ ሰባት እጥፍ የበቀል እርምጃ ይወሰድበታል” አላቸው። 25 አዳም ከሚስቱ ጋር እንደገና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ፣ እርሷም ወንድ ልጅ
ወለደች። “ቃየን በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ምትክ ሰጠኝ” በማለት ስሙን ሤት ብላ ጠራችው። 26 ለሤትም ወንድ ልጅ ተወለደለት፣ ስሙንም
ሄኖስ አለው። በዚያም ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ጀመሩ።

Chapter 5

1 የአዳም የትውልድ ሐረግ እንደሚከተለው ነው። እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ በራሱ አምሳያ ፈጠራቸው፤ 2 ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣
ባረካቸውም። በተፈጠሩም ጊዜ ‘ሰው’ ብሎ ጠራቸው። 3 አዳም ዕድሜው 130 ዓመት በሆነ ጊዜ፣ እርሱን የሚመስል ወንድ ልጅ ወለደ፣ ስሙንም ‘ሤት’
ብሎ ጠራው። 4 አዳም ሤትን ከወለደ በኋላ 800 ዓመታት ኖረ። ሌሎችን ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ፤ 5 930 ዓመት ሲሆነውም ሞተ። 6 ሤት
ዕድሜው 105 ሲሆን ሄኖስን ወለደ። 7 ሄኖስን ከወለደ በኋላ ሤት 807 ዓመት ኖረ። ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 8 ሤት 912 ዓመታት ከኖረ
በኋላ ሞተ። 9 ሄኖስ 90 ዓመት ሲሆነው ቃይናንን ወለደ። 10 ሄኖስ ቃይናንን ከወለደ በኋላ 815 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 11
ሄኖስ 905 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። 12 ቃይናን 70 ዓመት ሲሆነው መላልኤልን ወለደ። 13 ቃይናን መላልኤልን ከወለደ በኋላ 840 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች
ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 14 ቃይናን 910 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። 15 መላልኤል 65 ዓመት ሲሆነው ያሬድን ወለደ። 16 መላልኤል ያሬድን
ከወለደ በኋላ 800 ዓመታት ኖረ። ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 17 መላልኤል 895 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። 18 ያሬድ 162 ዓመት ሲሆነው
ሄኖክን ወለደ። 19 ያሬድ ሄኖክን ከወለደ በኋላ 800 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 20 ያሬድ 962 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። 21
ሄኖክ 65 ዓመት ሲሆነው ማቱሳላን ወለደ። 22 ሄኖክ ማቱሳላን ከወለደ በኋላ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል 300 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና
ሴቶች ልጆችን ወለደ። 23 ሄኖክ 365 ዓመታት ኖረ። 24 ሄኖክ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል ኖረ፣ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ስለወሰደው
አልተገኘም። 25 ማቱሳላ 187 ዓመት ሲሆነው ላሜሕን ወለደ። 26 ማቱሳላ ላሜሕን ከወለደ በኋላ 782 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን
ወለደ። 27 ማቱሳላ 969 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። 28 ላሜሕ 182 ዓመት ሲሆነው አንድ ወንድ ልጅ ወለደ። 29 “ይህ ልጅ እግዚአብሔር በረገማት ምድር
ከልፋታችንና ከብርቱ ሥራችን ያሳርፈናል” ሲል ስሙን ‘ኖህ’ ብሎ ጠራው። 30 ላሜሕ ኖህን ከወለደ በኋላ 595 ዓመታት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችንና ሴቶች
ልጆችን ወለደ። 31 ላሜሕ 777 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ። 32 ኖህ 500 ዓመታት ሲሆነው ሴም፣ ካምንና ያፌትን ወለደ።

---

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 6

1 የሰው ልጆች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው። 2 የእግዚአብሔር ልጆችም የሰዎች ሴቶች ልጆች የሚስብ ውበት እንዳላቸው
ተመለከቱ። ከእነርሱ መካከልም የመረጧቸውን ሚስቶች አድርገው ወሰዱ። 3 እግዚአብሔርም፦ “እርሱ ሥጋ ስለሆነ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፤
ዕድሜውም 120 ዓመት ይሆናል” አለ። 4 የእግዚአብሔር ልጆች ከሰዎች ሴቶች ልጆች ጋብቻ በፈጸሙና ልጆችን በወለዱበት በዚያን ጊዜ ከዚያም በኋላ
ኔፊሊም የተባሉ ግዙፍ ሰዎች በምድር ላይ ነበሩ። እነርሱም በጥንት ዘመን ዝናን ያተረፉ ኀያላን ነበሩ። 5 እግዚአብሔር የሰው ልጆች ክፋት በምድር ላይ እየበዛ
እንደሆነና የልቡም ሃሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ። 6 እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ ልቡም አዘነ። 7
በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር፦ “የፈጠርሁትን የሰው ልጅ ከምድር ገጽ አጠፋለሁ፤ ስለፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና ከእነርሱም ጋር እንስሳትን፣ በደረታቸው
የሚሳቡትን ፍጥረታትና የሰማይ ወፎችን ሁሉ አጠፋለሁ” አለ። 8 ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አገኘ። 9 የኖኅ ታሪክ እንደሚከተለው ነው። ኖኅ በዘመኑ
ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጻድቅና ከበደል የራቀ ሰው ነበር፤ የእግዚአብሔርንም መንገድ የሚከተል ሰው ነበር። 10 ኖኅ ሴም፣ ካምና ያፌት የተባሉትን ሶስት
ወንዶች ልጆች ወለደ። 11 በእግዚአብሔር ፊት በክፉ ሥራ ረከሰች በዓመፅም ተሞላች። 12 እግዚአብሔር ምድርን ተመለከተ፣ የተበላሸች እንደሆነችና በምድር
የሚኖሩትም ሰዎች ሁሉ በክፋት እንደሚኖሩ አየ። 13 እግዚአብሔርም ኖኅን፦ “ሥጋን የለበሰ ሁሉ ፍጻሜ ደርሶአል፣ ከእነርሱ የተነሳ ምድር በግፍ ተሞልታለችና።
እኔም በእርግጥ ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ። 14 አንተ ግን ከጥሩ እንጨት መርከብ ሥራ፤ መርከቧም ክፍሎች እንዲኖሯት አድርግ፤ ውስጧንና ውጭዋንም
በቅጥራን ለቅልቀው። 15 እንደዚህ አድርገህ ሥራት፦ ርዝመቷ 140 ሜትር፣ ወርዷ 23 ሜትር፣ ከፍታዋ 13. 5 ሜትር ይሁን። 16 ለመርከቧ ጣራ አብጅላት፣
ጣራና ግድግዳው በሚጋጠምበት ቦታ ግማሽ ሜትር ክፍተት ተው፤ ከጎኗ በር አውጣላት፤ ባለ ሦስት ፎቅ አድርገህ ሥራት። 17 እኔም ከሰማይ በታች የሕይወት
እስትንፋስ ያለባችውን ፍጡራን ሁሉ ለማጥፋት እነሆ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ አወርዳለሁ፤ በምድር ላይ ያለ ሁሉ ይጠፋል። 18 ከአንተ ጋር ግን ቃል ኪዳን
እገባለሁ፤ አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና የልጆችህ ሚስቶች ከአንተ ጋር ወደ መርከቧ ትገባላችሁ። 19 ከአንተ ጋር በሕይወት እንዲቆዩ ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ
ወንድና ሴት እያደረግህ ሁለት ሁለቱን ወደ መርከቧ ታስገባለህ። 20 ከእያንዳንዱ የወፍ ወገን፣ ከእያንዳንዱ የእንስሳ ወገን፣ በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጥረት ሁሉ
በየወገናቸው በሕይወት ይቆዩ ዘንድ ወደ አንተ ይምጡ። 21 ለአንተና ለእነዚህ ፍጥረቶች ሁሉ የሚበቃ ልዩ ልዩ ዓይነት ምግብ በመርከቡ ውስጥ አከማች።”
22 ኖኅም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ አደረገ።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 7

1 እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፦ “በዚህ ትውልድ መካከል አንተን ጻድቅ ሆነህ አግኝቼሃለሁና ቤተሰብህን በሙሉ ይዘህ ወደ መርከቧ ግባ። 2 ከንፁህ
እንስሳት ሁሉ ሰባት ሰባት ወንድና ሴት፣ ንፁሕ ካልሆኑት እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ወንድና ሴት ከአንተ ጋር አስገባ። 3 እንዲሁም ከሰማይ ወፎች ወገን
ሰባት ወንዶችና ሰባት ሴቶች በምድር ላይ ለዘር እንዲተርፉ ከአንተ ጋር ታስገባለህ። 4 ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በመድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁ፤
የፈጠርሁትንም ሕያው ፍጡር ሁሉ ከምድር ላይ አጠፋለሁ።” 5 ኖኅም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ አደረገ። 6 የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በወረደ ጊዜ ኖኅ
የ600 ዓመት ሰው ነበር። 7 ኖኅና ወንዶች ልጆቹ ሚስቱና የልጆቹ ሚስቶች ከጥፋት ውሃ ለማምለጥ ወደ መርከቡ ገቡ። 8 ንፁሕ ከሆኑትና ንፁሕ ካልሆኑት
እንስሳት ከወፎችና በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ 9 ጥንድ ጥንድ ወንድና ሴት ሆነው ወደ ኖኅ መጡ፤ እግዚአብሄር ኖኅን ባዘዘው መሠረትም ወደ
መርከቧ ገቡ። 10 ከሰባት ቀንም በኋላ የጠፋት ውሃ በምድር ላይ መጣ። 11 ኖኅ በተወለደ በ600ኛው ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በአሥራ ሰባተኛው ቀን
የታላቁ ጥልቅ ምንጮች በሙሉ ተነደሉ፤ የሰማይ መስኮቶችም ተከፈቱ። 12 ዝናቡም መዝነብ ጀመረ፣ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ባለማቋረጥ በምድር ላይ
ዘነበ። 13 ዝናቡ መዝነብ በጀመረበት ቀን ኖኅና ሚስቱ ከልጆቻቸው ጋር ከሴም ከካም ከያፌትና ከሶስቱም ልጆቻቸው ሚስቶች ጋር ወደ መርከቡ ገቡ። 14
ከአራዊት ከእንስሳት በደረታቸው እየተሳቡ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችና በሰማይ ከሚበሩ ወፎች ከእያንዳንዱ ዓይነት አብረዋቸው ገቡ። 15 የሕይወት እስትንፋስ
ያለባቸው ፍጡራን በሙሉ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ከኖኅ ጋር ወደ መርከቡ ገቡ። 16 ከሕያዋንም ፍጡራን ሁሉ እግዚአብሔር ኖኅን ባዘዘው መሠረት ወንድና ሴት
እየሆኑ ገቡ፤ ከዚያም እግዚአብሔር የመርከቡን በር ከውጭ ዘጋ። 17 የጥፋት ውሃም ለአርባ ቀናት ያለመቋረጥ በምድር ላይ ዘነበ ውሃው እየጨመረ በሄድ
መጠን መርከቧን ከምድር ወደ ላይ አነሳት። 18 ውሃው በምድር ላይ በጣም እየጨመረና ከፍ እያለ ሲሄድ፣ መርከቧ በውሃ ላይ ተንሳፈፈች። 19 ውሃው በጣም
ከፍ በማለቱ፣ ከሰማይ በታች ያሉትን ታላላቅ ተራሮች ሁሉ ሸፈናቸው። 20 ውሃው ከተራሮች ጫፍ በላይ 7ሜትር ያህል ከፍ አለ። 21 በምድር ላይ የነበሩ
ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፦ ወፎች፣ የቤት እንስሳት፣ አራዊት፣ በምድር የሚርመሰመሱ ፍጡራን ሰዎችም በሙሉ ጠፉ። 22 የሕይወት እስትንፋስ ያላቸው በምድር
የነበሩ ፍጡራን ሁሉ ሞቱ። 23 ሕይወት ያላቸው ፍጡራን ሁሉ ከሰዎች ጀምሮ እንስሳት፣ በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንና የሰማይ ወፎች ሁሉም ከምድር ገጽ
ጠፉ። ኖኅና ከእርሱ ጋር በመርከቧ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ። 24 ውሃውም ምድርን ሸፍኖ መቶ አምሳ ቀን ቆየ።

Chapter 8

1 እግዚአብሔር ኖኅንና ከእርሱ ጋር በመርከቧ ውስጥ የነበሩትን አራዊትና እንስሳት ሁሉ አሰበ። በምድር ላይ ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ ውሃውም ጎደለ። 2
የጥልቁ ምንጮችና የሰማይ መስኮቶች ተዘጉ፣ ዝናቡም መዝነቡን አቆመ። 3 ውሃው ከምድር ላይ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፤ ከመቶ ሃምሳ ቀን በኋላም የውሃው
ከፍታ እጅግ ቀነሰ። 4 በሰባተኛው ወር፤ በአሥራ ሰባተኛው ቀን መርከቧ በአራራት ተራሮች ላይ አረፈች። 5 ውሃው እስከ አሥረኛው ወር ድረስ ቀስ በቀስ እየጎደለ
ሄደ። በአሥረኛው ወር መጀመሪያው ቀን የተራሮች ጫፎች ታዩ። 6 ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ የሠራውን የመርከቧን መስኮት ከፍቶ፣ 7 ቁራን ወደ ውጭ ላከ፤
ቁራውም ውሃው ከምድር ላይ እስኪደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር። 8 ከዚያም በኋላ ኖኅ ውሃው ከምድር ላይ ገጽ ጎድሎ እንደሆነ ለማወቅ ርግብን
ላከ፤ 9 ነገር ግን ውሃው ገና ምድርን ሁሉ ሸፍኖ ስለነበር ርግቢቱ የምታርፍበት ቦታ አላገኘችም፤ ስለዚህ ኖኅ ወዳለበት መርከብ ተመልሳ መጣች፤ ኖኅም እጁን
ዘርግቶ ወደ መርከቡ ውስጥ አስገባት። 10 ሰባት ቀን ከቆየ በኋላ ኖኅ ርግቧን እንደገና ላካት። 11 እርሷም ወደ ማታ ተመለሰች፤ እነሆም የለመለመ የወይራ
ቅጠል በአፏ ይዛ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ኖኅ ውሃው ከምድር ላይ መጉደሉን አወቀ። 12 ደግሞም ሰባት ቀን ከቆየ በኋላ ኖኅ ርግቢቱን እንደገና አውጥቶ ላካት፤
በዚህ ጊዜ ግን ርግቢቱ ወደ እርሱ አልተመለሰችም። 13 ኖኅ በተወለደ 601ኛው ዓመት፣ በመጀመሪያው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ውሃው ከምድር ላይ
ደረቀ። ኖኅ የመርከቡን ክዳን አንሥቶ ዙሪያውን ተመለከተ፣ ምድሪቱም እንደደረቀች አየ። 14 በሁለተኛው ወር፣ በሃያ ሰባተኛው ቀን ምድሪቱ ሙሉ በሙሉ ደረቀች።
15 ከዚያም እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው። 16 “አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና የልጆችህ ሚስቶች ከመርከቧ ውጡ። 17 እንዲዋለዱ፣ እንዲራቡና በምድር
ላይ እንዲበዙ ከአንተ ጋር ያሉትን ወፎች፣ እንስሳትና በምድር ላይ የሚሳቡ ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ይዘሃቸው ውጣ።” 18 ስለዚህ ኖኅ ከልጆቹ፣ ከሚስቱና
ከልጆቹ ሚስቶች ጋር ወጣ። 19 እንስሳቱ ሁሉ፣ ወፎችም፣ በምድር የሚሳቡት፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ በየወገናቸው ከመርከቧ
ወጡ። 20 ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ። ንፁሕ ከሆኑት እንስሳትና ንፁሕ ከሆኑት ወፎች አንዳንዶቹን ወስዶ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ። 21
እግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን መዓዛ አሸተተ፣ በልቡም እንዲህ አለ፦ “ምንም እንኳ ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሐሳቡ ወደ ክፋት ያዘነበለ ቢሆንም በእርሱ
ምክንያት ሁለተኛ ምድርን አልረግማትም፤ አሁን እንዳደረግሁት ሕያዋን ፍጡራንን ዳግመኛ አላጠፋም። 22 ምድር እስካለች ድረስ የዘር ወቅትና መከር፣ ሙቀትና
ቅዝቃዜ፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አይቋረጡም።”

Chapter 9

1 ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን እንዲህ ሲል ባረካቸው፦ “ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፤ 2 አስፈሪነታችሁና አስደንጋጭነታችሁ በእንስሳት፣
በሰማይ ወፎች፣ በደረት በሚሳቡ ተንቀሳቃሽ ፍጡሮችና በባሕር ዓሦች፣ በምድር ላይ በሚገኙ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ላይ ይሁን። ሁሉም በሥልጣናችሁ ሥር
ይሁኑ። 3 ሕያውና ተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ፣ ለምለሙን ዕፅዋት እንደሰጠኋችሁ፣ አሁን ደግሞ ሁሉን ሰጠኋችሁ። 4 ነገር ግን ሕይወቱ ማለት
ደሙ ገና በውስጡ ያለበትን ሥጋ አትብሉ። 5 ሰውን የገደለ ሁሉ ስለሟቹ ደም ተጠያቂ ነው፤ የሟቹን ሰው ደም ከገዳዩ ከእንስሳም ይሁን ከሰው እሻለሁ። 6
የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል፤ በእግዚአብሔር አምሳል እግዚአብሔር ሰውን ሠርቶታልና። 7 እናንተ ግን ብዙ ተባዙ፣ ዘራችሁ በምድር ላይ
ይብዛ ይንሠራፋም።” 8 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ አላቸው፦ 9 “እነሆ ከእናንተና ከእናንተ በኋላ ከሚመጣው ዘራችሁ ጋር ኪዳኔን
እመሠርታለሁ፤ 10 እንዲሁም ከእናንተ ጋር ከነበሩት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ከወፎች፣ ከእንስሳት ከእናንተ ጋር ከመርከቧ ከወጡት በምድር ላይ ካሉት ሕያዋን
ፍጡራን ሁሉ ጋር ኪዳን አገባለሁ። 11 ከእንግዲህ ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ በጥፋት ውሃ እንደማይጠፋ፣ ዳግመኛም ምድርን የሚያጠፋ ውሃ ከቶ
እንደማይመጣ ከእናንተ ጋር ኪዳን አገባለሁ።” 12 እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፦ “በእኔና በእናንተ መካከል ከእናንተም ጋር ካሉ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፣
ከሚመጣው ትውልድ ሁሉ ጋር፣ የማደርገው የኪዳኑ ምልክት ይህ ነው፤ 13 ቀስተ ደመናዬን በደመና ላይ አድርጋለሁ፤ ይህም በእኔና በምድር መካከል ለገባሁት
ኪዳን ምልክት ይሆናል። 14 ደመናን በምድር ላይ በጋረድሁና ቀስቴም በደመና ላይ በሚታይበት ጊዜ ሁሉ 15 ከእናንተና ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር የገባሁትን
ኪዳን አስባለሁ፤ ሕይወት ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፣ ከእንግዲህ የጥፋት ውሃ ከቶ አይመጣም። 16 ቀስቱ በደመና ላይ ተገልጦ በማይበት ጊዜ ሁሉ በእኔና
በምድር ላይ ባሉ ሕያዋን ፍጡራን መካከል ያለውን ዘላለማዊ ኪዳን አስባለሁ።” 17 ከዚያ በኋላም እግዚአብሔር ለኖኅ፦ “ይህ በእኔና በምድር ላይ በሚኖሩ
ሕያዋን ሁሉ መካከል የገባሁት ኪዳን ምልክት ነው።” አለው። 18 ከመርከቧ የወጡትም የኖኅ ልጆች ሴም፣ ካምና ያፌት ነበር፤ ካም የከነዓን አባት ነው። 19
እነዚህ ሶስቱ የኖኅ ልጆች ሲሆኑ፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የተገኙት ከነዚሁ ነው። 20 ኖኅ ገበሬ መሆን ጀመረ፣ ወይንንም ተከለ። 21 ከወይኑም ጠጅ
ጠጥቶ ሰከረና በድንኳኑ ውስጥ እርቃኑን ተኛ። 22 የከንዓን አባት ካም የአባቱን ዕርቃነ ሥጋ አየ፤ ወደ ውጭም ወጥቶ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው። 23 ሴምና
ያፌት ግን ልብስ ወስደው በትከሻቸው ላይ አደረጉና የአባታቸውን ዕርቃነ ሥጋ እንዳያዩ ፊታቸውን አዙረው የኋሊት በመሄድ የአባታቸውን ዕርቃነ ሥጋ ሸፈኑ። 24
ኖኅ ከወይን ጠጁ ስካር ሲነቃ ታናሽ ልጁ ያደረገበትን አወቀ። 25 ከዚህም የተነሣ፦ “ከነዓን የተረገመ ይሁን፤ ለወንድሞቹም አገልጋይ ይሁን።” አለ። 26
ደግሞም፦ “የሴም አምላክ የሆነው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ ከነዓንም የሴም አገልጋይ ይሁን። 27 እግዚአብሔር የያፌትን ግዛት ያስፋ፤ ያፌት በሴም
ድንኳኖች ይኑር፤ ከነዓን የያፌት አገልጋይ ይሁን።” አለ። 28 ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ 350 ዓመት ኖረ። 29 ኖኅ በአጠቃላይ 950 ዓመት ኖሮ ሞተ።

Chapter 10

1 የኖኅ ልጆች የሴም፣ የካምና የያፌት ዝርያዎች የሚከተሉት ናቸው። ከጥፋት ውሃም በኋላ ልጆች ተወለዱላቸው። 2 የያፌት ልጆች፦ ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፣
ያዋን፣ ቶቤል፣ ሞሳሕና ቴራስ ነበሩ። 3 የጋሜር ልጆች፦ አስከናዝ፣ ሪፋትና ቴርጋማ ነበሩ። 4 የያዋን ልጆች፦ ኤሊሳ፣ ተርሴስ፣ ኪቲምና ሮዳኢ ነበሩ። 5
ከእነዚህም በየነገዳቸው በየጎሳቸውና በየቋንቋቸው ተከፋፍለው በባሕር ዳርና በደሴቶች በየምድራቸው የሚኖሩ ሕዝቦች ወጡ። 6 የካም ልጆች፦ ኩሽ፣
ምጽራይም፣ ፉጥና ከነዓን ነበሩ። 7 የኩሽ ልጆች፦ ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማና ሰበቀታ ነበሩ። የራዕማ ልጆች፦ ሳባና ድዳን ነበሩ። 8 ኩሽ በምድር ላይ
የመጀመሪያው ታላቅ ጦረኛ የነበረው የናምሩድ አባት ነበር። 9 እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ አዳኝ ነበር። ስለዚህም፣ “በእግዚአብሔር ፊት እንደ ናምሩድ
ብርቱ አዳኝ” ይባል ነበር። 10 የግዛቱም የመጀመሪያ ከተሞች በሰናዖር ምድር የነበሩት፦ ባቢሎን፣ አሬክ፣ አርካድና ካልኔ ነበሩ። 11 ከዚያም ወደ አሦር ምድር
ሄደና ነነዌን፣ ርሆቦትን፣ ካላሕን 12 እንዲሁም በነነዌና በካላሕ መካከል የነበረውን ታላቅ ከተማ ሬሴን የተባሉትን ከተሞች መሠረተ። 13 ምጽራይም
የሎዳማውያን፣የዐናሚማውያን፣ የላህሚማውያን፣ የነፍታሌማውያን፣ 14 የፈተሩሲማውያንና ፍልስጥኤማውያን የተገኙባቸው የካስሎሂማውያንና የቀፍቶርማውያን
አባት ነበር። 15 የከነዓንም የበኲር ልጅ ሲዶን ተከታዩም ሔት ይባሉ ነበር። 16 ሌሎቹም የከነዓን ዝርያዎች ኢያቡሳውያን፣ አሞራውያን፣ ጌርጌሳውያን፣ 17
ኤውያውያንን፣ ዓርቃውያን፣ ሲናውያን፣ 18 ኤርዋዳውያን፣ አርዋዳውያን፣ ደማራውያን፣ ሐማታውያን የሚባሉ ነበሩ። ከጊዜ በኋላ የከነዓን ጎሣዎች በየስፍራው
ተሠራጩ። 19 የከነዓን ወሰን ከሲዶና አንሥቶ በጌራራ በኩል ገሞራን አዳማንና ሰቦይን ይዞ እስከ ላሣ ይዘልቃል። 20 እነዚህም በየጎሣቸውና በየቋንቋቸው
በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ የካም ዝርያዎች ነበሩ። 21 ለያፌት ታላቅ ወንድም ለሴም ደግሞ ወንዶች ልጆች ተወለዱለት፤ እርሱም የዔቦር ልጆች
ሁሉ ቅድመ አያት ነበር። 22 የሴም ልጆች ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣ አራም ነበሩ። 23 የአራም ልጆች ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሶሕ ነበሩ። 24 አርፋክስድ
ሳላን ወለደ፤ ሳላም ኤቦርን ወለደ። 25 ዔቦርም ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ። በዘመኑ ምድር ተከፍላ ስለነበር የአንደኛው ልጅ ስም ፍሌቅ ተባለ፤ ወንድሙም
ዮቅጣን ተባለ። 26 ዮቅጣንም የአልሞዳድ፣ የሼሌፍ፥ የሐጸርማዌት፣ የዮራሕ፣ 27 የዐዶራም፣ የኢዛል፣ የዲቅላ፣ 28 የዖባል፣ የአቢማኤል፣ የሳባ፣ 29 የኦፊር፣
የሐዊላና የዮባብ አባት ነበር። እነዚህ ሁሉ የዮቅጣን ዝርያዎች ነበሩ። 30 መኖርያ ስፍራቸውም በስተምሥራቅ ባለው በተራራማው አገር ከሜሻ እስከ ስፋር
ይደርስ ነበር። 31 እነዚህም በየጎሣቸውና በየቋንቋቸው በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ የሴም ዝርያዎች ነበሩ። 32 የኖኅ ወንዶች ልጆች ጎሣዎች
እንደ ትውልዳቸው በየነገዳቸው እነዚህ ነበሩ። ከጥፋት ውሃ በኋላ ሕዝቦች በምድር ላይ የተሠራጩት ከእነዚሁ ነበር።

Chapter 11

1 በዚያ ዘመን መላው ዓለም የሚናገረውና የሚግባባው በአንድ ቋንቋ ነበር። 2 ወደ ምሥራቅ ሲጓዙ፣ በሰናዖር አንድ ሜዳማ ቦታ አግኝተው በዚያ ሰፈሩ። 3 እርስ
በርሳቸውም፣ “ኑ፣ ጡብ እንሥራና እስከበቃው ድረስ በእሳት እንተኩሰው” ተባባሉ። በድንጋይ ፈንታ ጡብ ተጠቀሙ፤ ጡቡን እርስ በርስ ለማያያዝም ቅጥራን
ተጠቀሙ። 4 ከዚያም፣ “ለስማችን መጠሪያ እንዲሆን ጫፉ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ። ያንን ካላደረግን በምድር ሁሉ ፊት መበታተናችን ነው” አሉ። 5
የአዳም ልጆች የሠሩትን ለማየት ያህዌ ወደ ከተማውና ወደ ግንቡ ወረደ። 6 ያህዌም፣ “አንድ ቋንቋ የሚናገሩ አንድ ሕዝብ በመሆናቸው ይህን ማድረግ ችለዋል!
ከእንግዲህ ማድረግ የፈለጉትን ለማድረግ ምንም የሚያቅታቸው አይኖርም። 7 ኑ እንውረድ፤ አርስ በርስ እንዳይግባቡም ቋንቋቸውን እንደበላልቀው” አለ። 8
ስለዚህ ያህዌ ከዚያ ቦታ ወደ መላው ዓለም በታተናቸው፣ እነርሱም ከተማዋን መሥራት አቋረጡ። 9 በዚያ የዓለምን ቋንቋ ስለ ደበላለቀ የከተማዋ ስም ባቤል
ተባለ። ከዚያም ያህዌ በመላው ዓለም በተናቸው። 10 የሴም ትውልድ ይህ ነው። የጥፋት ውሃ ከመጣ ሁለት ዓመት በኋላ ሴም መቶ ዓመት ሲሆነው
አርፋድሰድን ወለደ። 11 አርፋድሰድን ከወለደ በኋላ ሴም አምስት መቶ ዓመት ኖረ። ሌሎች ወንዶች እና ሴቶች ልጆችንም ወለደ። 12 አርፋክሰድ በሰለሣ
አምስት ዓመቱ ሰላን ወለደ፤ 13 ሰላን ከወለደ በኋላ አርፋክሰድ አራት መቶ ሦስት ዓመት ኖረ፤ እርሱም ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 14 ሳላ ሰላሣ
ዓመት ሲሆነው ዔቦርን ወለደ፤ 15 ዔቦርን ከወለደ በኋላ ሳላ አራት መቶ ሦስት ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ። 16 ዔቦር አራት ዓመት
ሲሆነው ፋሌቅን ወለደ፤ 17 ፋሌቅን ከወለደ በኋላ ዔቦር አራት መቶ ሰላሣ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 18 ፋሌቅ
ሰለሣ ዓመት ሲሆነው፣ ራግውን ወለደ፤ 19 ራግውን ከወለደ በኋላ ፋሌቅ ሁለት መቶ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን
ወለደ። 20 ራግው ሰለሣ ሁለት ዓመት ሲሆነው፣ ሴሮሕን ወለደ፤ 21 ሴሮሕን ከወለደ በኋላ ራግው ሁለት ሞት ሰባት ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ ሌሎች
ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 22 ሴሮሕ ሰለሣ ዓመት ሲሆነው፣ ናኮርን ወለደ፤ 23 ናኮርን ከወለደ በኋላ ሴሮሕ ሁለት መቶ ዓመት ኖረ፤ እርሱም እንዲሁ
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። 24 ናኮር ሃያ ዘጠኝ ዓመት ሲሆነው ታራን ወለደ፤ 25 ታራን ከወለደ በኋላ ናኮር አንድ መቶ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ኖረ፤
እርሱም እንዲሁ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ። 26 ታራ ሰባ ዓመት ሲሆነው አብራምን፣ ናኮርንና ሐራንን ወለደ። 27 የታራ ትውልድ ይህ ነው። ታራ፣
አብራምን፣ ናኮርንና ሐራን ወለደ። ሐራን ሎጥን ወለደ። 28 ሐራን አባቱ ታራ በሕይወት እያለ በተወለደበት ከተማ በከለዳውያን ዑር ሞተ። 29 አብራምና ናኮር
ሁለቱም ሚስት አገቡ። የአብራም ሚስት ሦራ ስትባል፣ የናኮር ሚስት ደግሞ ሚልካ ትባል ነበር፤ ሚልካ የሐራን ልጅ ስትሆን፣ ሐራን የሚልካና የዮሳካ አባት
ነበር። 30 ሦራ ምንም ልጅ ያልነበራት መካን ነበረች። 31 ታራ ልጁ አብራምን፣ የልጅ ልጁን ሎጥንና የአብራምን ሚስት ምራቱን ሦራን ይዞ ወደ ከነዓን ለመሄድ
በከለዳውያን ምድር ከምትገኘው ዑር አብረው ወጡ። ሆኖም፣ ካራን በደረሱ ጊዜ በዚያ ተቀመጡ። 32 ታራ ሁለት መቶ አምስት ዓመት ኖሮ በካራን ሞተ።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 12

1 በዚህ ጊዜ ያህዌ አብራምን እንዲህ አለው፤ “አገርህን፣ ወገንህንና የአባትህን ቤተ ሰብ ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ፤ 2 ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤
እባርክሃለሁ፤ ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎችም በረከት አደርግሃለሁ። 3 የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንና የሚያዋርዱህን እረግማለሁ። በአንተ
አማካይነት በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ይባረካሉ።” 4 ስለዚህ አብራም ያህዌ እንዳዘዘው ወጣ፤ ሎጥም አብሮት ሄደ። አብራም ከካራን ተነሥቶ ሲሄድ፣ የሰባ
አምስት ዓመት ሰው ነበር። 5 አብራም ሚስቱ ሦራን፣ የውንድሙ ልጅ ሎጥን አስከትሎ በካራን ያፈሩትን ሀብትና የነበራቸውን አገልጋዮች ይዞ በመጓዝ፣ ከነዓን
ምድር ገቡ። 6 አብራም በሞሬ ያለው ግዙፍ የወርካ ዛፍ እስካለበት እስከ ሴኬም ዘልቆ ሄደ። በዚያ ዘመን ከነሻናውያን በዚህ ምድር ይኖሩ ነበር። 7 ያህዌ
ለአብራም ተገልጦ፣ “ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ” አለው። ስለዚህ አብራም ለተገለጠለት ለያህዌ በዚያ መሠዊያ ሠራ። 8 ከዚያ በመነሣት ከቤቴል
በስተ ምሥራቅ ወዳለው ተራራማ አገር ሄደ፤ ቤቴል በስተ ምዕራብ፣ ጋይ በስተ ምዕራብ ባለችበት ቦታ ድንኳኑን ተከለ። እዚያ ለያህዌ መሠዊያ ሠራ፤ የያህዌንም
ስም ጠርቶ ጸለየ። 9 አብራም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ኔጌብ መጓዙን ቀጠለ። 10 በዚያ ምድር ጽኑ ራብ ስለ ነበር አብራም እዚያ ጥቂት ጊዜ ለመቆየት ወደ ግብፅ
ሄደ። 11 ግብፅ በመግባት ላይ እያለ አብራም ሚስቱ ሦራን እንዲህ አላት፤ “መቼም አንቺ ቆንጆ ሴት መሆንሽን አውቃለሁ። 12 ግብፃውያን ሲያዩሽ ‘ይህች
ሚስቱ ናት’ ይላሉ፤ እኔን ይገድሉኛል፤ አንቺን ግን ይተዉሻል። 13 ስለዚህ በአንቺ ምክንያት ለእኔ መልካም እንዲሆልኝ ሕይወቴም እንዲተርፍ እኅቱ ነኝ’ በዪ
አላት። 14 አብራም ወደ ግብፅ ሲገባ፣ ሦራ ምን ያህል ቆንጆ እንደ ሆነች ግብፃውያኑ አዩ። 15 የፈርዖን ሹማምንት ባዩአት ጊዜ እርሷን እያደነቁ ለፈርዖን ነገሩት፤
ወደ ቤተ መንግሥትም ተወሰደች። 16 በእርሷ ምክንያት ፈርኦን አብራምን በክብር አስተናገደው፤ በጎች፣ በሬዎች፣ ወንድ አህዮች ወንድና ሴት ባሪያዎች፣ ሴት
አህዮችና ግመሎች ሰጠው። 17 በአብራም ሚስት በሦራ ምክንያት ያህዌ ፈርዖንና ቤተ ሰቡን በታላቅ መቅሠፍት መታ። 18 ፈርዖን አብራምን አስጠርቶ እንዲህ
አለው፤ “ለመሆኑ ምን እያደረግህብኝ ነው? ሚስትህ መሆንዋን ለምን አልነገርከኝም? 19 ለምን እኅቴ ናት አልከኝ? እኅቴ ናት ስላልከኝ ሚስቴ ላደርጋት ነበር።
አሁንም ሚስትህ እቻት፤ ይዘሃት ሂድ” 20 ከዚያም ፈርዖን አብራምን በተመለከተ ለባለሟሎቹ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም አብራምን ከሚስቱና ከንብረቱ ሁሉ ጋር
አሰናበቱት።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 13

1 ስለዚህ አብራም ሚስቱንና ያለውን ንብረት ሁሉ ይዞ ከግብፅ ወደ ኔጌብ ሄደ። ሎጥም ከእነርሱ ጋር ነበረ። 2 በዚህ ጊዜ አብራም በከብት፣ በብርና በወርቅ
በልጽጎ ነበር። 3 ከኔጌብ ተነሥቶ እስከ ቤቴል ተጓዘ፤ ቀድሞ ድንኳን ተክሎበት ወደ ነበረው በቤቴልና በጋይ መካከል ወደ ነበረው ቦታ ደረሰ። 4 ይህ ቀድሞ
መሠዊያ የሠራበት ቦታ ሲሆን በዚያ ያህዌን ጠራ። 5 ከአብራም ጋር ይጓዝ የነበረው ሎጥ የራሱ በጎች፣ ከብቶችና ድንኳኖች ነበሩት። 6 ሁለቱ አንድ ላይ ይኖሩ
ስለ ነበር ስፍራው አልበቃቸውም፤ በዚህ ላይ ንብረታቸውም በጣም ብዙ ስለ ነበር አብረው መኖር አልቻሉም። 7 ይህም በመሆኑ በአብራምና በሎጥ እረኞች
መካከል ጠብ ተፈጠረ። በዚያ ዘመን ከነኣናውያንና ፌርዛውያን በዚያው አገር ይኖሩ ነበር። 8 አብራም ሎጥን እንዲህ አልው፤ “በእኔና በአንተ፣ በእኔ እረኞችና
በአንተ እረኞች መካከል ግጭት መኖር የለበትም፤ በዚህ ላይ ደግሞ ቤተ ሰብ ነን። 9 ይኸው እንደምታየው ምድሩ ሰፊ ነው፤ ብንለያይ ይሻላል። አንተ ግራውን
ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ ወይም አንተ ቀኙን ብትመርጥ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ። 10 ስለዚህ ሎጥ ዙሪያውን ሲመለከት እስከ ዞዓር ድረስ ያለው
የዮርዳኖስ ረባዳ ሜዳ ሁሉ እንደ ያህዌ ገነት እንደ የግብፅ ምድር በጣም ለም ሆኖ አገኘው። እንዲህ የነበረው እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ከማጥፋቱ በፊት
ነበር። 11 ሎጥ የዮርዳኖስን ረባዳ ሜዳ ሁሉ መርቶ ወደ ምሥራቅ ተጓዘ፤ በዚህ ሁኔታ ዘመዳሞቹ ተለያዩ። 12 አብራም መኖሪያውን በከነዓን ምድር አደረገ፤
ሎጥ ግን በረባዳው ሜዳ ባሉት ከተሞች መካከል ኖረ። እስከ ሰዶም ድረስ ባለው ቦታ ድንኳኖቹን ተከለ። 13 የሰዶም ሰዎች በጣም ዐመፀኞችና በያህዌም
ፊት እጅግ ኀጢአተኞች ነበሩ። 14 ሎጥ ከእርሱ ከተለየው በኋላ ያህዌ አብራምን እንዲህ አለው፤ “ካለህበት ቦታ ወደ ሰሜን፣ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና
ምዕራብ ተመልከት። 15 ይህን የምታየውን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁ። 16 ዘርህን እንደ ምድር ትቢያ አበዛዋለሁ፤ የምድር ትቢያ ሊቆጠር
እንደማይቻል ሁሉ የአንተም ዘር ሊቆጠር አይችልም። 17 እንግዲህ ምድሪቱን ስለምስጥህ ተነሣና በርዝመትና በስፋቱ ተመላለሰባት።” 18 ስለዚህ አብራም
ድንኳኑን ነቀለና በኬብሮን ወዳሉት የመምሬ ወርካ ዛፎች መጥቶ ኖረ፤ እዚያም ለያህዌ መሠዊያ ሠራ።

---

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 14

1 አምራፌል የሰናዖር ንጉሥ፣ አርዮክ የአላሳር ንጉሥ፣ ከሎደጎምር የኤላም ንጉሥ፣ ተድዓል የጎይም ንጉሥ፣ 2 በነበሩበት ዘመን፤ ከሰዶም ንጉሥ በላ፣ ከጎሞራ
ንጉሥ ከብርሳ፣ ከአዳማ ንጉሥ ከሰነአብ፣ ከሰቦይ ንጉሥ ከሰሜበር፣ እንዲሁም ዞዓር ከተባለች ከቤላ ንጉሥ ጋር ለመዋጋት ወጡ። 3 እነዚህ የኋለኞቹ አምስት
ነገሥታት የጨው ባሕር እየተባለች በምትጠራው በሲዶም ሸለቆ ተሰበሰቡ። 4 እነርሱም አሥራ ሁለት ዓመት ለኮሎዶጎምር ተገዙ፤ በአሥራ ሦስተኛው ዓመት ግን
ዐመፁ። 5 በአሥራ አራተኛው ዓመት ከሎዶጎምርና ከእርሱም ጋር የነበሩት ነገሥታት መጥተው ራፋይምን፣ በአስታሮት ቃርናይምን፣ በካም ዙዚምን፣ በሴዊ
ኑሚምን፣ በሸቮት ኢምንን፣ 6 የሖር ሰዎችንም በተራራማው አገር በሴይ በረሐማ አጠገብ እስካለው እስከ አልፋራን ድረስ ድል አደረጋቸው። 7 ከዚያም
ተመልሰው ዓይንሚስፓጥ ወደሚባለው ወደ ቃዴስ መጡ፤ የአማሌዋውያንና በሐሴስ ታማር ይኖሩ የነበሩትን የአሞራውያን ግዛት በሙሉ ድል አድርገው ያዙ። 8
ከዚያም የሶዶም፣ የገሞራ፣ የአዳማ፣ የሰቦይ እንዲሁም ዞዓር የተባለችው የቤላ ነገሥታት ወደ ሲዶም ሸለቆ ሄደው ለጦርነት ተዘጋጁ። 9 እነዚህ አምስቱ በኤላም
ንጉሥ በኮሎዶጎምር፣ በጎይም ንጉስ በቲድዓል፣ በሰናዖር ንጉሥ በአምራፌል፣ በአላሶር ንጉሥ በአርዮክ በእነዚህ ላይ ዘመቱባቸው። 10 በሲዲም ሸለቆ ብዙ
የቅጥራን ጉድጓዶች ነበሩ፤ የሰዶምና የጎመራ ነገሥታት ሲሸሹ ከሰዎቻቸው አንዳንዶቹ በእነዚህ ጉድጓዶች ውስጥ ወደቁ። የተረፉትም ወደ ተራሮች ሸሹ። 11
አራቱ ነገሥታትም በሰዶምና በጎሞራ ያገኙትን ሀብትና ምግብ ሁሉ ዘርፈው ሄዱ። 12 በሰዶም ይኖር የነበረውን የአብርሃምን ወንድም ልጅ ሎጥንና የነበረውን
ንብረት ሁሉ ይዘው ሄዱ። 13 ከዚያ ያመለጠ አንድ ሰው መጥቶ ለዕብራዊው ለአብራም ነገረው። በዚያ ጊዜ ይኖር የነበረው የአስኮና የእውናን ወንድም
በነበረው በአሞራዊው መምሬ ዋርካ ዛፎች አጠገብ ነበር፤ እነዚህ ሁሉ የአብራም አጋሮች ነበር። 14 ጠላት ዘመዶቹን ማርኮ መውሰዱን አብራም ሲሰማ በቤቱ
ተወልደው ያደጉ ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሰዎች ይዞ እስከ ዳን ድረስ ተከታተሏቸው። 15 አብራም ጠላቶቹን ለማጥቃት ሰራዊቱን ሌሊቱን በቡድን በቡድን
ከፋፍሎ ከደማስቆ በስተ ሰሜን እስከሚገኘው እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው። 16 ጠላት የማረከውን በሙሉ አስጣለ፤ ዘመዱ ሎጥንና ንብረቱን፣ እንዲሁም
ሴቶቹንና ሌሎች ሰዎችን አስመለሰ። 17 አብራም የኮሎዶጎምርንና ከእርሱ ጋር የነበሩ ነገሥታትን ድል አድርጎ ሲመለስ የሰዶም ንጉሥ የንጉሥ ሸለቆ ተብሎ
በሚጠራው በሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ። 18 የሰሌም ንጉሥ መልከጼዴቅ እንጀራና ወይን ጠጅ ይዞ መጣ። እርሱ የልዑል አምላክ ካህን ነበር። 19 አብራምም
እንዲህ በማለት ባረከው፣ “ሰማይና ምድርን የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር አብራምን ይባርክ። 20 ጠላቶችህን በእጅህ አሳልፎ የሰጠ ልዑል እግዚአብሔር
ይባረክ።” አብራምም ይዞት ከነበረው ሁሉ አንድ አሥረኛውን ሰጠው። 21 የሰዶም ንጉሥ አብራምን፣ “ሰዎቹን ለእኔ ስጠኝ፤ ንብረቱን ግን ለራስህ አስቀር”
አለው። 22 አብራምም ለሰዶም ንጉሥ እንዲህ አለው፤ “ከአንተ ብጣሽ ክርም ሆነ የጫማ ማሰሪያ እንኳ ቢሆን፣ 23 ደግሞም ‘አብራምን ባለጸጋ አደረግሁት’
እንዳትል የአንተ ከሆነ ምንም ነገር እንዳልወስድ ሰማይና ምድርን ወደ ፈጠረ አምላክ ወደ ያህዌ እጄን አንሥቻለሁ። 24 አብረውኝ ያሉት ሰዎች ከበሉትና
የእነርሱ ድርሻ ከሆነው በቀር ምንም ነገር አልወስድም። አውናን፣ ኤስኩልና መምሬ ድርሻቸውን ይውሰዱ።”

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 15

1 ከዚህ በኋላ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ አብራም መጣ፤ “አብራም ሆይ፣ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤ ታላቅ ሽልማትህም እኔው ነን።” 2 አብራምም፣
“ጌታ ያህዌ ሆይ፣ እኔ ልጅ የለኝም፤ የቤት ወራሽ የሚሆነው የደማስቆው ሰው ኤሊዔዘር ነው፤ ታዲያ አንተ ለእኔ የምትሰጠኝ ምንድን ነው?” አለ። 3
በመቀጠልም አብራም “አንተ ልጅ እስካልሰጠኸኝ ድረስ፣ ከቤቴ አገልጋይ አንዱ ወራሼ መሆኑ አይቀርም” አለ። 4 በዚህ ጊዜ የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እርሱ መጣ፤ “ይህ ሰው ወራሽህ አይሆንም፤ ይልቁንም ወራሽህ የሚሆነው ከአብራክህ የሚከፈል የራስህ ልጅ ይሆናል።” 5 ከዚያም ወደ ውጭ አወጣውና
እንዲህ አለው፤ “ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤ መቍጠር ከቻልህ ከዋክብቱን ቍጠር። ዘርህም እንዲሁ ይበዛል።” 6 አብራም ያህዌን አመነ፤ እርሱም
ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት። 7 እንዲህም አለው፤ “ይህችን ምድር እንድትወርስ ልሰጥህ ከከለዳውያን ምድር ከዑር ያወጣሁህ እኔ ያህዌ ነኝ።” 8 አብራምም፣
“ጌታ ያህዌ ሆይ፣ ይህችን ምድር እንደምወርስ እንዴት አውቃለሁ?” አለ። 9 በዚህ ጊዜ፣ “እያንዳንዳቸው ሦስት ዓመት የሆናቸው አንዲት ጊደር፣ አንዲት ፍየልና
አንድ በግ እንዲሁም ዋኖስና አንድ ርግብ አቅርብልኝ” አለው። 10 እርሱም እነዚህን ሁሉ አቀረበለት፤ ቆርጦም ሁለት ቦታ ከከፈላቸው በኋላ እያንዳንዱን ክፍል
በሌላው ወገን ትይዩ አስቀመጣቸው፤ ወፎቹን ግን አልከፈላቸውም። 11 አሞሮች ሥጋውን ለመብላት ወረዱ፤ አብራምም አባረራቸው። 12 ፀሓይ ልትጠልቅ
ስትል አብራም ከባድ እንቅልፍ ወሰደው፤ የሚያስፈራም ድቅድቅ ጨለማም መጣበት። 13 በዚህ ጊዜ ያህዌ አብራምን እንዲህ አለው፤ “ዘሮችህ የራሳቸው
ባልሆነ ምድር ባዕድ እንደሚሆኑና እዚያ ለአራቶ መቶ ዓመት በባርነት እንደሚኖሩ በእርግጥ ዕወቅ። 14 እኔም ባሪያዎች ባደረጓቸው ሕዝብ እፈርዳለሁ፤ በኋላም
ብዙ ሀብት ይዘው ይወጣሉ። 15 አንተ ግን በሰላም ወደ አባቶችህ ትሄዳለህ፤ ዕድሜም ጠግበህ ትቀበራለህ። 16 በአራተኛውም ትውልድ እንደ ገና ወደዚህ
ይመጣሉ፤ ምክንያቱም የአሞራውያን ኀጢአት ጽዋው ገና አልሞላም።” 17 ፀሓይ ገብታ ከጨለመ በኋላ የምድጃ ጢስና የሚንበለበል ፋና በተቆራረጡት
ሥጋዎች መካከል አለፈ። 18 በዚያን ቀን ያህዌ እንዲህ በማለት ከአብራም ጋር ኪዳን አደረገ፤ “ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ ኤፍራጥስ ድረስ
ያለውን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ፤ 19 የምሰጣቸውም የቄናውያንን፣ የቄንፌዛውያንን፣ የቃድሞናውያንን፣ 20 የኬጢያውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የራፋይምን፣ 21
የአሞራውያንን፣ የከነዓናውያን፣ የጌርሳውያንንና የኢያቡሳውያን ምድር ነው።”

---

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 16

1 የአብራም ሚስት ሦራ ልጅ አልወለደችለትም ነበር፤ ነገር ግን አጋር የምትባል ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት። 2 አብራምንም፣ "ያህዌ ልጅ እንዳልወደልድ
አድርጎኛል። ምናልባት በእርሷ በኩል ልጅ አገኝ ይሆናልና ክአገልጋዬ ጋር ተኛ" አለችው። አብራም ሦራ በነገረችው ተስማማ። 3 የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት
አገልጋይዋ ሚስት እንድትሆነው ለአብራም የሰጠችው አብራም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከኖረ በኋላ ነበር። 4 አብራም ክአጋር ግን'ኙንት አደረገ እርሷም
ፀነሰች። አጋር መፅነሷን ባወቀች ጊዜ እመቤቷን በንቀት ማየት ጀመረች። 5 በዚህ ጊዜ ሦራ አብራምን፣ "ይህ በደል የደረሰብኝ በአንተ ምክንያት ነው። ኀቅፍህ
ውስጥ እንድትሆን አገልጋዬን ሰጠሁ፤ እርሷ ግን መፅነሷን ስታውቅ እኔን መናቅ ጀመረች። ያህዌ በእኔና በአንተ መካከ ይፍረድ" አለችው። 6 አብራምም መልሶ
ሦራን፣ "አገልጋይሽ እኮ በእጅሽ ውስጥ ናት እርሷ ላይ የፈለግሽውን ማድረግ ትችያልለሽ" አላት። ስለዚህ ሦራ ስላሠቃየቻት፣ አጋር ከቤት ጠፍታ ሄደች። 7
የያህዌ መልአክ አጋርን ምድረ በዳ ውስጥ በነበረ አንድ ምንጭ አጠገብ አገኛት፤ ያ ምንጭ ወደ ሱር በሚወስደው መንገድ ላይ ነበር። 8 መልአኩም፣ "የሦራ
አገልጋይ አጋር ሆይ፣ ከየት መጣሽ ወዴትስ እየሄድሽ ነው?" አላት። እርሷም፣ "ከእመቤቴ ከሦራ ኮብልዬ እየሄድሁ ነው" አለችው። 9 የያህዌ መልአክ፣ "ወደ
እመቤትሽ ተመለሺ፤ ራስሽንም ለሥልጣንዋ አስገዢ" አላት። 10 ከዚያም የያህዌ መልአክ፣ "ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ፤ ከበምዛቱም የተነሣ ሊቆጠር
አይቻልም" አላት። 11 የያህዌም መልአክ በተጨማሪ እንዲህ አላት፤ "እነሆ ፀንሰሻል ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ያህዌ ችግርሽን ሰምቷልና ስሙን እስማኤል
ትዪዋለሽ። 12 እርሱ እንደ ዱር አህያ ይሆናል። ከሰው ሁሉ ጋር ይጣላል፤ ሰው ሁሉም ከእርሱ ጋር ይጣላል፤ ከወንድሞቹ ሁሉ ተነጥሎ ይኖራል።" 13 እርሷም
ይሚያናግራትን ያህዌን፣ "አንተኮ እኔን የምታይ አምላክ ነህ"በማለት ጠራችው፤ ምክንያቱም፥ "እርሱ እኔን እንዳየ ሁሉ እኔም እርሱን አየው ይሆን?" ብላ ነበር።
14 ስለዚህ ያ ምንጭ ብኤርልያህሮኢ ተባለ፤ የሚገኘው በቃዴስና በባሬድ መካከ ልነው። 15 አጋር ለአብራም ወድን ልጅ ወለደችለው፤ አብራምም አጋር
የወለደችለትን ልጅ እስማኤል ብሎ ጠራው። 16 አጋር እስማኤልን በወለደች ጊዜ አብራም ሰማንያ ስድስት ዓመት ሆኖት ነበር።

Chapter 17

1 አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው እያለ ያህዌ ተገለጠለትና እንዲህ አለው፤ "እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ ነቀፋም አይኑርብህ። 2 በእኔና
በአንተ መካከል የተደረገውን ኪዳን አጸናለሁ፤ አንተንም እጅግ አበዛሃለሁ።" 3 አብራም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤ እግዚአበሔርም እንዲ አለው፤ 4 "እነሆ
ኪዳኔ ክአንተ ጋር ነው። የብዙ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ። 5 ከእንግዲህ ስምህ አብራም መባል የለበትም፤ ስምህ አብርሃም መባል እለበት፤ ምክንያቱም የብዙ
ሕዝብ አባት አድርጌሃለሁ። 6 እጅግ አበዛሃለሁ፣ ሕዝቦች ክአንተ ይገኛሉ፤ ነገሥታትም ክአንተ ይወጣሉ። 7 በእኔና በአንተ፣ ክአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር ኪዳኔን
እመሠርታለሁ፤ ለአንተ ከአንተም በኋላ ለዘርህ በዘላለም ኪዳን አምላክ እሆናችኋለሁ። 8 ለአንተና ከአንተም በኋላ ለዘርህ ይህች አሁን የምትኖርባትን የከነዓንን
ምድር በሙሉ ለዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣላለሁ፤ አምላካቸውም እሆናለሁ።" 9 ከዚያም እግዚአብሔር አብርሃምን፣ "በአንተም በኩል፣ አንተና ከአንተ በኋላ
የሚመጣው ዘርህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ኪዳኔን መጠበቅ አለባችሁ። 10 በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በእኔና በዘርህ መካከል መጠበቅ
ያለባችሁ ኪዳኔ ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያለ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። 11 እናንተ ሸለፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእናንተ መካከል ያለው ኪዳን ምልክት
ይሆናል። 12 በመካከላችሁ ያለው ማንኛውም ስምንት ዓመት የሞላው ወንድ የሚመጣው ትውልድ ሁሉ ይገረዝ። ይህ በቤትህ የተወለደውን በገንዘብህ
የተገዛውን ሁሉ ይጨምራል። 13 ቤትህ ውስጥ የተወለደና በገንዘብህ የገዛኸው መገረዝ አለባቸው። ስለሆነም ኪዳኔ በዘላለም ኪዳን ሥጋችሁ ላይ ይሆናል።
14 ሸለፈቱን ያልተገረዘ ማንኛውም ወንድ ኪዳኔን አፍርሷልና ከወገኖቹ ይወገድ።" 15 እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው፤ "ሚስትህ ሦራን ክአንግዲህ
ሥራ እንጂ ሦራ ብለህ አትጥራት። 16 እባርክሃለሁ፤ ከእርሷ ወንድ ልጅ እሰጥሃለሁ። እባርካታለሁ። እርሷም የብዙ ሕዝብ እናት ትሆናለች፤ የሕዝቦችም ነገሥታት
ክአርሷ ይወጣሉ። 17 በዚህ ጊዜ አብርሃም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፍቶ እየሳቀ በሉ እንዲህ አለ፤ "ለመሆኑ የመቶ ዓመት ሽማግሌ ልጅ መውልደድ ይችላል?
የዘጠና ዓመቷ አሮጊት ሥራስ ብትሆን ልጅ መውለድ ይሆንላታል?" 18 አብርሃም እግዚአብሔርን፣ "ይልቅ፣ እስማኤልን ብቻ ባኖርህልኝ!" አለ። 19
እግዚአብሔርም፣ "እንደዚያ አይደለም፤ ሚስትህ ሥራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ። የዘላለም ኪዳኔን ከእርሱ ጋር፣
ከእርሱም በኋላ ከዘሩ ጋር እመጸርታለሁ። 20 እስማኤልን በተመለከተም ልምናህን ሰምቻለሁ። እነሆ እርሱንም እባርከዋለሁ፤ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፤ እጅግም
አበዛዋለሁ። የአሥራ ሁለት ነገዶች አባት ይሆናል፤ ታላቅ ሕዝብ እንዲሆንም አደርጋለሁ። 21 ኪዳኔን ግን፣ የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ሣራ ከምትወልድህል
ከይስሐቅ ጋር እመሠርታለሁ።" 22 ከእርሱ ጋር መነጋገሩን ከጨረሰ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ላይ ወጣ። 23 በዚያኑ ዕለት አብርሃም ልጁ ይስሐቅን፣ በቤቱ
ውስጥ የተወለዱትን በሙሉ፣ በገንዘቡ የገዛቸውን ሁሉ፣ ቤቱ ውስጥ ያለ ማንኛውንም ወንድ ሁሉ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት ገረዛቸው። 24 አብርሃም
በተገረዘ ጊዜ እድሜው ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ነበር። 25 ልጁም እስማኤል በተገረዘ ጊዜ እድሜው አሥራ ሦስት ነበር። 26 በዚያው ቀን አብርሃምና ልጁ
እስማኤልም ተገረዙ። 27 ቤቱ ውስጥ የተወለዱትን፣ ከውጭ በገንዘብ የተገዙትን ጨምሮ ቤቱ ውስጥ የነበሩ ወንዶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ተገረዙ።

Chapter 18

1 ቀኑ በጣም ሞቃት በሆነ ጊዜ አብርሃም በመምሬ ወርካ ዛፎች አቅራቢይ ኣድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ እያለ ያህዌ ተገለጥለት። 2 እርሱም ቀና ብሎ ሦስት ሰዎች
ፊት ለፊቱ ቆመው አየ። ባያቸውም ጊዜ ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ፈጥኖ ወደ እነርሱ ሄዶ፣ ወደ መሬት ዝቅ ብሎም እጅ ነሣ። 3 አብርሃም እንዲህ አለ፤ "ጌታዬ፣
በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ ባሪያህን አልፈህ አትሂድ። 4 ጥቂት ውሃ ትምጣላችሁና እግራችሁን ታጠቡ፤ ከዚያም ዛፉ ሥር ዐረፍ በሉ። 5 ወደ እኔ
ወዳገልጋያችሁ ከመጣችሁ የደከመ ሰውነታችሁ እንዲበረታ እስቲ ጥቂት እህል ላምጣላችሁና ብሉ፤ ከዚያ ጉዞአችሁን ትቀጥላላችሁ።" እነርሱም.
"እንዳልኸው አድርግ" አሉት። 6 ያኔውኑ አብርሃም በፍጥነት ሣራ ወደ ነበረችበት ድንኳን ገብቶ፣ "ቶሎ ብለሽ ሦስት መስፈሪያ ስልቅ ዱቄት አቡኪና ቂጣ
ጋግሪ" አላት። 7 ከዚያም ወደ መንጋው በፍጥነት ሄዶ አንድ ፍርጥም ያለ ሥጋው ግን ገር የሆነ ጥጃ መረጠና ለአገልጋዩ ሰጠው፤ እርሱም በአስቸኳይ
አደረሰው። 8 አብርሃምም እግሮ፣ ወተትና የተዘጋጀውን የጥጃ ሥጋ አቀበላቸው፤ እነርሱ እየበሉ እያለ እርሱ ዛፉ ሥር አጠገባቸው ቆሞ ነበር። 9 እነርሱም እንዲህ
አሉት፤ "ሚስትህ ሥራ የታለች?" እርሱም፣ "ድንኳን ውስጥ ናት" አለ። 10 እነርሱም፣ "የዛሬ ዓመት በፀደይ ወቅት ልክ በዚሁ ጊዜ በእርግጥ ተመልሼ
እመጣለሁ፤ ሚስትህ ሥራ ልጅ ትወልዳለች" አለ። ሥራ ከጀርባ በነበረው ድንኳን ደጃፍ ሆና ታዳምጥ ነበር። 11 በዚህ ጊዜ አብርሃምና ሥራ በጣም አርጅተው
ነበር፤ ሥራማ ልጅ የመውለጃ ጊዜ አልፎባት ነበር። 12 ስለዚህ ሣራ በልቧ፣ "ይህን ያህል ካረጀሁና ጌታዬም ከደከመ በኋላ በዚህ ነገር መደሰት ይሆንልኛልን?"
ብላ ሳቀች። 13 ያህዌ አብርሃምን እንዲህ አለው፤ "ካረጀሁ በኋላ እንዴት አድርጌ ልጅ እወልዳለሁ ስትል ሣራ የሳቀችው ለምንድን ነው? 14 ለመሆኑ ለያህዌ
የሚሳነው ነገር አለ? እኔ በወሰንሁት የፀደይ ወቅት ወደ እናንተ እመለሳለህ፤ በሚመጣው ዓመት በዚህ ጊዜ ሥራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች።" 15 ሣራ ግን ፈርታ
ስል ነበር፣ "ኧረ እልሳቅሁም" በማለት ካደች። እርሱም፣ "የለም፤ ስቀሻል እንጂ" አላት። 16 ሰዎቹ ለመሄድ ሲነሡ ቁልቁል ወደ ሰዶም ተመለከቱ። አብርሃምም
ሊሸኛቸው ከእነርሱ ጋር ሄደ። 17 በዚህ ጊዜ ያህዌ እንዲህ አለ፤ "እኔ የማደርገውን ክአብርሃም መደበቅ አለብኝን? 18 አብርሃም በእርግጥ ታላቅና ብርቱ ሕዝብ
ይህሆናል፤ የምድር ሕዝቦችም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ። 19 ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የያህዌን መንገድ እንዲጠብቁ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቡን
እንዲያስተምር እኔ አብርሃምን መርጬዋለሁ፤ ይኸውም ለአብርሃም የነገረውን ሁሉ ያህዌ እንዲፈጽምለት ነው።" 20 ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤
"በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ክስ በጣም ስለ በዛ፣ ኀጢአታቸውም በጣም ትልቅ ስል ሆነ፤ 21 ወደ እኔ የመጡ ክሶች ምን ያህል እውነት መሆናቸውን
ለማየት ወደዚያ እወርዳለሁ፤ እንደዚይ ካልሆነም አውቃለሁ።" 22 ሰዎቹም ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅንተው ሄዱ፤ አብርሃም ግን ያህዌ ፊት እንደ ቆመ ነበር።
23 አብርሃም ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ፣ "በእርግጥ ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር ታጠፋለህን? 24 ምናልባት በከተማዋ ሃምሳ ጻድቃን ቢገኙስ? እዚያ ባሉ ጻድቃን
ስትል ከተማዋን ሳታድን ታጠፋታለህን? 25 ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር በመግደል፣ ኀጢአተኛ ላይ የደረሰው በእርሱም እንዲደርስ ማድረግን የመሰለ ንገር
ከአንተ ይራቅ! እንዲህ ያለው ከአንተ ይራቅ! የምድር ሁሉ ዳኛ እውነተኛ ጻድቅ የሆነውን አያደርግምን? 26 ያህዌም እንዲህ አለ፤ "በሰዶም ከተማ ውስጥ
ሃምሳ ጻድቃን ካገኘሁ ፣ ለእነርሱ ስል ያንን ቦታ እምራለሁ።" 27 አብርሃምም መልሶ እንዲህ አለ፤ "እኔ ትቢያና ዐመድ ሆኜ ሳለሁ ከጌታዬ ጋር ለመናገር አንዴ
ደፍሬአለሁ፤ 28 ለመሆኑ ከአምሳዎቹ ጻድቃን አምስት ቢጎድሉ፣ በጎደሉት አምስቱ ምክንያት ከተማዋን በሙሉ ታጠፋለህን?" እርሱም፣ "እዚያ አርባ አምስ
ጻድቃንካገኘሁ አላጠፋትም" አለ። 29 አብርሃምም እንደ ገና፣ "ምናልባት አርባ ጻድቃን ቢገኙስ?" እለ፤ እርሱም፣ "ለአርባዎቹ ስል አላደርገውም" እለ። 30
አብርሃምም፣ "እባክህን ጌታዬ ይህን ያህል በመናገሬ አትቆጣኝ። እንደው ምናልባት ሰለሣ ቢገኙስ" አለ። እርሱም መልሶ፣ "ሰላሣ ጻድቃን ካገኘሁ
አላደርገውም" በማለት መለሰ። 31 አብርሃምም፣ "መቼም አንዴ ከጌታዬ ጋር መናገር ጀምሬአለሁ! እንደው ምናልባት ሃያ ቢገኙስ" አለ። እርሱም መልሶ፥
"ለሃያዎቹ ስል አላደርገውም" አለ። 32 በመጨረሻም እንዲህ አለ፤ "እባክህ ጌታዬ አትቆጣኝ፤ አንዴ ብቻ ልናገር፤ ምናልባት አሥር ቢገኙስ። እርሱም፣
"ለአሥሩ፣ ሲል አላጠፋትም" አለ። 33 ከአብርሃም ጋር መነጋገሩን እንደ ጨረሰ ያህዌ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

Chapter 19

1 ሁለቱ መላእክት ምሽት ላይ ወደ ሰዶም መጡ፤ በሰዶም ከተማ መግቢያበር ላይ ተቀምጦ ነበር። ሎጥ ሲያያቸው ሊቀበላቸው ተነሣ፤ በግንባሩም መሬት ላይ
ተደፋ። 2 እርሱም፣ "እባካችሁ ጌቶቼ ወደ እኔ ወደ ባሪያችሁ ቤት ጎራ በሉ፤ እግራችሁን ታጠቡ፤ ሌሊቱንም ከእኛ ጋር አሳልፉ፤ ከዚያ ጧት በማለዳ ተነሥታችሁ
ጉዞአችሁን ትቀጥላላችሁ።" እነርሱም፣ "የለም፤ እዚሁ አደባባዩ ላይ እናድራለን" አሉት። 3 ሎጥ ግን አጥብቆ ስለ ለመናቸው እርሱ ቤት ለማደር አብረውት
ገቡ። ከዚያም ቂጣ ጋግሮ አቀረበላቸው፤ እነርሱም በሉ። 4 ሆኖም፣ ገና ከመተኛታቸው በፊት የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ወጣቶችና ሽማግሌዎች
ከየአካባቢው መጥተው ቤቱን ከበቡት። 5 ሎጥን በመጣራት፣ "በዚህ ምሽት ወደ ቤትህ የመጡ ሰዎች የታሉ? ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው ወደ ውጭ
አውጣልን" አሉት። 6 ሎጥ ሊያነጋግራቸው ወደ ውጭ ወጣ መዝጊያውን ከበስተ ኋላው ዘጋ። 7 እንዲህም አለ፤ "ወንድሞቼ እንዲህ ያለ ክፉ ነገር እንዳታደርጉ
እለምናችኋለሁ። 8 ከወንድ ጋር ተኝተው የማያውቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ፤ እነርሱን ላውጣላችሁና የወደዳችሁትን አድርጉባቸው። በእነዚህ ሰዎች ላይ ግን
ምንም ነገር አታድርጉባቸው፤ እኔን ብለው ወደ ቤቴ ተብተዋልና።" 9 እነርሱ ግን፣ "ዞር በል!" ይኸ ሰውዬ ስደተኛ ሆኖ እዚህ ለመኖር መጣ፤ ደግሞ ዳኛ
ሆነብን! ይልቁ በእነርሱ ላይ ካሰብነው የከፋ እንዳይደርስብህ ዘወር በልልን" አሉት ሎጥንም እየገፈታተሩ የበሩን መዝጊያ ለመስበር ተቃርበው ነበር። 10
ሰዎቹ እጃቸውን ዘርግተው ሎጥን ወደ ቤት አስገቡትና በሩን ዘጉ። 11 ከቤቱ ውጪ የነበሩትን ውጣቶችንም ሆን ሽማግሌዎችን ግን የሎጥ እንግዶች
ዐይናቸውን አሳወሩአቸው፤ እነርሱም በሩን ለማግኘት ይደነባበሩ ጀመር። 12 ከዚያም ሰዎቹ ሎጥን እንዲህ አሉት፤ "በከተማዋ የሚኖሩ የአንተ የሆኑ ሰዎች
አሉህ? ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን፣ የወንዶች ልጆችህን ሚስቶች፣ የሴቶች ልጆችህን ባሎችና ሌሎች ዘመዶችህን ሁሉ ከዚህ አውጣ። 13 ምክንያቱም ይህን
ቦታ ልናጠፋ ነው፤ በያህዌ ፊት ከተማዋ ላይ የሚቀርቡ ክሶች በጣም እየጮኹ በመሆናቸው እንድናጠፋት እርሱ ልኮናል።" 14 ሎጥ ከቤቱ ወጥቶ የሴት
ልጆቹን ባሎች፣ የሴት ልጆቹን እጮኞች፣ "ቶሎ ከዚህ ቦታ ውጡ፤ ያህዌ ከተማዋን ሊያጠፋ ነው" አላቸው። የሴት ልጆቹ ባሎች ግን የሚቀልድ መሰላቸው። 15
ሲነጋጋም መላእክቱ ሎጥን፣ "ከተተማዋ ላይ በሚመጣው ቅጣት አብራችሁ እንዳትጠፉ ሚስትህንና ሁለቱ ሴት ልጆችህን ይዘህ ከዚህ ቦታ በፍጥነት ውጣ"
እያሉ አቻኮሉት። 16 ሎጥ አመነታ፤ ያህዌ ምሕረት ስላደረገላቸው ሰዎቹ የእርሱ፣ የሚስቱንና የሁለት ሴት ልጆቹን እጅ ይዘው ከከተማዋ አወጣቸው። 17
ከከተማው ካወጧቸው በኋላ ከሰዎቹ አንዱ፣ "ሕይወታችሁን ለማዳን ሩጡ! ወደ ኋላችሁ አትመልከቱ፤ ወይም ረባዳው ስፍራ ላይ አትቆዩ። ወደ ተራሮች ሽሹ፤
አለበለዚያ ትጠፋላችሁ።" 18 ሎጥም እንዲህ አላቸው፤ "ጌቶቼ ሆይ፣ 19 እኔ ባሪያችሁ በፊታችሁ ሞገስ አግኝቻለሁ፤ ሕይወቴን ለማዳን ታላቅ ርኅራኄ
አድርጋችሁልኛል፤ እኔ እንደ ሆንኩ ወደ ተራሮቹ ሸሽቼ ማምለጥ ስለማልችል የሚወርደው መዓት ደርሶ ያጠፋኛል። 20 ወደዚያ ሸሽቶ ለማምለጥ ቅርብ ቦታ ያለች
ትንሽ ከተማ አለች ሸሽቼ ወደዚያ ብሄድ ሕይወቴን ማዳን እችላለሁ።" 21 እርሱም፣ "ይሁን እሺ፤ ልመናህን ተቀብብያለሁ፤ ያክካትንም ከተማ አላጠፋትም። 22
አንተ እዚያ እስክትደርስ ምንም ማድረግ ስለማልችል በል ቶሎ ፍጠንና ወደዚያ ሽሽ" አለው። ስለዚህ ያቺ ከተማ ዞዓር ተባለች። 23 ሎጥ ዞዓር ሲደርስ ፀሓይ
በምድሩ ወጥታ ነበር። 24 ከዚያ ያህዌ ሰዶምና ጎሞራ ላይ ድኝና እሳት አዘነበ። 25 እነዚያን ከተሞችና ረባዳ ቦታዎቹን፣ የከተሞቹ ነዋሪዎችንና እዚይ ኣያሉ
ለምለም ነገሮችን ሁሉ አጠፋ። 26 ከኋላው የነበረችው የሎጥሚስት ግን ወደ ኋላዋ ስለ ተመለከተች የጨው ዐምድ ሆና ቀረች። 27 አብርሃም ጠዋት ማለዳ
ተነሥቶ ያህዌ ፊት ቆሞ ወደ ነበረበት ቦታ ሄደ። 28 ቁልቁል ሰዶምና ጎሞራን፣ እንዲሁም በረባዳው ስፍራ የነበረውን ምድር ተመለከተ። ከምድጃ የሚወጣ
የመሰለ ጢስ ከምድሩ እየወጣ ነበር። 29 እግዚአብሔር በረባዳው ቦታ የነበሩ ከተሞችን ባጠፋ ጊዜ አብርሃምን አሰበው። ሎጥ የነበረበትን ከተሞች
ቢያጠፋም፣ እርሱ ግን ከጥፋት መሐል አወጣው። 30 ሎጥ ግን በዞዓር መኖር ስለ ፈራ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር ተራሮቹ ላይ ለመኖር ከዞዓር ወደ ላይ ወጣ።
ስለዚህ እርሱና ሁለት ሴቶች ልጆቹ ዋሻ ውስጥኖሩ። 31 ታላቋ ልጅ ታናሺን እንዲህ አለቻት፣ "አባታችን አርጅቷል፤ በምድር ሁሉ እንደሚኖሩ ሰዎች ወግ ከእኛ
ጋር የሚተኛ ወንድ በአካባቢያችን የለም። 32 ስለዚህ አባታችንን የወይን ጠጅ እናጠጣውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፤ የትውልድ ሐረጋችን እንዳይቋረጥ ከአባታችን
ዘር እናትርፍ።" 33 ስለዚህ በዚያ ምሽት አባታቸውን የወይን ጠጅ አጠጡት። ታላቂቱ ልጅ ሄዳ ክአባቷ ጋር ተኛች፤ እርሷ ስትተኛም ሆነ ስትነሣ አላወቅም። 34
በሚቀጥለው ቀን ታላቂቱ ታናሺቱን እንዲህ አለቻት፤ "ትናንት ሌሊት እኔ ከእባቴ ጋር ተኛሁ። ዛሬም እንደ ገና የወይን ጠጅ እናጠጣው፣ ከዚያ አንቺ ሄደሽ ከእርሱ
ጋር ትተኛለሽ፣ የአባታችንንም ዘር እናተርፋለን።" 35 ስለዚህ በዚያም ምሽት አባታቸውን ወይን ጠጅ አጠጡት፤ ታናሺቱ ልጅ ሄዳ ከእርሱ ጋር ተኛች፤ እርሷ
ስትተኛም ሆነ ስትነሣ አላወቀም። 36 ሁለቱ የሎጥ ልጆች ክአባታቸው አረገዙ። 37 ታላቂቱ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሞዓብ አለችው። እርሱም ዛሬ ያሉት
ሞዓባውያን አባት ሆነ። 38 ታናሺቱም እንዲሁ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ቤንአሚ አለችው። እርሱም ዛሬ ያሉት አሞናውያን አባት ሆነ።

Chapter 20

1 አብርሃም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ኔጌብ አካብቢ ሄደ፤ በቃዴስና በሱር መካከልም መኖር ጀመረ። ለጥቂት ጊዜ በጌራራ ተቀመጠ። 2 አብርሃም ሚስቱ ሥራራን፣
"እኅቴ ናት" ይል ነበር፤ ስለዚህ ይጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክ ሰዎች ልኮ ሣራን ወሰዳት። 3 እግዚአብሔር ግን በሕልም ወደ እቢሜሌክ መጥቶ፣ "እነሆ
በወሰድካት ሴት ምክንያት አንተ ምውት ነህ፤ ምክንያቱም እርሷ ባለ ባል ናት" አለው። 4 አቢሜሌክ ገና አልሰረሰባትም ነበርና እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ፣ በደል
ያልተገኘበትን ሕዝብ ልታጠፋ ነውን? 5 'እኅቴ ናት' ያለኝ እርሱ ራሱ አይደለምን? እርሷም ብትሆን 'ወንድሜ ነው' ብላኛለች። እኔ እንዲህ ያደረግሁት በቅን
ልቦናና በንጹሕ እጅ ነው።" 6 በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሕልም እንዲህ አለው፤ "አዎን፣ ይህን ያደረግኸው በልብ ቅንነት እንደ ነበር እኔም አውቃለሁ፤ እኔ ላይ
ኀጢአት እንዳትፈጽም የጠበቅሁህና እንዳትነካትም ያደረግሁት በዚህ ምክንያት ነው፤ 7 ስለዚህ የሰውየውን ሚስት መልስለት፤ እርሱ ነቢይ ስለ ሆነ
ይጸልይልሃል አንተም ትድናለህ። እርሷን ካልመለስህ፣ እንተና የአንተ የሆነው ሁሉ በእርግጥ እንደምትጠፉ ዐውቃለሁ።" 8 አቤሜሊክ ጧት በማለዳ ተነሥቶ
ሹማምንቶቹን ሁሉ ጠራ። የሆነውን ሁሉ ሲነግራቸው በጣም ፈሩ። 9 ከዚያም አቤሜሌ አብርሃምን አስጠርቶ፣ "ለመሆኑ፣ ምን እያደረግህብን ነው? በእኔና
በግዛቴ ላይ እንዲህ ያለውን ትልቅ መዘዝ ያመጣህብኝ ምን ብበድልህ ነው? መደረግ ያልነበረትን አድርገህብኛል" አለው። 10 በመቀጠልም፣ አብርሃምን፣
"እንዲህ እንድታደርግ ያነሣሣህ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። 11 አብርሃምም፣ "በዚህ ቦታ እግዚአብሔርን መፍራት የለም፤ ለሚስቴ ሲሉ ይገድሉኛል በማለት
ስላሰብሁ ነው። 12 በዚህ ላይ ደግሞ ከእናቴ ባትወለድም የአባቴ ልጅ እኅቴ ናት፤ በኋላም ሚስቴ ሆነች። 13 የአባቴን ቤት ትቼ በየአገሩ እንድዞር እግዚአብሔር
ሲያዝዘኝ፣ "ለእኔ ለባልሽ ያለሽን ታማኝነት በዚህ አሳዪኝ፤ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ 'ወንድሜ ነው' በዪ አልኳት።" 14 ከዚያ አቤሜሊክ በጎችና በሬዎች፣
ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ለአብርሃም ሰጠው። ሚስቱ ሣራንም ለአብርሃም መለሰለት። 15 አቤሜሌክ እንዲህ አለ፤ "አገሬ አገርህ ነው፤ ደስ በሚያሰኝህ ቦታ
ተቀመጥ።" 16 ሣራንም፣ "ለወንድምሽ አንድ ሺህ ጥሬ ብር እሰጠዋለሁ። ይህም፣ በአንቺ ላይ ለተፈጸመው በደል ካሣ እንዲሆንና አብረውሽ ያሉ ሁሉ አንቺ
ንጹሕ ሴት መሆንሽን እንዲያውቁ ነው።" 17 ከዚያም አብርሃም ለአቤሜሌክ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን፣ ሚስቱንና ሴት አገልጋዮቹን ፈወሳቸው፤ ልጅ
ለመውለድም በቁ። 18 ከአብርሃም ሚስት ከሣራ የተነሣ በአቢሜሌክ ቤት የሚገኙ ሴቶችን ሁሉ ያህዌ ማኅፀናቸውን ዘግቶ ነበር።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 21

1 ለአብርሃም በሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት እግዚአብሔር ሳራን አሰባት፤ እንደገባላት የተስፋ ቃልም አደረገ ፤ 2 ስለዚህም ሳራ አርግዛ በእርጅናው ጊዜ
ለአብርሃም ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ልጁም የተወለደው «በዚህ ጊዜ ይወለዳል» ብሎ እግዚአብሔር በተናገረበት ጊዜ ነው። 3 አብርሃም ሚስቱ ሳራ
የወለደችለትን ልጅ «ይስሐቅ» ብሎ ስም አወጣለት። 4 ይስሐቅ ከተወለደ ከስምንት ቀን በኋላ እግዚአብሔር ባዘዘው መሰረት አብርሃም ገረዘው። 5 ልጁ
ይስሐቅ በተወለደለት ጊዜ አብርሃም መቶ ዓመት ሆኖት ነበር። 6 ሳራም «እግዚአብሔር ሳቅ አደረገልኝ ስለዚህ ይህንን ነገር የሚሰማ ሁሉ ከእኔ ጋር
ይስቃል»አለች። 7 ቀጥላም «ሳራ ለአብርሃም ልጆችን ወልዳ ታጠባለች» ብሎ የሚናገር ከቶ ማን ነበር አሁን ግን እነሆ በእርጅናው ዘመን ወንድ ልጅ
ወለድሁለት» አለች። 8 ልጇም አድጎ ጡት መጥባት ተወ፤ ጡት ባስጣሉበትም ቀን አብርሃም ታላቅ ግብዣ አደረገ። 9 ግብጻዊትዋ አጋር ለአብርሃም
የወለደችለት እስማኤል ከዕለታት አንድ ቀን በሳራ ልጅ በይስሐቅ ላይ ሲያሾፍበት ሳራ አየች። 10 ስለዚህ ሳራ አብርሃምን«ይህችን አገልጋይ ከነ ልጅዋ ወዲያ
አባርልኝ የዚህች አገልጋይ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አብሮ መውረስ አይገባውም» አለችው። 11 እስማኤልም ልጁ ስለሆነ ይህ ጉዳይ አብርሃምን በብርቱ
አስጨነቀው 12 እግዚአብሔር ግን አብርሃምን «ስለ ልጁና ስለ አገልጋይቱ ስለ አጋር አትጨነቅ። ዘር የሚወጣልህ በይስሃቅ በኩል ስለሆን እርሳ የምትልህን
ሁሉ አድርግ። 13 የአገልጋይቱም ልጅ የአንተ ዘርያ ስልሆን ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ» አለው 14 አብርሃም በማለዳ ተነሳ ጥቂት ምግብ ውሃም በአቁማዳ
ለአጋር በትከሻዋ አደረገላት። ልጁንም በጀርባዋ አሳዝሎ ከቤት አስወጣት፤ እርስዋም በቤርሳቤህ በረሃ ትንከራተት ጀመር። 15 በአቁማዳ የነበረው ውሃ ባለቀ
ጊዜ ልጁን በቁጥቋጦ ስር አስቀምችጠችው። 16 እርስዋም «ልጄ ሲሞት ማየት አልፈልግም» በማለት ጥቂት ከልጅዋ ርቃ ተቀመጠች፤ እዚያም ሆና ድምጻን
ከፍ አድርጋ ታለቅስ ጀመር። 17 እግዚአብሔሬም ልሉ ምርር ብሎ ሲያለቅስ ሰማ የእግዚአብሔርም መልአክ ከሰማይ አጋርን «አጋር ሆይ የምትጨነቂበት ነገር
ምንድር ነው? እግዚአብሔር የልጁን ለቅሶ ሰምቶአልና አትፍሪ። 18 ተነሺ ሂንና ልጁን አንስተስ አባብይው፤ የእርሱንም ዘር አበዛለሁ ታላቅ ሕዝብም
አደርገዋለሁ። 19 በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ዓይኖችዋን ከፈተላትና አንድ የውኃ ጉድጋድ አየች፤ ሄዳም በአቁማዳ ውሃ ሞላች ለልጅዋም አጠጣችው። 20 ልጁ
እያደገ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር። 21 በፋራንም በረሓ ኖረ፤ ቀስት በመወርወርም የታወቀ አዳኝ ሆነ። እናቱም ከአንዲት ግብጻዊት
ጋር አጋባችው። 22 በዚያን ጊዜ አቤሜሌክ ከሰራዊቱ አለቃ ከፊኮል ጋር ሄደና አብርሃምን «በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው፤ 23 እኔንም ሆነ
ልጆቼን ወይም ዝርያዎቼን እንዳትዋሸኝ አሁን በእግዚአብሔር ስም ማልልኝ። እኔ ለአንተ ታማኝነትን አሳይቻለሁ፤ አንተም ለእኔና ለዚህች ለምትኖርባትአገር
ታማኝንትን እንደምታሳይ ማልልኝ» አለው። 24 አብርሃምም «እሺ እምላለሁ» አለ። 25 አብርሃም የአቢሜሌክ አገልጋዮች ስለ ወሰዱበት የውሃ ጉድጋድ
ለአቤሜሌክ አቤቱታ አቀረበ፤ 26 አቤሜሌክም «ይህን ያደረገ ማን እንደሆን አላውቅም። አንተም አልነገርኸኝም ይህንን ነገር ገና ዛሬ መስማቴ ነው» አለው።
27 ከዚህ በኋላ አብርሃም ብዙ በጎችና ከብቶች አምጥቶ ለአቢሜሌክ ሰጠው፤ በዚያን ቀን ሁለቱም የስምምነት መሀላ አደረጉ። 28 በዚያን ጊዜ አብርሃም
ሰባት እንስት የበግ ጠቦቶችን ከመንጋው ለየ፤ 29 አቤሜሌክም «እንዚህን ሰባት ጠቦቶች ለይተህ ያቆምሃቸው ለምንድር ነው?» አለው። 30 አብርሃምም
«እነዚህን ሰባት እንስት ጠቦቶች ተቀበለኝ እነርሱን ከተቀበልከኝ ይህን ጉድጋድ የቆፈርሁ እኔ መሆኔን ምስክር እንዲሆን ነው» አለው፤ 31 ሁለቱ ተማምለው
የተስማሙበት ስፍራ በመሆኑ የዚያ ቦታ ስም ቤርሳቤህ ተባል፤ 32 ይህን ስምምንት በቤርሳቤህ ተስማምተው ካደረጉ በኋላ አቤሜሌክና የሰራዊቱ አለቃ ፊኮል
ወደ ፍልስጥኤም ምድር ተመለሱ 33 ከዚህ ብኃላ አብርሃም በቤርሳቤህ የታማሪስክ ዛፍ ተከልና የዘላለም አምላክ ለሆነው ሰገደ፤ 34 አብርሃም
በፍልስጥኤም ምድር በእንግድነት ለረዥም ጊዜ ኖረ።

---

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 22

1 ሁሉ ነገር በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ እግዚአብሔርም «አብርሃም»ብሎ ጠራው፤ «እነሆ አለሁኝ» ብሎ መለሰ። 2 እግዚአብሔርም
«የምትወደውን አንድ ልጅህን ወደ ሞሪያ ምድር ሂድ። እዚያ በማሳይህ አንድ ኮረብታ ላይ እርሱን የሚቃጠል መስዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ» አለው፤ 3
አብርሃም በማለዳ ተነስቶ ለመስዋዕት የሚሆን እንጨት ቆረጠና በአህያው ላይ ጫነው፤ከእርሱ ጋር ልጁን ይስሐቅን ና ሁለት ወጣት ሰዎችን ይዞ እግዚአብሔር
ወደ ነገረው ቦታ ለመሄድ ጉዞ ጀመረ። 4 በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለከት ቦታውን በሩቅ አየ። 5 ከዚህ በኃላ አብርሃም የርሱን ወጣቶች «እናንተ
ከአህያው ጋር በዚህ ቆዩ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን ከሰገድን በኃላ እንመለሳለን፤ 6 አብርሃምም የሚቃጠለውን መስዋዕቱን ማቃጠያ እንጨት አንስቶ ለልጁ
ለይስአቅ አሸከመው፤ እርሱ ግን ቢላዋውንና እሳቱን ያዘ ሁለቱም አብረው ሄዱ። 7 ይስሐቅ አብርሃምን «አባባ» አለው፤ እርሱም «እነሆ አለሁ ልጄ» አለው፤
ይስሐቅም «እነሆ እሳትና እንጨት ይዘናል ታዲያ ለመስዋዕት የሚሆነው በግ የት አለ?» በማለት አብርሃምን ጠየቀው። 8 አብርሃምም «ልጄ ሆይ ለመስዋዕት
የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር እራሱ ያዘጋጃል» አለው። ሁለቱም አብረው መንገዳቸውን ቀጠሉ። 9 እግዚአብሔር ነገረው ቦታ በደረሱ ጊዜ አብርሃም መሰዊያ
ሰርቶ እንጨቱን ረበረበው፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ ከእንጨቱ በላይ በመሰዊያው ላይ አጋደመው። 10 ልጁን ለማረድ ቢላዋ አንስቶ እጁን ዘረጋ። 11 ነገር ግን
የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ «አብርሃም! አብርሃም!» ብሎ ጠራው። እርሱም «እነሆኝ አለሁኝ» አለ። 12 እርሱም «በልጁ ላይ እጅህን አትጫንበት፣
ምንም ዓይነት ጉዳትም አታድርስበት፣ እነሆ እግዚአብሔርን የምትፈራ መሆንህን ተረድቻለሁ፤ አንድ ልጅህን እንኳ ለእኔ ከመስጠት አልተቆጠብህም» አለው።
13 አብርሃም ዙሪያውን በተመለከት ጊዜ ከበስተጀርባው ቀንዶቹ በቁጥቋጥ ዛፍ የተያዙ አንድ በግ አየ፤ አብርሃምም ሄዶ በጉን አመጣና በልጁ ፋንታ
የሚቃጠል መስዋዕት አድርጎ አቀረበው። 14 አብርሃምም ያን ቦታ «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ጠራው። ዛሬም ቢሆን ሠዎች «እግዚአብሔር በተራራው
ላይ ያዘጋጃል» ይላሉ። 15 የእግዚአብሔር መልአክ ለሁለተኛ ጊዜ አብርሃምን ከሰማይ ጠራውና፤ 16 እንዲህ አለው፤ «እግዚአብሔር ብዙ በረከት
እንድምሰጥህ በራሴ ስም እምላለሁ» ይላል፤ ይህን ስላደረግህና አንድ ልጅህንም ለእኔ ለመስጠት ስላልተቆጠብህ፤ 17 እኔም ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብትና
እንደ ባህር ዳር አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዝርያዎችህም ጠላቶቻቸውን ድል ነስተው፤ ከተሞቻቸውን ይይዛሉ። 18 ትዕዛዜን ስለ ፈጸምህ የዓለም ህዝቦች ሁሉ በዘርህ
ይባረካሉ»፤ 19 ከዚህ በኋላ አብርሃም ወደ ወጣቶችሁ ተመለሰና በአንድነት ሆነው ወደ ቤርሳቤህ ሄዱ፤ አብርሃምም በቤርሳቤህ ተቀመጠ። 20 ከዚህ ሁሉ
በኋላ እንዲህ ተብሎ ለአብርሃም ተነገረው «ሚልካ ልጆችን ለወንድምህ ለናኮር ወልዳለች፤ 21 እነርሱም የመጀመሪያው ልጅ ዑፅ ወንድሙም ቡዝ የአራም
አባት ቀሙኤል፤ 22 ኬሰድ፣ ሐዞ፣ ፊልዳሽ፤ ይድላፍና በቱኤል ናቸው። 23 በቱኤል ርብቃን ወለደ። ሚልካ እነዚህን ስምንት ልጆች ለአብርሃም ወንድም ለንኮር
ወለደችለት፤ 24 ረኡማ የተባለች የናኮር ቁባት ደግሞ ጤባሕን፣ ገሐምን፣ ተሐሽና ማዕካን ወለደችለት።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 23

1 ሣራ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት ኖረች። እነዚህን ዓመታት ነበር ሳራ የኖረችው። 2 በከነዓን ምድር ባለችው ቂርያት አርባ ተብላ በምትጠራው በኬብሮን ከተማ
ሞተች፤ አብርሃም በሣራ ሞት ምክንያት እጅግ ሃዘነ አለቀሰም። 3 ከዚያም አብርሃም ከተቀመጠበት ከሚስቱ ሬሳ አጠገብ ተነሳ፣ ኬጢያውያንን እንዲህ
አላቸው፤ 4 «እኔ በመካከላችሁ በእንግድነት የምኖር ነኝ። እባካችሁ የመቃብር ቦታ ስጡኝ፤ የሚስቴንም ሬሳ ልቅበርበት።» 5 የኬጢ ልጆችም ለአብርሃም
እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤ 6 «ጌታ ሆይ ስማን፣ አንተ በእኛ መካከል ከእግዚአብሔር አለቃ ነህ። ከመቃብር ቦታችን በመረጥከው ስፍራ ሬሳህን መቅበር
ትችላለህ፣ ማናችንም ብንሆን የሞተብህን ሰው እንዳትቀብርበት የምቃብር ቦታችንን አንከለክልህም።» 7 አብርሃም ተነሣ በኬጢያውያን ልጆች ፊት እጅ ነስቶ
እንዲህ አለ። 8 የሚስቴን አስከሬን እዚህ እንድቀብር ከፈቀዳችሁልኝ የጾሐር ልጅ ዔፍሮምን ስለ እኔ ሆናችሁ ልምኑልኝ፤ 9 በእርሻው ዳር ያለችውን መክፈል
የተባለችውን ዋሻውን እንዲሸጥልኝ ጠይቁልኝ፣ ይህ ስፍራ የመቃብር ቦታ እንዲሆንልኝ በእናንት ፊት ሙሉ ዋጋ ከፍዬ እንድገዛው አድርጉልኝ።» 10 ኤፍሮንም
በኬጢ ልጆች መካከል ተቀምጦ ነበር፤ የኬጢም ሰው ኤፍሮንም የኪጥ ልጆችና ወደ ከተማ የሚገቡ ሲስሙ ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ 11
«አይደለም ጌታዬ፣ ስማኝ። እርሻውን፣ በርሱም ዳር ያለውን ዋሻ፤ በወገኔ ልጆች ፊት ሰጥቼአለሁ። ሬሳህን ቅበር።» 12 አብርሃምም በአገሩ ሰዎች ፊት ሰገደ።
13 የአገሩ ሰዎችም እየሰሙ ለኤፍሮን እንዲህ ሲል ተናገረ፤ «እባክህ ፈቃደኛ ብትሆን አድምጠኝ፤ የእርሻውን ዋጋ እሰጥሃለሁ። አንተም ከእኔ ዘንድ ውሰድ፤
ሬሳዬንም በዚያ እቀብራለሁ 14 ኤፍሮንም ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ 15 «ጌታዬ ሆይ እኔን ስማኝ፤ የመሬቱ ዋጋ እራት መቶ ሰቅል ቢሆን ነው፤ ታዲያ
ይሄ በእኔና በአንተ መካከል ምንድር ነው? ሬሳህንም ቅበር» 16 አብርሃምም የኤፍሮንን ነገር ሰማ፤ አብርሃምም በኬት ልጆች ፊት የነገረውን አራት መቶ ሰቅል
መዝኖ ለኤፍሮን ሰጠው፤ ብሩንም በወቅቱ የንግድ መለኪያ መሰረት መዘነለት። 17 በዚህም ሁኔታ በመምሬ አጠገብ በመክፈላ ያለውን የኤፍሮንን እርሻ ቦታ
ከነዋሻው በከልሉ ካሉት ዛፎች ሁሉ ጭምር ለአብርሃም በርስትነት ተላለፈ፤ 18 እርሻው በእርሱ ያለውን ዋሻው በእርሻውም ውስጥ በዙሪያውም ያለው እንጨት
ሁሉ በኬጢ ልጆችና በከተማይቱ በር በሚገቡ ሁሉ ፊት ለአብርሃም ርስቱ ሆነ። 19 ከዚያም በኋላ ኬብሮን በምትባል በምምሬ ፊት በከነአን ፊት ባለው እርሻ
ባለ ድርብ ክፍሌ በሆነው ዋሻ ውስጥ ሚስቱን ሳራን ቀበረ። 20 እርሻውና በርሱ ያለው ዋሻው በኪጥ ልጆች ዘንድ ለአብርሃም የመቃብር ርስት ሆኖ ጸና።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 24

1 በዚህ ጊዜ አብርሃም ሸመገለ፤ ዕድሜውም ገፋ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን በሁሉ ነገር ባረከው። 2 አብርሃምም የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ የቤቱ ሁሉ አዛዥ
የሆነውን አገልጋይ እንዲህ አለው፤ እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ 3 እኔም በመካከላቸው ከምኖረው ከከነዓናዊያን ለልጄ ሚስት እንዳታጭለት በሰማይና በምድር
አምላክ እግዚአብሔር አስምልሃለሁ። 4 ነገር ግን ወደ ገዛ ሀገሬ እና ወደ ወገኖቼ ሄደህ ለልጄ ለይስሐቅ ሚስትን ታጭለታለህ። 5 አገልጋዩም «ምናልባት
የምመርጥለት እጮኛ ከእንይ ጋሬ ወደዚህ አገር ለመምጣት እምቢ ብትልስ? ልጅህን ቀድሞ አንተ ወደ ነበርክበት አገር እንዲመለስ ላድርገው?» ብሎ ጠየቀ።
6 አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ «በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን ልጄን ወደዚያ አገር መልሰህ እንዳትወስድ ተጠንቀቅ፤ 7 የሰማይ አምክክ እግዚአብሔር
ከአባቴ ቤትና ከትውልድ አገሬ አውጥቶ አምጥቶኛል፤ ይህንንም ምድር ለዝርያዎቼ እንደሚሰጥ በመሃላ ቃል ገብቶልኛል፤ ከዚያ ለልጄ ሚስት ማግኘት
እንድትችል እግዚአብሔር መልአኩን በፊትህ ይልካል። 8 ልጅትዋ ከአንተ ጋር ለመምጣት ፈቃደኛ ባትሆንከዚህ መሓላ ነፃ ትሆናለህ፤ ልጄን ግን በምንም ዓይነት
ሁኔታ ወደዚያ አትመልሰው።» 9 ከዚህ በኋላ አገልጋዩ እጁን በጌታው በአብርሃም ጉልበት ላይ አድርጎ አብርሃም ያዘዘውን ሁሉ እንደሚፈፅም በመሐላ ቃል
ገባ። 10 የአብርሃም ንብረት ኀላፊ የነበረው መጋቢ ከጌታው ቤት ምርጥ የሆኑ የስጦታ ዕቃዎችን በዕሥር ግመሎች ጭኖ በሰሜን መስጴጦምያ ናኮር
ወደሚኖርበት ከተማ ሄደ። 11 እዚያ በደረሰ ጊዜ ከከተማው ውጭ ባለ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ግመሎቹ ተንበርክከው እንዲያርፉ አደረገ፤ ሰዓቱም ሊመሽ
ተቃርቦ፣ ሴቶች ውሃ ለመቅዳት የሚወጡበትን ጊዜ ነበር፤ 12 አገልጋዩ እንዲህ ብሎ ጸለየ፣ "የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ዛሬ የእኔን አሳብ
በመፈፀም ለጌታዬ ለአብርሃም ዘላለምዊ ፍቅርህን ግለጥ። 13 እነሆ፣ እኔ በዚህ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ የከተማይቱም ልጃገረዶች ውሃ ሊቀዱ
ወደዚህ ይመጣሉ፤ 14 ከእነሱም አንድዋ ልጃገረድ 'እንስራሽን ዘንበል አድርገሽ ውሃ አጠጪኝ' እላታለሁ፤ 'አንተም ጠጣ፤ ግመሎችህም እንዲጠጡ ውኃ
ቀድቼ አመጣለሁ' ካለችኝ ለአገልጋይህ ለይስሐቅ ፍቅርህን እንዳሳየኸው ዐውቃለሁ።" 15 ገና ጸሎቱን ሳፅቸርስ ርብቃ እንስራ ተሸክማ መጣች፤ የዚህችም
ልጅ አባት ባቱኤል ይባል ነበር፤ እርሱም የአብርሃም ወንድም ናኮር ከሚስቱ ከሚልካ የወለደው ነው። 16 ርብቃ ገና ወንድ ያልደረሰባት በጣም ቆንጆ ልጃገረድ
ነበረች፤ እርስዋ ወደ ውሃው ጉድጓድ ወርዳ በእንስራዋ ውሃ ከቀዳች በኋላ ተመለሰች። 17 አገልጋዩም ወደ እርስዋ ሮጦ ሄዳና "እባክሽ ከእንስራሽ ከእንስራሽ
ጥቂት ውሃ አጠጪኝ"አላት። 18 እርስዋም "እሺ ጌታዬ ጠጣ" አለችና እንስራዋን ከትከሻዋ አውርዳ ዘንበል አድርጋ ያዘችለት። 19 ጠጥቶም ከረካ በኋላ
"ለግመሎችህም ውሃ እቀዳላቸዋለሁ፤ እስኪበቃቸውም ድረስ ይጠጡ" አለችው። 20 ወዲያውኑ፤ በእንስራዋ የያዘችውን ውሃ ግመሎቹ በሚጠጡበት ገዳን ላይ
ገልብጣ ግመሎቹ ሁሉ ጠጥተው እስከሚረኩ ድረስ እየተጣደፈች ከጉድጓድ ውሃ መቅዳት ቀጠለች። 21 ሰውየውም እግዚአብሔር የሄደበትን ተልእኮ
አቃንቶለት እንደሆን ለማረጋገጥ የምታደርገውን ሁሉ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር። 22 ግመሎቹ ጠጥተው በኋላ ሰውየው አምስት ግራም ያህል የሚመዝን
የወርቅ ጎታቻ አውጥቶ በጆሮዋ ላይ አደረገላት፤ መቶ ዐሥር ግራም ያህል የሚመዝን ሁለት የወርቅ አምባሮችንም አውጥቶ በእጆችዋ ላይ አደረገላትና፤ 23
"የማን ልጅ ነሽ? እስቲ እባክሽ ንገሪኝ፤ ለእኔና አብረውኝ ቤት ይገኛልን?" ብሎ ጠየቃት። 24 እርስዋም "የባቱኤል ልጅ ነኝ፤ የባቱኤል አባት ናኮር፣ እናቱም
ሚልካ ይባላሉ፤ 25 በቤታችን ብዙ ገለባና ድርቆሽ አለ፤ ለእናንተም ማደሪያ ቦታ ይገኛል" አለችው። 26 ሰውየምውም በመንበርከክ ለእግዚአብሔር ሰግዶ፣ 27
"ለጌታዬ የገባውን ቃል ኪዳንና ዘላለማዊ ፍቅሩን የጠበቀ የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፤ በቀጥታ መርቶ ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት
ያመጣኝ እርሱ ነው" አለ። 28 ልጅትዋ ወደ ቤት ሮጣ ሄደችና የሆነውን ሁሉ ለእናትዋና ለእርስዋ ጋር ላሉት ሁሉ ነገረቻቸው። 29 ርብቃ ላባ የተባለ ወንድም
ነበራት፤ እርሱ የአብርሃም አገልጋይ ወዳለበት ውሃ ጉድጓድ እየሮጠ ሄደ። 30 ላባ ወደ ሰውየው የሄደው እኅቱ በጆሮዋ ላይ ያደረገችውን ጉትቻና በእጆችዋ ላይ
ያደረገቻቸውን አንባሮች ስላየና ርብቃ ሰውየው ጉድጓድ አጠገብ ከግመሎቹ ጋር ቆሞ አገኘው። 31 ስለዚህ ላባ "አንተ እግዚአብሔር የባረከህ ሰው! ና ወደ ቤት
እንሂድ፤ በውጭ የቆምኸው ለምንድን ነው? በቤታችን ለአንተ ማደሪያ የተዘጋጀ ቦታ አለ" አለው። 32 ከዚህ በኋላ ሰውየው ወደ ቤት ሄደ፤ ላባም በግመሎቹ
ላይ የነበረውን ጭነት አረግፎ ገለባና ድርቆሽ አቀረበላቸው፤ ቀጥሎም የአብርሃም አገልጋይና አብረውት የነበሩት ሰዎች እግራቸውን የሚታጠቡበትን
አመጣላቸው። 33 ገበታ በቀረበው ጊዜ ጊዜ ሰውየው "የተላክሁበትን ጎዳይ ከመናገሬ በፊት እህል አልቀምስም" አለ። ላባም "ይሁን ተናገር" አለው። 34
እርሱም "እኔ የአብርሃም አገልጋይ ነኝ፤ 35 እግዚአብሔር ጌታዬ እጅግ ባርኮል፤ ባለጸጋም አድርጎታል፤ ብዙ የበግ፣ የፍየልና የከብት መንጋ፣ ብርና ወርቅ፣
ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮች ግመሎችና አህዮች ሰጥቶታል። 36 የጌታዬ ሚስት ሣራ በእርጅናዋ ዘምን ወንድ ልጅ ወልዳለታለች፤ ጌታዬም ያለውን ሀብት ሁሉ
ለዚሁ ልጅ አውርሶታል። 37 ጌታዬ አብርሃም 'እኔ በመካከላቸው ከምኖረው ከከነዓናዊያን ሴቶች ልጆች መካከል ለልጄ ሚስት እንዳላጭለት፤ 38 ነገር ግን ወደ
አባቴ ቤተሰብና ወደ ዘመዶቼ ሄደህ ለልጄ ሚስት እጭለት' ሲል በመሐላ ቃል ኪዳን አስገብቶኛል።' 39 እኔም ጌታዬን 'ልጅቷ ከእኔ ጋር ለመምጣት ፈቃደኛ
ባትሆንስ ምን ላድርግ?' ብዬ ጠየኩት። 40 እርሱም እንዲህ አለኝ 'ዘውትር የማገለግለው እግዚአብሔር መልአኩን ከአንተ ጋር ይልካል፤ ጉዞህም የተቃና
እንዲሆን ያደርጋል፤ በዚህ ሁኔታ አንተም ከአባትቴ ቤተሰብና ከዘመዶቼ መካከል ለልጄ ሚስት ልታጭለት ትችላለህ፤ 41 ከመሐላህ ነፃ የምትሆነው ወደ
ዘመዶቼ ሄደህ እነርሱ ልጅትዋን አንሰጥም ብለው የከለከሉህ እንደሆነ ብቻ ነው።' 42 "ከዚያም በኋላ ዛሬ ወደ ውሃው ጉድጓድ ስመጣ እንዲህ ብዬ ጸለይሁ
'የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! እባክህ የመጣሁበት ጉዳይ እንዲቃና አድርግልኝ፣ 43 እነሆ በዚህ ውሃ ጉድጓድ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ አንዲት
ልጃገረድን ውሃ ልትቀዳ ስትመጣ፣ 'እባክሽ ከእንስራሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ' ብዬ እጠይቃታለሁ፤ 44 እርስዋም 'እሺ ጠጣ፤ ለግመሎችህም
እቀዳቸዋለሁ'የምትለኝ ብትሆን፣ ለጌታዬ ልጅ ሚስት እንድትሆን አንተ የመረጥሃት እርስዋ ትሁን። 45 የኅሊና ጸሎትን ገና ሳልጨርስ ርብቃ እንስራ ተሸክማ ብቅ
አለች፤ ወደ ጉድጓዱም ሄዳ ውሃ ቀዳች፤ እኔም 'እባክሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ አልኋት። 46 እርስዋም እንስራዋን በፍጥነት ከጀርባዋ አወረደችና ዘንበል አድርጋ
'እሺ ጠጣ፤ ግመሎችህንም አጠጣልሃለሁ' አለችኝ፤ ስለዚህ እኔም ጠጣሁ፤ ግመሎቼንም አጠጣችልኝ። 47 እኔም 'የማን ልጅ ነሽ?' ብዬ ጠየቅኋት።
እርስዋም 'የባቱኤል ልጅ ነኝ፤ የባቱኤል አባት ናኮር እናቱም ሚልካ ይባላሉ' አለችኝ። ከዚህ በኋላ ጉትቻ በጆሮዋ ላይ፣ አንባሮቹንም በእጆዎችዋ ላይ
አደረግሁላት፤ 48 ከዚህ በኋላ በጉልበቴ ተንበርክኬ ለእግዚአብሔር ሰገድሁ፤ የጌታዬን የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር አመሰገንሁ፤ ምክንያቱም ለጌታዬ ልጅ
ሚስት የምትሆነዋን ሴት ወዳገኘሁበት ወደ ጌታዬ ወንድም ቤት በቀና መንገድ የመራኝ እርሱ ነው። 49 እንግዲህ የጌታዬን ዐደራ በእውነት ተቀብላችሁ እርሱን
ደስ ለማሰኘት የምትፈቅዱ እንደሆነ ንገሩኝ፤ የማትፈቅዱም እንደሆነ ቁርጡን ነገሩኝ፤ እኔም እግዚአብሔር ወደሚመራኝ እሄዳለሁ።" 50 ላባና ባቱኤልም "ይህ
ነገር ከእግዚአብሔር የመጣ ስለሆነ፣ መከልከል አልችልም፤ 51 ርብቃ ይችውልህ፤ እነሆ ይዘሃት ሂድ፤ እግዚአብሔር ራሱ እንደተናገረው ለጌታዬ ልጅ ሚስት
ትሁን" አሉት። 52 የአብርሃም አገልጋይ ይህን በሰማ ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ ለእግዚአብሔር ሰገደ፤ 53 ከውርቅና ከብር የተሠሩ ጌጣጌጦችን፣ እንዲሁም
ልብስ አውጥቶ ለርብቃ ሰጣት፤ ለወንድምዋና ለእናትዋም በጣም ውድ የሆኑ ስጦታዎችን አውጥቶ ሰጣቸው። 54 ከዚህ በኋላ የአብርሃም አገልጋይና
አብረውት የነበሩ ሰዎች በልተው ጠጥተው እዚያው አደሩ፤ ጠዋት በተነሡ ጊዜ የአብርሃም አገልጋይ "እንግዲህ ወደ ጌታዬ እንድመለስ ፍቀዱልኝ" አለ። 55
ነገር ግን የርብቃ ወንድምና እናትዋ "ልጅትዋ ዐሥር ቀን ያህል ከእኛ ጋር ትቆይ፤ ከዚህ በኋላ ከአንተ ጋር ልትሄድ ትችላለች" አሉት። 56 እርሱ ግን "እባካችሁ
አታቆዩኝ፤ እግዚአብሔር የመጣሁበትን ጉዳይ ስላቃናልኝ ቶሎ ብዬ ወደ ጌታዬ ልመለስ" አላቸው። 57 እነርሱም "እስቲ ልጅቷን እንጥራትና እርስዋ የምትለውን

እንስማ" አሉ። 58 ስለዚህ ርብቃን ጠሩና "ከዚህ ሰው ጋር መሄድ ትፈልጊያለሽ?" ብለው ጠየቅዋት። እርስዋም "አዎ እሄዳለሁ"አለች። 59 ስለዚህ ርብቃ
ሞግዚትዋን አስከትላ፣ ከአብርሃም አገልጋይና ከእርሱ ሰዎች ጋር እንድትሄድ ፈቀዱላት። 60 "አንቺ እኅታችን የብዙ ሺ ሕዝብ እናት ሁኚ፤ ዝርያዎችሽም
የጠላቶችሽን ከተሞች ይውረሱ" ብለው ርብቃን መረቁአት። 61 ከዚህ በኋላ ርብቃ ከተከታዮችዋ ጋር ለመሄድ ተነሣች፤ በግመሎቹ ላይ ተቀምጠው ከአብርሃም
አገልጋይ ጋር ለመሄድ ተዘጋጁ። በዚህ ዐይነት የአብርሃም አገልጋይ ርብቃን ይዞ ሄደ። 62 በዚህ ጊዜ ይስሐቅ "ብኤር ላሐይ ሮኢ ወይም የሚያየኝን ሕያው
አምላክ"የተባለው ኲሬ ወዳለበት በረሓ መጥቶ በኔጌብ ተቀምጦ ነበር። 63 ከለዕታት አንድ ቀን ወደ ማታ ጊዜ እያሰላሰለ በመስክ ውስጥ ሲዘዋወር ሳለ
ግመሎች ሲመጡ በሩቅ አየ። 64 ርብቃ ይስሐቅ ባየች ጊዜ ከግመሏ ወረደችና፣ 65 "ያ በመስክ ውስጥ ወደ እኛ የሚመጣው ሰው ማን ነው?" ስትል
የአብርሃምን አገልጋይ ጠየቀችው። አገልጋዩም "እርሱ ጌታዬ ነው!" አላት። ስለዚህ በጥፍነት በሻሽ ፊትዋን ሸፈነች። 66 አገልጋዩም ያደረገውም ነግር ሁሉ
ለይስሐቅ ነገረው። 67 ከዚህ በኋላ ይስሐቅ እናቱ ሣራ ትኖርበት ወደነበረው ድንኳን ርብቃን ይዞአት ገባ፤ ሚስትም ሆነችው፤ ይስሐቅ ርብቃን ወደዳት፤ በእናቱ
ሞት ምክንያት ከደረሰበትም ሐዘን በዚህ ሁኔታ ተጽናና።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 25

1 አብርሃም ቀጡራ የምትባል ሌላ ሚስት አገባ፤ 2 እርስዋም ዚምራንን፣ ዮቅሻንን፣ መዳንን፣ ምድያምን፣ ዩሽባቅንና ሹሐን ወለደችለት። 3 ዮቅሻንም ሳባንና
ደዳንን ወለደ፤ የዳደንም ዝርያዎች አሹራውያን፣ ሌጡሻውያንና ሌአማውያን ናቸው። 4 የምድያም ልጆች ዔፋ፣ ዔፈር፣ ሐኖክ፣ አቢዳዕና ኤልዳዓ ናቸው፤ እነዚሁ
ሁሉ የቁጠራ ዝርያዎች ናቸው። 5 አብርሃም ያለው ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ አወረሰው፤ 6 ከሌሎች ሴቶች ለተወለዱትም ልጆች ገና በሕይወት ሳለ ስጦታ
ሰጣቸው፤ ከዚህ በኋላ እነዚህ ሌሎች ልጆች ከይስሐቅ ርቀው ወደ ምሥራቅ አገር እንዲሄዱ አደረጋቸው። 7 የአብርሃም ዕድሜ በአጠቃላይ መቶ ሰባ አምስት
ዓመት ነበር፤ 8 በዚህም ዐይነት አብርሃም በቂ ዕድሜ አግኝቶ ካረጀ በኋላ ሞተ፤ 9 ልጆቹ ይሰሐቅና እስማኤል ማክጴላ በተባለ ዋሻ ቀበሩት፤ ይህም ዋሻ
ከመምሬ በስተምሥራቅ በሒታዊ በጾሐር ልጅ በዔፍሮን እርሻ ውስጥ የሚገኘው ነው። 10 እነሱም አብርሃም ከሒታዊያን ላይ የገዛው የመቃብር ቦታ ነው፤ በዚህ
ዐይነት አብርሃም ሚስቱ ሣራ በተቀበረችበት ዋሻ ተቀበረ። 11 አብርሃም ከሞተ በኋላ ልጁን ይስሐቅን እግዚአብሔር ባረከው፤ ይስሐቅ "ብኤርላሐይሮኢ
ወይም የሚያየኝ ሕያው አምላክ" ተብሎ በመጠራት ኲሬ አጠገብ ይኖር ነበር። 12 የሣራ አገልጋይ ግብፃዊትዋ አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን እስማኤል፤ 13
ከዚህ በታች በዕድሜአቸው ቅደም ተከተል ተራ የተዘረዘሩትን ልጆች ወለደ፤ እነርሱም፦ ነባዮት፣ ቄዳር፣ አድብኤል፣ ሚብሣም፣ 14 ሚሽማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣ 15
ሐዳድ፣ ቴማ፣ ይጡር፣ ናፊሽና ቄድማ ናቸው። 16 እነዚህ የእስማኤል ልጆች ለአሥራ ሁለት ነገዶች ቅድመ አያቶች ነበሩ፤ ስማቸውም በኖሩባቸው ከተሞችና
ስፍራዎች ሲጠራ ይኖራል። 17 እስማኤል መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ሲሆነው ሞተ። 18 የእስማኤል ዝርያዎች ከግብፅ በስተምጅራቅ ወደ አሦር በምትወስደው
መንገድ በሐዊላና በሹር መካከል ይኖሩ ነበር። የኖሩበትም ከሌሎቹ የአብርሃም ዝርያዎች ጋር በጥላቻ ተራርቀው ነበር። 19 የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ታሪክ ይህ
ነው። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ። 20 ይስሐቅ የባቱኤልን ልጅ ርብቃን ሲያገባ አርባ ዓመት ሆኖት ነበር፤ የርብቃ አባት ባቱኤልና ወንድምዋ ላባ በመስጴጦምያ
የሞኖሩ ሶሪያውያን ነበሩ። 21 ርብቃ መኻን ስለ ነበረች ይስሐቅ ስለ እርስዋ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ስለ ሰማ ርብቃ ፀነሰች፤ 22
የተፀነሱትም መንትያዎች ስለነበሩ እርስ በርሳቸው በማሕፀንዋ ውስጥ ይገፋ ነበር፤ እርስዋም "ይህን ዐይነት በገር ለምን ደረሰብኝ?" በማለት ወደ
እግዚአብሔር ለመጸለይ ተነሣሣች። 23 እግዚአብሔርም ያሉት ሁለት ሕዝቦች ናቸው፤ እርስ በርሳቸው የማይስማሙ ሁለት ወገኖች ትወልጃለሽ፤ አንዱም
ከሌላው የበረታ ይሆናል፤ ታላቁም ታናሹ አገልጋይ ይሆናል" አላት። 24 የመውለጃዋም ሰዓት በደረሰ ጊዜ ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ። 25 የመጀመሪያው ልጅ
መልኩ ቀይ፣ ሰውነቱ ጠጉራም ነበር፤ ስለዚህ ዔሳው ተባለ። 26 ሁለተኛው ልጅ ሲወለድ የዔሳውን ተገረዝ ይዞ በመውጣቱ ያዕቆብ ተባለ፤ ልጆቹ በተወለዱ
ጊዜ ይስሐቅ ስልሳ ዓመት ሆኖት ነበር። 27 ሁለቱም ልጆች አደጉ፤ ዔሳው በዱር መዋል የሚወደ ብልኀ አዳኝ ሆነ፤ ያዕቆብ ግን በቤት መዋል የሚወድ ጭምት
ሰው ነበር። 28 ይስሐቅ ዔሳውን ይወድ ነበር። ምክንያቱም ዔሳው እያደነ ሥጋ ያበላው ነበር።ርብቃ ግን ያዕቆብን ትንን ነበር። 29 ለዕለታት አንድ ቀን ያዕቆብ
ቀይ የምስር ወጥ በመሥራት ላይ እንዳለ ዔሳው ከአደን መጣ፤ በጣም እርቦት ነበር፤ 30 ስለዚህም ያዕቆብ "ከዚህ ከቀይ ወጥ ሰጠኝ" አለው። ኤዶም
የተባለውም ነዚሁ ምክንያት ነበር። 31 ያዕቆብም "በመጀመሪያ ብኩርናህን ሸጥልኝ" አለው። 32 ዔሳውም "እኔ በረሀብ መሞቴ ነው፤ ታዲያ ብኩርና ምን
ያደርግልኛል?" አለው። 33 ያዕቆብም "እንግዲያውስ ብኩርናህን እንደምትሸጥልኝ መጀመሪያ ማልልኝ" አለው። ስለዚህ ዔሳው ምሎ ብኩርናውን ለያዕቆብ
ሸጠ። 34 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ የምስሩን ወጥ በእንጀራ አድርጎ ሰጠው፤ ዔሳውም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነሥቶ ሄደ፤ በዚህ ዐይነት ዔሳው ብኩርናውን በመናቅ
አቃለላት።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 26

1 በአብርሃም ዘመን ከደረሰው ረሀብ ሌላ ዳግመኛ ረሀብ በምድር ላይ መጣ፤ በዚህ ምክንያት ይስሐቅ የፍልስጥኤማዋን ንጉሥ አቢሜሌክ ወዳለበት ወደ
ገራር ሄደ፤ 2 በዚህም እግዚአብሔር ለይስሐቅ ተገለጠለትና እንዲህ አለው፣ "ወደ ግብፅ አገር አትሂድ፤ እንድትኖርበትም በምነግርህ በዚህ ምድር ተቀመጥ፤ 3
እዚሁ ኑር፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁ፤ ይህም ምድር ለአንተና ለዝርይዎችህ እሰጣለሁ፤ በዚህ ዐይነት ለአባትህ ለአብርሃም የገባሁትን ቃል ኪዳን
እፈፅማለሁ፤ 4 ዘርህን እንደ ሰማይ ክዋክብት አበዛዋልለሁ፤ ይህንንም ሁሉ ምድር አወርሳቸዋለሁ፤ ይህንንም ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ። 5 አንተን
የምባርክበትንም ምክንያት አባትህ አብርሃም ለእኔ ታዛዥ በመሆን የሰጠሁት ሕግና ሥርዓት ሁሉ ስለ ጠበወ ነው። 6 ስለዚህ ይስሐቅ መኖሪያውን በገራር
አደረገ፤ 7 በዚያ አገር ስሰዎችም ስለ ርብቃ "ምንህናት" ብለው በጠየቁት ጊዜ "እኅቴ ናት" አላቸው፤ ይህንንም ያለበት ምክንያት ርብቃ በጣም ቆንጆ ስለ ነበረች
የዚያ አገር ሰዎች በእርስዋ ሰበብ እንዳይገድሉት በመፍራት ነው። 8 ይስሐቅ እዚያ አገር ብዙ ጊዜ ከቆያ በኋላ የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ በመስኮት ወደ
ውጪ ሲመለከት ይስሐቅና ርብቃ እንደባልና ሚስት በመዳራት ሲጫወቱ አየ። 9 ስለዚህ አቢሜሌክ ይስሐቅን አስጠርቶ "ለካስ ርብቃ ሚስትህ ናት! ታዲያ
"እኅቴ ናት' ያልከው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። እርሱም "ሚስቴ ነች ያልኩ እንደሆን ሰዎች ይገድሉኝል ብዬ አስፈራሁ ነው" ብሎ መለሰ። 10 አቢሜሌክ
"ይህ በእኛ ላይ ያደረግኸው ነገር ምንድን ነው? ከእኛ ሰዎች አንዱ በቀላሉ ሚስትህን ለመድፈር በቻለ ነበር፤" 11 ቀጥሎም አቢሜሌክ "ይህን ሰው ወይም
ሚስቱን የሚነካ ሰው በሞቱ ይቀጣል"የሚል ማስጠንቀቂያ ለሕዝቡ ሰጠ። 12 ይስሐቅ በዚያች ምድር ዘርን ዘራ፤ እግዚአብሔር ስለባረከውም በዚያኑ ዓመት
መቶ እጥፍ አመረተ፤ 13 ሀብት በሀብት ላይ እየተጨመረበት ዘመን የእርሱ አገልጋዮች ቁፍረዋቸው የነበሩትን የውሃ ጉድጓዶች ሁሉ ዐፈር ሞልተው ደፈኑአቸው።
14 ብዙ የበግና የከብት መንጋ፤ እንዲሁም ብዙ አገልጋዮች ስለ ነበሩት ፍልስጥኤማውያን ቀኑበት። 15 ስለዚህ የይስሐቅ አባት አብርሃም በሕይወት በነበረበት
ዘመን የእሱን አገልጋዮች ቁፍረዋቸው የነበሩትን ውሃ ጉድጓዶች ሁሉ ዐፈር ሞልተው ደፈኑአቸው። 16 በዚያን ጊዜ አቢሜሌክ ይስሐቅን "ኀይልህ ከእኛ ይልቅ
እየበረታ ስለሄደ፤ አገራችንን ለቀህ ውጣ" አለው። 17 በዚህ ምክንያት ይስሐቅ ያንን ቦታ ለቆ በገራር ሸለቆ ውስጥ ሰፈረ፤ እዚያም ተቀመጠ። 18 አብርሃም
በሕይወት ሳለ አስቆፍሮአቸው የነበሩትን አብርሃም ከሞተ በኋላ ግን ፍልስጥኤማውያን የደፈኑአቸውን የውሃ ጉድጓዶች ይስሐቅ እንደገና እንዲቆፍሩ አደረገ፤
አባቱ ባወጣላቸ ስሞችም ጠራቸው። 19 የይስሐቅ አገልጋዮች በሸለቆው ውስጥ የውሃ ጉድጓድ ቁፍሩና ጥሩ የምንጭ ውሃ አገኙ፤ 20 የገራር እረኞች ግን "ይህ
ውሃ የእኛ ነው" በማለት ከይስሐቅ እረኞች ጋር ተጣሉ።በዚህ ምክንያት ይስሐቅ ጉድጓዱን "ዔሤቅ" ብሎ ሰየመው። 21 የይስሐቅ አገልጋዮች ሌላ የውሃ
ጉድጓድ ቁፈሩ፤ በዚህኛውም ጉድጓድ ምክንያት ሌላ ጠብ ተነሣ፤ ስለዚህ ይስሐቅ ይህን ጉድጓድ "ስጥና" ብሎ ሰየመው። 22 ከዚያም እልፍ ብሎ ሌላ የውሃ
ጉድጓድ ምክንያት ምንም ጠብ ስላልተናሳ "እነሆ አሁን እግዚአብሔር ሰፊ ቦታ ሰጠን፤ በምድር ላይም እንበዛለን ሲል ያንን ቦታ 'ረሖቦት" ብሎ ሰየመው። 23
ከዚያ በኋላ ይስሐቅ ወደ ቤርሳቤህ ወጣ፤ 24 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር ተገለጠለትና "እኔ የአባትህ አምላክ ነኝ፤እኔ ከአንተ ጋር ስለሆንኩ አትፍራ!
ለአገልጋዬ ለአብርሃም በገባሁት ቃል ኪዳን መሠረት እባርክሃለሁ፤ ዘርህንም አበዛዋለሁ" አለው። 25 ይስሐቅ በዚያ መሠዊያ መሠዊያ ሠራና ለእግዚአብሔር
ሰገደ፤ መኖሪያውንም እዚያ አደረገ፤ አገልጋዮቹም ሌላ ጉድጓድ ቆፈሩ። 26 አቢሜሌክ ከአማካሪው ከአሑዘትና ከሠራዊቱ ኣዥ ኮፊኮል ጋር ይስሐቅን
ለመጎብኘት ከገራር ወት፤ 27 ስለዚህ ይስሐቅ "ከዚህ በፊት ጠልታችሁን አገራችሁ እንድወጣ አድርጋችሁኛል፤ ታዲያ አሁን ልትጎበኝ የመጣችሁት ለምንድን
ነው?" አላቸው። 28 እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፣ "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር መሆኑን በግልጥ ዐውቀናል፤ ስለዚህ በእኛና በአንተ መካከል በሰላም
ለመኖር የሚያስችል ስምምነት በመሐላ ለመፈፀም አስበናል፤ በዚህም መጀረት ቃል ኮዳን እንድትገባልን የሚንፈለገው፣ 29 በእኛ ላይ ምንም ዐይነት በደል
እንዳታደርስብን ነው፤ ምክንያቱም እኛ በአንተ ላይ ምንም ግፍ አልሠራንም፤ ዘውትር መልካም ነገር አደረግንልህ እንጂ ክፉ አላደረግብህም፤ ከአገራችንም
የወጣኸው በሰላም ነው፤ አሁንም እግዚአብሔር ባርኮሃል።" 30 ከዚህ በኋላ፣ ይስሐቅ ግብዣ አደረገላቸው፤ እነሱም በሉ፣ ጠጡ። 31 በማግሥቱ ጠዋት
በማለዳ ተነሡና ተማማሉ፤ ይስሐቅ ካሰናበታቸው በኋላም በሰላም ሄዱ። 32 ከዚያኑ ቀን የይስሐቅ አገልጋዮች መጥተው ስለ ቁፈሩት ጉድጓድ ለይስሐቅ
ነገሩት፤ "ውሃ አገኘን" ብለውም አበሠሩት። 33 እርሱም የውሃን ጉድጓድ "ሳቤህ"ብሎ ጠራው፤ ስለዚህም የከተማይቱ ስም እስከ ዛሬ "ቤርሳቤህ" እየተባለ
ይጠራል። 34 ዔሳው አርባ ዓመት ሲሆነው የብኤሪን ልጅ ዮዲትንና የኤሎንን ልጅ ባሴማትን አገባ፤ ሁለቱም ሒታውያን ነበሩ። 35 ይህም ጋብቻ ይስሐቅንና
ርብቃን ሲያዝናቸው ይኖር ነበር።

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 27

1 ይስሐቅ አርጅቶ ዐይኖቹም ታውረው ነበር፤ ታላቁ ልጁን ዔሳውን፤ "ልጄ ሆይ!" ብሎ ጠራው፤ ልጁም "እነሆ አለሁ" አለ። 2 ይስሐቅም እንዲህ አለው፣
"እንደምታየኝ አርጅቻለሁ፤ የምሞትበትንም ቀን አላውቅም፤ 3 ስለዚህ የምታድንበትን ቀስትና ፍላጻ ያዝ፤ ወደ ዱር ሂድና አውሬ አድነህ ሥጋ አምጣልኝ፤ 4 ልክ
እንደምወደው አድርገህ ምግብ ሥራልኝ ከበላሁም በኋላ ከመሞቴ በፊት የመጨረሻ ምርቃቴን እሰጥሃለሁ።" 5 ይስሐቅ ለልጁ ለዔሳው ወደ አደን ከሄደ በኋላ፣
6 ርብቃ ልጅዋን ያዕቆብን "አባትህ ዔሳውን እንዲህ ሲለው ሰማሁ፣ 7 አውሬ አድነህ ሥጋ አምጣልኝ፤ ልክ እንደምወደው አድርገህ የጣፈጠ ምግብ ሥራልኝ፤
ሳልሞትም በእግዚአብሔር ፊት እነርቅሃለሁ፤ 8 አሁንም ልጄ ሆይ! የምነግርህን አድምጥ፤ የማዝህንም አድርግ፤ 9 አባትህ እንደሚወደው አጣፋጩ ጥሩ
ምግብ እንድሠራለት፣ ወደ መንጋዎች ሂድና ሁለት የሰቡ የፍየል ጥቦቶች አምጣልኝ፤ 10 አንተም ያዘጋጀሁትን ምግብ እንዲበላ ለአባትህ ወስደህ
ታቀርብለታለህ፤ በዚህ ዐይነት አባትህ ከመሞቱ በፊት ይመርቅሃል።" 11 ያዕቆብ ግን እናቱን ርብቃን "የወንድሜ የዔሳው ገላ ጠጉራም ነው፤ የ እኔ ገላ ግን
ምንም ጠጉር የሌለው ለስላሳ ነው፤ 12 ምናልባት አባቴ ቢዳስሰኝና እንዳታለልኩህ ቢያውቅ በምርቃት ፈንታ እርግማን እንደማተርፍ ታውቂ የለምን?" አላት።
13 እናቱም "ልጄ ሆይ! የአንተ እርግማን በእኔ ላይ ይሁን፤ አሁንም እንደነገርሁህ አድርግ፤ ሄድህ ጥቦቶቹን አምጣልኝ" አለችው። 14 ስለዚህ ሄዶ ጥቦቶቹን
አመጣለት እርስዋም ልክ አባቱ እንደሚወደው እድርጋ ጥሩ ወጥ ሠራች፤ 15 የታላቁ ልጅዋን የዔሳውን የክት ልብስ ከተቀመጠበት ቦታ አውጥታ ለያዕቆብ
አለበሰችው። 16 የፍየሎቹንም ቆዳ በክንዶቹ ላይና ጠጉር በሌለበት በአንገቱ ላይ አለበሰችው። 17 ያዘጋጀውንም ጥሩ ወጥ ከጋገረችው እንጀራ ጋር ልልጅዋ
ለያዕቆብ ሰጠችው። 18 ያዕቆብ ወደ አባቱ ሄደና "አባባ!" አለው፤ እርሱም "እነሆ አለሁ! ለመሆኑ አንተ የትኛው ልጄ ነህ!" አለ። 19 ያዕቆብም "የበኲር
ልጅህ ዔሳው ነኝ፤ እነሆ እንዳዘዝከኝ አድርጌአለሁ፤ እንድትመርቀኝ እስቲ ቀና በልና ያመጣሁልህን የአደን ሥጋ ተመገብ" አለው። 20 ይስሐቅም "ልጄ ሆይ!
እንዴት ቶሎ ልታገኝ ቻልህ?" አለው። ያዕቆብም "አምላክህ እግዚአብሔር ስለረዳኝ በቶሎ ለማግኘት ቻልሁ" አለው። 21 ይስሕቅም "እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በልና
ልዳብስህ፤ በእርግጥ አንተ ዔሳው ነህን?" አለው። 22 ያዕቆብም ወደ አባቱ ተጠጋ፤ አባቱም ዳሰሰውና "ድምፅህ የያዕቆብ ድምፅ ይመስላል፤ ክንድህ ግን
የዔሳውን ክንድ ይመስላል" አለው። 23 ክንዶቹ እንደ ዔሳው ክንዶች ጠጉራም ስለ ነበሩ ይስሐቅ ያዕቆብን ለይቶ ማውቅ አልቻለም፤ ሊመርቀው ከዝዘጋጀ
በኋላ፣ 24 "እርግጥ አንተ ልጄ ዔሳው ነህን?" ሲል እንደገና ጠየቀው፤ እርሱም "አዎ ነን" አለ። 25 ይስሐቅም "ልጄ! በል ከአደንከው ሥጋ አቅርብልኝ፤
ከበላሁም በኋላ እመርቅህለሁ" አለው። ያዕቆብም ምግቡን አቀረበለት፤ የወይን ጠጅም እንዲጠጣ አመጣለት። 26 ከዚህ በኋላ አባቱ ይስሐቅ "ልጄ ሆይ!
ቀረብ በልና ሳመኝ" አለው፤ 27 ያዕቆብም ቀርቦ ሳመው። ይስሐቅ የያዕቆብ ልብስ ባሸተተ ጊዜ እንዲህ ሲል መረቀው፣ "እነሆ የልጄ መልካም ሽታ
እግዚአብሔር እንደባረከው የእርሻ ሽታ ነው፤ 28 እግዚአብሔር ከሰማይ የሚያረሰርሰው ተል ይስጥህ፤ ምድርህን ያለምልምልህ፤ እህልንና የወይን ጠጅህን
ያብዛልህ፤ 29 መንግሥታት ይገዙልህ፤ ሕዝቦችህም ያገልግሉህ፤ በወንድሞችህ ሁሉ ላይ አለቃ ሁን፤ የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ፤ የሚረግሙህ የተረገሙ
ይሁኑ፤ የሚመርቁህ የተመረቁ ይሁኑ።" 30 ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ እንዳበቃና ያዕቆብም አባቱን ፊት እንደወጣ ወዲያውኑ ዔሳው ከአደን ተመልሶ መጣ። 31
እርሱም በበኩሉ የጣፈጠ ወጥ ሠርቶ ለአባቱ አቀረበለትና "አባቴ ሆይ እንድትመርቀኝ፣ እስቲ ቀና ብለህ ካመጣሁልህ የአደን ሥጋ ብላ" አለው። 32 ይስሐቅም
'አንተ ማን ነህ?" አለው፤ እርሱም "እኔ የበኲር ልጅ ዔሳው ነኝ" አለ። 33 ይስሐቅም እጅግ ደንግጦ እየተነቀጠቀጠ "ታዲያ አውሬ አድኖ ያመጣልኝ ማን
ነበረ? ልክ አንተ ከመምጣትህ በፊት ተመገብሁ የመጨረሻ ምርቃቴንም ሰጠሁት፤ ምርቃቱም ተእርሱ ሆኖ ይኖራል"አለው። 34 ዔሳው ይህን በሰማ ጊዜ
ድምፁን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ እያለቀሰ "አባቴ ሆይ! እኔንም መርቀኝ!" አለ። 35 ይስሐቅም "ወንድምህ መጥቶ እኔን በማታለል የአንተን ምርቃት
ወስዶብሃል"አለው። 36 ዔሳውም "እርሱ እኔን ሲያሰናክለኝ ይህ ሁለተኛው ነው፤ ያዕቆብ መባሉ ተገቢ ነው፤ ከዚህ በፊት ብኩርናዬን ወሰደብኝ፤ አሁን ደግሞ
ምርቃቴን ቀማኝ፤ ታዲያ ለእኔ ያስቀረከው ምንም ምርቃት የለምን? አለው። 37 ይስሐቅም "ቀድሞ ብዬ እርሱን የአንተ ጌታ አድርጌዋለሁ፤ ወንድሞቹ ሁሉ
የእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ አድርጌአለሁ፤ እህልና የወይን ጠጅ እንዲበዛለት አድርጌአለሁ፤ ልጄ ሆይ! እንግዲህ ለአንተ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?" አለው።
38 ዔሳውም "አባቴ ሆይ! ምርቃትህ እንዲት ብቻ ናትን? እባክህ እኔንም መርቀኝ" እያለ ለማልቀስ አባቱን ነዘነዘው። 39 ይስሐቅም አንዲህ አለው። "በረከት
ከሞላበት ለምለም ምድር ርቀህ ትኖራለህ፤ የሰማይ ጠልም አታገኝም፤ 40 በሰይፍም ኀይል ትኖራለህ፤ የወንድምህም አገልጋይ ትሆናለህ፤ በተቃወምከውም
ጊዜ ግን ከእርሱ ጭቁና ትላቀቃለህ።" 41 አባቱ ስለመረቀው ዔሳው ያዕቆብን አጥብቆ ጠላው፤ በልቡም "አባቴ በቅርብ ቀን ይሞታል፤ ከዚህ በኋላ ወንድሜን
ያዕቆብን እገድለዋለሁ"ብሎ አሰበ። 42 ነገር ግን ርብቃ የዔሳውን ዕቅድ ስለ ሰማች፣ ያዕቆብን ጠርታ እንዲህ አለችው፣ "አድምጠኝ፤ ወንድምህ ዔሳው አንተን
በመግደል ሊበቀልህ አስቦአል፤ 43 አሁንም ልጄ ሆይ! የምልህን አድርግ፤ ተነሥተህ በካራን ወደሚገኘው ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሽሽ፤ 44 የወንድምህ ቁጣ
እስኪበርድ ድረስ ለጥቂት ጊዜ እዚያው ቆይ፤ 45 ቁጣውም ሲበርድ ያደረግህበትን ነገር ይረሳል፤ ከዚያ በኋላ ሰው ልኬ አስመጣሃለሁ፤ ሁለታችሁም በአንድ
ቀን ማጣት አልፈልግም። 46 ርብቃ ይስሐቅን "ዔሳው ባገባቸው በእነዚህ በሖታውያን ሴቶች ምክንያት መኖሬን ጠላሁት፤ ያዕቆብ ደግሞ ከነዚህ ከሒታውያን
ሴቶች አንዲቱ ከገባ ለመኖር ይልቅ ሞቴን እመርጣለሁ"አለችው።

Genesis 27:1

ዓይኖቹ ደክመው

ይህ የሚናገረው ዓይኖች እንደ መብራት ብርሃን እየቀነሱ እንደሄዱ እና ማየት ወደ መሳን ደረጃ እንደደረሱ ነው:: አት: “ዓይኖቹ ማየት ተስኖአቸው” ወይም “ዓይኖቹ ወደ መታወር ደርሰው” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

እርሱም እርሱን አለው

“ዔሣው መለሰለት”“ዔሣው መለሰለት”

እነሆ አለው

“እነሆ አለሁ” ወይም “እየሰማሁ ነኝ” በዘፍጥረት 22:1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እርሱም አለው

“ከዚያም ይሥሐቅም አለ”

ይሄው ተመልከት

“ይኼው ተመልከት” የሚለው ሀረግ ለሚቀጥለው ሃሳብ አጽንዖት የሚሰጥ ነው:: አት: “በጥንቃቄ ስማ ግምታዊ እውቀት” ወይም “ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ”

የምሞትበትን ቀን አላውቅም

ይህ ይስሐቅ ቅርብ ጊዜ እንደሚሞት የሚያመለክት ነው:: አት: “ከማንኛውም ጊዜ ለሞት ይሆናል”:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ሞት
አካላዊ ሞትን ይገልጻል

Genesis 27:3

አጠቃላይ መረጃ
“ይስሐቅ ለታላቅ ልጁ ለዔሣው መመሪያልችን ይሰጣል”

የአደን መሣሪያህን
“የአደን መሣሪያዎችህን”

የፍላጻ ኩሮጃ
የፍላጻ ኩሮጃ የቀስቶች መሸከሚያ ነው:: አት: “የቀስቶች መሸከሚያ ኩሮጃ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አድነህም አምጣልኝ
“የዱር እንስሳት አድነህ አምጣልኝ”

የምወደው ዓይነት ጣዕም ያለው ምግብ አዘጋጅተህ
“ጣዕም ያለው” የሚለው ቃል እጅግ በጣም ጣፋጭ የሆነውን ነገር ያመለክታል:: አት: “የምወደው ዓይነት የሥጋ ምግብ አዘጋጅልኝ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እንዲመርቅህ
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን አባት መደበኛ የሆነ መንገድ ልጆችን ይመርቃል

Genesis 27:5

“በወቅቱ”
በወቅቱ የሚለው ቃል ትኩረቱ ወደ ርብቃና ያዕቆብ መዞሩን ያሳያል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ርብቃም ይስሐቅ ለልጁ ለዔሣው ሲነግር ትሰማ ነበር
“ይስሐቅ ለልጁ የተናገረውን ርብቃ ትሰማ ነበር”

ዔሣው ... ለማምጣት ሄደ:: ርብቃም ያዕቆብን እንዲህ አለችው
ዔሣው ከወጣ በኋላ ርብቃ የሰማችውን ለያዕቆብ ተናገረች:: አት: “ዔሣው ለማምጣት በወጣ ጊዜ ርብቃም ለያዕቆብ ተናገረች” (አያየዥ ቃላት ይመልከቱ)

ለዔሣው ለልጁ .... ለያዕቆብ ልጅዋን
ዔሣውና ያዕቆብ ሁለቱም የይስሐቅና የርብቃ ልጆች ናቸው አንድ ወላጅ አንዱን ልጅ ከሌላኛው ልጅ አብልጦ እንደሚወድ ተደርገው የእርሱ ልጅ እና የእርስዋ ልጅ ተብለው ተጠርተዋል::

ይሄው ተመልከት
“ይኼው ተመልከት” የሚለው ሀረግ ለሚቀጥለው ሃሳብ አጽንዖት የሚሰጥ ነው:: አት: “በጥሞና ስማ ግምታዊ እውቀት” ወይም “ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ”

እርሱም አለ ከመሞቴ በፊት በእግዚአብሔር ፊት እንዲመርቅህ ጥሩ ጣዕም ያለው ምግብ እንድበላ አዘጋጅልኝ
ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ነው:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል አት: “ለዔሣውም ነገረው; ‘የዱር እንስሳ እንዲያድንና የሚወደውን ጣዕም የሥጋ ምግብ እንዲያዘጋጅለት’ ከዚያም ከመሞቱ በፊት በእግዚአብሔር ፊት የስሐቅ ዔሣውን እንዲባርከው” (በጥቅስ ውስጥ ጥቅሶችንና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)::

አድነህም አምጣልኝ
“የዱር እንስሳት አድነህ ገድለህ አምጣልኝ”

የምወደው ዓይነት ጣዕም ያለው ምግብ አዘጋጅተህ
“የምወደው ዓይነት የሥጋ ምግብ አዘጋጅልኝ” ይህን በዘፍጥረት 27:4 እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

በእግዚአብሔር መገኘት እንዲመርቅህ
“በእግዚአብሔር ፊት እንዲመርቅህ”

Genesis 27:8

አጠቃላይ መረጃ
ርብቃ ለሁለተኛ ልጅዋ ለያዕቆብ መናገርዋን ቀጠለች

አሁንም
ይህ በዚያ ወቅት የሚለውን የሚናገር አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው::

እኔ በማዝዝህን ድምጼን ስማኝ
ርብቃ “ድምጼን” ያለችው የምትናገረውን ነገር ለማመልከት ነው:: አት: “ታዘዘኝ የምናገረውንም ነገር አድርግ” (ተዛማጅ ባሕሪይ የሚገልጽ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እነርሱንም አባትህ እንደሚወደው ዓይነት ጣፋጭ ምግብ አዘጋጅለታለሁ
ጣፋጭ የሚለው ቃል በጣም ጥሩ ጣዕም ያለውን ነገር ያመለክታል:: በዘፍጥረት 27:4 ተመሳሳይ ቃል እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

ወደ አባትህም ይዘህ ግባለት
“ከዚያም ወደ አባትህ ይዘህ ግባ”

እንዲበላ እንዲመርቅህ
ከበላ በኋላ ይመርቅሃል

ይመርቅህ ይሆናል
ምርቃት የሚለው ቃል አባት ልጆቹን የሚናገረው መደበኛ ምርቃት ነው

ከሞቱ በፊት
ከመመቱ በፊት

Genesis 27:11

እኔ ለስላሣ ነኝ
“የእኔ ገላ ለስላሣ ነው” ወይም “እኔ ጸጉራም አይደለሁም”

በምርቃት ፈንታ ርግማን አተርፋለሁ
መረገም ወይም መባረክ ምርቃት ወይም በረከት በአንድ ሰው ላይ እንደሚሆን ዕቃ ተደርገው ተነግረዋል አት ከዚያም ከዚህም የተነሣ ይረግመኛል ወይም አይባርከኝም (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 27:13

ልጄ ሆይ ማንኛውም ርግማን በእኔ ላይ ይድረስ
“ልጄ ሆይ መርገምህ በእኔ ላይ ይሁን” መረገም ርግማን በአንድ ሰው ጫንቃ ላይ እንደሚሆን ዕቃ ተደርጐ ተገለጾአል:: አት “ልጄ ሆይ አባትህ አንተን ከመርገም እኔን ይርገመኝ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ድምጼን ታዘዝ
ርብቃ “ድምጼን” ያለችው የምትናገረውን ነገር ለማመልከት ነው:: አት: “የሚናገርህን ታዘዝ” ወይም “ታዘዘኝ” (ተዛማጅ ባሕሪይ የሚገልጽ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እነርሱን አምጣልኝ
“ጠቦቶቹን አምጣልኝ”

ልክ አባቱ እንደሚወደው ዓይነት ጣፋጭ ምግብ አዘጋጀችለት::
ጣፋጭ የሚለው ቃል በጣም ጥሩ ጣዕም ያለውን ነገር ያመለክታል:: በዘፍጥረት 27:4 ተመሳሳይ ቃል እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

Genesis 27:15

ጠቦቶቹን ቆዳ በእጆቹ ላይ አለበሰችው
የጠቦቶች ቆዳዎች ጸጉር ነበረባቸው

የሠራችውን ጣፋጭ መብልና እንጀራውን ለልጅዋ ለያዕቆብ በእጁ ሰጠችው
“የሠራችውን ጣፋጭ መብልና እንጀራውን ለልጅዋ ለይዕቆብ ሰጠችው”

Genesis 27:18

እርሱም አለው
“እናም አባቱ መለሰው” ወይም “ይስሐቅም መለሰው”

እነሆኝ
“አዎን እየሰማሁ ነኝ” ወይም “አዎን ምንድነው?” በዘፍጥረት 22 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

የተናገርከኝ ወይም ያዘዝከኝን አድርጌአለሁ
እንዳደርገው የነገርከኝን አድርጌአለሁ

አደን አድኜ ካመጣሁት ከፊሉ
“የታደነ” የምለው ቃል አንድ ሰው የዱር እንሰሳትን አድኖና ገድሎ የሚያቀርበውን ያመለክታል:: በዘፍጥረት 27:3 “የታደነ” የሚለው እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Genesis 27:20

እርሱም አለው
ያዕቆብም መለሰው

አሳካልኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር ለሁኔታው ምክንያን እንደሆነ ይገልጻል:: አት: “በማድንበት ጊዜ እንዲሳካልኝ ረድቶኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገሮች ይመልከቱ)::

በእርግጥ እውነተኛው ልጄ ዔሣው መሆንህን
“በእርግጥ ልጄ ዔሣው መሆንህን”

Genesis 27:22

ያዕቆብ ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ቀረበ
“ያዕቆብ ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ተጠጋ”

ይህ ድምጽ የያዕቆብ ድምጽ ነው
እዚህ ይስሐቅ የያዕቆብ ድምጽ ያዕቆብን እንደሚወክል ይናገራል። አት፡ “ድምጽህ የያዕቆብ ይመስላል” (ክፍልን እንደ ሙሉ ወይም ሙሉውን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

እጆቹ ግን የዔሣው እጆች ናቸው
እዚህ ይስሐቅ የዔሣው እጆች ዔሣውን እንደሚወከሉ ይናገራል። አት፡ እጆች ግን የኤሣው እጆች እንደሆኑ ይሰሙኛል። (ክፍልን እንደ ሙሉ ወይም ሙሉውን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 27:24

እርሱም አለ
ይስሐቅ ልጁን ከመባረኩ በፊት ይህን ጥቃቄ ይጠይቀዋል:: አት: “ነገር ግን መጀመሪያ ይስሐቅ ጠየቀው” (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

አድነህ ካቀረብክልኝ ልብላ
የታደነ የሚለው ቃል ሰዎች አድነውና ገድለው የሚያቀርቡትን የዱር እንሰሳ ያመለክታል:: በዘፍጥ 27:7 የታደነ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

ጠጣም
“ይስሐቅ ጠጣ”

Genesis 27:26

እርሱም ልብሶቹን ካሸተተ በኋላ መረቀው
ልብሶች የኤሣው ልብሶች ሽታ እንዳሸቱ ግልጽ ነው:: አት: “እርሱም ልብሶቹን አሸተተ እናም ሽታው እንደ ዔሣው ልብሶች ሽታ ስለሆነ ባረከው” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አሸተተ
ይስሐቅ አሸተተ

ሽታ
ጠረን

ባረከው
“ከዚያም ባረከው” ይህ አባት ልጆቹን የሚባረከውን መደበኛ በረከት ያመለክታል::

እነሆ የልጄ ጠረን
“እነሆ” የሚለው ቃል ይህ እውነት ነው የሚለውን ለመግለጽ የተጠቀመ አበክሮአዊ ሥዕላዊ አገላለጽ ነው:: አት: “በእውነት የልጄ ጠረን”

እግዚአብሔር እንደባረከው
እዚህ በረከት የሚለው ቃል እግዚአብሔር በእርሻው መልካም ነገሮች እንዲሆኑና ፍሬያማ እንዲሆን እንዲያደርግ ነው:: አት: “ያም እግዚአብሔር ፍሬያማ እንዲያደርግ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 27:28

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የይስሐቅ ባረኮት ነው ለኤሳው የተናገረው መሰለሙ ነገር ግን የተናገረው ለያዕቆብ ነው

ይስጥህ
እዚህ “ይስጥህ” ነጠላና ያዕቆብን የሚያመለክት ነው በረከቱ ግን ለያዕቆብ ትውልድም የሚሆን ነው:: (ሁለተኛ ሰው አጠቃቀምንና ክፍልን እንደ ሙሉ እና ሙሉን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የሰማይን ጠል
ጠል በሌሊት በተክሎች ላይ የሚሆን የውሃ ጠብታ ነው:: በትርጉም ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ተክሎችዎን ለማጠጣት የሌሊት ጠል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የምድርንም በረከት
ለም መሬት የመኖር መሬት ስብና ሀብታም እንደሆነች ተደርጐ ተገለጾአል:: አት: “እህልን የሚያመርት መልካም መሬት ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ”

የተትረፈረፈ እህልና አዲስ የወይን ጠጅ
“እህል”ና “ወይን” ያልተገለጹ እስከሆነ ድረስ ጠቅለል ባለ መልክ መግለጽ ይቻላል:: አት: “የተትረፈረፈ መብልና መጠጥ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 27:29

አንተ.... ያንተ
እዚህ እነዚህ ተውላጤ ስሞች በነጠላ የተገለጹና የዕቆብን ያመለክታሉ በረከቱ ግን ለያዕቆብ ትውልድም ነው (ሁለተኛ ሰው አገላለጽንና ክፍልን እንደ ሙሉ እና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ሕዝቦች ተደፍተው እጅ ይንሡህ ወይም ይስገዱልህ
እዚህ ሕዝቦች ሰዎችን ያመለክታል አት የሁሉም ሕዝቦች ሰዎች ተደፍተው እጅ ይንሡህ:: (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ይስገዱልህ
ይህ ጐንበሥ በማለት አንድ ሰው አክብሮት መስጠትን ይገልጻል ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ

የወንድሞችህ ጌታ ሁን
በወንድምችህ ላይ ጌታ ወይም ገዢ ሁን

ወንድሞችህ ...የእናትህም ልጆች
ይስሐቅ ይህን በረከት በቀጥታ ለያዕቆብ ይናገራል ነገር ግን ይህ የያዕቆብ ትውልድ በኤሣው ትውልድና በሌሎች ማናቸውም የያዕቆብ ወንድሞች ትውልድ ላይ ገዢዎች እንደሚሆኑ ለእነርሱም ይሆናል። (ክፍል ለሙሉና ሙሉን ለክፍል የመጠቀም አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ
የእናትህም ልጆች የሰግዱልሃል

የምረግሙህ የተረገሙ ይሁኑ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር የሚረግሙህን ሁሉ ይርገማቸው“ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የሚባርኩህ የተባረኩ ይሁኑ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር የሚባርኩህን ሁሉ ይባርካቸው“ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 27:30

ያዕቆብም ገና ከአባቱ ዘንድ ሳይወጣ ወዲያውኑ
“ከአባቱን ከይስሐቅን ድንኳን እንደወጣ”

ጣፋጭ ምግብ
የምወደው ጣፋጭ ሥጋ በዘፍጥረት 27፡3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ልጅህ ካደንሁት
እዚህ “ልጅህ” ኤሣው ካደነው ያዘጋጀውን ምግብ በትህትና ያቀረበበት መንገድ ነው:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ልጅህ ካደነው
የታደነ የሚለው ቃል ሰዎች አድነውና ገድለው የሚያቀርቡትን የዱር እንስሳ ያመለክታል:: በዘፍጥ 27:7 የታደነ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

ባርከኝ
ይህ አንድ አባት ልጆቹን የሚባርክበት መደበኛ መንገድ ያመለክታል

Genesis 27:32

ለእርሱም አለው
ዔሣውን አለው

ይስሐቅም ተንቀጠቀጠ
ይስሐቅም መንቀጥቀጥ ጀመረ

በአደን የታደነ
የታደነ የሚለው ቃል ሰዎች አድነውና ገድለው የሚያቀርቡትን የዱር እንስሳ ያመለክታል:: በዘፍጥ 27:7 የታደነ እንዴት አንደተተረጐመ ይመልከቱ::

Genesis 27:34

ድምጹን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ አለቀሰ
የዔሣው ምሬት አንድ መራራ ጣዕም ካለው ነገር ጋር የሚመሳሰል ነበር:: አት: “በከፍተኛ ድምጽ አለቀሰ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ምርቃትህን ወስዶብሃል
ይህ ያዕቆብ የዔሣውን በረከት እንደወሰደ የሚገልጽ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው አት በአንተ ፈንታ እርሱን ባርከአለሁ (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 27:36

ያዕቆብ መባሉ የሚታወቅ አይደለምን?
ዔሣው በያዕቆብ ላይ ያለውን ቁጣ ለመጨመር ጥያቄ ይጠቀማል:: አት ያዕቆብ በእርግጥ ለወንድሜ ትክክለኛ ስም ነው:: (ቅኔያዊ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ያዕቆብ
ተርጓሚዎች እንዲህ የሚለውን የግርጌ ማስታወሻ ይጠቀማሉ ያዕቆብ የሚለው ስም ተረከዙን ያዘ የሚል ትርጉም አለው በመሠረታዊው ቋንቋ ቃሉ አታላይ የሚል አንድምታ አለው::

ብኩርናዬን ወሰደብኝ
ይህ ብኩርና እንደ አንድ ዕቃ ከሰው እንደሚወሰድ አድርጐ ይናገራል:: አት: “የእኔ የሆነው ብኩርና በማታለሉ ምክንያት የእርሱ ሆኖአል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

አሁን ደግሞ ምርቃቴን ቀማኝ
ይህ ምርቃት እንደ አንድ ዕቃ ከሰው እንደሚቀማ አድርጐ ይናገራል:: አት : “አታልሎህ በእኔ ፈንታ እርሱን እንዲትመርቅ አደረጐሃል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)::

ለእኔ ያስቀረኼው ምንም ምርቃት የለም?
ያዕቆብን የባረከውን ዓይነት በረከት አባቱ እንደማይባርከው ዔሣው ያውቃል ይስሐቅ ያዕቆብን በሚባርክበት ጊዜ ሳይናገር የቀረው ካለ ዔሣው ይጠይቀዋል

ልጄ ለአንተ ምን ላደርግልህ እችላለሁ?
ይስሐቅ ጥያቄ በመጠቀም ምንም ሊያደርገው የሚችለው ነገር እንደሌለ በአጽንዖት ይናገራል:: አት “ለአንተ የማደርገው የቀረ ነገር የለም” (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 27:38

አባቴ ሆይ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን?
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊነገር ይችላል:: አባቴ ሆይ አንድ የቀረ መረከት ለእኔ የሚሆን አለህን?

Genesis 27:39

እርሱን አለው
ዔሣውን አለው

ቦታውን ተመልከት
ትኩረት አድርግ ስለቦታው የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነው

ከምድር በረከት የራቀ
ይህ ስለምድር ለምነት የሚናገር ምሳሌያዊ አነጋገር ነው አት ለም ያልሆነ መሬት

ለአንተ.... አንተ
በ27:39-40 እነዚህ ተውላጤ ስሞች ነጠላና ዔሣውን ያመለክታሉ:: ነገር ግን ይስሐቅ የሚናገረው ለዔሣው ትውልድም የሚሆን ነው:: ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ::

ከላይም ከሰማይ ጠል
ጠል በሌሊት በተክሎች ላይ የሚሆን የውሃ ጠብታ ነው:: በትርጉም ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ተክሎችዎን ለማጠጣት የሌሊት ጠል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሰይፍ ትኖራለህ
ሰይፍ ለአመጽ የሚቆም ነው:: አት: “ለመኖር የሚያስፈልግህን ለማግኘት ሰዎችን ትዘርፋለህ ትገድላለህ” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል ስለመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ቀንበሩ ከጫንቃህ ላይ ወዲያው ትጥላለህ
ይህ አንድ ጌታ እንዳለውና የጌታውም የበላይ አገዛዝ እንደሚሸከምበት ቀንበር እንደተጫነበት ተደርጐ ተነግሮአል አት ከግዛቱ ራስህን ነጻ ታወጣለህ:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 27:41

ዔሣውም በልቡ እንዲህ ብሎ አሰበ
“ልብ” ራሱ ዔሣውን ያመለክታል:: አት: “ዔሣው ለራሱ እንዲህ አለ” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ) የአባቴ የለቅሶ ቀን ቀርቦአልና ይህ የቤተሰብ አባል ሲሞት አንድ ሰው የሚያዝንበት ቀናት ያመለክታል

የታላቅ ልጇ የኤሣው ሀሳብ ለርብቃ ተረገራት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “አንድ ሰው የዔሣውን ዕቅድ ለርብቃ ነገራት“ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እይ
“ተመልከት” “አዳምጥ” “ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጥ”

ራሱን እያረጋጋ ነው
ራሱን ጥሩ ስሜት እንዲሰማው እያደረገ ነው

Genesis 27:43

አሁንም
ይህ “አሁን ጊዜ” ማለት አይደለም:: ነገር ግን የሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል::

ወደ ላባን ቶሎ ሽሽ
ቶሎ ከዚህ ሽሽ እናም ወደ ላባን ሂድ

ለጊዜ
ለተወሰነ ጊዜ

የወንድምህ ቁጣ እስኪበርድ
ወንድምህ እስኪበርድ

የወንድምህ ቁጣ ከአንተ እስኪመለስ
ያለ መቆጣት ቁጣ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደሚዞር ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “በአንተ ላይ መቆጣቱን እስኪተው ድረስ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሁለታችሁን በአንድ ቀን ለምን ለጣ?
ርብቃ ሥጋትዋን ለመግለጽ ጥያቄ ትጠቀማለች አት ሁለታችሁን በአንድ ቀን ማጣት አልፈልግም! (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ሁለታችሁን በአንድ ቀን አጣለሁ
ይህ የሚገልጸው ኤሣው ያዕቆብን ከገደለ እርሱ ደግሞ ገዳይ በመሆኑ ስለሚገድሉት ነው:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አጣለሁ
ልጆቹዋ እንደሚሞቱባት የሚያመላክት ለዛ ያለ አገላለጽ ነው (ንጉብነት ወይም ለዛ ባለ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 27:46

መኖር አስጠልቶኛል
ኤሣው የኬጢያውያን ሴት በማግባቱ ርብቃ መንኛ እንደተናደደች በማግነን ትኩረት መስጠትዋ ነው:: አት: “በማምረር ጠልቸዋለሁ” (hyperbole and Generalization/

የኬጢያውያን ሴት ልጆች
“እነዚህ የኬጢያውያን ሴቶች” ወይም “የኬጢያውያን ትውልጆች”

እንደነዚህ ሴቶች ከዚህ አገር ሴቶች ልጆች
“የአገሩ ሴቶች ልጆች” የአገሩ ሴቶች ማለት ነው:: አት: “በአገሩ የሚኖሩ እንደ እነዚህ ሴቶች” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

በሕይወት መኖር ለምኔ ነው?
ያዕቆብ ከኬጢያውያን ሴት ልጆች የሚያገባ ከሆነ ርብቃን ማነኛ እንደሚያስከፋት በማግነን ጥያቄ ትጠቀማለች:: አት: “ሕይወቴ የከፋ ይሆናል”

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 28

1 ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ መረቀው፤ እንዲህም ሲል አዘዘው፣ "ከነዓናዊት ሴት እንድታገባ፤ 2 ይልቅስ ተነሥተህ በመስጴጦምያ ወዳለው ወደ እናትህ አባት
ወደ ባቱኤል ቤት ሂድ፤ እዚያም ከአጎትህ ከገባ ሴቶች ልጆች አንዷን አግባ፤ 3 ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ይባርክህ፤ ብዙ ልጆችም ይስጥህ፤ የብዙ
ሕዝቦችም አባት ያድርግህ፤ 4 አብርሃምን እንደባረከ አንተንና ዘርህን ይባርክ፤ ይህንንም ለአብርሃም ሰጥቶት የነበረውንና አንተም ደስተኛ ሆነህ የኖርክበት ምድር
ርስት አድርጎ ይስጥህ።" 5 በዚህ ሁኔታ ይስሐቅ ያዕቆብን አሰናበተው፤ ያዕቆብም በመስጴጦምያ ወደሚያኖረው ወደ ላባ ሄደ፤ ላባ የያዕቆብና የዔሳው እናት
የርብቃ ወንድም ነበረ፤ አባቱም ሶርያዊው ባቱኤል 6 ይስሐቅ ያዕቆብን እንደመረቀና ሚስት እንደሚፈልግ ወደ መስጴጦምያ እንደላከው ዔሳው ተረዳ፤ ይስሐቅ
ያዕቆብን ሲመርቀው "ከነዓናዊት ሴት እንዳታገባ" ብሎ ያዘዘው መሆኑንም ሰማ፤ 7 ያዕቆብ ለአባቱና ለእናቱ በመታዘዝ ወደ መስጴቶምያ መሄዱንም ተረዳ፤ 8
በዚህም አባቱ ይስሐቅ የከነዓንያውያንን ሴቶች እንደማይወድ ዔሳው ተገነዘበ፤ 9 ስለዚህ ከዚህ በፊት ከገባቸው ሌላ በተጨማሪ ወደ አብርሃም ልጅ ወደ
እስማኤል ሄዶ ልጁን ማሕላትን አገባ፤ እርስዋም የነባዮት እኅት ናት። 10 ያዕቆብ ቤርሳቤህን ትቶ ወደ ካራን ለመሄድ ተነሣ፤ 11 ፀሐይ በጠለቀች ጊዜ ወደ
አንድ ስፍራ መጥቶ ዐፈር፤ በዚያም አንድ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፤ 12 በሕልሙም ከመሬት እስከ ሰማይ የሚደርሰው መሰላል አየ፤ በመሰላሉም የእግዚአብሔር
መላእክት ወደ ላይ ይውጡና ወደ ታች ይውረዱ ነበር። 13 እግዚአብሔር በአጠገቡ ቆሞ እንዲህ አለው፣ "እኔ የአባትህ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ
እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአንተና ለዝርያዎችህ እንዲሆን ይህን የተገኘበት ምድር እሰጥሃለሁ። 14 ዘርህን እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ፤ እነርሱ በሁሉ አቅጣጫ
ይዞታቸውን ያስፋፋሉ፤ በአንተና በዘርህ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ። 15 አይዞህ! እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚያም
ምድር በደህና እመልስሃለሁ፤ የገባሁልህን ቃል ኪዳን ሁሉ እፈፅምልሃለሁ፤ ከቶም አልተውህም።" 16 ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቃና "በእርግጥ እግዚአብሔር
በዚህ ስፍራ አለ፤ እኔ ግን ይህን አላወቅሁም ነበር"አለ። 17 በጣም ፈርቶም ስለነበር "ይህ እንዴት የሚያስፈራ ቦታ ነው፤ ይህ የእግዚአብሔር ቤት መሆን
አለበት፤ ወደ ሰማይ የሚያስገባው በር ይህ ነው"አለ። 18 ያዕቆብ በማግሥቱም ጠዋት በማለዳ ተነሣ፤ ተንተርሶት የነበረውንም ድንጋይ መታሰቢያ እንዲሆን
እንደ ሐውልት አቆመው፤በላዩ ላይም የወይራ ዘይት አፈሰሰበት። 19 ይህንንም ስፍራ "ቤትኤል"ብሎ ሰየመው፤ ይህ ስፍራ ከዚያ በኋላ ሎዛ እየተባለ ይጠራ
ነበር። 20 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ለእግዚአብሔር ተሳለ "ከእኔ ጋር ሆነህ በምትሄድበት መንገድ ብትጠብቀኝ፣ የሚያስፈልገኝን ምግብና ልብስ
ብትሰጠኝ፣ 21 ወደ አባቴም ቤት በሰላም ብትመልሰኝ፤ አንተ አምላኬ ትሆናለህ፤ 22 ይህ ለመታሰቢያነት ያቆምሁት ድንጋይ ወደ ፊት የእግዚአብሔር ቤት
ይሆናል፤ ከምትሰጠኝም ሁሉ ከዐሥር አንዱን እጅ ለአንተ እሰጣለሁ።"

Genesis 28:1

አታግቡ
አታግባ

ተነሣ ሂድ
ወዲያውኑ ሂድ

ጳዳን አራም
ይህ የመስጴጦምያ ግዛት ሌላ ስሙ ሲሆን የአሁኑ ራቅ የሚገኝበት ቦታ ነው:: በዘፍጥረት 25:20 ይህ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ቤት
የሰውየው ትውልድ ወይም ሌሎች ዘመዶች: አት: “ቤተሰብ” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ባቱኤል
ባቱኤል የርብቃ አባት ነው በዘፍጥረት 22፡22 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

የእናትህ አባት
ወንድ አያትህ

ሴት ልጆች መካከል
ከሴት ልጆች

የእናትህ ወንድም
አጐትህ

Genesis 28:3

አጠቃላይ መረጃ
ይስሐቅ ለያዕቆብ መናገሩን ቀጠለ

ልጆች አፍራ ዘርህን ያብዛው
ያብዛው የሚለው ቃል እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዴት ፍሬያማ እንደሚያደርገው ይገልጻል:: አት: “ብዙ ልጆችንና ትውልድ ይሰጥሃል” (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ለአብርሃም የሰጠውን በረከት ለአንተና ለዘሪህ ይስጥ
ይህ የሚናገረው አንድን ሰው ስለመባረክ ሲሆን በረከት አንድ ሰው ሊሰጥ እንደሚችል ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል ረቂቅ ስም “በረከት” “ይባርክ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት: “አብርሃምን እንደባረከ አንተንና ዘርህን እግዚአብሔር ይባርክ” ወይም “ለአብርሃም የገባውን ተስፋ ለአንተና ለዘርህ እግዚአብሔር ይስጥ”:: (ዜይቤያዊ አነጋገርና ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ምድሪቱን ያወርስህ ዘንድ
እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለያዕቆብና ለዘሩ መስጠቱ ልጅ ከአባቱ ገንዘብ ወይም ሀብት እንደሚወርስ ተደርጐ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የሚትኖርበትን ይህችን ምድር
“እስከአሁን ያለህበትን ምድር”

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን
እግዚአብሔር ለአብርሃም ተሰፋ የሰጠውን

Genesis 28:5

ጳዳን አራም
ይህ የመስጴጦምያ ግዛት ሌላ ስሙ ሲሆን የአሁኑ ራቅ የሚገኝበት ቦታ ነው:: በዘፍጥረት 25:20 ይህ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ባቱኤል
ባቱኤል የርብቃ አባት ነው በዘፍጥረት 22፡22 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 28:6

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ ከያዕቆብ ወደ ዔሣው ይዞራል

አሁንም
ይህ ቃል እዚህ የተጠቀመው ከተነገረው ታሪክ ወደ ዔሣው የሕይወት መረጃ ፍሰቱ መቀየሩን ለማመልከት ነው (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ጳዳን አራም
ይህ የመስጴጦምያ ግዛት ሌላ ስሙ ሲሆን የአሁኑ ራቅ የሚገኝበት ቦታ ነው:: በዘፍጥረት 25:20 ይህ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ሚስት ያግባ
ሚስትን ያግባ

እንዲሁም ደግሞ ይስሐቅም እንደባረከው አየ
እንዲሁም ይስሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው ኤሣው አየ

የከነዓን ሴቶች
የከነዓን ሴት ልጆች ወይም የከነዓናዊያን ሴቶች

Genesis 28:8

አጠቃላይ መረጃ
የዔሣውን ታሪካዊ ዳራ ይቀጥላል

ዔሣው አየ
ዔሣው ተገነዘበ

ከነዓናውያን ሴቶች በአባቱ በይስሐቅ ዘንድ ተጠልተዋል
አባቱ ይስሐቅ የከነዓናውያንን ሴቶች አልተቀበለም

የከነዓን ሴቶች
የከነዓን ሴት ልጆች ወይም የከነዓናዉያን ሴቶች

ስለዚህም ሄዱ
በዚህ ምክንያት ሄዴ

በሚስቶቹ ተጨማሪ
ከነበሩ ሚስቶች ተጨማሪ

ማዕሌት
የእስማኤል ሴት ልጆች አንዷ ነች (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ነባዮት
ከእስማኤል ወንድ ልጆች አንዱ ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 28:10

አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ እንደገና ወደ ያዕቆብ ይመለሳል

ወደ አንድ ሥፍራም ደረሰ ጸሐይም ጠልቃ ነበርና ከዚያ አደረ
ወደ አንድ ሥፍራ ደረሰ ጸሐይም ጠልታ ስለነበር አዳሩን ከዚያ ለማድረግ ወሰነ

Genesis 28:12

እርሱም ሕልም ዐለመ
ያዕቆብ ሕልም ዐለመ

በምድር ላይ ቆሞ
ታችኛው አካል መሬትን በነካ መንገድ ቆሞ

ጫፉ ሰማይ የሚደርስ
ይህ እግዚአብሔር የሚኖርበትን ቦታ ያመለክታል

እነሆም
እነሆም የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት ነው

እግዚአብሔር በጫፉ ላይ ቆሞ
ተገቢ ትርጉሞች 1 እግዚአብሔር በመሰላሉ ጫፍ ላይ ቆሞ 2 እግዚአብሔር በያዕቆብ ጐን ቆሞ

ለአብርሃም ለአባትህ
እዚህ “አባት” ቅድመ ዘር ማለት ነው:: አት: “አብርሃም ለዘርህ” ወይም “አብርሃም ለቅድመ አያትህ”

Genesis 28:14

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለያዕቆብ በሕልም መናገሩን ቀጠለ

ዘርህ እንደምድር አሸዋ ይሆናል
በቁጥር መብዛትን አግንኖ ለማሳየት እግዚአብሔር የያዕቆብን ዘር ከምድር አሸዋ ጋር ያነጻጽራል:: አት: “መቁጠር ከምትችሉት በላይ ብዙ ዘር ይሆንላችኋል” ተመሣሣይ አባባል/simile ይመልከቱ

እስከ ምዕራብ ትስፋፋለህ
ትስፋፋለህ በነጠላ የተቀመጠና ያዕቆብን ያመለክታል እዚህ ያዕቆብ ዘሩን ይወክላል:: አት: “መቁጠር ከሚትችለው በላይ ብዙ ዘር ይሆንልሃል” (ተዛማጅ ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ትስፋፋለህ
ይህም ሕዝቡ የምድራቸውን ድንበር የሰፋሉ እናም ብዙ ምድር ይወርሳሉ ማለት ነው

ወደ ምዕራብ ወደ ምሥራቅ ወደ ሰሜን ወደ ደቡብ
እንዚህ ሀረጐች በጣምራ “ወደ ሁሉም አቅጣጫዎች” የሚል ትርጉም ለመስጠት ተጠቅመዋል:: (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተና በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በአንተና በዘርህ በምድር ያሉ ሕዝቦችን እባርካለሁ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

እነሆ እኔ
ትኩረት ስጥ እኔ የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነው፤ እኔ

አልተውህም ሁሉንም እፈጽምልሃለሁ
ሁሉንም እስከሚፈጽምልህ ድረስ አልተውህም

እጠብቅሃለሁ
“ደኅንነትህን እጠብቃለሁ” ወይም “እከላከልልሃለሁ”

እንደገና ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ
ወደዚህች ምድር እመልስሃለሁ

Genesis 28:16

ከእንቅልፉ ሲነሣ
ከእንቅልፉ ሲነቃ

የእግዚአብሔር ቤት ... የሰማይ ደጅ
የሰማይ ደጅ የሚለው ሀረግ የሚገልጸው የእግዚአብሔር ቤት እና የእግዚአብሔር መኖሪያ መግቢያ ቦታ እንደሆነ ነው (ድርብ ቃላትና አባባሎች ይመልከቱ)

ይህ የሰማይ ደጅ ነው
ይህ ስለ እግዚአብሔር መኖሪያ ቦታ መግቢያ የሚናገረው በአካል እንደሚታይ አንድ ሰው በር ከፍቶ ሰዎችን እንደሚያስገባው የመንግሥት ቤት ተደረጐ ተገልጾአል:: (ዘይቤያዊ አባባል ይመልቱ)

Genesis 28:18

ሐውልት
ትልቅ ድንጋይ ወይም በጫፉ ቅርጽ ያለበት ለማስታወሻነት የቆመ ሐውልት ነው

በላዩ ላይ የወይራ ዘይት አፈሰሰበት
ያዕቆብ ሐውልቱን ለእግዚአብሔር መቀደሱን የሚያመለክት ድርጊት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ሐውልቱን ለእግዚአብሔር ለመቀደስ ዘይት በላዩ ላይ አፈሰሰበት” (ምልክታዊ ድርጊት ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ቤተል
ቤተል ማለት የእግዚአብሔር ቤት የሚለውን ተረጓሚዎች እንደ ግርጌ ማስታወሻ ያስቀምጣሉ

ሎዛ
ይህ የከተማይቱ ስም ነው

Genesis 28:20

ስእለት ተሳለ
“ስእለት አደረገ” ወይም “በተለይ ለእግዚአብሔር ቃል ገባ”

እግዚአብሔር እንዲህ.... እግዚአብሔር አምላኬ ይሆናል
ያዕቆብ እግዚአብሔርን በሶስተኛ ሰው አገላለጽ ያናግረዋል ይህ በሁለተኛ ሰው አገላለጽ ሊገለጽ ይችላል:: አት: አንተ እንዲህ…የማመልከው አምላኬ ትሆናለህ” (ተዛማጅና ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የሚበላውን እንጀራ ቢትሰጠኝ
እዚህ “እንጀራ” አጠቃላይ ምግብ ይገልጻል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ አባቴ ቤት
“ቤት” ለያዕቆብ ቤተሰብን ይገልጻል አት ወደ አባቴና ወደሌሎች የቤተሰብ አባላት (ተዛማጅና ተመሣሣይ ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የተቀደሰ ድንጋይ
ድንጋዩ እግዚአብሔር የተገለጠበትን ቦታ ያመለክታልና ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቦታ ይሆናል

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 29

1 ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ በስተ ምሥራቅ ወዳለው አገር ደረሰ፤ 2 እዚያም በሜዳ ላይ አንድ የውሃ ጉድጓድ አየ፤ በሦስት የተከፈሉ የበግ መንጋዎች በጉድጓድ
ዙሪያ ነበሩ፤ መንጋዎቹ ውሃ የሚጠጡት ከዚሁ ጉድጓድ ነበር፤ ጉድጓዱም የሚዘጋበት ድንጋይ ትልቅ ነበር፤ 3 መንጋዎቹ ሁሉ እዚያ ከተሰበሰቡ በኋላ እረኞቹ
ድንጋዩን አንከባለው ከጉድጓዱ ውሃ ያጠቱአቸው ነበር፤ መንጋዎቻቸውን ካጠጡ በኋላ ግን ድንጋዩንም መልሰው በጉድጓዱ አፍ ላይ ይከዱኑታል። 4 ያዕቆብም
እረኞቹን "ወዳጆቼ ሆይ! ከየት ነው የመጣችሁት?" ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም "እኛ የመጣነው ከካራን ነው" አሉት። 5 እርሱም "የናኮርን የልጅ ልጅ ላባን
ታውቁታላችሁን?" ብሎ ጠየቃቸው። እነሱም "አዎ እናውቀዋለን" አሉት። 6 እርሱም "ለመሆኑ እርሱ ደኅና ነውን?" አላቸው። እነርሱም "አዎ፣ ደኅና ነው፤
እንዲያውም ልጁ ራሔል ያችውልህ! በጎች እየነዳች በመምጣት ላይ ነች" አሉት። 7 ያዕቆብም "ጊዜው ገና ቀን ነው፤ መንጋዎቻቸውንም ወደ ቤት
የምታስገቡበት ሰዓት ገና አልደረሰም፤ ታዲያ ለምን ውሃ አጠጥታችሁ አታሰማሩአቸውም? ፤ አለ። 8 እነርሱም "እረኞች ሁሉ መንጋዎቻቸውን ይዘው እዚህ
ከመሰብሰባቸው በፊት ምንም ማድረግ አንችልም፤ ሁሉም እዚህ ከመጡ በኋላ ግን ድንጋዩን በኅብረት አንከባለን በጎቹን እናጠጣቸዋለን" አሉት። 9 ያዕቆብም
ከእረኞቹ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለ ራሔል የአባትዋን በጎች ይዛ ወደዚያ መጣች፤ ምክንያቱም እርስዋ የበጎች እረኛ ነበረች። 10 ያዕቆብ ያጉቱን የላባን በጎች
እየነዳች ስትመጣ ራሔልን አይቶ ወደ ጉድጓድ ሄደ፤ ጉድጓዱ የተከደነበትንም ድንጋይ አንከባሎ በጎቹን አጠጣቸው። 11 ከዚያ በኋላ ራሔልን ሳማት።
ከደስታውም ብዛት የተነሣ አለቀሰ፤ 12 "እኔ የአባትሽ እኅት የሆነችው የርብቃ ልጅ ሄደች። 13 ላባም የእኅቱ ልጅ ያዕቆብ መምጣቱን በሰማ ጊዜ ሊቀበለው
ፈጥኖ ሄደ፤ አቅፎ ከሳመውም በኋላ ወደ ቤት አመጣው፤ ያዕቆብ የሆነውን ሁሉ ለላባ ነገረው፤ 14 ላባም "በእርግጥ አንተ ቅርብ የሥጋ ዘመዴ ነህ" አለው፤
ያዕቆብም አንድ ወር ያህል ከአጎቱ ጋር ተቀመጠ። 15 ላባ ያዕቆብን "ዘመዴ በመሆንህ ብቻ በነፃ ልታገለግለኝ አይገባህም፤ ስለዚህ ምን ያህል ደመወዝ
ላስብልህ? አለው። 16 ላባ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ ታላቂቱ ልያ፤ ታናሽቱ ራሔል ይባሉ ነበር። 17 ልያ ዐይነ ልም ስትሆን፣ ራሔል ግን ቁመናዋ የሚያምር
የደስ ደስ ያላት ነበረች። 18 ያዕቆብ ራሔልን እጅግ ስለወደዳት "ራሔልን ብትድርልኝ ሰባት ዓመት አገለግልሃለሁ" አለ። 19 ላባም "ለሌላ ሰው ከምሰጣት
ይልቅ ለአንተ ብሰጥህ ይሻለኛል፤ እሺ ተስማምቼአለሁ፤ እዚሁ ከእኔ ጋር ኑር" አለው። 20 ያዕቆብ ራሔልን ለማግባት ሰባት ዓመት አገለገለ፤ ይሁን እንጂ
ራሔልን በጣም ይወዳት ስለነበር የቆየበት ጊዜ ጥቂት ቀን ብቻ መስሎ ታየው። 21 ከዚያ በኋላ ያዕቆብ ላባን "እነሆ የአገልግሎት ዘመኔ ተፈፅሞአል፤ ሚስት
እንድትሆነኝ ልጅህን ስጠኝ" አለው። 22 ላባም የሠርግ ድግስ አዘጋጅቶ በአቅራቢያው የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ ጠራ። 23 ነገር ግን ላባ በራሔል ምትክ ልያን
ለያዕቆብ ሰጠው፤ ያዕቆብም ከልያ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ። 24 ላባ ሴት አገልጋዩን ዚልፋን አገልጋያዋን እንድትሆን ለልጁ ለልያ ሰጣት። 25
በማግስቱ ጠዋት ያዕቆብ አብራው ያደረችው ልያ መሆንዋን ባወቀ ጊዜ ወደ ላባ ሄዶ "ይህ ያደረግህብኝ ነገር ምንድን ነው? ያገለገልሁህ ራሔልን ለማግኘት
አልነበረም? ታዲያ ለምን አታለልከኝ"አለው። 26 ላባም "ታላቂቱ ሳትዳር፤ ታናሺቱን መዳር የአገራችን ልማድ አይደለም፤ 27 የልያ ሠርግ ሰባት ቀን እስኪሞላው
ድረስ ጠብቅ፤ ከእንግዲህ ወዲይ ሰባት ዓመት የምታገለግለኝ ከሆነ ራሔልን እሰጥሃለሁ" አለው። 28 ያዕቆብም ነገሩ ተስማማ፤ ከልያ ጋር ሰባት ቀን ተሞሽሮ
ከቆየ በኋላ፤ ላባ ልጁን ራሔልን ለያዕቆብ ሳረለት። 29 ላባ ሴት አገልጋዩን ባላን አገልጋይዋ እንድትሆን ለልጁ ለራሔል ሰጣት። 30 ያዕቆብ ከራሔልም ጋር
የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ፤ ከልያም አብልጦ ወደዳት፤ ከዚያ በኋላ ላባን ሰባት ዓመት አገለገለው። 31 ልያ የራሔልን ያህል እንዳልተወደደች እግዚአብሔር
ባየ ጊዜ መውለድ እንድትችል ማሕፀንዋን ከፈተላት፤ ራሔል ግን መኻን ሆነች፤ 32 ልያ ርርግዛ ወንድ ልጅ ወለደች፤ "እግዚአብሔር መከራዬን ተመለከተ፤
ከእንግዲህስ ወዲያ ባሌ ይወደኛል" ስትል ስሙን ሮቤል አለችው። 33 እንደገና አረገዘችና ሌላ ወንድ ልጅ ወደች፤ "እግዚአብሔር እንዳልተወደድሁ ሰማ፤
ይህንንም ልጅ ደግሞ ሰጠኝ' ስትል ስሙን ስምዖን አለችው። 34 እንደገና 'አረገዘችና ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች፤ "እንግዲህ ሦስት ወንዶች ልጆች ስለ
ወለድሁለት ባሌ ከእኔ ጋር በፍቅር ይጠመዳል" ስትል ስሙን ሌዊ አለችው፤ 35 እንደገና አረገዘችና ውንድ ልጅ ወለደች፤ "አሁንስ እግዚአብሔርን
አመሰግነዋለሁ" ስትል ስሙን ይሁዳ አለችው፤ ከዚህ በኋላ መውለድ አቋረጠች።

Genesis 29:1

የምሥራቅ ሰዎች
ከከነዓን ምድር በስተምሥራቅ የሚገኙ የጳዳን አራም ሰዎች ማለት ነው::

እነሆ በአንድ ሜዳ ላይ ሶስት የበግ መንጋዎች ተኝተው በነበሩበት
እነሆ የሚለው ቃል በትልቁ ታሪክ ውስጥ አንድ ሌላ ክስተት መጀመሩን ያመለክታል:: በሚትተረጉሙበት ቋንቋ ይህን የመግለጽ መንገድ ሊኖሮት ይችላል::

ከዚያ ጉድጓድ
ከዚሁ ጉድጓድ ይህ ሀረግ ታሪኩን ወደ ዳራው መረጃ ይመልስና እንዴት እረኞች በጐችን ውሃ እንደሚያጠጡ ይናገራል

እነርሱ ውሃ ያጠጣሉ
“እረኞች ውሃ ያጠጣሉ” ወይም “በጐችን የሚጠብቁ ውሃ ያጠጣሉ”

የጉድጓዱ አፍ
አፍ ጉድጓዱ የተከፈተበትን ቦታ ያሳያል:: አት: “ጉድጓዱ የተከፈተበት ቦታ”

Genesis 29:4

ያዕቆብም እነርሱን አለ
ያዕቆብም እረኞቹን አለ

ወንድምቼ
ይህ ለእንግዶች በትህትና ሰላምታ የማቅረብ መንገድ ነው

የናኮር ወንድ ልጅ ላባ
አዚህ ወንድ ልጅ ወንድ ዘርን ያመለክታል ሌላ ተገቢ ትርጉም የናኮር የልጅ ልጅ ላባ

እነሆ ተመልከት ራሔል በጎችን እየነዳች በመምጣት ላይ ነች
አሁን ተመልከት የእርሱ ሴት ልጅ ራሔል ከበጎች ጋር በመምጣት ላይ ነች

Genesis 29:7

ገና ቀትር ነው
“ገና ጸሐይ በሰማይ ላይ ነች/ጊዜው ገና ነው” ወይም “ጸሐይ ገና በማብራት ላይ ነች”

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

መንጎች እስኪሰበሰቡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “መንጐችን እስኪሰበስቡ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

መሰብሰብ
ይህም ሌሊቱን እንዲያሳልፉ በቅጥር ውስጥ መሰብሰብ ማለት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀት እና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወደ ግጦሽ ይመለሱ
በሜዳ ያለውን ሣር ይመገቡ

ውሃ ሊናጠጣቸው አንችልም
ውሃ ሊናጠጣቸው መጠበቅ አለብን ይህ ፈቃደኝነት ሳይሆን ጊዜን በሚመለከት ነው

መንጐቹ ሁሉ እስኪሰበሰቡ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ሌሎች እረኞች መንጐቻቸውን እስኪሰበስቡ” (ተሻጋረ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

ከጉድጓዱ አፍ
እዚህ አፍ ጉድጓዱ የተከፈተውን ቀዳዳ ያመለክታል አት ከጉድጓዱ ወይም ጉድጓዱ በተከፈተበት (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 29:9

የእናቱ ወንድም
አጐቱ

የጉድጓዱ አፍ
እዚህ “አፍ” የተከፈተበትን ቦታ ያመለክታል:: አት: “ጉድጓዱ” ወይም “ጉድጓዱ የተከፈተበትን ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 29:11

ያዕቆብም ራሔልን ሳማት
በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ በመሳም ሰላምታ መለዋወጥ የተለመደ ነው:: ነገር ግን በወንዶች ዘንድ እምብዛም የታወቀ ነው:: በሚትተረጐሙበት ቋንቋ ባህል እንዲህ ዓይነቱ ስሜትን በመግለጽ ዘመዳሞች ሰላምታ የመለዋዋጥ ነገር ካለ ይህን ይጠቀሙ:: ከሌለ ግን ሌላ ተገቢ አባባል ይጠቀሙ::

ድምጹን ከፍ አድርጐ አለቀሰ
ያዕቆብ የሚያለቅሰው ደስተኛ በመሆኑ ነው የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የአባትዋ ዘመድ
ለአባትዋ የሚዛመድ

Genesis 29:13

የእርሱ እኅት ልጅ
የእኅቱ ልጅ

አቀፈው
አቀፈው

ሳመው
በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ በመሳም ለዘመድ ሰላምታ ማቅረብ የተለመደ ነው:: ነገር ግን ይህ በወንዶች መካከል የታወቀ ነው:: በሚተረጐሙት ቋንቋ ለዘመድ የሚቀርብ ሰላምታ ስሜትን የሚገልጽ ከሆነ ይህን ይጠቀሙበት:: ካለሆነ ግን ሌላ ተገቢ አባባል ይጠቀሙ::

ያዕቆብም ሁኔታውን ሁሉ ለላባ ነገረው
“ከዚያም ያዕቆብ ለራሔል የነገረውን ሁሉ ለላባ ነገረው”

የአጥንቴ ፍላጭ የሥጋዬ ቁራጭ
እነዚህ ሀረጐች በቀጥታ የሚዛመዱ ናቸው:: አት: “የእኔ ዘመድ” ወይም “የቤተሰቤ አባል” (ተዛማጅ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 29:15

ዘመዴ በመሆንህ ብቻ በነጻ ሊታገለግለኝ አይገባምና...?
ስለሚሠራለት ሥራ ለያዕቆብ መክፈል ስለአለበት ላባን ይህንን አግንኖ ለመናገር ጥያቄ ይጠቀማል:: ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ዘመዴ ቢትሆንም ለሚትሠራልኝ መክፈል በእርግጥ ትክክል ነው” See:RhetoricalQuestionandLitotes

የልያ ዐይን ልም ነው
ተገቢ ትርጉሞች 1 የልያ ዓይኖች ልም ነበሩ 2 የልያ ዐይኖች ታማሚ ነበሩ

ያዕቆብ ራሔልን ወደደ
እዚህ ወደደ የሚለው ቃል በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚሆን ስሜታዊ ወዋደድን ያመለክታል

Genesis 29:19

ለሌላ ወንድ ከሚሰጣት ይልቅ
ለሌላ ወንድ ከሚድራት ይልቅ

እነዚያ ጥቂት ቀናት ብቻ ሆኖ ታየው
“ነገር ግን ጊዜው ጥቂት ቀናት ሆኖ ታየው”

ለእርስዋ ካለው ፍቅር
“ለእርስዋ ያለውን ፍቅር ስመዝን” ወይም “ለእርስዋ ካለው ፍቅር የተነሣ”

Genesis 29:21

እንዳገባት ዘንድ ሚስቴን ስጠኝ ቀኔ ተፈጽሞአልና
ቀኔ ተፈጽሞአል የሚለው ሀረግ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: ይህ emphatic ዐረፍተ ነገር ነው:: አት: “ለአንተ መሥራት የሚገባኝን ጊዜ ስለፈጸምሁ እንዳገባት ሚስቴን ስጠኝ” ወይም “ለሰባት ዓመታት ስላገለገልሁ እንዳገባት ራሔልን ስጠኝ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሠርግ አዘጋጀ
የጋብቻ ሠርግ አዘጋጀ ምናልባት ላባን ሌሎች ሰዎች እንዲያዘጋጁ አደረገ:: አት: “ሌሎች የጋብቻ ሠርግ እንዲያዘጋጁ አደረገ”:: (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)::

Genesis 29:23

አብሮአት ተኛ
ይህ የሚገልጸው ምሽት ስለነበረና ስላላያት ከልያ ጋር መሆኑን ያዕቆብ አላወቀም ነበር:: የዐረፍተ ነገሩ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ላባን ዘለፋ የተባለች አገልጋዩን ለልጁ ለልያ ደንገጡር እንድትሆን ሰጣት
እዚህ ጸሐፊው ላባን ዘለፋን ለልያ እንደሰጠ መረጃ ይሰጣል። ዘለፋን ለልያ ከሠርግ በፊት ሳይሰጣት አይቀርም:: (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

እነሆ ልያ ሆና ተገኘች
ያዕቆብም ልያ በአልጋ አብሮአት በማየቱ ተገረመ:: “እነሆ” የሚለው ቃል ያዕቆብ ባየው ነገር እንዴት እንደተደነቀ የሚያሳይ ነው፡፡

ምነው እንደዚህ አደረግህብኝ?
ያዕቆብ ቁጣውንና መገረሙን ለመግለጽ ጥያቄ ይጠቀማል ይህ ቅኔ አዘልጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡ “ይህን ለእኔ ታደርጋለና ብዬ አላምንህም” (See: RhetoricalQuestion)

ያገለገልሁህ ለራሔል ብዬ አልነበረምን?
ያዕቆብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው ላባን ያታለለውን ጉዳቱን ለመግለጽ ነው ይህ ቅኔ አዘል ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል ራሔልን ለማግባት ሰባት ዓመት አገልግየሃለሁ (See: Rhetorical Question)

Genesis 29:26

እንሰጥ ዘንድ ወግ አይደለም
በቤተሰባችን እንሰጥም

ለዚህች ሴት ልጅ ይህን የጫጉላ ሳምንት ፈጽም
የልያን ጫጉላ ሳምንት ፈጽም

ሌላኛይቱን ደግሞ እንሰጣለን
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት በሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ ራሔልን እንሰጥሃለን (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 29:28

ያዕቆብም እንዲሁ አደረገ እናም የልያን ሳምንት ፈጸመ
ያዕቆብ ላባን የጠየቀውን አደረገ እናም የልያን ጫጉላ ሳምንት ማክበርን ፈጸመ

ባላ
ይህ የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ያዕቆብም ከራሔል ጋር ተኛ
ጋብቻዊ ግንኙነት እንደፈጸሙ የሚገልጽ አክብሮታዊ ወይም ለዛ አባባል ነው

ራሔልን ወደዳት
በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል የሚሆን ስሜታዊ ፍቅር ያመለክታል

Genesis 29:31

ልያ አልተወደደችም
ይህ ተሻሪ ግሥ በያዘ መልክ ወይም በገቢር ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ያዕቆብ ልያን አልወደዳትም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እንዳልተወደደች
ያዕቆብ ራሔልን ከልያ ይልቅ እንደወደዳት በማተኮር አግንኖ የሚናገር ነው አት ከራሔል አሳንሶ ወደዳት (አግንኖና በገሃድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ማሕጸንዋን ከፈተላት
እግዚአብሔር ልያ እንዲትጸንስ ማድረጉ እግዚአብሔር ማሕጸንዋን እንደከፈተ ተደርጐ ተነግሮአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መካን ነበረች
ሊትጸንስ አልቻለችም

ልያ ጸነሰች ልጅም ወለደች
ልያ ጸነሰች ወንድ ልጅም ወለደች

ስሙን ሮቤል አለችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: ሮቤል የሚለው ስም ‘ወንድ ልጅ እየሁ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መከራዬን ስለተመለከተልኝ
ልያ ያዕቆብ ስላልተቀበላት በስሜታዊ ሕመም ነበራት:: “መከራ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር እንደተሰቃየሁ አየኝ” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Genesis 29:33

እንደገናም ጸነሰች
እንደገናም ልያ ጸነሰች

ልጅ ወለደች
ወንድ ልጅ ወለደች

ስሙን ስምዖን ብላ ጠራችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ስምዖን የሚለው ስም ‘ተሰማ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ባሌ ያቀርበኛል
ባሌ ያቅፈኛል

ሶስት ወንዶች ልጆች ስለወለድሁለት
ለእርሱ ሶስት ወንጆ ልጆች ወለድሁለት

ስው ሌዊ ይባላል
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ሌዊ የሚለው ስም ‘የተጠጋ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 29:35

እንደገናም ጸነሰች
ልያ እንደገና አረገዘች

ወንድ ልጅ ወለደች
ወንድ ልጅን ወለደች

ስሙንም ይሁዳ ብላ ጠራችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ይሁዳ የሚለው ስም ‘ምሥጋና’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Chapter 30

1 ራሔል ለያዕቆብ አንድም ልጅ እንዳልወለደችለት ባየች ጊዜ በእኅቷ ቀናች። ያዕቆብንም፣ “ልጅ ስጠኝ አለበለዚያ እሞታለሁ” አለችው። 2 ያዕቆብም ራሔልን
ተቆጥቶ፤ “እኔ የሆድሽን ፍሬ በነሳሽ በእግዚአብሔር ቦታ ነኝን?” አላት። 3 እርሷም፣ “እነሆ፣ አገልጋዬ ባላ አለችልህ፣ ልጆች እንድትወልድልኝና እኔም ደግሞ
በእርሷ አማካይነት ልጆች እንዳገኝ ከእርሷ ጋር ተኛ” አለችው። 4 ስለዚህ ባላን እንደሚስት አድርጋ ሰጠችው፤ ያዕቆብም ከእርሷ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት
አደረገ። 5 ባላም አረገዘችና ወንድ ልጅ ወለደችለት። 6 ራሔልም፦ “እግዚአብሔር ፈረደልኝ፣ ልመናዬንም ሰምቶ ወንድ ልጅ ሰጥቶኛል” አለች። ስለዚህ ስሙን
ዳን ብላ ጠራችው። 7 የራሔል አገልጋይ ባላ ዳግመኛ አረገዘችና ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች። 8 ከእኅቴ ጋር ብርቱ ትግል ታግዬ አሸነፍኋት” አለች።
ስለዚህ ስሙን ንፍታሌም ብላ ጠራችው። 9 ልያም ልጅ መውለድ ማቆሟን እንደተረዳች፣ አገልጋይዋን ዘለፋን ሚስት እንድትሆነው ለያዕቆብ ሰጠችው። 10 የልያ
አገልጋይ ዘለፋም ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት፣ 11 ልያም፣ “እንዴት የታደልሁ ነኝ!” ስትል ስሙን ጋድ ብላ ጠራችው። 12 የልያም አገልጋይ ዘለፋ ለያዕቆብ
ሁለተኛ ልጅ ወለደችለት፤ 13 ልያም፣ “እጅግ ደስ ብሎኛል፣ ከእንግዲህ ወዲያ ሴቶች ‘ደስተኛዋ’ ይሉኛል አለች፤ ስሙንም ‘አሴር’ ብላ ጠራችው። 14 በስንዴ
መከር ወራት ሮቤል ወደ ዱር ሄዶ እንኮይ አገኘ፤ ለእናቱ ለልያም አመጣላት፤ ራሔልም ልያን፣ “እባክሽን ልጅሽ ካመጣልሽ እንኮይ ስጪኝ” አለቻት። 15
ልያም፦ “ባሌን የቀማሽኝ አነሰና የልጄን እንኮይ ደግሞ ልትወስጂ አማረሽ?” አለቻት። ራሔልም፣ “ስለልጅሽ እንኮይ ዛሬ ያዕቆብ ከአንቺ ጋር ይደር” አለቻት።
16 በዚያ ምሽት ያዕቆብ ከእርሻ ሲመለስ፣ ልያ ወጥታ ተቀበለችውና፣ “በልጄ እንኮይ ስለተከራየሁህ የዛሬው አዳርህ ከእኔ ጋር ነው” አለችው። ያዕቆብም
በዚያች ሌሊት ከእርሷ ጋር አደረ። 17 እግዚአብሔር የልያን ጸሎት ሰማ፣ ስለዚህ አረገዘችና ለያዕቆብ አምስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደችለት። 18 ልያም፦
“አገልጋዬን ለባሌ በመስጠቴ እግዚአብሔር ደመወዜን ከፈለኝ” አለች። ስሙንም ይሳኮር አለችው። 19 ልያ አሁንም ደግማ ፀነሰች፤ ለያዕቆብም ስድስተኛውን
ወንድ ልጅ ወለደች። 20 እርሷም፣ “እግዚአብሔር በከበረ ስጦታ አድሎኛል፣ ስድስት ወንዶች ልጆች ስለወለድሁለት ከእንግዲህ ባሌ አክብሮ ይይዘኛል” አለች፤
ስሙንም ዛብሎን አለችው። 21 ከዚያም በኋላ ሴት ልጅ ወለደች ስምዋንም ዲና አለቻት። 22 እግዚአብሔርም ራሔልን አሰበ፤ ጸሎትዋንም ሰምቶ ልጅ
እንድትወልድ አደረጋት፤ 23 አርግዛም ወንድ ልጅ ወለደችና፣ “እግዚአብሔር ዕፍረቴን አስወገደልኝ” አለች፤ 24 ደግሞም ሌላ ወንድ ልጅ ይጨምርልኝ ስትል
ስሙን ዮሴፍ ብላ ጠራችው። 25 ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ ላባን እንዲህ አለው፦ “ወደ ተወለድሁበት አገር እንድመለስ አሰናብተኝ፤ 26 አንተን
በማገልገል ያገኘኋቸውን ሚስቶቼንና ልጆቼን ስጠኝና ልሂድ፤ ምን ያህል አገልግሎት እንዳበረከትኩልህ ታውቃለህ።” 27 ላባም፣ “በአንተ ምክንያት
እግዚአብሔር እንደባረከኝ በንግርት መረዳቴን ልነግርህ እወዳለሁ፤ 28 የምትፈልገውን ደመወዝ ንገረኝና እከፍልሃለሁ” አለው። 29 ያዕቆብም እንዲህ አለው፦
“እንዴት እንዳገለገልሁህና የከብትህም መንጋ በእኔ ጠባቂነት እንዴት እንደረባልህ አንተ ታውቃለህ፤ 30 እኔ ከመምጣቴ በፊት ጥቂት የነበሩት መንጋዎችህ
አሁን እጅግ በዝተዋል፤ በተሰማራሁበት ሁሉ እግዚአብሔር በረከቱን አብዝቶልሃል። ታዲያ፣ ለራሴ ቤት የሚያስፈልገኝን የማቀርበው መቼ ነው?” 31 ላባም፣
“ታዲያ ምን ያህል ልክፈልህ?” ብሎ ጠየቀው። ያዕቆብም እንዲህ ሲል መለሰ፦ “እኔ የምልህን አንድ ነገር ብቻ ብታደርግልኝ መንጋህን ማሰማራቴንና
መጠበቄን እቀጥላለሁ፤ 32 ዛሬ በመንጋዎችህ መካከል ልለፍና ዝንጉርጉርና ነቁጣ ጥቁርም የሆኑትን በጎች ሁሉ ልለይ፤ እንዲሁም ነቁጣና ዝንጉርጉር
የሆኑትን ፍየሎች እመርጣለሁ፤ እነርሱም ደመወዜ ይሆናሉ፤ 33 ወደፊት ደመወዜን ለመቆጣጠር በምትመጣበት ጊዜ ታማኝነቴ ይታወቃል፤ ደመወዜን
ለመቆጣጠር ስትመጣ ዝንጉርጉር ያልሆነ ወይም ነቁጣ የሌለበት ፍየል ብታገኝ፣ እንዲሁም ጥቁር ያልሆነ በግ ብታገኝ የተሰረቀ መሆኑን መረዳት ትችላለህ”
አለው። 34 ላባም፣ “እሺ አንተ ባልከው እስማማለሁ” አለ። 35 ነገር ግን በዚያኑ ዕለት ከተባት ፍየሎች ሽመልመሌ የሆኑትን ወይም ነቁጣ ያለባቸውን ሁሉ
እንዲሁም ከእንስት ፍየሎች ነቁጣ ያለባቸውን ዝንጉርጉር የሆኑትን ሁሉ መረጠ፤ ደግሞም ጥቋቁር የሆኑትንም በጎች ሁሉ ለየና ወንዶች ልጆቹን አስጠበቃቸው።
36 ከዚህ በኋላ ላባ መንጋውን ነድቶ የሦስት ቀን መንገድ ያህል ከያዕቆብ ርቆ ሄደ፤ ያዕቆብም የቀሩትን የላባን መንጋዎች መጠበቁን ቀጠለ። 37 ያዕቆብም
ልብን፣ ለውዝና ኤርሞን ከሚባሉ ዛፎች እርጥብ በትሮችን ወሰደ፤ በበትሮቹ ያለው ነጭ እንዲታይ ሽመልመሌ አድርጎ ላጣቸው፤ 38 መንጋዎቹ ውሃ ለመጠጣት
ሲመጡ ከፊት ለፊት እንዲያዩአቸው የተላጡትን በትሮች በውሃ ማጠጫዎቹ ውስጥ አደረጋቸው። መንጎቹም ስሜታቸው ሲነሣሣና ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ፣
39 በትሮቹን ፊት ለፊት እያዩ ይሳረሩ ነበር፤ ሽመልመሌ፣ ዝንጉርጉርና ነቁጣ የጣለባቸውንም ግልገሎች ወለዱ። 40 ያዕቆብ እነዚህን ግልገሎች ለብቻ ለየ፤
የቀሩትን ግን ዝንጉርጉርና ጥቁር በሆኑት በላባ መጋዎች ፊት ለፊት አቆማቸው፤ በዚህ ዓይነት የራሱን መንጋ ከላባ መንጋ ጋር ሳይቀላቅል ለብቻ አቆማቸው። 41
ያዕቆብም ብርቱ እንስቶች አውራ ፈልገው በሚቅበጠበጡበት ጊዜ በትሮቹ አቅራቢያ እንዲጠቁ በትሮቹን በውሃ ገንዳዎች ውስጥ ፊት ለፊታቸው ያስቀምጥ
ነበር፤ 42 ደካማ በሆኑት እንስቶች ፊት ግን በትሮቹን አያስቀምጥም ነበር፤ ስለዚህ ደካሞቹ ለላባ ሲሆኑ፣ ብርቱዎቹ ለያዕቆብ ሆኑ። 43 በዚህም ሁኔታ ያዕቆብ
እጅግ ባለጸጋ ሆነ፤ ብዙ መንጋዎች፤ ሴቶችና ወንዶች አገልጋዮች፣ ብዙ ግመሎችና አህዮችም ነበሩት።

Genesis 30:1

ራሔል ለያዕቆብ ልጅን እንዳልወለደች ባየች ጊዜ
ራሔል ማርገዝ እንዳልቻለች ባወቀች ጊዜ

እሞታለሁ
ራሔል ልጅ ባለመኖርዋ ምነኛ እንደተከፋች ማጋነንዋ ነው:: አት: ምንም እንደማልጠቅም ይሰማኛል:: (በማጋነንና በገሃድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ልጅ ስጠኝ
እንዳረግዝ አድርገኝ

ያዕቆብም ቁጣ በራሔል ላይ ነደደ
የያዕቆብ ቁጣ እንደ እሳት ተደርጐ ተገልጾአል። አት፡ “ያዕቆብ ራሔልን በጣም ተቆጣት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እኔ እንዳትወልጂ ያደረግሽን እግዚአብሔርን መሰልኩሽን?
ይህ ያዕቆብ ራሔልን ለመቆጣት የተጠቀመው ቅኔያዊ ጥያቄ ነው:: ይህም እንደ ዐረፍተ ነገር ልተረጐም ይችላል:: አት፡ “እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም! ልጅ እንዳትወልጂ የሚከለክለው እኔ አይደለሁም” (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 30:3

እርስዋም አለች
ራሔል አለች

እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ስማ” ወይም “ሊናገር ስላለሁ ነገር ትኩረት ስጥ”

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

አገልጋዬ ባላ አለችልህ .... ከእርስዋ ልጆች እንዳገኝ
በዚያን ጊዜ መካን ሴት በሕጋዊነት ልጅ የሚታገኝበት ተቀባይነት ያለው መንገድ ይህ ነው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ስም ነው። በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

በጉልበቶቼ ወይም በጭኖቼ
ይህ ባላ የሚትወልደው ልጅ ለራሔል እንደሚሆን የሚገልጽ አባባል ነው:: አት: "ለእኔ" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በእርሷ አማካኝነት ልጅ ይኖረኛል
በዚህ መንገድ ልጅ እንዲኖረኝ ታደርጋለች

Genesis 30:5

ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ስም ነው። በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ወንድ ልጅም ወለደችለት

ስሙንም አወጣችለት
ራሔል ስም አወጣችለት

ዳን ብላ ጠራችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: "ዳን የሚለው ስም 'እርሱ ይፈርዳል' ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:7

ባላ እንደገና ጸነሰች
ባላ እንደገና አረገዘች

ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅን ወለደችለት

ከእኅቴ ጋር ብርቱ ትግልን ታገልሁ
ትግልን ታገልሁ የሚለው ሀረግ አጽንዖትን የሚሰጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ራሔል እንደ እኅትዋ አንድን ልጅ ለማግኘት ያደረገችው ከልያጋር አካላዊ ትግል እንዳደረገች የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው:: አት: "እንደ ታላቅ እኅቴ ልያ ልጅን ለማግኝት ትልቅ ተጋድሎ አድርጌያለሁ:: (ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቻልኩኝ
አሸነፍሁ ወይም ተሳክቶልኛል

ስሙንም ንፍታለም ብላ አወጣችለት
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: "ንፍታለም የሚለው ስም 'ትግሌ' ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:9

ልያም ባየች ጊዜ
ልያም በተረዳች ጊዜ

አገልጋይዋን ዘለፋን ወሰደች ሚስት ትሆነውም ዘንድ ለያዕቆብ ሰጠችው
አገልጋይዋን ዘለፋን ሚስት እንዲትሆነው ለያዕቆብ ሰጠችው

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ወንድ ልጅን ወለደችለት

ምን ዓይነት መታደል ነው!
እንዴት ያለ መታደል ነው! ወይም ምን ዓይነት ዕድል ነው!

ስሙንም ጋድ ብላ አወጣችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: "ጋድ የሚለው ስም 'እድለኛ' ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:12

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት

ምነኛ ደስተኛ ሆንሁ!
እንዴት የተባረኩ ነኝ! ወይም እንዴት ደስተኛ ነኝ !

ሴቶች ልጆች
ሴቶች ወይም ልጃገረዶች/ወጣት ሴቶች

ስሙንም አሴር ብላ አወጣችለት
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: "አሴር የሚለው ስም 'ደስታ' ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:14

ሮቤል ወደ ሜዳ ወጣ
ሮቤልም ወጣ

ስንዴ በሚታጨድበት ቀናት
ቀናት የሚለው አባባል በዓመት ውስጥ ያለ ወቅት ወይም ጊዜ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: አት "በዓመት ስንዴ በሚታጨድበት ጊዜ" ወይም "ስንዴ በሚታጨድበት ወቅት" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እንኮይ
ከፍቅረኛ ጋር ለመተኛት ስሜት የሚያነሣሣና ፍሬን የሚጨምር የአትክልት ፍሬ ነው:: አት: "የፍቅር ፍሬ" (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ባሌን....ጥቂት ነገር ነውን?
ባሌን .... አይሰማሽምን? ይህ ራሔልን ለመቆጣት የተጠቀመችው ቅኔያዊ ጥያቄ ነው ይህ ጥያቄ በስድ ዐረፍት ነገር ሊገለጽ ይችላል:: ባሌን የማያስከፋ ነው:: (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ) ...ደግሞ ሊትወስጂ አማረሽ? ይህንም ቅኔ አዘል ጥያቄ የተጠቀመችው ራሔልን ለመቆጣት ነው ይህ ጥያቄ በስድ ዐረፍት ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት: አሁን ደግሞ... አማረሽ! (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ከዚያም ይተኛ
“ከዚያም ያዕቆብ ይተኛ” ወይም “ያዕቆብ እንዲተኛ እፈቅዳለሁ”

Genesis 30:16

በልጄ እንኮይ
ለልጄ “እንኮይ” ዋጋ በዘፍጥረት 30;14 እንኮይ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ጸነሰች
አረገዘች

ለያዕቆብ አምስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
አምስተኛ ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለደች

እግዚአብሔር ዋጋዬን ከፈለልኝ
እግዚአብሔር ልያን መካሡ ለሚሠራው ሠራተኛ አንድ አለቃ ድርጐውን እንደሚከፍል እንደከፈለላት ተደርጐ ተገልጾአል “እግዚአብሔር የድርሻዬን ሰጠኝ” ወይም “እግዚአብሔር ካሠኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ስሙንም ይሳኮር ብላ አወጣችለት
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ይሳኮር የሚለው ስም ‘ካሣ አለ’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:19

ልያ አሁንም ደግሞ ጸነሰች
ልያ እንደገና አረገዘች

ለያዕቆብ ስድስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች
ስድስተኛ ወንድ ልጅም ለያዕቆብ ወለደች

ስሙንም ዛብሎን አለችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ዛብሎን የሚለው ስም ‘ክብር’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ስምዋንም ዲና አለቻት
ይህ የልያ ሴት ልጅ ስምዋ ነው።(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 30:22

እግዚአብሔርም ራሔልን አሰባት ልመናዋንም ሰማ
አሰባት የሚለው አባባል አስተዋላት ማለት ነው:: ይህ እግዚአብሔር ራሔልን ረስቶአታል ማለት አይደለም:: ጥያቄዋን አሰበ ማለት ነው:: አት: “እግዚአብሔርም ራሔልን አሰበ የፈለገችውንም ሰጣት” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ኀፍረተን አስወገደልኝ
እግዚአብሔር ራሔል እንዳታፍር ያደረገው ሐፍረት አንድ ሰው ከአንድ ሰው ወስዶ እንደሚያስወግድ ዕቃ ተደርጐ ተነገሮአል:: ረቂቅ ስም ሐፍረት እንደ እፍረት ሊገለጽ ይችላል::

አት: እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲህ እንዳላፍር አድርጐኛል። (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ) ስሙንም ዮሴፍ አለችው
ተረጓሚዎች የሚከተለውን አንደ ግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ:: “ዮሴፍ” የሚለው ስም ‘እርሱ ይጨምር’ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሌላ ወንድ ልጅ ጨምሮ ይሰጠኝ
የራሔል የመጀመሪያዎቹ ወንድ ልጆች ከሴት አገልጋይዋ ከባላ ነበር

Genesis 30:25

ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ
ራሔልም ዮሴፍን ከወለደች በኋላ

እናም እመለስ ዘንድ
እንዲመለስ

እንዳገለገልሁህ ታውቃለህ
ያዕቆብ ላባንን የተስማሙበትን ኮንትራት ያስታውሳል (ዘፍጥረት 29 :27) ረቂቅ ስም “አገልግሎት” እንደ “አገለገለ” ሊገለጽ ይችላል:: አት: ለረጅም ጊዜያት እንዳገለገልሁህ ታውቃለህ:: (ረቂቅ ስሞች ይጠቀሙ)

Genesis 30:27

ላባንም እንዲህ አለው
ላባንም ያዕቆብን እንዲህ አለው

በአይንህ ፊት ሞገስን የማገኝ ቢሆን
አይኖች ማየትን ይወክላሉ እናም ማየት ሃሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል:: አት: “በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ” ወይም “በእኔ የተደሰትህ ከሆንህ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሞገስ ማግኘት
አንድ ሰው በሌላኛው ሰው ዘንድ ሞገስ ማግኘቱን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቆይ ምክንያቱም
ተቀመጥ ምክንያቱም

በንግርት ተረድቸአለሁ
በመንፈሳዊና ማጅካዊ ልምምዶቼ ተረድቸአለሁና

በአንተ የተነሣ
በአንተ ምክንያት

ደመወዝህን ንገረኝ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት እዚሁ ላቆይህ ምን ያህል መክፈል እንዳለብኝ ንገረኝ። (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 30:29

ያዕቆብም አለው
ያዕቆብ ላባንን አለው

ከብቶችህ በእኔ ጥበቃ ምን ያህል እንደተመቻቸው
ጥበቃ ከጀመርኩባቸው ጊዜ ከብቶች እንዴት እንደተመቻቸው

እኔ ከመምጣቴ በፊት ጥቂት ነበሩ
ለአንተ ሥራ ከመጀመረ በፊት መንጐችህ ጥቂት ነበሩ

እናም ይህ በመጨመር ተትረፍርፎአል
ነገር ግን አሁን ሀብትህ በጣም ጨምሮአል

አሁንም እኔ ደግሞ ለቤቴ የሚሆነውን የማቀርበው መቼ ነው?
አሁንም እኔ ደግም ለቤተሰቤ የምሠራው መቼ ነው? ያዕቆብ ለቤተሰቡ የሚሆነውን ማቅረብ እንዳለበት ለማጽናት ጥያቄ ይጠቀማል ይህም ጥያቄ

በዐረፍተነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “አሁን ለቤተሰበ የሚሆነውን ማሰብ አለብኝ” (ቅኔ አዘል ጥያቄችን ይመልከቱ)

Genesis 30:31

ታዲያ ምን ልስጥህ?
“ታዲያ ምን መክፈል እችላለሁ?” ወይም “ታዲያ ምን መስጠት እችላለሁ?” ይህ የበለጠውኑ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት እንዲትቆይና እንዲትሠራልኝ ዘንድ ምን መክፈል እችላለሁ?(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)

ይህንም ነገር ቢታደርግልኝ
ያዕቆብ ሊናገር ያለው እርሱ ከተናገረው ጋር እንደሚጻረር ለማሳየት አገናኝ ቃል “ነገር ግን” በመግቢያው ሊጠቀም ይቻላል:: አት: “ነገር ግን ይህንም ነገር ቢታደርግልኝ” (አገናኝ ቃላት ይመልከቱ)

ይህ ነገር
“ይህ ነገር” የሚለው ሀረግ ያዕቆብ በቁጥር 32 የሚያቀርበውን ያመለክታል::

መንጎችህን እመግባለሁ/አሠማራለሁ እጠብቃለሁ
መንጎችህን እመግባለሁ እጠብቃለሁ

ከበጐቹ መካከል ዝንጉርጉር የሆኑትን ነቁጣ ያለባቸውንና ጥቋቁሮቹን እንዲሁም ከፍዬሎች ነቁጣ ያለበቸውንና ዥንጉርጉሮቹን እለያለሁ
ማንኛውንም ዥንጉርጉርና ጥቁር የሆነውን በግና ዝንጉርጉር የሆነውን ፍዬል እለያለሁ

እነዚህ ደመወዜ ይሁኑ
እንዚህ እዚሁ ለሚቆየው ዋጋዬ ይሁኑ

Genesis 30:33

ታማኝነቴ ይታወቃል
ታማኝነት የሚለው ቃል አማንነት ማለት ነው ይህም ታማኝነት አንድ ሰው ሰለሌላኛው ሰው በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚሰጠው ምሥክርነት እንደሆነ ይናገራል:: አት: “ለአንተ ታማኝ መሆነንና አለመሆነን በኋላ ታውቀዋለህ”:: (ሰውኛ አገላለጽ ይመልከቱ)

በመንጋቼ መካከል ዥንጉርጉር ወይም ነቁጣ የሌለበት ፍዬል ወይም ጥቁር ያልሆነ ቢገኝ ያ እንደተሰረቀ ይቆጠር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ ገቢራዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት ማንኛውም ዥንጉርጉር ያለሆነ ፍዬልና ጥቁር ያልሆነ በግ ቢታገኘው እንደተሰረቀ መቁጠር ትችላለህ:: (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዙ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እነሆ እንደቃልህ ይሁን
“እንደተናገርከው ይሁን” ወይም “አንተ እደተናገርከው እናደርጋለን”

Genesis 30:35

ሽመልመሌ የሆኑትን ወይም ነቁጣ ያለባቸውን
ሽመልመሌና ነቁጣ ያለባቸውን

ነቁጣ ያለባቸውንና ዥንጉርጉር የሆኑትን
ነቁጣ ያለባቸውን

ማንኛውንም ነጭ ያለበትን
ማንኛውም ነጭ ያለበት በግ

ከበጎች ሁሉ ጥቋቁር የሆኑትን
ጥቁር በጎችን ሁሉ

በእነርሱ እጅ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” “ቁጥጥር” ወይም “ጥበቃ” የሚተካ ነው:: አት: “ልጆቹ እንዲጠብቁ አደረጋቸው” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 30:37

እርጥብ የልብን የለውዝንና የኤርሞን
እነዚህ ሁሉ ነጭ ዛፎች ናቸው:: (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቅርፊታቸውን ልጦ የበትሮቹ ውስጠኛው ነጩ አካል እንዲታይ አደረገ
የቅርፊታቸውን አንዳንድ ክፍሎችን በመላጥ የበትሮቹ ውስጠኛው ነጭ አካል እንዲታይ አደረገ

በማጠጫ ገንዳዎች
ከብቶችን ለማጠጣት ውሃን የሚይዙ ረጅምና ክፍት የሆኑ ገንዳዎች

Genesis 30:39

መንጋዎች ይሳረሩ ነበር
“የመንዎች እንስሳት ይጸልሱ ነበር” ወይም “ይጠቃቁ ነበር”

ሽመልመሌ ዝንጉርጉርና ነቁጣ የጣለባቸውን ግልገሎች ወለዱ
ዝንጉርጉርና ነቁጣ ያለባቸውን ግልገሎት ወለዱ

ያዕቆብም ለያቸው
ይህ ለብዙ ዓመታት እንደተረገ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ለሚቀጥሉት ብዙ ዓመታት ያዕቆብ ለያቸው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ፊታቸውን መልሰው
ፊት ለፊት እያዩ

ከመንጋዎቹ ለራሰ ለያቸው
የራሱን መንጋ ለየ

Genesis 30:41

በመንጋዎች ዐይን ፊት
እዚህ የመንጋዎች ዐይን በጎችን ወይም መንጋዎችን የሚያመለክትና የሚያዩትን እንደሚያተኩር ነው:: አት: (መንጋው እንዲያየው ዘንድ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉውን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በበትሮቹ መካከል
በበትሮቹ ፊትለፊት

በከሱ እንስሳት
በደካማዎች እንስሳት

ስለዚህ ደካማ ደካማዎቹ ለላባን ሲሆኑ ብርቱ ብርቱዎቹ ለያዕቆብ ሆኑ
ይህን ይበልጥኑ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ደካማ ደካማዎቹ ዝንጉርጉርና ነቁጣ ስለሌላቸው ለላባን ሲሆኑ ብርቱ ብርቱዎች ዝንጉርጉርና ነቁጣ ስላላቸው ለያዕቆብ ሆኑ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 30:43

ይህ ሰው
ያዕቆብ

እጅግ ባለጠጋ ሆነ
“እጅግ በለጸገ” ወይም “ሀብታም ሆነ”

Chapter 31

1 የላባ ወንዶች ልጆች፣ “ያዕቆብ የአባታችንን ሀብት እንዳለ ወስዶታል፤ ይህ ሁሉ እርሱ ያከማቸውም ሀብት ከአባታችን የተገኘ ነው” እያሉ ሲያወሩ ያዕቆብ
ሰማ። 2 በላባም ዘንድ እንደቀድሞ ተወዳጅ አለመሆኑን ተረዳ። 3 እግዚአብሔርም ያዕቆብን፣ “ወደ አባቶችህ ወደ ዘመዶችህ አገር ተመለስ፤ እኔም ከአንተ ጋር
እሆናለሁ” አለው። 4 ስለዚህ ያዕቆብ መንጋዎቹ ወደ ተሰማሩበት መስክ እንዲመጡ ራሔልንና ልያን አስጠራቸው፤ 5 እንዲህም አላቸው፤ “አባታችሁ ስለ እኔ
ያለው አመለካከት እንደ ቀድሞ አለመሆኑን ተረድቻለሁ፤ ቢሆንም የአባቴ አምላክ አልተለየኝም፤ 6 መቼም ባለኝ አቅም አባታችሁን ማገልገሌን እናንተ
ታውቃላችሁ። 7 አባታችሁ ደመወዜን ዐሥር ጊዜ እየለዋወጠ አታልሎኛል፣ ሆኖም እንዲጎዳኝ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም። 8 እርሱ፣ ‘ደመወዝህ ዝንጉርጉሮቹ
ይሆናሉ ሲለኝ፣ መንጎቹ ሁሉ ዝንጉርጉር ወለዱ’፤ ደግሞም፣ ‘ደመወዝህ ሽመልመሌዎቹ ይሆናሉ ሲለኝ፣ መንጎቹ ሁሉ ሽመልመሌ መልክ ያላቸውን ወለዱ፤ 9
ስለዚህ እግዚአብሔር የአባታችሁን ከብቶች ወስዶ ለእኔ ሰጠኝ። 10 እንስሳቱ በሚጠቁበት ወራት የሚያጠቋቸው አውራ ፍየሎች ሽመልመሌ፣ ዝንጉርጉርና
ነቁጣ መሆናቸውን በሕልም አየሁ። 11 በዚያው ሕልም የእግዚአብሔር መልአክ፦ ‘ያዕቆብ’ ብሎ ጠራኝ፣ እኔም ‘እነሆ አለሁ’ አልሁ። 12 እርሱም እንዲህ
አለኝ፦ ‘መንጋዎቹን የሚያጠቋቸው አውራ ፍየሎች ሽመልመሌ፣ ዝንጉርጉርና ነቁጣ ያለባቸው መሆናቸውን ተመልከት፣ ላባ የፈጸመብህን በደል አይቻለሁ። 13
የድንጋይ ሐውልት በማቆም ዘይት ቀብተህ የተሳልህባት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ፤ አሁንም ይህን አገር ፈጥነህ ልቀቅ ወደ ተወለድህበትም ምድር ተመልሰህ ሂድ’
አለኝ።” 14 ራሔልና ልያም እንዲህ ብለው መለሱለት፦ “ከአባታችን የምንወርሰው ድርሻ አለን? 15 እርሱ እኛን የሚያየን እንደ ባዕዳን አይደለምን? ደግሞም
እኮ እኛን ሸጦናል፣ የተሸጥንበትንም ዋጋ ራሱ በልቶታል። 16 እግዚአብሔር ከአባታችን ወስዶ ለአንተ የሰጠው ሀብት ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው፤ ስለዚህ
እግዚአብሔር የነገረህን ሁሉ አድርግ።” 17 ከዚያም ያዕቆብ ተነሥቶ ልጆቹንና ሚስቶቹን በግመሎች ላይ አስቀመጠ፤ 18 በመስጴጦምያ ካፈራው ሀብት ሁሉ
ጋር ከብቶቹን በሙሉ ወደፊት አስቀደመ፣ ወደ አባቱም ወደ ይስሐቅ አገር፣ ወደ ከነዓን ምድር ጉዞውን ቀጠለ። 19 ላባ በጎቹን ሊሸልት ሄዶ ስለነበር፣ እርሱ
በሌለበት ራሔል ከቤት የነበሩትን የአባቷን ጣዖቶች ሰርቃ ሄደች። 20 ያዕቆብ መሄዱን ለላባ ሳይገልጥለት አታሎት ሄደ፣ 21 የራሱ የሆነውን ሀብት ይዞ
በፍጥነት ታኋዘ፤ የኤፍራጥስንም ወንዝ ተሻግሮ ወደ ኮረብታማው አገር ወደ ገለዓድ ሄደ። 22 ያዕቆብ መኮብለሉን ለላባ በሦስተኛው ቀን ተነገረው። 23
ከዘመዶቹ ጋር ሆኖ ያዕቆብን ተከታተለው፤ ሰባት ቀን ከተጓዙ በኋላ ገለዓድ በተባለው ተራራማ አገር ላይ ሊደርስበት ተቃረበ። 24 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር
ለላባ በሕልም ተገለጠለትና “ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ” አለው። 25 ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኮረብታማ ስፍራ ድንኳኑን በመትከትል
ሰፍሮ ሳለ ላባ ደረሰበት፤ ላባና ዘመዶቹም እዚያው ድንኳናቸውን ተክለው ሰፈሩ። 26 ከዚህ በኋላ ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው፦ “ስለምን እንዲህ አድርገህ
አታለልኸኝ፤ ሴቶች ልጆቼንስ በጦርነት እንደተማረኩ ያህል ይዘሃቸው ለምን ሄድህ? 27 ሳትነግረኝ ተሰውረህ በመሄድ ለምን አታለልኸኝ? ነግረኸኝ ቢሆን
በከበሮና በመሰንቆ እየተዘፈነ በደስታ በሸኘሁህ ነበር። 28 ልጆቼንና የልጅ ልጆቼን በመሳም እንድሰናበታቸው ባለማድረግህ የሞኝነት ተግባር ፈጽመሃል። 29
ጉዳት ሳደርስብህ እችል ነበር፣ ነገር ግን ባለፈው ሌሊት የአባትህ አምላክ፣ ‘ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ አንድ ቃል እንዳትናገረው’ ብሎ አስጠነቀቀኝ፣ 30 ወደ
ትውልድ አገርህ ለመመለስ ባለህ ብርቱ ፍላጎት እንደተለየኸኝ አውቃለሁ፣ ታዲያ የቤቴን ጣዖቶች የሰረቅኸብኝ ለምንድነው?” 31 ለላባ እንዲህ ሲል መለሰለት፦
“ሴቶች ልጆችህን በኃይል ነጥቀህ ታስቀርብኛለህ ብዬ ስለ ፈራሁ ነው በድብቅ የሄድኩት። 32 ነገር ግን ከእኛ መካከል የአንተን የጣዖት ምስል የሰረቀ ሰው
ካለ ይሙት። የአንተ የሆነ አንዳች ነገር ከኔ ዘንድ ቢገኝ፣ አንተው ራስህ ዘመዶቻችን ባሉበት ፈልግና ውሰድ።” እንደዚህ ሲል ራሔል የጣዖታቱን ምስል መስረቋን
ያዕቆብ አያውቅም ነበር። 33 ላባም ወደ ያዕቆብ ድንኳንና ወደ ልያ ድንኳን እንዲሁም ወደ ሁለቱ ደንገጡሮቹ ድንኳን ገባ፤ ነገር ግን ምንም አላገኘም። ከልያ
ድንኳን ከወጣ በኋላ ወደ ራሔል ድንኳን ገባ። 34 ራሔል ግን ጣዖቱቹን ወስዳ በግመሉ ኮርቻ ሥር በመሰወር በላያቸው ተቀምጣባቸው ነበር። ላባ በድንኳኑ
ውስጥ ያለውን ጓዝ ሁሉ በርብሮ ምንም ነገር አላገኘም። 35 ራሔልም አባቷን፦ “በፊትህ ተነሥቼ መቆም ስላልቻልሁ፣ ጌታዬ አትቆጣ የወር አበባዬ መጥቶ
ነው” አለችው፤ ስለዚህ በረበረ፤ የጣዖቱን ምስል ግን ማግኘት አልቻለም። 36 በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ተቆጣ፤ ላባንም እንዲህ ሲል ወቀሰው፦ “እስቲ ወንጀሌ
ምንድን ነው? ይህን ያህል የምታሳድደኝ ኃጢአቴ ምን ቢሆን ነው? 37 ዕቃዬን አንድ በአንድ በርብረሃል፤ ታዲያ የአንተ ሆኖ ያገኘኸው ዕቃ የትኛው ነው? ካለ፣
እስቲ በአንተም በእኔም ዘመዶች ፊት አቅርብና እነርሱ ያፋርዱን። 38 ሃያ ዓመት አብሬህ ኖሬአለሁ፤ በጎችህና ፍየሎችህ አልጨነገፉም፤ ከመንጋህም አንድ ጠቦት
እንኳ አልበላሁም። 39 አውሬ የሰበረውንም ቢሆን እተካ ነበር፣ በቀንም ሆነ በሌሊት የተሰረቁትን ሁሉ ስታስከፍለኝ ኖረሃል። 40 ብዙ ጊዜ በቀን ሐሩርና በሌሊት
ቁር እሠቃይ ነበር፤ በቂ እንቅልፍ ያገኘሁበት ጊዜ አልነበረም። 41 ሃያ ዓመት በቤትህ የኖርሁት በዚህ ሁኔታ ነበር፤ ዐሥራ አራት ዓመት ለሁለቱ ልጆችህ ብዬ
አገለገልሁ፤ ስድስት ዓመት ስለመንጋዎችህ ስል አገለገልሁ፤ ይህም ሆኖ ደመወዜን ዐሥር ጊዜ ለዋውጠኽብኛል። 42 የአባቴ አምላክና እርሱም የሚፈራው
የአብርሃም አምላክ ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ ባዶ እጄን ሰድደኸኝ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን መከራዬን ዐይቶ፣ ልፋቴን ትመልክቶ ትናንት ሌሊት ገሠጸህ።” 43
ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እነዚህ ሴቶች የእኔው ልጆች ናቸው፤ ልጆቻቸውም የእኔ ናቸው፤ እነዚህም መንጋዎች የእኔ ናቸው፤ ይህ የምታየው ሁሉ
የራሴ ነው፤ ታዲያ በእነዚህ ሴቶች ልጆቼና በወለዷቸው ልጆቻቸው ላይ ዛሬ ምን ማድረግ እችላለሁ? 44 በል አሁን ቃል ኪዳን እንጋባ፤ ኪዳኑም በአንተና በእኔ
መካከል ምስክር ይሁን።” 45 ያዕቆብም ድንጋይ ውስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፤ 46 ከዚያም ዘመዶቹን “ድንጋይ ሰብስቡ” አላቸው። እነርሱም ድንጋይ
እያመጡ ከመሩ፤ በክምሩም አጠገብ ምግብ በሉ። 47 ላባም ክምር ድንጋዩን ይጋርሠሀዱታ ብሎ ጠራው፤ ያዕቆብ ደግሞ ገለዓድ አለው። 48 ላባም “ይህ
ክምር ድንጋይ በእኔና በአንተ መካከል ዛሬ ምስክር ነው” አለው። ገለዓድ ተብሎ የተጠራውም በዚሁ ምክንያት ነው፤ 49 ደግሞም ምጽጳ ተባለ ምክንያቱም ላባ
እንዲህ ብሎአልና፤ “እንግዲህ ከዚህ በምንለያይበት ጊዜ እግዚአብሔር እኔንና አንተን ይጠብቀን፤ 50 ልጆቼን ብትበድላቸው ወይም ሌሎችን በላያቸው ብታገባ፣
ማንም ከእኛ ጋር ባይኖርም እንኳ እግዚአብሔር በአንተና በእኔ መካከል ምስክር መሆኑን አትርሳ።” 51 ላባም ያዕቆብን እንዲህ አለው፦ “ክምር ድንጋዩ እነሆ፤
በአንተና በእኔ መካካል ያቆምሁትም ሐውልት እነሆ፤ 52 ይህን ክምር ድንጋይ አልፌ አንተን ለማጥቃት ላልመጣ፣ አንተም ይህን ክምር ድንጋይና ይህን ሐውልት
አልፈህ እኔን ለማጥቃት ላትመጣ፤ ይህ ክምር ድንጋይ ምስክር ነው፤ ይህም ሐውልት ምስክር ነው። 53 የአብርሃም አምላክ፣ የናኮር አምላክ፣ የአባታቸውም
አምላክ በመካከላችን ይፍረድ።” ስለዚህ ያዕቆብ አባቱ ይስሐቅ በሚፈራው በእግዚአብሔር ማለ። 54 ያዕቆብ በኮረብታማው አገር ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤
ዘመዶቹንም ምግብ እንዲበሉ ጋበዛቸው፤ እነርሱም ከበሉ በኋላ እዚያው አደሩ። 55 በማግስቱም ማለዳ ላባ የልጅ ልጆቹን እንዲሁም ሴቶች ልጆችን ስሞ
መረቃቸው፤ ከዚያም ወደ አገሩ ተመለሰ።

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 31:1

ይህን
ይህ ቃል የታሪኩን ትረካ መሥመር ለማቋረጥ ተጠቅሞአል በዚህ ጸሐፊው አዲስ ታሪክ ይጀምራል

ያዕቆብ የላባን ወንዶች ልጆች ያሉትን ነገር ሰማ
ያዕቆብ የላባን ወንዳች ልጆች የሚሉትነ ሰማ

ያዕቆብ የአባታችን የሆነውን ሁሉ ወስዶታል
የላባን ወንዶች ልጆች ከመቆጣታቸው የተነሣ አጋንነው ይናገራሉ አት ያዕቆብ የወሰደው ነገር ሁሉ የአባታችን ነበር:: (ማጋነንና ገሃዳዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

ያዕቆብም የላባን ፊት አየ አመለካከቱም እንደተለወጠበት ተገናዘበ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረት አንድ ናቸው:: ሁለተኛው ያዕቆብ በላባን ፊት ያየውን ይገልጻል:: አት: “ያዕቆብም ላባን እንዳለተደሰተበት ተረዳ” (ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

አባቶችህ
አባትህ ይስሐቅና አያትህ አብርሃም

Genesis 31:4

ያዕቆብም ልኮ ራሔልንና ልያን ወደ በጎቹ ሥፍራ ወደ ሜዳ ጠራቸው
ያዕቆብ መንጎቹ ወደተሠማሩበት መስክ እንዲመጡ ራሔልንና ልያን አስጠራቸው

ለመንጋው እናም እንዲህ አላቸው
እነዚህ ሁለት አጫጭር ዐረፍተ ነገሮች ናቸው:: አት “ለመንጋው:: እንዲህም አላቸው” (የዐረፍተ ነገር ውቅር ይመልከቱ)

አባታችሁ ስለእኔ ያለው አመለካከት እንደቀድሞው አለመሆኑን ተረድቻለሁ
አባታችሁ በእኔ ደስተኛ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ

ባለኝ ጉልቤቴ ሁሉ አባታችሁን እንዳገለገልሁ እናንተ ታውቃላችሁ
እናንተ የሚለው ቃል ራሔልንና ልያን ያመለክታል እንዲሁም ደግሞ ትኩረትን ይጨምራል። አት: “አባታችሁን ባለኝ ጉልበት ሁሉ እንዳገለገልሁ እናንተው ራሳችሁ ታውቃላችሁ” (ሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 31:7

አታልሎኛል
ዋሽቶኛል ወይም በፍትሃዊነት አላስተናገደኝም

ደመወዜ
ሊከፍለኝ የተናገረውን

ሊጐዳኝ
ተገቢ ትርጉሞች 1 አካላዊ ጥቃት በማንኛውም መንገድ ለያዕቆብ መከራ መንስኤ በመሆን

ነቁጣ እንስሳት
ነጭ ምልክት ያላቸው እንስሳት

መንጎቹ ወለዱ
በጎቹ ወለዱ

ዝንጉርጉር
ዝንጉርጉር ቀለም ያላቸው እንስሳት

በዚህ መንገድ እግዚአብሔር የአባታችሁን ከብቶች ወስዶ ለእኔ ሰጠኝ
ይህም እንዴት እግዚአብሔር የአባታችሁን እንስሳት ለእኔ እንደሰጠኝ ነው

Genesis 31:10

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ታሪኩን ለሚስቶቹ ለልያና ለራሔል መናገሩን ይቀጥላል

የሚጠቁበት ወራት በሚሆንበት ጊዜ
በሚጠቁበት ወራት

መንጋው በሚጠቃበት
እዚህ “መንጋው” ሴት ፍዬሎችን ያመለክታል:: አት: “ሴት ፍዬሎች በሚጠቁበት” (ክፍልን ለሙሉና ሙሉውን ለክፍል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሽመልመሌ ዝንጉርጉርና ነቁጣ
ዝንጉርጉር ትንሽ ነቁጣና ትልቅነቁጣ ያላቸው

የእግዚአብሔር መልአክ
ተገቢ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በሰው መልክ ሲገለጥ 2) ከእግዚአብሔር መልእክተኞች አንዱሲገለጥ ሀረጉ በተክክል እስካልተገለጸ ለ”መልአክ” የሚንጠቀመውን መደበኛ ቃል በመጠቀም በቀላሉ እንደ “እግዚአብሔር መልእክተኛ” መተረጐም ተገቢ ነው::

እኔም አልሁ
እኔም መለስሁ

እነሆኝ
አዎን እየሰማሁ ነኝ ወይም አዎን ምንድነው? በዘፍጥረት 22: 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Genesis 31:12

አጠቃላይ መረጃ
የእግዚአብሔርም መልአክ ያዕቆብን መናገር ቀጠለ:: (ዘፍጥረት 31:10 ይመልከቱ)

ዐይኖችህን ቀና አድርግ
ይህ ቀና ብለህ ተመልከት ማለት ነው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መንጎቹን የሚያጠቁቸውን
እዚህ “መንጋ” እንስት ፍዬሎች ብቻ ያመለክታል:: አት “የመንጋው እንስት ፍዬሎችን የሚያጠቁቸውን” (ክፍል ለሁሉና ሁሉን ለክፍል የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሽመልመሌ ዝንጉርጉርና ነቁጣ
ዝንጉርጉርና ነቁጣ ያለባቸው

ዘይት የቀባሄው ሐውልት
ያዕቆብም ሐውልቱን ዘይፍ በመቀባት ለእግዚአብሔር የቀደሰው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

የትውልድህ ምድር
የተወለድህበት ምድር

Genesis 31:14

ራሔልና ልያም እንዲህ ብለው መለሱ
ይህ በተመሣሣይ ጊዜ ተናግረዋል ማለት አይደለም እንተስማሙ ያጸናል

ከአባታችን ሀብት የሚናገኘው ምን ድርሻ ወይም ውርስ አለን?
ራሔልና ልያ በጥያቄ መልክ አባታቸው ሊሰጣቸው ምንም እንዳልቀረ አጥብቀው ይናገራሉ። አት: “ከአባታችን ልንወርሰው በፍጹም የቀረ ምንም ነገር የለም!” (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እኛን የሚያየን እንደባዕድ አይደለምን?
አባታቸው እንዴት እንደሚያዩአቸው ያላቸውን ቁጣ በጥያቄ ይገልጻሉ:: አት: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ገቢራዊ ዓረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል አት አባታችን እንደ ሴት ልጆቹ ሳይሆን እንደባዕድ ሴቶች ያየናል:: (ቅኔ አዘል ጥያቄዎችና ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ)

ሸጦናል
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: ለራሱ ጥቅም ሸጦናል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ደግሞም ዋጋችንን በፍጹም በልቶታልና
ላባን ለሴት ልጆቹ መስጠት የነበረበትን ገንዘብ በፍጹም ለራሱ መጠቀሙ የዱር አራዊት እንደ ምግብ ገንዘቡን እንደበሉት ተደርጐ ተነግሮአል:: አት: “በፍጹም ገንዘባችንን ተጠቅሞአል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው
ለእኛና ለልጆቻችን ይገባል

አሁንም
እዚህ አሁን የአሁን ጊዜ አይደለም ነገር ግን ለሚከተለውን አስፈላጊ ነጥብ ትኩረት ለመስጠት ነው።

እግዚአብሔር ያለህን ሁሉ አድርግ
እግዚአብሔር የነገረህን ሁሉ አድርግ

Genesis 31:17

ወንዶች ልጆቹ
ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ ወሰደ:: ወራሾች ስለሆኑ ወንዶች ልጆቹን ብቻ የጠቀሳል:: አት: “ልጆቹን” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከብቶቹን ሁሉ ነዳ
ሁሉን ከብቶች ነዳ:: እዚህ “ከብቶች” ሁሉን የቤት እንስሳትን ይወክላል።

በጳዳን አራም ካፈራው ሀብት ሁሉ ጋር
በጳዳን አራም እያለ ያፈራቸውን ሌሎች ከብቶችንም

ከዚያም ወደ አባቱም አገር ወደ ይስሐቅ ወደ ከነዓን ጉዞውን ቀጠለ
አባቱ ይስሐቅ ወደሚኖርበት አገር ወደ ከነዓን ሄዴ

Genesis 31:19

ላባን በጐቹን ሊሸልት ሄዶ ሳለ
ላባን የበጐቹን ጸጉር ሊያስቆርጥ በሄደበት ጊዜ

ወንዞን
የኤፍራጥሰ ወንዝ ያመለክታል

አመራ
ተጓዘ

ወደ ኮረብታማው አገር ወደ ገለአድ
ወደ ገለአድ ተራራዎች ወይም ወደ ገለአድ ተራራ

Genesis 31:22

በሶስተኛው ቀን
የወጡበትን ቀን እንደ አንድ ቀን መቁጠር የአይሁድ ለማድ ነው:: አት: “ከወጡበት ሁለት ቀናት በኋላ”

ለላባን ተነገረው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት አንድ ሰው ለላባን ነገረው ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች ይመልከቱ

ያዕቆብም ኮበለለ
የቤተሰቡ መሪ ስለሆነ ያዕቆብ ብቻ ተጠቅሶአል ቤተሰቡ ከእርሱ ጋር እንደተጓዙ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “ያዕቆብ ከሚስቶቹና የልጆቹ ጋር ኮበለለ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ይዞ ተነሣ
ላባን ይዞ ተነሣ

ተከታተለው
አሳደደው

ለሰባት ቀናት ጉዞ
ያዕቆብን ደርሶ ለመያዝ ላባን ሰባት ቀናት ተጓዘ

ደረሰበት
ያዘው

Genesis 31:24

ከዚያም እግዚአብሔር ለሶሪያዊው ለላባን በሕልም ተገልጦ
“ከዚያም” የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩን ወደ ላባን የሕይወት ዳራ መረጃ ለመቀየር ነው አት: “በዚያ ሌሊት እግዚአብሔር ለላባን ተገልጦ” (የዳራ መረጃዎች ይመልከቱ)

ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ አለው
“ክፉ ሆነ ደግ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው “ምንም” ለማለት ነው። አት፡ ያዕቆብን ከመሄድ ለማቋረጥ ለመሞከር ምንም ነገር እንዳትናገር (See: Merism)

ከዚያም ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኰረብታማ አገር ድንኳን ተክሎ ሳለ ላባ ደረሰበት ላባና ዘመዶቹ በዚያው ሠፈሩ::
“ከዚያም” የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩን ወደ ያዕቆብናላባን የሕይወት ዳራ መረጃ ለመቀየር ነው:: አት: “ላባን ያዕቆብን በደረሰበት ጊዜ ያዕቆብ በኰረብታማው አገር ድንኳን ተክሎ ነበር: ከዚያም ላባንና ዘመዶቹ ደግሞ በኰረብታማው ገለዓድ አገር ድንኳን ተከሉ” (የዳራ መረጃዎች ይመልከቱ)

Genesis 31:26

ልጆቼን የጦር ምርኮኛ ይመስል አካልበህ ወሰድናቸው
ያዕቆብ ቤተሰቡን ከራሱ ጋር ወደ ከነዓን ምድር መውሰዱ ልክ ያዕቆብ እንደ የጦር ምርኮኞችን እናም አስገድዶአቸው እየወሰደ እንዳለ ላባን ይናገራል ላባን ስለተቆጣና ያዕቆብ ስላደረገው ነገር ጸጸት እንዲሰማው አግንኖ ይናገራል:: (ተመሣሣይ ንጽጽር የማጋነንና ገሃዳዊ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ተደብቀህ ሄድህ
በድብቅ ሸሸህ

ፍስሐ በማድረግ
በደስታ

በከበሮ/ ታምቡርና በበገና
እነዚህ መሣሪያዎች ሙዝቃን የሚገልጹ ናቸው፡፡ አት፡ “እናም በሙዝቃ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ታምቡር
የከበሮ ዓይነት ለምት የሚሆን እናት ያለው ዙሪያሙ ክብረት የተሠራና መሣሪያው በሚመታበት ጊዜ የሚርገበገብ የሙዝቃ መሣሪያ ነው ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ

ወንዶች የልጅ ልጆቼን እንዲስማቸው
እዚህ ወንዶች የልጅ ልጆች ወንድ ሆነ ሴት ሁሉን የልጅ ልጆችን ይወክላሉ:: አት: “የልጅ ልጆቼን እንዲስማቸው” (በወንዴ ጾታ የተጠቀሱ ሴት ጾታንም የመግለጽ አባባል ይመልከቱ)

አሁን የሠራሄው የጅል ሥራ ነው
በጅልነት አድርገሄዋል

አሁንም
ይህ የዚያን ጊዜ ማለተ አይደለም ነገር ግን ለሚከተለውን ጠቃሚ ነገር ትኩረት እንደሰጥበት ነው

Genesis 31:29

እናንተን ልጐዳችሁ ነበር
እዚህ “እናንተ” ብዙና ከያዕቆብ ጋር ያሉትን ሁሉ ያመለክታል:: አት: “ሊጐዳችሁ የሚያስችለኝ ከእኔ ጋር ብዙ ሰዎች ነበሩ” (የሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ አለኝ
“ክፉ ሆነ ደግ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው “ምንም” ለማለት ነው፡፡ በዘፍጥረት 31:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት፡ “ያዕቆብን ከመሄድ ለማቋረጥ ለመሞከር ምንም ነገር እንዳትናገር” (See: Merism)

አንተም ሄደሃል
አንተ የሚለው ነጠላና ያዕቆብን ያመለክታል:: (የሁለተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ወደ አባትህም ቤት
እዚህ ቤት ቤተሰብን ይወክላል:: አት: “ወደ አባትህና ሌሎች ቤተሰብህ ቤት ለመመለስ” (ክፍልን ሙሉና ሙሉውን ክፍል አድርጐ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

አምላኮቼን
ጣዖቶቼን

Genesis 31:31

ልጆችህን ከእኔ የምትቀማ ስለመሰለኝና ስለፈራሁ በድብቅ ወጣሁ፡፡
በድብቅ የወጣሁት ልጆችህን ከእኔ ነጥቀህ ታስቀርብኛለህ ብዬ ስለፈራሁ ነው፡፡

ከእኛ መካከል የአንተን የጣዖታት ምስል ደብቆ የተገኘ ሰው ካለ ይሙት
ይህ በአዎንታዊ መንገድ መገለጽ ይችላል አት ጣዖቶችህን የሰረቀ ማንም ቢገኝ እንገድላለን (ምጸት ይመልከቱ)

ዘመዶቻችን/የእኛ ዘመዶች ባሉበት
የእኛ የሚለው ቃል የያዕቆብ ዘመዶችንና የላባን ዘመዶች ያመለክታል:: ሁሉም ዘመዶች ፍትሃዊና ግልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ያዩታል (ሁሉ አቀፍ አንደኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

ያንተ የሆነ አንዳች ነገር ከኔ ዘንድ ቢገኝ ውሰድ
በእኛ ዘንድ ካለው ያንተ የሆነውን ፈልግና ውሰድ

ያዕቆብ ራሔል እነዚያን/ጣዖታቱን መስረቋን አያውቅም ነበር
ይህም ታሪኩን ወደ ያዕቆብ ሕይወት ዳራ መረጃ ይቀይራል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 31:33

ሁለቱ ደንገጡሮቿ
ዘለፋንና ባላን ያመለክታል

አላገኛቸውም
ጣዖታቱን አላገኘም

Genesis 31:34

ከዚያም ራሔል በላያቸው ተቀምጣ ነበር
ከዚያም የሚለው ቃል ታሪኩን ወደ ራሔል ሕይወት ዳራ መረጃ የቀይራል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ኮርቻ
ሰው እንዲቀመጥበት በጋማ እንስሳት ጀርባ የሚደረግ መቀመጫ ነው

ጌታዬ
አንድን ሰው “ጌታዬ” ብሎ መጥራት የማክበር መንገድ ነው

በፊትህ ተነስቼ መቆም ስላልቻልሁ
ይህ ከማሕጸንዋ ወራዊ ደም የሚፈስበት ጊዜ ውስጥ እንዳለች ያለመክታል:: (ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ በተዘዋዋሪ አንድን ነገር ስለመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 31:36

እርሱም እንዲህ አለው
ያዕቆብ ላባንን እንዲህ አለ

ወንጄሌ ምንድነው? ይህን ያህል የምታሳድደኝ ኃጢአቴ ምን ቢሆን ነው?
ወንጄሌ ምንድነው እና ኃጢአቴ ምን ሆን የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ያዕቆብ ላባንን ምን ስህተት እንደሠራ ይጠይቀዋል አት ይህን ያህል በጽኑ የምታሳድደኝ ምን ስህተት ቢፈጽም ነው? (ተጓዳኝ ተነጻጻሪ አባባል ይመልከቱ)

በጽኑ
እዚህ “ጽኑ” የሚለው ቃል ላባን በማጣደፍ ያዕቆብን ለመያዝ ባለው ተነሣሽነት እንዳሳደደው ይገልጻል (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

ከቤትህስ ዕቃ ሁሉ ምን አገኘህ?
ያንተ ሆኖ ያገኘሄው ዕቃ የትኛው ነው?

በእኛ ዘመዶች ፊት አቅርብ
እዚህ እኛ የሚለውቃል የያዕቆብ ዘመዶችና የላባንን ዘመዶች ያመለክታል:: አት: ያገኘሄውን ማንኛውንም ነገር በዘመዶቻችን ፊተ አቅርብ (አካታች አንደኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

እነርሱ ሁለታችንን ይፍረዱ ወይም እነርሱ ይፍረዱን
እዚህ “ሁለታችን” ያዕቆብንና ላባን ያመለክታል:: “ይፍረዱን” የሚለው አባባል ከክርክሩ የትኛው ትክክል እንደሆነ ይወስኑ ማለት ነው፡፡

Genesis 31:38

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ለላባን መናገሩን ቀጠለ

ሃያ ዓመታት
20 ዓመታት (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ሴት በግ
እንስት የበግ ጠቦት

አልጨነገፉም
በእርግዝና ወቅት የተቀጨ ወይም ሞቶ የተወለደ ጠቦት አልነበረም ማለት ነው

በአውሬ የተሰበረውን አምጥቼ አላውቅም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት አውሬ ከእንሰሳትህ አንዱን በገደለ ጊዜ በድኑን ለአንተ አምጥቼ አላውቅም (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ያጣሄውን እተካ ነበር
ያዕቆብ ከመንጋው የላባንን ሙት እንስሳት ምትክ መቁጠር በጫንቃው እንደተሸከመው ሸክም እንደነበር ተደርጐ ተገልጾአል:: አት: "ከመንጋህ እንደጠፋ ከመቁጠር ከመንጋዬ እንደጠፋ ቆጥረዋለሁ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በቀን በሐሩር ሌሊት በቁር ይበላኝ ነበር
በሞቃትና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ መሠቃየት የአየር ሁኔታዎች ያዕቆብ እንደ አውሬዎች እንደበሉ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት በቀን ሐሩርና በሌሊት ቁር ከመንጋዎችህ ጋር ነበርሁ (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 31:41

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ለላባን መናገሩን ቀጠለ

እነዚህ ሃያ ዓመታት
እነዚህ 20 ዓመታት (ቁጥሮች ይመልከቱ)

አሥራ አራት ዓመታት
14 ዓመታት (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ደመወዘን አሥር ጊዜ ለዋውጠህብኛል
መክፈል ያለበትን አሥር ጊዜ ለዋውጦብኛል:: በዘፍጥረት 31:7 ደመወዜን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የአባቴ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ፍርሃት ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ
የአብርሃምና የአባቴ የይስሐቅ አምላክ ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ

የአባቴ አምላክ
እዚህ "አባቴ" የሚለው ቃል አባቱን ይሰሐቅን ያመለክታል::

ይስሐቅ የሚፈራው
እዚህ "ፍርሃት" ለእግዚአብሔር ያለውን ፍርሃት ያመለክታል።

ባዶ እጄን
ይህ ምንም አለመኖር ማለት ነው:: አት: "ፍጹም ባዶ" (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መከራዬን አይቶ ልፋቴን ተመልክቶ
መከራ የሚለው ረቂቅ ስም መከራ አየ በሚቶል ሊገለጽ ይችላል:: አት: "እግዚአብሔር ልፋቴን አይቶ እንዴት መከራ እንዳሳየሄኝ ተመልክቶ" (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Genesis 31:43

ነገር ግን በእነዚህ ሴቶች ልጆቼና በወለዷቸው ልጆቻቸው ላይ ዛሬ ምን ማድረግ እችላለሁ?
ላባን ምንም ማድረግ እንደማይችል አግንኖ ለመቅለጽ ጥያቄ ይጠቀማል ይህ አጋናኝ ጥያቄ በዐረፍተነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: "ነገር ግን ከእኔ ጋር ወደ ኋላ ለመመለስ በልጆቼና በልጅ ልጆቼ ምንም ላደርግ አልችልም" (አግናኝ ጥቃቄዎች ይመልከቱ)

ምስክር ይሁን
እዚህ "ምስክር" የሚለው ቃል ሰውን አያመለክትም ነገር ግን ያዕቆብና ላባ የሚገቡትን ቃልኪዳን የሚያመለክትና በምሳለያዊነት የተጠቀመ ነው:: ምስክሩ ሁለቱ በሰላማዊ መንገድ ስስማሙ እንደተገኘ ሰው ተደርጐ ተነግሮአል (ሰውኛ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 31:45

ሐውልት
ይህ በክስተቱ ማብቂያ ያቆመው ትልቅ ድንጋይ ሲሆን አስፈላጊ ክስተት እንደተከናወነ ለማመለከት ነው

ድንጋይ ከመሩ
ድንጋዩን አንዱን በአንዱ ላይ በማድረግ ከመሩ

ከዚያም በድንጋዩ ክምር አጠገብ በሉ
አብሮ ምግብን መመገብ ቃል ኪዳን መፈጸሚያ አካል አንዱ ነው የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ይጋርሠሀዱታ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: "ይጋርሠሀዱታ" የሚለው ስም በላባን ቋንቋ "ክምር ምስክርነት" ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ገለዓድ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: "ገለዓድ" የሚለው ስም በላባን ቋንቋ "ክምር ምስክርነት" ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 31:48

ይህ ክምር በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ነው
ድንጋዮች በእርግጥ እንደሰው ምስክር ሊሆኑ አይችሉም:: አት: "ይህ ክምር በእኔና በአንተ መካከል ማስታወሻ ይሆናል" (በሰውኛ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ገለዓድ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: "ገለዓድ" የሚለው ስም በላባን ቋንቋ "ክምር ምስክርነት" ማለት ነው:: በዘፍጥረት 31:47 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ምጽጳ
ተርጓሚዎች የማከተውን እንደግርጌ ማስናታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: "ምጽጳ" የሚለው "የመጠበቂያ ማማ" ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እኛ በማንተያይበት ጊዜ
እዚህ “አለመተያየት” በተለያየን ይወክላል:: አት “በተለያየን ጊዜ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ማንም ከእኛ ጋር ባይኖር
እዚህ “እኛ” ያዕቆብንና ላባን ያመለክታል:: አት: “ማንም የሚያየን ባይኖር”

እይ
“ተመልከት” “አስተውል” “ለሚናገረው ነገር ትኩረት ስጥ”

Genesis 31:51

ይህ ክምር መሥክር ነው... ይህም ሐውልት ምሥክር ነው
የሰላም ስምምነታቸውን በሚመለከት እነዚህ የድንጋይ ክምሮች ለላባና ለያዕቆብ የማስታወሻና ድንበር ምልክቶች ናቸው:: እነዚህ እንደሰው ምሰክሮች እንደሆኑ ተደርጐ ተነግሮአል (በሰውኛ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የአባቱ የይስሐቅ ፍርሃት
እዚህ “ፍርሃት” ይስሐቅ ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮትና ያንንም በመታዘዝ መግለጹን ያመለክታል።

Genesis 31:54

ዘመዶቹንም ምግብ እንዲበሉ ጋበዛቸው
አብሮ ምግብ መብላት አብሮ ቃል ኪዳን የመግባት አካል ነው የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በማግስቱም ማለዳ...ወደ አገሩ ተመለሰ
ቁጥር 55 በመጀመሪያው የዕብራይስጡ መጽሐፍ የምዕራፍ 32 የመጀመሪያ ቁጥር ነው ነገር ግን በአብዛኛዎቹ ዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች የምዕራፍ 31 የመጨረሻ ቁጥር ነው በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች የተጠቀመውን የቁጥር አቀማመጥ በቋንቋዎ እንዲጠቀሙ ይመከራል

የተባረከ
አዎንታዊና ጠቃሚ ነገሮች ለአንድ ሰው እንዲደረጉ መሻትን የሚገልጽ ማለት ነው

Chapter 32

1 ያዕቆብ በጉዞ ላይ ሳለ የእግዚአብሔር መላእክት በመንገድ ተገናኙት። 2 ባያቸውም ጊዜ፤ “ይህ የእግዚአብሔር ሰፈር ነው” አለ፤ የዚያንም ቦት ስም
መሃናይም አለው። 3 ያዕቆብም በኤዶም አገር ሴይር በተባለው ምድር ወደሚኖረው ወንድሙ ወደ ዔሳው መልእክተኞችን አስቀድሞ ላከ፤ 4 እንዲህም ብሎ
አዘዛቸው፤ “ጌታዬን ዔሳውን እንዲህ ትሉታላችሁ፤ ‘አገልጋይህ ያዕቆብ እንዲህ ብሎአል በሉት፤ ከላባ ዘንድ ተቀምጬ እስካሁን ድረስ እዚያው ኖርሁ፤ 5 ከብቶች፣
አህዮች፣ የበግና የፍየል መንጎች እንደዚሁም የወንድን የሴት አገልጋዮች አሉኝ፤ አሁንም ይህን መልእክት ለጌታዬ መላኬ በአንተ ዘንድ ሞገስ አገኛለሁ በሚል
ተስፋ ነው።’” 6 የተላኩትም ሰዎች ወደ ያዕቆብ ተመልሰው፣ “ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሄደን ነበር፤ እርሱም ከአንት ጋር ለመገናኘት በመምጣት ላይ ነው፤
ከእርሱም ጋር አራት መቶ ሰዎች አሉ” አሉት። 7 በዚህ ጊዜ ያዕቆብ እጅግ በመፍራት ተጨነቀ፤ አብረውት የነበሩትንም ሰዎች በሁለት ክፍል መደባቸው፤
እንዲሁም በጎቹን፣ ፍየሎቹን፣ ከብቶቹንና ግመሎቹን በሁለት በሁለት መደባቸው። 8 ይህንንም ያደረገው፡- “ዔሳው የመጀመሪያውን ክፍል ቢያጠቃ፣ ሌላው
ክፍል ሊያመልጥ ይችላል” ብሎ በማሰብ ነው። 9 ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ “የአባቴ የአብርሃም አምላክ፣ የአባቴ የይስሐቅ አምላክ ሆይ፣ ‘ወደ አገርህና ወደ
ዘመዶችህ ተመልስ፣ እኔም በጎ ነገር አደርግልሃለሁ’ ያልኸኝ እግዚአብሔር ሆይ፣ 10 እኔ ባሪይህ እስካሁን ላደረግህልኝ ቸርነትና ታማኝነት ብቁ አይደለሁም፤
ዮርዳኖስን ስሻገር በእጄ ላይ ከነበረው በትር በስተቀር ምንም አልነበረኝም፤ አሁን ግን ይኸው ሁለት ሠራዊት ሆኛለሁ። 11 ከወንድሜ ከዔሳው እጅ እንድታድነኝ
እለምንሃለሁ፤ መጥቶ እኔንም ሆነ እነዚህን እናቶች ከነልጆቻቸው ያጠፋናል ብዬ ፈርቻለሁኝ፤ 12 ነገር ግን አንተ ራስህ፣ ‘አበለጽግሃለሁ፤ ዘርህንም ሊቆጠር
እንደማይችል እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ’ ብለኸኛል።” 13 በዚያችም ሌሊት ያዕቆብ እዚያው አደረ፤ ካለው ሀብት ለወንድሙ ለኤሳው እጅ መንሻ እንዲሆኑ
እነዚህን መረጠ፡- 14 ሁለት መቶ እንስት ፍየሎችና ሃያ አውራ ፍየሎች፣ ሁለት መቶ እንስት በጎችና ሃያ አውራ በጎች፣ 15 ሠላሳ የሚያጠቡ ግመሎች
ከነግልገሎቻቸው፣ አርባ ላሞችና ዐሥር ኮርማዎች፣ ሃያ እንስት አህዮችና ዐሥር ተባት አህዮች። 16 እነዚህንም በየመንጋው ለይቶ፣ የሚነዱአቸውን ጠባቂዎች
መደበላቸው፤ ጠባቂዎችንም እናንተ ቀድማችሁ ሂዱ፣ መንጋዎቹንም አራርቃችሁ ንዱአቸው” አላቸው። 17 ቀድሞ የሚሄደውንም እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ዔሳው
አግኝቶህ ‘የማን ነህ? ወዴትስ ትሄዳለህ? የምትነዳውስ ይህ ሁሉ ከብት የማን ነው?’ ብሎ ቢጠይቅህ፣ 18 ‘የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው፤ ለጌታዬ ለዔሳው
እጅ መንሻ የሰደዳቸው ናቸው፤ እርሱም ከበስተኋላችን እየመጣ ነው’ ብለህ ንገረው 19 እንዲሁም ሁለተኛውን፣ ሦስተኛውንና መንጎቹን የሚነዱትን ሌሎቹንም
ሁሉ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ ‘ዔሳውን ስታገኙት ይህንኑ ትነግሩታላችሁ፤ 20 በተጨማሪም ‘አገልጋይህ ያዕቆብ ከኋላችን እየመጣ ነው’ በሉት። ይህንንም
ያዘዘው፣ ‘ዔሳው ከእኔ ጋር ከመገናኘቱ በፊት እጅ መንሻዬ አስቀድሞ ቢደርሰው ምናልባት ልቡ ይራራና በሰላም ይቀበለኛል’ ብሎ ስላሰበ ነበር። 21 ስለዚህ
የያዕቆብ እጅ መንሻ ከእርሱ አስቀድሞ ተላከ፤ እርሱ ራሱ ግን እዚያው በሰፈሩ ቦታ አደረ። 22 በዚያኑ ሌሊት ያዕቆብ ተነሣ ሁለቱን ሚስቶቹን፣ ሁለቱን ሴት
አገልጋዮቹንና ዐሥራ አንዱን ልጆቹን ይዞ የያቦቅን ወንዝ ተሻገረ። 23 ወንዙን አሻግሮ ከሸኛቸው በኋላ፣ ጓዙን ሁሉ ሰደደ። 24 ያዕቆብም ብቻውን እዚያ ቀረ፤
አንድ ሰውም እስኪነጋ ድረስ ሲታገለው አደረ። 25 ያም ሰው ያዕቆብን ታግሎ ማሸነፍ እንዳቃተው በተረዳ ጊዜ፣ የጭኑን ሹልዳ መታው፣ ያዕቆብም
በሚታገልበት ጊዜ ጭኑ ከመገጣጠሚያው ላይ ተለያየ፤ 26 በዚያን ጊዜ ሰውዬው፣ “እንግዲህ መንጋቱ ስለሆን ልቀቀኝና ልሂድ” አለው። ያዕቆብም፣
“ካልባረክኸኝ አልለቅህም” አለው። 27 ሰውዬውም፣ “ስምህ ማን ነው?” አለው። እርሱም፣ “ያዕቆብ ነው” አለ። 28 ሰውዬውም፣ “ከእግዚአብሔርም
ከሰዎችም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ ስምህ እስራኤል እንጂ ያዕቆብ አይባልም” አለው። 29 ያዕቆብም፣ “እባክህ ስምህን ንገረኝ” ብሎ ጠየቀው።
ሰውዬውም፣ “ስሜን ለማወቅ ለምን ፈለግህ?” አለው፤ በዚያም ስፍራ ባረከው። 30 ስለዚህ ያዕቆብ “እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ዐይቼ እንኳ ሕይወቴ
ተርፋለች” ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል አለው። 31 ጵኒኤልንም እንዳለፈ ፀሐይ ወጣችበት፣ እርሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር። 32 ከዚህም የተነሣ
የእስራኤል ልጆች ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘውን ሥጋ አይበሉም፤ ምክንያቱም ያዕቆብ ከሰውዬው ጋር ሲታገል ሰውዬው ሹልዳውን መትቶት ስለነበር ነው።

Genesis 32:1

መሃናይም
ተርጓሚዎች በግርጌ ማስታወሻዎች ሊጨምሩ ይችላሉ:: መሃናይም የሚለው ስም “ሁለት ሰፈሮች” ማለት ነው

Genesis 32:3

ሴይር
ይህ በኤዶምያስ ግዛት ተራራማው ቦታ ነው:: ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

ጌታዬን ዔሣውን እንዲህ ትሉታላችሁ “አገልጋይህ ያዕቆብ እንዲህ ብሎአል በሉት “እስካሁን …. በፊትህ’”
ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ አለው:: ቀጥታው ጥቅስ እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ ‘ይህ ለጌታዬ ለዔሣው ሊነግር የሚወደው ነው:: እስከዚህ እንዳለሁት ……በፊቱ’” (ጥቅስን በጥቅስ ውቅጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ጌታዬ ዔሣው
ያዕቆብ ወንድሙን ጌታው አድርጎ በማቅረብ የትህትና ቃል ይጠቀማል

አገልጋይህ ያዕቆብ
ያዕቆብ ራሱን እንደአገልጋዩ በማድረግ የትህትና ቃል ይጠቀማል

በአንተ ፊት ሞገስ ባገኝ
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ማትረፍን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው አት “መቀበልህን እንዲታረጋግጥልኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሣሣይ ምትክ ቃላትና ዘይቤያዊ አባባሎች ይመልከቱ)

Genesis 32:6

አራት መቶ ሰዎች
400 ሰዎች ቁጥሮች ይመልከቱ

ፍርሃት
አንድ ሰው በራሱ ወይም ከሌሎች ሥጋት የሚፈጥር ጉዳት ሲደረስበት የማሰማው ስሜት ነው

ጭንቀት
ተስፋ መቁረጥ ወይም መረበሽ

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

በአንደኛው ሠፈር ላይ አደጋ ቢጥል ሌላው ሠፈር ሊያመልጥ ይችላል
እዚህ ሠፈር ሰዎችን ይወክላል አት በአንዱ ሠፈር ባለው ሰው አደጋ ቢጣል በሌላው ሠፈር ያለው ሰው ያመልጣል። (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 32:9

የአባቴ የአብርሃም አምላክ የአባቴ የይስሐቅ አምላክ ሆይ
ይህ ለተላያዩ አማልክት ሳይሆን ሁሉም ያመለኩትን አንድ እግዚአብሔርን ያመለክታል አት የአያተ የአብርሃምና የአባተ የይስሐቅ አምላክ እግዚአብሔር (ግምታዊ እውቀትና ጥብቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወደ አገርህና ወደ ዘመዶችህ ተመለስ እኔም በጐ ነገርን አደርግልሃለሁ ያልከኝ እግዚአብሔር ሆይ
ይህ በጥቅ ውስጥ የሚገኝ ጥቅሰ ነው:: በተዘዋዋሪ ጥቅስ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ወደ አገሩና ወደ ሕዝቤ እንድመለስና በጐ ነገርንም አደርግልሃለሁ ያልከው እግዚአብሔር”

ወደ ዘመዶችህ
ወደ ቤተሰብህ

በጐ ነገር አደርግልሃለሁ
መልካም ነገር አደርግልሃለሁ ወይም በመልካምነት እንከባከብሃለሁ

እኔ ባሪያህ እስካሁን ላደረክልኝ የቃልኪዳን ቸርነትና ታማኝነት ብቁ አይደለሁም
ረቂቅ ስሞች ቸርነትና ታማኝነት እንደ ቸር እና ታዛዥ ሊገለጹ ይችላሉ አት እኔ ባሪያህ እስካሁን ላደረክልኝ የቃልኪዳን ታማኝ አይደለሁም ወይም ታዛዥ አይደለሁም (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተነገር ይመልከቱ)

ባሪያህ
“እኔ” የሚለው በትህትና ቃል ሲገለጽ ነው

አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ
ሆንሁ የሚለው ሐረግ ያለውን ሀብት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው:: አት: “አሁን ግን ከእኔ ጋር በሁለት ክፍል ሠራዊት በቂ ሰዎች መንጋዎችና ሀብት አሉኝ” ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ

Genesis 32:11

አድነኝ
አትርፈኝ

ከወንድሜ እጅ ከዔሣው እጅ
እዚህ “እጅ” ጉልበትን ያመለክታል ሁለቱም ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ሁለተኛው የሚገልጸው ያዕቆብ የሚያስበው ወንድመ ዔሣው እንደሆነ ነው። አት፡ ከወንድሜ ከዔሣው ጉልበት ወይም ከወንድሜ ከዔሣው (ተመሣሣይ ምትክ ቃል ወይም ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

እንዳያጠፋ እኔ እፈራለሁና
እንደሚያጠፋ ፈርቼያለሁና

ነገር ግን አንተ ራስህ አበለጽግሃለሁ ዘርህን ሊቈጠር....
ይህ በጥቅስ ውስጥ ያለ ጥቅስ ነው እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ነገር ግን አንተ ራስህ አብለጽግሃለሁ እናም የዘረንም ቁጥር..” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና በዘዋዋሪ ጥቅችን ይመልከቱ)

አበለጽግሃለሁ
መልካም ነገርን አደርግልሃለሁ ወይም በመልካምነቴ አሳይሃለሁ

ዘርህን እንደ ባህር አሸዋ አበዛዋለሁ
የያዕቆብን ዘር ቁጥር እጅግ ብዙ ማድረጉ ቁጥሩ እንደ ባህር አሸዋ ቁጥር እንደሚሆን ተደርጐ ተነግሮአል (ተመሣሣይ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሊቆጠር እንደማይችል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት: “ያም ከቁጥራቸው የተነሣ ማንም መቁጠር እስከማይችል” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 32:13

ሁለት መቶ
200 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሃያ .... ሠላሣ .... አርባ ... አሥር
20 .... 30 .... 40 ....10 (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ግልገሎች
እየጠቡ ያሉ ለጋ እንስሳት

እነዚህንም መንጐች በየወገኑ ከፍሎ በባሪያዎች እጅ አደረጋቸው
እዚህ “በእነሱ እጅ” በእነሱ ቁጥጥር ሥር አደረገ ማለት ነው:: አት በየወገኑ ከፈለቸው እናም እያንዳንዱን መንጋ በእያንዳንዱ ባሪያ ቁጥጥር ሥር አደረገ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መንጋውንና መንጋውን አራርቁት
አንዱ መንጋ ከሌላው መንጋ በርቀት እንዲጓዝ አድረጉ

Genesis 32:17

መመሪያ ሰጠው
አዘዘው

በፊትህ ያለው... የማን ነው? ብሎ የጠየቀህ እነደሆነ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ያለ ጥቅስ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “የማን ነህ? ወዴትስ ተሄዳለህ? የምትነዳውስ ይህ ሁሉ ከብት የማን ነው? ብሎ ቢጠይቅህ” (ጥቅስ በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶች ይመልከቱ)

የማን ነህ?
ጌታህ ማን ነው?

በፊትህ ያለው ይህ ሁሉ ከብት የማን ነው?
በፊትህ ያለው የዚህ ሁለ ከብት ባለቤት ማን ነው?

በዚያን ጊዜ አንተ ለጌታዬ ለዔሣው እጅ መንሻ የሰደደው የባሪያህ የያዕቆብ ነው እርሱም ደግሞ ከኋላችን እየመጣ ነው፤ በለው
ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ነው በተዘዋዋሪ ጥቅስ መልክ ሊገለጽ ይችላል፤ አት፤ “በዚያን ጊዜ እነዚህ ሁሉ የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው፤ ለጌታዬ ለዔሣው እጅ መንሻ የሰደዳቸው ናቸው፤ እርሱም ሊገናኝህ ከበስተኋላችን እየመጣ ነው፤ ብለህ እንዲትነግረው እፈልጋለሁ::” (ጥቅስ በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶች ይመልከቱ)

የአገልጋይህ የያዕቆብ ናቸው
የዕቆብ ራሱን ትህትናን በተሞላ መንገድ የዔሣው ባሪያ አድርጐ ያቀርባል

ለጌታዬ ለዔሣው
ያዕቆብ በትህትና ዔሣውን እንደ ጌታው መቁጠሩን ያመለክታል

ከእኛ ኋላችን እየመጣ ነው
እኛ የሚናገረውን ባሪያ ያመለክታል እናም ሌሎች ባሪያዎችም ለዔሣው እጅ መንሻ ይዘው እየመጡ እንዳለ ይገለጻል (ብዙና ነጠላ "እኛ" ይመልከቱ)

Genesis 32:19

ለሁለተኛው ቡድን መመሪያ ሰጠ
ሁለተኛውን ቡድን አዘዘ

ይህኑን ትነግሩታላችሁ ባሪያህ ያዕቆብ
አማራጭ ተገቢ ትርጉሞች 1) "ደግሞም እንዲህ ትነግሩታላችሁ ባሪያህ ያዕቆብ" 2) "ደግሞም እንዲህ ትላላችሁ ባሪያህ ያዕቆብ"

አስደስት ይሆናል
አረጋጋው ይሆናል ወይም ቁጣው እንዲርቅ አደርግ ይሆናል

ይቀበለኛል
በርኅራኄ ይቀበለኛል

የያዕቆብ እጅ መንሻ ከእርሱ አስቀድሞ ተላከ
እዚህ እጅ መንሻ እጅ መንሻውን ይዘው የሄዱ ባሪያዎች ይወክላል (ምትክ አባባሎችን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እርሱ ራሱ ግን እዚያው አደረ
እዚህ "ራሱ" ያዕቆብ ከባሪያዎቹ ጋር እንዳለሄደ አበክሮ ይናገራል (ተጣቃሽ ተውላጤ ስም ይመልከቱ)

Genesis 32:22

ሁለት ሴት ባሪያዎቹ/አገልጋዮቹ
ሁለት ባሪያ/አገልጋይ ሚስቶቹ፤ ዘለፋና ባላ ማለት ነው

የወንዝ መልካ
በወንዝ ጥልቅ ያልሆነ በቀላሉ የሚያሻግር ቦታ

ያቦቅ
ይህ የወንዝ ስም ነው ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ይመልከቱ

ንብረቱን ሁሉ
ያለውን ነገር ሁሉ

Genesis 32:24

እስኪነጋ
ንጋት ድረስ

የጭኑ ሹልዳ ሲታገለው ደነዘዘ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ልገለጽ ይችላል፤ አት: "በሚታገልበት ጊዜ የሚታገለው ሰው የያዕቆብን ሹልዳ ጐዳው" (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ጭን
ከዳሌ ጋር የተያያዘ ላይኛው የእግር አካል ነው

ሊነጋ ሲል
ጸሐይ ከመውጣትዋ በፊት

መባረክ
በአንድ ሰው ላይ በረከትን ማዘዝና ለዚያ ሰው መልካም ነገር እንዲሆኑለት ማድረግ ነው

ካልባረክሄኝ አልለቅህም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ልገለጽ ይችላል፤ አት: "በእርግጥ አልለቅህም መጀመሪያ ባርከኝና ከዚያም እለቅሃለሁ" (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ) (ድርብ አሉታዊ አባባሎች ይመልከቱ)

Genesis 32:27

እስራኤል
ተርጓሚዎች የግርጌ መስታወሻ እንደሚከተለው ሊጨምሩ ይችላሉ እስራኤል የሚለው ስም ከእግዚአብሔር ጋር ይታገላል ማለት ነው ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ

ሰዎች
ሰዎችን በገሃድ የሚገልጽ ነው

Genesis 32:29

እርሱም ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? አለው
እርሱም ስለ ስሜ ለምን ተቀጠይቃለህ አለው ይህ አግናኝ ጥያቄ ያዕቆብን የሚያደነግጠው የሚገሥጸውና በእርሱና ከእርሱ ጋር ሲታገል በቆየው ሰው መካከል ምን እንደተከሰተ እንዲያስብ የሚያደርገው ነው:: አት: "ስሜን አትጠይቅ" (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ጵንኤል
ተርጓሚዎች የግርጌ መስታወሻ እንደሚከተለው ሊጨምሩ ይችላሉ:: "ጵንኤል" የሚለው ስም "የእግዚአብሔር ፊት" ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)።

ፊት ለፊት
"ፊት ለፊት" ሁለት ሰዎች በቅርበት በአካል የሚተያዩበት ማለት ነው::

ሕይወቴ ተርፋለች
ይህ በሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ሕይወቴን አትርፎአታል:: (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 32:31

ከዚህም የተነሣ እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ታሪኩ ወደ እስራኤል ዘር ዳራ ትረካ እንተለወጠ አመላካች ነው (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

የጭኑ ሹልዳ
ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኝ የጡንቻ ሥጋ ያመለክታል

ተነክቶ ነበር
ሲታገል ተነክቶ ነበር

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 33

1 ያዕቆብ አሻግሮ ተመለከተ፤ እነሆ፣ ዔሳው አራት መቶ ሰዎች አስከትሎ እየመጣ ነበር። ስለዚህ ያዕቆብ ልጆቹን ለልያ ለራሔልና ለሁለቱ አገልጋዮቹ
አከፋፈላቸው። 2 ከዚያም ሁለቱን አገልጋዮች ከነልጆቻቸው አስቀደመ፤ ልያንና ልጆቿንም አስከተለ፤ ራሔልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉ ኋላ እንዲሆኑ አደረገ። 3
እርሱ ራሱም ቀድሞአቸው ሄደ፤ ወንድሙም ዘንድ እስኪደርስ ድረስ ሰባት ጊዜ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ። 4 ዔሳው ግን ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጦ ሄዶ
አቀፈው፤ በአንገቱም ላይ ተጠምጥሞ ሳመው፤ ሁለቱም ተላቀሱ። 5 ከዚያም ዔሳው ቀና ብሎ ሲመለከት ሴቶቹንና ልጆቹን ዐየ፤ እርሱም፣ “እነዚህ አብረውህ
ያሉ እነማን ናቸው?” ብሎ ጠየቀው። ያዕቆብም መልሶ፣ “እነዚህማ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው” አለው። 6 በዚህ ጊዜ
ሁለቱ ሴት አገልጋዮችና ልጆቻቸው ቀርበው እጅ ነሡ፤ 7 ከዚያም ልያና ልጆቿ መጥተው እጅ ነሡ፤ በመጨረሻም ዮሴፍና ራሔል መጡ፤ እነርሱም ቀርበው እጅ
ነሡ። 8 ዔሳውም፣ “ወደ እኔ ተነድቶ የመጣው ይህ ሁሉ መንጋ ምንድነው?” አለው። ያዕቆብም፣ “ጌታዬ ሆይ፣ በአንተ ዘንድ ሞገስ ባገኝ ብዬ ነው” አለው። 9
ዔሳው ግን፣ “ወንድሜ ሆይ፤ እኔ በቂ አለኝ፤ የራስህን ለራስህ አድርገው” አለው። 10 ያዕቆብም፣ “የለም፣ እንዲህ አይደለም፤ በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ
እንደሆነ፣ እጅ መንሻዬን ተቀበል፤ በመልካም ሁኔታ ተቀብለኸኝ ፊትህን ማየት መቻሌ ራሱ፣ የእግዚአብሔርን ፊት የማየት ያህል እቆጥረዋለሁ። 11
እግዚአብሔር በቸርነቱ አሟልቶ ስለ ሰጠኝ የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝና ያቀረብሁልህን እጅ መንሻ እባክህ ተቀበለኝ” አለው። ያዕቆብ አጥብቆ ስለለመነው፣
ዔሳው እጅ መንሻውን ተቀበለ። 12 ዔሳውም፣ “እንግዲህ እንሂድ፤ እኔም ከአንተ ቀድሜ እሄዳለሁ” አለው። 13 ያዕቆብ ግን እንዲህ አለው፤ “ጌታዬ
እንደምታየው ልጆቹ ይህን ያህል የጠኑ አይደሉም፣ ለሚያጠቡት በጎችና ጥገቶች እንክብካቤ ማድረግ አለብኝ፤ እንስሳቱ ለአንዲት ቀን እንኳ በጥድፊያ ቢነዱ
በሙሉ ያልቃሉ። 14 ስለዚህ ጌታዬ፣ አንተ ቀድመኸኝ ሂድ፤ እኔም በምነዳቸው እንስሳትና በልጆቹ ጉዞ አቅም ልክ እያዘገምሁ ሴይር ላይ እንገናኛለን” 15
ዔሳው፣ “እንግዲያስ ከሰዎቼ ጥቂቶቹን ልተውልህ” አለው። ያዕቆብ ግን፣ “ለምን ብለህ? በአንተ ዘንድ ሞገስ ማግኘቴ ይበቃኛል” አለው። 16 ስለዚህ ዔሳው
በዚሁ ዕለት ወደ ሴይር ለመመለስ ተነሣ። 17 ያዕቆብ ግን ወደ ሱኮት ሄደ፤ እዚያም ለራሱ መጠለያ፣ ለከብቶቹም በረት ሠራ፤ ከዚህም የተነሣ የቦታው ስም
ሱኮት ተባለ። 18 ያዕቆብ ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ በከነዓን ምድር ወዳለችው ወደ ሴኬም በሰላም ደረሰ፤ በከተማይቱም ፊት ለፊት ሰፈረ። 19 ድንኳኑን
የተከለበትንም ቦታ የሴኬም አባት ከነበረው ከኤሞር በመቶ ጥሬ ብር ገዛው፤ 20 በዚያም መሠዊያ አቁሞ፤ ኤል ኤሎሄ እስራኤል ብሎ ጠራው።

Genesis 33:1

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ለሚያስደንቀው ለታሪኩ አድስ ክፍል ትኩረት እንዲንስጥ ያደርጋል

አራት መቶ ሰዎች
400 ሰዎች (ቁጥሮች ይመልከቱ)

ያዕቆብ ልጆቹን ..... ለሴት አገልጋዮች አከፋፈላቸው
ይህ እያንዳንዷ ሴት ተመሣሣይ ቁጥር ልጆች እንዲኖራት ያዕቆብ ልጆቹን አከፈላቸው ማለት አይደለም እያንዳንዱ ልጅ ከእናቱ ወይም ከእናትዋ ጋር የሆን ዘንድ ያዕቆብ ለጆቹን አከፋፈላቸው (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሴት አገልጋዮች
“አገልጋይ ሚስቶች” ዘለፋንና ባላን ያመለክታል

እርሱ ራሱ ቀድሞአቸው ሄደ
እዚህ ራሱ የሚለው ያዕቆብ ራሱ በሌሎች ፊት ቀድሞ እንደሄደ ትኩረት ይሰጣል (ተጣቃሽ ተውላጤ ስም ይመልከቱ)

ጐንበስ ብሎ እጅ ነሣ
ጐንበስ ማለት አንድን ሰው በትህትና መቀበልንና ማክበርን ይገልጻል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 33:4

ሊገናኘው
ያዕቆብን ሊገናኝ

ዐቀፈው በአንገቱም ላይ ተጠምጥሞ ሳመው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ዔሣው በያዕቆብ ላይ እጆቹን ጠምጥሞ አቀፈው እናም ሳመው”

ከዚያም ሁለቱ አለቀሱ
ይህ በግልጽ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ከዚያም እንደገና በመተያየታቸው ተደስተው ዔሣው ያዕቆብ አለቀሱ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሴቶቹንና ልጆቹን አየ
ከያዕቆብ ጋር ያሉ ሴቶቹንና ልጆቹን አየ

እነዚህማ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው
የአንተ አገልጋይ የሚለው ሀረግ ያዕቆብ ራሱን በትህትና ያቀረበው መንገድ ነው:: አት: “እነዚህ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለአገልጋይህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 33:6

አገልጋይ ሴቶች
ሴት አገልጋዮች። ባላንና ዘለፋን ያመለክታል።

ጐንበስ አለ
በሌላ ሰው ፊት ትህትናንና አክብሮትን የሚያሳይ ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ወደ እኔ ተነድቶ የመጣው ይህ ሁሉ መንጋ ምንድን ነው?
“ይህ ሁሉ” የሚለው ሀረግ ያዕቆብ በየቡድኑ በባሪያዎች ለዔሣው የላከውን ስጦታዎች ያመለክታል:: አት: “እነኛ የተለያዩ ቡድኖች ሁሉ እንዲገናኙኝ ለምን ላክሃቸው?”

በጌታዬ ፊት ሞገስ ባገኝ ብዬ ነው
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማረጋገጥ የሚል ትረጉም የያዘ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው እንዲሁም ደግሞ ፊት ፍርድን ወይም ግማገማን ይወክላል አት አንተ ጌታዬ እንዲትደሰትብኝ ነው (ፈሊጣዊና ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ጌታዬ
ጌታዬ ዔሣው በትህት መንገድ ዔሣው የተገለጸበት ነው:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 33:9

እኔ በቂ አለኝ
እንስሳት ወይም ንብረት የታወቁ ቃላት ናቸው:: አት: “በቂ እንስሳት አለኝ ወይም በቂ ንብረት አለኝ” (ድብቅ አገላለጽ ይመልከቱ)

በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ሰለማኘት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው እዚህ ዓይን የማየት ምትክ ቃል ሲሆን ማየት ግምገማውን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው:: አት: “በእኔ የተደሰትህ እንደሆነ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እጅ መንሻዬ
“እጅ” ያዕቆብን ያመለክታል አት ይህ ለአንተ የሚሰጠው እጅ መንሻዬ ነው (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በውኑ እጅ መንሻዬ
እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አት: “በእርግጥም እጅ መንሻዬ”

የእግዚአብሔርን ፊት እንደሚያይ ፊትህን አይቼአለሁና
ይህ ተመሣሣይ አባባል ግልጽ አይደለም ተገቢ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው 1 እግዚአብሔር ይቅር እንዳለለት ዔሣውም ይቅር እንዳለው ያዕቆብ ደስተኛ ነው ወይም 2 ያዕቆብ እግዚአብሔርን በመገናኘቱ እንደተደነቀው ሁሉ ዔሳውን በመገናኘቱ ተደንቆአል 3 ያዕቆብ በእግዚአብሔር መገኘት ራሱን እንዳዋረደው ሁሉ በዔሣው ፊት ራሱን ያዋርዳል (ተመሣሣይ አባባሎችን ይመልከቱ)

ፊትህን አይቻለሁ
እዚህ ፊት ዔሣውን ያመለክታል ይህ ፊት በመባል ሊተረጐም ይችላል፤ ምክንያቱም “ፊት” የሚለው ቃል በዘፍጥረት 32:30 “የእግዚአብሔር ፊት” እና “ፊት ለፊት” ለመግለጽ ተጠቅሞአል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ይህችንም ያመጣሁልህ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ይህም አገልጋዮቼ ያመጡልህ” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በቸርነቱ አሟልቶ ስለሰጠኝ
እግዚአብሔር በቸርነቱ ስለመለከተኝ ወይም እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለባረከኝ

ያዕቆብም አጥብቆ ስለለመነው ዔሣው እጅ መንሻውን ተቀበለ
አንድን ሥጦታ ላለመቀበል መገዳደር ነገር ግን ከዚያ በኋላ ሰጪው እንዳያዝን መቀበል የተለመደ ባህላዊ መንገድ ነው

Genesis 33:12

ጌታዬ ያውቃል
ይህ በትህትናና በመደበኛ መንገድ ዔሣውን ማመልከት ነው:: አት: “አንተ ጌታዬ ታውቃለህ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ልጆች የጠኑ አይደሉም
ትርጉሙም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት: “በፍጥነት ለመጓዝ ልጆች ገና የጠኑ አይደሉም”:: (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)

አንዲት ቀን እንኳ በጥድፍያ ቢነዱ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ለአንድ ቀን እንኳ በፍጥነት እንዲጓዙ ቢናጣድፋቸው” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ጌታዬ ከባሪያው ቀድሞ ይሂድ
ይህ ያዕቆብ ራሱን በመደበኛና በትህትና መንገድ የሚገልጸው ነው:: አት: “ጌታዬ እኔ ባሪያህ ነኝ” (ከፊቴ ቀድመህ ሂድ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በሚነዱአቸው እንስሳት እርምጃ ልክ
“በሚነዱአቸው እንስባት እርምጃ ፍጥነት መጠን”

ሴይር
በኤዶም ግዛት የሚገኝ ተራራማ ሥፍራ ነው። በዘፍጥረት 32 3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 33:15

ለምንድር ነው?
ዔሣው ሰዎቹን መተው እንደሌለበት ለማጽናት ያዕቆብ ጥያቄን ይጠቀማል:: አት: “ይህን አታድርገው” ወይም “ይህን ማድረግ አይገባህም” (አግናኝ ጥያቄዎች ይመልከቱ)

ጌታዬ
ይህ በመደበኛና በትህትና ዔሣውን የሚገለጽ ነው:: አት: “አንተ ጌታዬ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ሱኮት
ተርጓሚዎች እንደግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ ሱኮት የሚለው ስም መጠለያዎች ማለት ነው ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ

ለራሱ ቤትን ወይም መጠለያን ሠራ
ይህ የተሠራው ቤት ለቤተሰቡም እንደሆነ ያመለክታል። አት: “ለራሱና ለቤተሰቡ ቤት ሠራ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ለመንጋው
ለሚጠብቁአቸው እንስሳት

Genesis 33:18

አጠቃላይ መረጃ
ይህ አድስ የታሪኩን አካል ይጀምራል በሱኮት ካረፈ በኋላ ያዕቆብ ምን እንዳደረገ ጸሓፊው ይገልጻል

ያዕቆብ ወደ ጳዳን አራም በመጣ ጊዜ
ያዕቆብ ..... ደረሰ ..... ሠፈረ

ይህ ያዕቆብ የቤሰቡ መሪ ስለሆነ እርሱን ብቻ ይጠቅሳል::
የእርሱም ቤተሰብ ከእርሱ ጋር እንደነበር ግልጽ ነው (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አጠገብ ሠፈረ
በቅርበት ሠፈረ

ከፊል መሬት
ከፊል ቦታ

ኤሞር
የአንድ ሰው ስም ነው

የሴኬም አባት
ሴኬም የሰውዬውና የከተማይቱ ስም ነው

አንድ መቶ
100 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ኤል ኤሎሄ እስራኤል
ተርጓሚዎች የግርጌ ማስታወሻ እንደሚከተለው ሊጨምሩ ይችላሉ አት ኤል ኤሎሄ የሚለው ቃል እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Chapter 34

1 ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ሴት ልጅ ዲና፤ አንድ ቀን የዚያን አገር ሴቶች ለማየት ወጣች። 2 የአገሩ ገዥ የኤዊያዊ የኤሞር ልጅ ሴኬም ባያት ጊዜ ያዛት
በማስገደድም ክብረ ንጽሕናዋን ደፈረ። 3 ልቡ በያዕቆብ ልጅ በዲና ተማረከ፤ ልጅቷንም በጣም ወደዳት፤ በጣፈጠም አንደበት አናገራት። 4 ሴኬምም አባቱን
ኤሞርን፣ “ይህችን ልጅ አጋባኝ” አለው። 5 ያዕቆብ የልጁን የዲናን ክብረ-ንጽሕና ሴኬም እንደደፈረ ሰማ፤ ነገር ግን ወንዶች ልጆቹ የከብት መንጋ ይዘው
ተሰማርተው ስለነበር፣ እነርሱ እስኪመጡ ዝም ብሎ ቆየ፤ 6 ከዚያም የሴኬም አባት ኤሞር፣ ያዕቆብን ሊያነጋግረው ወጣ። 7 የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም
የተፈጸመውን ድርጊት እንደሰሙ ወዲያውኑ ከመስክ መጡ፤ ሴኬም መደረግ የማይገባውን አስነዋሪ ነገር በእስራኤል ላይ በመፈጸም የያዕቆብን ልጅ ስለደፈረ
አዘኑ እጅግም ተቆጡ። 8 ኤሞር ግን እንዲህ አላቸው፤ “ልጄ ሴኬም ልጃችሁን በጣም ወዶአታል፤ ስለዚህ እንዲያገባት ፍቀዱለት፤ 9 በጋብቻ እንተሳሰር፣ ሴት
ልጃችህን ስጡን፣ የእኛንም ሴቶች አግቡ። 10 አብራችሁንም መኖት ትችላላችሁ፤ አገራችን አገራችሁ ናት፣ ኑሩባት፤ ነግዱባት፣ ሀብት ንብረትም አፍሩባት። 11
ሴኬም ደግሞ የዲናን አባትን ወንድሞች እንዲህ አላቸው። “በእናንተ ዘንድ ሞገስ ላግኝ እንጂ የተጠየቅሁትን ሁሉ እሰጣለሁ፤ 12 ለሙሽራዋም ጥሎሽ
የፈለጋችሁትን ያህል ጠይቁኝ፤ እርሷን እንዳገባ ፍቀዱልኝ እንጂ፣ የፈለጋችሁትን ሁሉ ለመጠት ዝግጁ ነኝ።” 13 ሴኬም እኅታቸውን ዲናን አስነውሮ ስለነበር
የያዕቆብ ልጆች ለእርሱና ለአባቱ በተንኮል እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፣ 14 እንዲህ አሉአቸው፤ “እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው ብንሰጥ ውርደት ስለሚሆንብን፣
እንዲህ ያለውን ነገር አናደርገውም። 15 ሆኖም የምንስማማበት አንድ መንገድ ብቻ አለ፤ ይኸውም አንተና በእናንተ ዘንድ ያሉት ወንዶች ሁሉ እንደኛ የተገረዛችሁ
እንደሆነ ነው። 16 እንዲህ ከሆነ እናንተ የእኛን ሴቶች ልጆች ታገባላችሁ፣ እኛም የእናንተን ሴቶች ልጆች እናገባለን፣ አንድ ሕዝብ ሆነንም አብረን እንኖራለን። 17
ዐሳባችንን ባትቀበሉና ባትገረዙ ግን እኅታችንን ይዘን እንሄዳለን። 18 ያቀረቡትም ዐሳብ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም መልካም መስሎ ታያቸው። 19 ከአባቱ
ቤተሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው ይህ ወጣት የያዕቆብን ልጅ እጅግ ወዶአት ስለነበር፣ ያሉትን ለማድረግ ጊዜ አልወሰደበትም። 20 ስለዚህ ኤሞርና ልጁ ሴኬም
ይህንኑ ለወገኖቻቸው ለመንገር ወደ ከተማቸው በር ሄዱ፤ 21 እንዲህም አሏቸው፤ “እነዚህ ሰዎች ከእኛ ጋር የሚኖሩት በሰላም ነው፣ በምድሪቱ ላይ አብረው
ይቀመጡ፣ ተዘዋውረውም እንዲነግዱ እንፍቀድላቸው፤ ምድሪቱ እንደሆን ለእኛም ለእነርሱም ትበቃለች። ሴቶች ልጆቻቸውን እናገባለን፤ እነርሱም የእኛን ሴቶች
ልጆች ያገባሉ፤ 22 ሆኖም ሰዎቹ ከእኛ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው አብረውን ለምኖር ፈቃደኞች የሚሆኑት፣ የእኛ ወንዶች እንደ እነርሱ የተገረዙ እንደሆነ ብቻ
ነው። 23 ታዲያ እንዲህ ብናደርግ ከብታቸው ንብረታቸው፣ እንስሶቻቸውም ሁሉ የእኛው ይሆኑ የለምን? ስለዚህ ባሉት እንስማማ፣ እነርሱም አብረውን ይኑሩ።”
24 የከተማይቱ ነዋሪዎች ሁሉ ኤሞርና ሴኬም ባቀረቡት ዐሳብ ተስማምተው ወንዶቹ ሁሉ ተገረዙ። 25 በሦስተኛውም ቀን የሁሉም ቁስል ገና ትኩስ ሳለ
ከያዕቆብ ልጆች ሁለቱ፣ የዲና ወንድሞች ስምዓንና ሌዊ፣ ሰይፋቸውን መዘው ሳይታሰብ ወደ ከተማይቱ ገብተው ወንዶቹን በሙሉ ገደሏቸው። 26 ኤሞርንና
ሴኬምንም በሰይፍ ገድለው፣ እኅታቸውን ዲናን ከሴኬም ቤት አውጥተው ይዘዋት ተመለሱ። 27 የቀሩትም የያዕቆብ ልጆች እኅታቸውን ስለደፈሩባቸው ወደ
ሞቱት ሰዎች ቤት እየገቡ ከተማይቱን በሙሉ ዘረፉ። 28 የበግና የፍየል መንጎቻቸውን፣ ከብቶቻቸውንና አህዮቻቸውን እንዲሁም በከተማይቱና በአካባቢው
የሚገኘውን ንብረታቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፤ 29 ሀብታቸውን ሁሉ ዘርፈው ሴቶቻቸውንና ሕፃናቶቻቸውን ሁሉ ማርከው በየቤቱ ያገኙትን ሁሉ ይዘው ሄዱ። 30
ያዕቆብ ስምዖንና ሌዊን እንዲህ አላቸው፤ “በእኔ ላይ ከባድ ችግር አመጣችሁብኝ፤ እነሆ፣ በዚህ ድርጊት የተነሣ በዚህች ምድር የሚኖሩ ከነዓናውያንና
ፌርዛውያን ይጠሉኛል፤ እኛ በቁጥር አነስተኞች ነን፣ እነርሱ ተባብረው ቢያጠቁን እኔና ቤተሰቤ እንጠፋለን።” 31 ስምዖንና ሌዊ ግን፣ “ታዲያ ሴኬም እኅታችንን
እንደዝሙት አዳሪ ይድፈራትን?” አሉት።

Genesis 34:1

አሁንም
በዚህ ይህ ቃል የታሪኩን አድስ ክፍል ለማመልከት ተጠቅሞአል።

ዲና
የልያ ሴት ልጅ ነች በዘፍጥረት 30:21 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኤዊያዊ
ይህ የብሔር ስም ነው:: በዘፍጥረት 10:17 ኤዊያዊያን የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የአገሩ ገዢ
ይህ ሴኬምን ሳይሆን ኤምርን ያመለክታል በዚህ ቦታ ገዢ የንጉሥ ልጅ ማለት አይደለም ይህም ኤሞር በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች መሪ እንደነበር ነው

አስነወራት ከእርስዋም ጋር ተኛ
ሴኬም ዲናን ደፈራት (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል ወይም በተዘዋዋሪ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ ዲና ተሳበ
“በዲና ተማረከ” ዲናን እንደወደዳትና ከእርስዋ ጋር ለመሆን አንድ ነገር ወደ ዲና እንዲመጣ እንዳስገደደው ስለ ሴኬም ይናገራል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ከዲና ጋር ለመሆን እጅግ በጣም ፈልጐአል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በጣፈጠ አንደበት አናገራት
እንደሚወዳትና እንዲትወደው ለማድረግ ሊያሳምናት በሚስብ መንገድ አናገራት ማለት ነው

Genesis 34:4

አሁንም ያዕቆብ
“አሁን” የተጠቀመው ከታሪኩ ወደ ያዕቆብ ዳራ መረጃ ለውጥ ማድረግን ለማመልከት ነው

ያዕቆብም ... እርሱ ... ሰማ
“እርሱ” የሚለው ቃል ሴኬምን ያመለክታል

አስነወራት
ሰኬም በጉልበት ከእርስዋ ጋር በመተኛት ዲናን እጅግ በጣም አዋረዳት ክብርዋን ነፈጋት ማለት ነው

ታግሶ ቆዬ
ያዕቆብ ስለ ጉዳዩ ምንም አላደረገም ወይም አልተናገረም ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 34:6

ኤሞር ያዕቆብን ሊያነጋግረው ወጣ
ኤሞር ያዕቆብን ሊያነግረው ሄደ

የያዕቆብ ወንዶች ልጆች አዘኑ
ወንዶች ልጆች እጅግም ተቆጡ ወይም ደነገጡ

እስራኤልን አስነወረ
እዚህ እስራኤል የሚለው ቃል እያንዳንዱን የእስራኤል ቤተሰብ አባል ያመለክታል እስራኤል እንደብሔር ተደፍሮአል:: አት: “የእስራኤልን ቤት አዋርዶአል” ወይም “የእስራኤልን ሰዎች አሳፍሮአል” (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘጥቤ ይመልከቱ)

የያዕቆብን ሴት ልጅ ስለደፈረ
የያዕቆብን ልጅ ስለደፈራት

ይህ ዓይነት ተግባር መደረግ አይገባውም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እንደዚህ አስነዋሪ ነገር ማድረግ አይገባውም ነበር” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 34:8

ኤሞርም እንዲህ ብሎ ነገራቸው
ኤሞር ለያዕቆብና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ነገራቸው

በልጃችሁ ፍቅር ተነድፎአል
ፍቅር የሚለው ቃል በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚሆን ስሜታዊ ፍቅር ነው አት ወድዶአታልና ሊያገባት ይፈልጋል

ሚስት እንዲትሆነው እርሷን ስጡት
በአንዳንድ ባህሎች ልጆች ማግባት ያለባቸውን ወላጆች ይወስናሉ

በጋብቻ እንተሳሰር
በጋብቻ መተሣሠር ከሌላ ዘር ብሔር ባህልና ጐሣ ሰዎች ጋር መጋባት ማለት ነው:: አት: “በእናንተና በእኛ ሰዎች መጋባትን እንፍቀድ”

ምድሪቱ በእናንተ ፊት ናት
ምድሪቱ የእናንም ናት

Genesis 34:11

ሴኬም ደግሞ አባትዋን እንዲህ አለ
ሴኬም የዲናን አባት ያዕቆብን እንዲህ አለ

በእናንት ፊት ሞገስ ላግኝ እንጂ የጠየቅሁትን ሁሉ እሰጣለሁ
“ሞገስ ማግኘት” የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማረጋገጥ የሚናገር ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ደግሞም ዓይኖች ማየትን ሲወክሉ ማየት ሀሳብን ወይም ፍረጃን ያመለክታሉ:: አት: “እንደተቀበላችሁን ካረጋገጥሁ የሚትጠይቁኝን ሁሉ እሰጣለሁ”:: (ፈሊጣዊና ዜይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ጥሎሽ
በአንዳንድ ባህሎች በጋብቻ ጊዜ ለሙሽሪቱ ቤተሰብ ሙሽራው በገንዘብ በንብረት በእንስሳትና በሌላም መልክ ስጦታ መስጠት የተለመደ ነው

የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም ለሴኬምና ለኤሞር የሚያታልል መልስ ሰጡ
ማታለል የሚለው ረቂቅ ስም መዋሸት እንደሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: ነገር ግን የያዕቆብ ወንዶች ልጆች ለሴኬምና ለኤሞር በመለሱአቸው ጊዜ ዋሹአቸው (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)

ሴኬም ዲናን አስነውሮአታል
ከእርሱ ጋር እንዲትተኛ በመድፈሩ ሴኬም ዲናን እጅግ በጣም አዋርዶአታል አስነውሮአታል ማለት ነው:: በዘፍጥረት 34:5 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

Genesis 34:14

እነርሱም እንዲህ አሉአቸው
የያዕቆብ ወንድ ልጆች ለሴኬምና ለኤሞር እንዲህ አሉ

እኅታችንን ብንሰጥ እንዲህ ያለውን ነገር አናደርገውም
ዲናን በጋብቻ ሊንሰጥ አንስማማም

ይህም ለእኛ ውርደት ነው
ይህም እኛን ያሳፍረናል:: እዚህ “እኛ” የያዕቆብን ወንዶች ልጆችንና የእስራኤልን ልጆች በአጠቃላይ ያመለክታል (የሚያካትትና የማያካትት እኛን ይመልከቱ)

ሴቶች ልጆቻችንን እንሰጣችኋለን የእናንተን ሴቶች ልጆች እንወስዳለን
ይህም ከያዕቆብ ቤተሰብ የሆነ ሰው በኤሞር ምድር የሚኖረውን ሰው ያገባል ማለት ነው

Genesis 34:18

ያቀረቡትም ሃሳብ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም መልካም መስሎ ታየቸው
ኤሞርና ልጁ ሴኬም የያዕቆብ ወንዶች ልጆች ባቀረቡት ሃሳብ ተስማሙ

ያሉትን ለማድረግ
ለመገረዝ

የያዕቆብ ሴት ልጅ
የያዕቆብ ሴት ልጅ ዲና

ከአባቱ ቤተሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: እጅግ ስለሚያከብሩት ሌሎች ሰዎች ለመገረዝ እንደሚስማሙ ሴኬም እንደተረዳ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “እርሱ በእነርሱ ዘንድ የተከበረ በመሆኑ የአባቱ ቤተሰብ ወንዶች ሰዎች ሁሉ ለመገረዝ እንደሚስማሙ ሴኬም ያውቅ ነበር” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)::

Genesis 34:20

ወደ ከተማቸው በር
ሕጋዊ ውሳኔ ለመወሰን በከተሞች በር መሰባሰብ በመሪዎች የተለመደ ነው

እነዚህ ሰዎች
ያዕቆብ ወንዶች ልጆቹና የእስራኤል ሰዎች

በእኛ ዘንድ የሰላም ሰዎች
እዚህ “እኛ” ኤሞር ልጁንና የተናገሩአቸው በከተማው በር ያሉ ሰዎችን ሁሉ ያቀፈ ነው (ሁሉን ያቀፈ “እኛ” ይመልከቱ)

በምድራችን ይኑሩ ይነግዱበትም
በምድሪቱ ይኑሩ ይነግዱበትም

እነሆ ምድሪቱ በእርግጥ ሰፊ ናት
ለዐረፍተ ነገሩ ትኩረት ለመስጠት ሴኬም “በእርግጥ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል:: “እነሆ ምድሪቱ በእርግጥ ለእነርሱም ሰፊ ናት” ወይም “እነሆ ለእነርሱ የሚበቃ በቂ መሬት አለ”

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ሴት ልጆቻቸውን እንውሰድ ለእነርሱም ሴት ልጆቻችንን እንስጥ
ይህ በአንዱ ቡድን ሴቶች በሌላው ቡድን ወንዶች መካከል የሚፈጸሙ ጋብቻዎችን ያመለክታል። በዘፍጥረት 34፡9 ተመሣሣይ ሀረጐችን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Genesis 34:22

አጠቃላይ መረጃ
ኤሞርና ልጁ ሴኬም ለከተማዋ ሽማግሌዎች መናገራቸውን ቀጠሉ

አንድ ሕዝብ ሆነን ከእኛ ጋር ይቀመጡ ዘንድ በዚህ ነገር ብቻ እሺ ይሉናል እነርሱ እንደተገረዙ ወንዶቻችንን ሁሉ ብንገርዝ
ሰዎቹ ከእኛ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው አብረውን ለመኖር ፈቃደኞች የሚሆኑት የእኛ ወንዶች እንደ እነርሱ የተገረዙ እንደሆነ ብቻ ነው

ታዲያ እንዲህ ብናደርግ ከብቶቻቸው ንብረታቸው እንስሶቻቸው ሁሉ የእኛው ይሆኑ የለምን?
የያዕቆብ እንስሶችና ንብረቶች ለሴኬም ሰዎች እንደሚሆን ሴኬም ጥያቄ ምልክት በመጠቀም አበክሮ ይናገራል:: ይህ እንደዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “የእነርሱ እንስሳትና ንብረት ሁሉ ለእኛ ይሆናል” አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ::

Genesis 34:24

ወንዶች ሁሉ ተገረዙ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ስለዚህ ኤሞርና ሴኬም ወንዶችን ሁሉ የሚገርዙ ነበሩአቸው (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘበት ዐረፍት ነገር ይመልከቱ)

በሶስተኛውም ቀን
ሶስት ተራ ቁጥር ሶስት ነው:: ያለ ተራ ቁጥር ሊነገር ይችላል:: አት: “ከሁለት ቀን በኋላ”

ሁሉም ቆስለው ሳሉ
የከተማው ወንዶች ቆስለው ሳሉ

እያንዳንዱ ሰይፉን መዝዞ
ሰይፋቸውን መዘው

ከተማዋን ወጉት
ከተማ ሰዎችን ይወክላል አት እነርሱ የከተማይቱን ሰዎች ተዋጉ (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ጥበቃ፤ እናም ወንዶችን ሁሉ ገደሉ
ይህ እንደአዲስ ዐረፍት ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ጥበቃ፡ ስምዖንና ሌዊ የከተማይቱን ወንዶች ሁሉ ገደሉ።”

Genesis 34:27

ሬሳዎች
የኤሞር የሴኬምና ወንዶች ስዎቻቸው ሬሳ

ከተማዋን ዘረፉ
በከተማይቱ ያለውን ጠቃሚ ነገር ሁሉ ወሰዱ

ሰዎች እህታቸውን ስላረከሱአት
ሴኬም ብቻውን ዲናን አርክሶአት ነበር ነገር ግን የያዕቆብ ልጆች የሴኬም መላው ቤተሰብና በከተማው ያለው ሁሉ ሰው ለዚህ ድርጊት ተጠያቂ አድርገው ቆጥረዋል

አረከሳት
ከእርሱ ጋር እንዲትተኛ በመድፈር ሴኬም ዲናን አዋረዳት ወይም ክብርዋን ነፈጋት/አሳፈራት ማለት ነው:: በዘፍጥረት 34: 5 አረከሳት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

መንጎቻቸውን ወሰዱ
የያዕቆብ ልጆች የሰዎችን መንጋ ወሰዱ

ሀብቶቻቸውን ሁሉ
ንብረታቸውንና ገንዘባቸውን ሁሉ ሕጻናቶቻቸውንና ሴቶቻቸውን ሁሉ ማረኩ

Genesis 34:30

አስጨነቃችሁኝ
ለአንድ ሰው የጭንቀት ምክንያት መሆን ጭንቀት በአንድ ሰው ላይ እንደሚመጣና እንደሚቀመጥ ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል አት: “ትልቅ ችግሮችን ፈጥራችሁብኛል” (ዜይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

በዚህ አገር በሚኖሩ ዘንድ እንደጥንብ አስቆጠራችሁኝ
ያዕቆብ በዙሪያው በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ እንዲጠላ ማድረግ የያዕቆብ ልጆች እርሱን እንደ መጥፎ ሽታ እንዳደረጉ ተገልጾአል ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በምድሪቱ በሚኖሩ ዘንድ የተጠላሁ እንዲሆን አድርጋችሁኛል” (ዜይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

እኔ በቁጥር አነስተኞች ነኝ ቢያጠቁኝ እኔንና ቤተሰቤን ያጠፋሉ
እዚህ “እኔ” እና “እኔን” የሚሉ ቃላት ያዕቆብን ቤተሰብ በአጠቃላይ ይወክላሉ:: ያዕቆብ የቤተሰቡ መሪ ከመሆኑ የተነሳ “እኔ” ወይም “እኔን” ይጠቀማል:: አት: “ቤተሰብ አነስተኛ ነው … ተባብረው ቢነሡብኝና ቢያጠቁኝ ሁላችንንም ያጠፋሉ::” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ተባብረ ይነሡና ያጠቁኛል
ሠራዊት ይፈጥሩና ያጠቁኛል ወይም ሠራዊት ይፈጥሩና ያጠቁናል

እኔም እጠፋለሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ያጠፉኛል ወይም ያጠፉናል ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ”

ሴኬም በሴተኛ አዳሪ/በጋለሞታ እንደሚደረግ በእኅታችን ያደርግባትን?
ሴኬም ያደረገው ጥፋትና ሞት እንደሚገባው አበክረው ለመግለጽ ሌዊና ስምዖን ጥያቄ ይጠቀማሉ:: አት: “ሴኬም እህታችንን እንደ ሴተኛ አዳሪ/ ጋለሞታ አድርጐ ባልቆጠረ ነበር!” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Chapter 35

1 እግዚአብሔር ያዕቆብን፣ “ተነሣና ወደ ቤቴል ሂድ፣ እዚያም ኑር። ከወንድምህ ከዔሳው ሸሽተህ በሄድህ ጊዜ ለተገለጠልህ አምላክ በዚያ መሠዊያ ሥራ
አለው። 2 ስለዚህም ያዕቆብ ለቤቱ ሰዎችና አብረውት ለነበሩት ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ “በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልክት አስወግዱ፤ ሰውነታችሁን አንጹ፤
ልብሳችሁንም ለውጡ። 3 ተነሥተን ወደ ቤቴል እንሂድ፤ እዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ በሄድሁበትም ስፍራ ሁሉ ላልተለየኝ አምላክ መሠዊያ እሠራለሁ። 4
ስለዚህ በእነርሱ ዘንድ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት ሰብስበው፣ የጆሮ ጉትቾቻቸውን አውልቀው ለያዕቆብ ሰጡት። ያዕቆብም ወስዶ ሴኬም አጠገብ ካለው
ዋርካ ዛፍ ሥር ቀበራቸው። 5 ያንንም ቦታ ለቀው ሄዱ፤ እግዚአብሔርም በዙሪያቸው በነበሩት ከተሞች ሁሉ ላይ ፍርሃትና ድንጋጤ ስለለቀቀባቸው ያሳደዳቸው
አልነበረም። 6 ያዕቆብና አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ በከነዓን ወደምትገኘው፣ ቤቴል ወደተባለችው ወደ ሎዛ ደረሱ። 7 ያዕቆብም በዚያ ስፍራ መሠዊያ
ሠርቶ፣ ስሙን ኤል ቤቴል አለው፤ ምክንያቱም ከወንድሙ ሸሽቶ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር የተገለጠለት በዚህ ቦታ ነበር። 8 በዚህ ጊዜ የርብቃ ሞግዚት ዲቦራ
ሞተች፣ ከቤቴል ዝቅ ብሎ በሚገኘው የዋርካ ዛፍ ሥር ተቀበረች። ከዚህ የተነሣም ያ ቦታ አሎንባኩት ተባለ። 9 ያዕቆብ ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ
እግዚአብሔር ዳግመኛ ተገለጠለትና ባረከው። 10 እግዚአብሔርም፣ “እስካሁን ስምህ ያዕቆብ ነበር፤ ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም፤ ነገር ግን ስምህ
እስራኤል ይባላል” አለው። ስለዚህም እስራኤል ብሎ ጠራው። 11 ደግሞም እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ አለው፤ “እኔ ሁሉም ማድረግ የሚችል አምላክ
ነኝ፤ ብዙ ልጆች ይኑሩህ፤ ዘርህም ይብዛ፤ የብዙ ሕዝብ አባት ሁን፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወለዱ። 12 ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠኋትን ምድር ለአንተ
እሰጣለሁ፤ ከአንተም በኋላ ይህችን ምድር ለዘርህ አሰጣለሁ።” 13 እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ከዚያ ስፍራ ወደ ላይ ወጣ። 14 ያዕቆብ
እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በተነጋገረበት ስፍራ የድንጋይ ሐውልት አቆመ፣ በሐውልቱ ላይ የመጠጥ ቍርባን አፈሰሰ፤ ዘይትም አፈሰሰበት። 15 ያዕቆብም
እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው። 16 ከዚያም ከቤቴል ተነሥተው ሄዱ፤ ኤፍራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ራሔልን ምጥ
ያዛት፣ ምጡም ጠናባት። 17 ምጧ እየበረታ በሄደ ጊዜ አዋላጅቱ፣ “አይዞሽ አትፍሪ፤ ሌላ ወንድ ልጅ ልትወልጂ ነው” አለቻት። 18 እርስዋ ግን ልትሞት
ታጣጥር ስለነበር ከመሞቷ በፊት ልጅዋን ‘ቤንኦኒ’ አለችው፤ አባቱ ግን ‘ብንያም’ አለው። 19 ራሔል ሞተች፤ ወደ ኤፍራታ በሚወስደው መንገድ በቤተልሔም
ተቀበረች። 20 ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ ሐውልት አቆመ፤ እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ይኸው ሐውልት ነው። 21 ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ
በዔዴር ግንብ ባሻገር ድንኳን ተክሎ ሰፈረ። 22 ያዕቆብ በዚያ ምድር ሲኖር ሳለ፣ ሮቤል ከአባቱ ቁባት ከባላ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት አደረገ፤ ያዕቆብም ይህን
ነገር ሰማ ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት፣ እነርሱም፦ 23 የልያ ልጆች፦ የያዕቆብ የበኩር ልጅ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዛብሎን፤ 24
የራሔል ልጆች፦ ዮሴፍ፣ ብንያም፤ 25 የራሔል አገልጋይ የባላ ልጆች፦ ዳን፣ ንፍታሌም፤ 26 የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆች፦ ጋድ፣ አሴር፣ ናቸው። እነዚህ ወንዶች
ልጆች ያዕቆብ በመስጴጦምያ ሳለ የተወለዱለት ናቸው። 27 ያዕቆብ በቂርያት አርባቅ (በኬብሮን) አጠገብ መምሬ በምትባል ስፍራ ወደሚኖረው አባቱ ወደ
ይስሐቅ ሄደ፤ ይህም ስፍራ አብርሃምና ይስሐቅ የኖሩበት ነው። 28 ይስሐቅ መቶ ሰማንያ ዓመት ኖረ፤ 29 አርጅቶ ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ወደ ወገኖቹ ተሰበሰበ፤
ልጆቹም ዔሳውና ያዕቆብ ቀበሩት።

Genesis 35:1

ወደ ቤተል ውጣ

ውጣ የሚለው ቃል የተጠቀመው ቤቴል ከሴኬም በከፍታ ላይ ስለሚገኝ ነው

በዚያ መሠዊያ ሥራ

እግዚአብሔር ስለራሱ በሶስተኛ ሰው መንገድ ይናገራል:: አት: “ለእኔ ለአምላክህ መሠዊያ ሥራ” (እንደ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው መግለጽን ይመልከቱ)

ለቤቱ ሰዎች እንዲህ አላቸው

ለቤተሰቡ እንዲህ አላቸው

በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልእክት አስወግዱ

“ጣዖታትን አስወግዱ” ወይም “ሐሰተኞች አማልእክትን አስወግዱ”

ራሳችሁን አንጹ ልብሳችሁን ለውጡ

ይህ እግዚአብሔርን ለማምለክ ከመቅረብ በፊት በአካላዊና ሥነምግባራዊ ሕይወት ራስን የማንጻት ልምድ ነበር

ልብሳችሁን ለውጡ

አድስ ልብሶችን መልበስ ወደ እግዚአብሔር ከመቀረባቸው በፊት ራሳቸውን ንጹህ የማድረጋቸው ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በመከራዬ ቀን

በመከራዬ ጊዜ ወይም በጭንቀተ ጊዜ

Genesis 35:4

ስለዚህ ሰጡት

“ሁሉም የያዕቆብ ቤት ሰጠ” ወይም “የያዕቆብ ቤተሰብና አገልጋዮቻቸው ሰጡት”

በእጃቸው ያሉትን

እዚህ “በእጃቸው ያሉት” የእነርሱ የሆኑትን ይወክላል:: አት: “ሀብታቸው የሆኑትን ወይም ያላቸውን” (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የጆሮ ጉትቾቻቸውን

ጉትቾቻቸውን ተገቢ ትርጉሞች እነሆ 1 የጆሮቻቸውን ወርቅ ብዙ ጣዖታትን ሊሠሩ ሊጠቀሙ ይችላሉ 2 እነዚህ ጉትቾች የሴኬም ከተማ ሰዎችን በተዋጉና ሁሉን ሰዎች በገደሉ ጊዜ የበዘበዙአቸው ናቸው:: ጉትቾች ስለኃጢአታቸው የሚያውሱ ይሆናሉና::

በዙሪያው ባሉ ከተሞች ሁሉ እግዚአብሔር ድንጋጤ ለቀቀባቸው

ያዕቆብንና ቤተሰቡን የከተሞች ሰዎች እንዲደነግጡ እግዚአብሔር ያደረገው ድንጋጤ እንደ አንድ ነገር በከተሞች እንደወደቀ ተደርጐ ተገልጾአል:: “ድንጋጤ” የተባለው ረቂቅ ስም እንደ “ፍርሃት” ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እግዚአብሔር በዙሪያው ያሉ የከተሞች ሰዎች ያዕቆብንና በቤተሰቡን እንዲፈሩ አደረገ” ዘይቤያዊ አነጋገርና ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ

በከተሞች ላይ

“ከተሞች” በከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ::

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

የያዕቆብ ወንዶች ልጆች
ከያዕቆብ ቤተሰብ ማንም እንዳልተጠቃ ይገልጻል ነገር ግን የያዕቆብ ሴት ልጅ ከተደፈረች በኋላ ስምዖንና ሌዊ የሴኬምን ከነዓናዊያን ዘመዶችን አጠቁአቸው በዘፍረት 34:30 ያዕቆብ ሊበቀሉ ይፈልጉ ይሆናል ብሎ ፈርቶአል አት የያዕቆብ ቤት ወይም የያዕቆብ ቤተሰብ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 35:6

ሎዛ
ይህ የከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 28 19 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኤል ቤቴል
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ኤል ቤተል የሚለው ስም የቤተል አምላክ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የተገለጠለት በዚህ ቦታ ነበር
እግዚአብሔር ራሱን ለያዕቆብ ያስታወቀበት በዚህ ቦታ ነበር

ዲቦራ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው ስምችን ስለመተርጐም ይመልከቱ

የርብቃ ሞግዚት
ሞግዚት የሌላ ሴት ልጅን የሚትንከባከብ ሴት ማለት ነው ሞግዚት እጅግ የተከበረችና በቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ነች

ከቤተል ዝቅ ብሎ .... ተቀበረች
“ዝቅ ብሎ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው እርስዋ የተቀበረችው ቦታ ከፍታ ከቤተል ዝቅ ብሎ ስለሚገኝ ነው::

አሎንባኩት
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “አሎንባኩት የሚለው ስም ለቅሶ ያለበት ዋርካ ዛፍ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:9

ያዕቆብ ከጳዳን አራም በተመለሰ ጊዜ
በቤተል እንደነበሩ ግልጽ ማድረግ ይቻላል አት ያዕቆብም ከጳዳን አራም ከተመለሰ በኋላ በቤተል በነበረበት ጊዜ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ባረከውም
በረከት ለአንድ ሰው መልካም ነገር እንዲደረግለትና በዚያው ሰው ላይ የረከት ቃል መናገር ነው

ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ስምህ ያዕቆብ አይባልም” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 35:11

እግዚአብሔር እርሱን እንዲህ አለው
እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ አለው

ብዛ ተባዛ
ብዙ ልጆች እንዲኖሩት ያዕቆብ ብዙ ልጆችን እንዲወልድ እግዚአብሔር ተናገረው ብዛ የሚለው እንዴት መባዛት እዳለበት ይገልጻል በዘፍጥረት 1:22 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ድርብ ቃላትና ፈሊጣዊ ንግግር ይመልከቱ)

ሕዝብና የሕዝቦች ማኅበር ከአንተ ይወጣሉ
እዚህ ሕዝብ እና ሕዝቦች የያዕቆብ ዘሮች እነዚህን ሕዝቦች እንደሚመሠርቱ ነው:: (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከእርሱ.... ወደ ላይ ወጣ
ወደ ላይ ወጣ የተጠቀመው ከምድር ከፍ ብሎ እግዚአብሔር እንደምኖር ለመግለጽ ነው:: አት: “እግዚአብሔር ተለየው”

Genesis 35:14

ሐውልት
ይህ በጫፉ መከሎ/ቅርጽ ያለው ትልቅ ድንጋይ ለመታሰቢያነት የቆመ ሐውልት ነው

የመጠጥ መስዋዕትንም በእርሱ ላይ አፈሰሰ ዘይትንም አፈሰሰበት
ይህም ሐውልቱን ለእግዚአብሔር የመሰደስ ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በቴል
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “በቴል የሚለው ስም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:16

ኤፍራታ
ይህ የቤተልሔም ከተማ ሌላው ስም ነው

በከባድ ምጥ ውስጥ ሳለች
ምጡ አስጨንቆአት ሳለ

አዋላጅ
አንድ ሴት ልጅን በሚትወልድበት ጊዜ የሚታግዝ ሴት

ስትሞት ነፍስዋ በሚትወጣበት ጊዜ
“ነፍስ መውጣት” አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የመጨረሻ እስትንፋስ ማለት ነው። አት “ከመሞትዋ በፊት በመጨረሻዋ እስትንፋስ ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ቤንኦኒ
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ቤንኦኒ የምለው ስም የጭንቀቴ ልጅ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ብንያምን
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ብንያምን የምለው ስም የቀኝ እጁ ልጅ ማለት ነው” የቀኝ እጅ የሚለው ሀረግ ልዩ የሚወደድ ቦታ ማለት ነው::

ተቀበረች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “እነርሱ ቀበሩአት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በሚወስድ መንገድ
በሚወስደው መንገድ

እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ይሄው ሐውልት ነው
ይህ እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ነው

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

እስከዛሬ
እስካሁን ጊዜ ይህ ጸሐፊው፤ ይህ መልእክት የጻፈበትን ጊዜ ያመለክታል።

Genesis 35:21

እስራኤልም ጉዞውን በመቀጠል
የእስራኤል ቤተሰብና አገልጋዮቹ ከእርሱ ጋር እንደነበሩ ይገልጻል የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ባላ
የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::

ያዕቆብ አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት
ይህ ዐረፍተ ነገር በሚከተሉት ቁጥሮች የሚቀጥለውን አድስ አንቀጽ ይጀምራል

አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች
12 ወንዶች ልጆች

Genesis 35:23

ባላ
የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:26

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በጳዳን አራም የተወለዱ ነበሩ
ይህ በከነዓን ምድር በቤተልሔም አጠገብ የተወለደውን ብንያምን እንደማያካትት ይናገራል:: አብዛኛዎቹ የተወለዱት በጳዳን አራም ስለሆነ ይህንኑን ይጠቅሳል:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በከነዓን ምድር ከተወለደው ከብንያምን በስተቀር በጳዳን አራም የተወለዱለት” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ያዕቆብ ወደ ይስሐቅ መጣ
መጣ የተባለው ሄዴ በሚለው ሊተካ ይችላል (ሄዴ እና መጣ ይመልከቱ)

መምሬ
የሔብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው የአብርሃም ወዳጆች በኖሩበት በመምሬ ስም ተጠርቶ ይሆናል በዘፍጥረት 13 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቅርያትአርባቅ
ይህ የከተማ ስም ነው በዘፍጥረት 23 2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 35:28

መቶ ሰማንያ ዓመት
180 ዓመት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ይስሐቅም ነፍሱን ሰጠ ሞተም
ይስሐቅም የመጨረሻውን እስትንፋስ ሰጠ ሞተም እንትንፋሱን ሰጠ/ነፍሱን ሰጠ ወይም ሞተ የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ አንድ ትርጉም አላቸው:: በዘፍጥረት 25:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት: “ይሥሐቅም ሞተ” (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ነፍሱን ሰጠ
ይህ አንድ ሰው መሞቱን ትሁትና መንገድ የሚገልጽ ነው:: በዘፍጥረት 25:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ንኅብነት ለዛ ባለ ወይም በተዘዋዋሪ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

ወደ ወገኖቹ ተከማቸ/ተሰበሰበ
ይስሐቅ ከሞተ በኋላ ከዚህ በፊት የሞቱ ወገኖች ነፍስ ወዳለበት ቦታ ነፍሱ ሄደች ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት የሞቱትን የቤተሰብ አባላትን ተቀላቀለ ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ይመልከቱ)

አርጅቶ እድሜ ጠግቦ
አረጅቶ እና እድሜ ጠግቦ የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: አበክረው የሚናገሩት ይስሐቅ ብዙ ዓመታትን እንደኖረ ነው:: አት: “ብዙ ዓመታትን ኖሮ ከአረጀ በኋላ” (ድርብ አባባል ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 36

1 ኤዶም የተባለው የዔሳው የትውልድ ታሪክ የሚከተለው ነው፤ 2 ዔሳው ከነዓናውያን ሴቶችን አገባ፤ እነርሱም የኬጢያዊው የዔሎን ልጅ ዓዳን፣ የኤውያዊው
የፅብዖን ልጅ ዓና የወለዳት አህሊባማ፣ 3 እንዲሁም የነባዮት እኅት የሆነችውን የእስማኤል ልጅ ቤስሞት ነበሩ። 4 ዓዳ ለዔሳው ኤልፋዝን ወለደችለት። 5
እንደዚሁም አህሊባማ የዑስን፣ የዕላምንና ቆሬን ወለደችለት፤ እነዚህ ዔሳው በከነዓን አገር የወለዳቸው ልጆቹ ናቸው። 6 ዔሳው ሚስቶቹንና ወንዶችና ሴቶች
ልጆቹን፣ ቤተ ሰቦቹን በሙሉ እንደዚሁም የቀንድ ከብቶቹንና ሌሎቹንም እንስሳት ሁሉ በከነዓን ምድር ያፈራውን ሀብት እንዳለ ይዞ ከወንድሙ ከያዕቆብ ራቅ
ወዳለ ቦታ ሄደ። 7 ብዙ ሀብት ስለነበራቸው አብረው መኖር አልቻሉም፣ የነበሩበትም ስፍራ ከከብቶቻቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃቸው አልቻለም። 8 ስለዚህ ዔዶም
የተባለው ዔሳው መኖሪያውን በተራራማው አገር በሴይር አደረገ። 9 በተራራማው አገር በሴይር የሚኖሩ የኤዶማውያን አባት፣ የዔሳው ዝርያዎች እነዚህ ናቸው፤
10 የዔሳው ልጆች ስም፦ የዔሳው ሚስት የዓዳ ልጅ ኤልፋዝና የዔሳው ሚስት የቤሴሞት ልጅ ራጉኤል፤ 11 የኤልፋዝ ልጆች፦ ቴማን፣ ኦማር፣ ስፎ፣ ጎቶም
ቄኔዝ፤ 12 የዔሳው ልጅ ኤልፋዝ ትምናዕ የምትባል ቁባት ነበረችው፤ እርሷም አማሌቅን ወለደችለት፤ የዔሳው ሚስት የዓዳ የልጅ ልጆች እነዚህ ናቸው። 13
የራጉኤል ልጆች፦ ናሖት፣ ዛራ፣ ሣማና ሚዛህ፤ እነዚህም ደግሞ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት የልጅ ልጆች ናቸው። 14 የፅብዖን የልጅ ልጅ፤ የዓና ልጅ የዔሳው
ሚስት አህሊባማ ለዔሳው የወለደቻቸው ልጆች፦ የዑስ፣ የዕላማና ቆሬ፤ 15 ከዔሳው ዝርያዎች እነዚህ የነገድ አለቆች ነበሩ፤ የዔሳው የበኩር ልጅ የኤልፋዝ
ልጆች፦ ቴማን፣ ኦማር፣ ስፎ፣ ቄኔዝ 16 ቆሬ፣ ጎቶምና አማሌቅ፤ እነዚህ በኤዶም ምድር ከኤልፋዝ የተገኙ የነገድ አለቆች፣ የዓዳ የልጅ ልጆች ነበሩ። 17 የዔሳው
ልጅ የራጉኤል ልጆች፦ ናሖት፣ ዛራ፣ ሃማና፣ ሚዛህ፤ እነዚህ በኤዶም ምድር ከራጉኤል የተገኙ የነገድ አለቆች፣ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት የልጅ ልጆች ነበሩ። 18
የዔሳው ሚስት የአሕሊባማ ልጆች፦የዑስ፣ የዕላማና ቆሬ፤ እነዚህ ከዓና ልጅ ከዔሳው ሚስት አሕሊባማ የተገኙ የነገድ አለቆች ነበሩ። 19 እነዚህም ኤዶም
የተባለው የዔሳው ልጆችና የነገድ አለቆቻቸው ነበሩ። 20 በኤዶም ምድር ነዋሪዎች የነበሩት የሴይር ልጆች የነበሩ የሖራውያን አለቆች፦ ሎጣን፣ ሦባል፣ ፅብዖን፣
ዓና፣ 21 ዲሶን፣ ኤድርና ዲሳን፤ እነዚህ በኤዶም የነበረው የሴይር ልጆች፣ በሖራውያን የነገድ አለቆች ነበሩ። 22 የሎጣን ልጆች፦ ሖሪና ሔማም የሎጣንም
እኅት ቲምናዕ ትባል ነበር። 23 የሦባል ልጆች፦ ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔባልና ስፎና አውናንም፤ 24 የፅብዖን ልጆች፦ አያና፣ ዓና፤ ይህ ዓና የአባቱን የፅባዖንን
አህዮች ሲጠብቅ፣ የፍልውሃ ምንጮችን በምድረበዳ ያገኘ ሰው ነው። 25 የዓና ልጆች፦ዲሶንና የዓና የሴት ልጅ አህሊባማ፤ 26 የዲሶን ልጆች፦ ሔምዳን፣
ሴስባን፣ ይትራንና ክራን፤ 27 የኤድር ልጆች፦ ቢልሐን፣ ዛዕዋንና ዓቃን፤ 28 የዲሳን ልጆች፦ዑፅና አራን። 29 የሖራውያን የነገድ አለቆች እነዚህ ነበሩ፦ሎጣን፣
ሦባል፣ፅዖን፥ ዓና፣ 30 ዶሶን፣ ኤድርና ዲሳን፤ እነዚህ በሴይር ምድር እንደየነገዳቸው የሖራውያን የነገድ አለቆች ነበሩ። 31 ንጉሥ በእስራኤል ከመንገሡ በፊት፣
በኤዶም የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ነበሩ፦ 32 የቢዖር ልጅ ባላቅ በኤዶም ነግሦ ነበር፤ የከተማውም ስም ዲንሃባ ይባል ነበር። 33 ባላቅ ሲሞት፣ በስፍራውም
የባሶራው የዛራ ልጅ ኢዮባብ ነገሠ። 34 የባሶራው የዛራ ልጅ ኢዮባብ ሲሞት የቴማኒው ሑሳም ነገሠ። 35 ሑሳም ሲሞት፣ የምድያምን ሰዎች በሞዓብ ምድር
ድል ያደረጋቸው የባዳድ ልጅ ሃዳድ በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ዓዊት ይባል ነበር። 36 ሃዳድ ሲሞት፣ የመሥሬቃው ሠምላ በምትኩ ነገሠ። 37 ሠምላ
ሲሞት፣ በወንዙ አጠገብ ያለው የርሆቦቱ ሳኦል በምትኩ ነገሠ። 38 ሳኦል ሲሞት፣ የዓክቦር ልጅ በልሐናን በምትኩ ነገሠ። 39 የዓክቦር ልጅ በልሐናን ሲሞት፣
ሃዳር በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ፋው ይባል ነበር፤ የሚስቱም ስም መሄጣብዔል ሲሆን፣ እርሷም መጥሬድ የወለደቻት የሜዛሃብ ልጅ ነበረች። 40
ከዔሳው የተገኙት የነገድ አለቆች ስም፣ እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው ይህ ነው፦ ቲምናዕ፣ ዓለዋ፣ የቴት፣ 41 አህሊባማ፣ ኤላ፣ ፊኖን፣ 42 ቄኔዝ፣ ቴማን፣
ሚብሳር፣ 43 መግዲኤልና ዒራም፣ እነዚህ በያዙት ምድር እንደየይዞታቸው ከኤዶም የተገኙ የነገድ አለቆች ነበሩ። ይህም ዔሳው የኤዶማውያን አባት ነበር።

Genesis 36:1

የዔሣው ትውልድ ይህ ነው እርሱም ኤዶም ነው

ኤዶም የተባለው የዔሣው ትውልድ ይህ ነው ይህ በዘፍረት 36:1-8 የተጠቀሰውን የዔሣው ትውልድን ያስታውቃል:: አት "ይህ ኤዶም የተባለው የዔሣው ትውልድ ነው" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ዓዳ አህሊባማ

እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስም ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዔሎን ኬጢያዊው

"ዔሎን የኬጥ ትውልድ" ወይም "ዔሎን የኬጥ ልጅ" ይህ የአንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 26:34 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና ... ጽብዖን .... ነባዮት

እነዚህ የመንዶች ሰዎች ስም ናቸው

ኤዋዊ

ይህ ትልቅ ሕዝብ ቡድንን ያመለክታል። በዘፍጥረት 10:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ቤሴሞት

ከዔሣው ሚስቶች የአንዷ ስም ነው:: ዘፍጥረት 26:34 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ነባዮት

ከእስማኤል ወንዶች ልጆች የአንዱ ስም ነው:: ዘፍጥረት 28:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:4

ዓዳ ... ቤሴሞት ... አህሊባማ

እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:2-3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኤልፋዝ ራጉኤል የዑስ የዕላም ቆሬ

እነዚህ የዔሣው ወንድ ልጆት ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:6

በከነዓን ምድር ያፈራውን ሀብት

ይህ በከነዓን ምድር በሚኖርበት ጊዜ የሰበሰበውን ወይም ያፈራውን ሁሉን ነገር ያመለክታል አት በከነዓን ምድር በሚኖርበት ጊዜ ያፈራውን ሀብት (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወዳለ ቦታ ሄደ

ወደ ሌላ ቦታ ሂዶ በዚው ኖረ ማለት ነው:: አት: "በሌላ ቦታ ለመኖር ሄደ" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ሀብቶቻቸው
የዔሣውና የያዕቆብ ሀብቶች

ከከብቶቻቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃቸው አልቻለም
ያዕቆብና ዔሣው ያሉአቸውን ከብቶቻቸውን ለማሠማራት ምድሪቱ በቂ አልነበረችም:: አት “ከብቶቻቸውን ለማሠማራት አልበቃቸውም” ወይም “ለያዕቆብ ከብቶችና ለዔሣው ከብቶች በቂ አልነበረም” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የነበሩበት ሥፍራ
የነበሩበት የሚለው ቃል ወደ አንድ ቦታ የመሄድና በዚያ መኖር ያመለክታል:: አት: “የሄዱበት ሥፍራ ወይም ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 36:9

ይህ የዔሣው ትውልድ ነው
ይህ ዐረፍተ ነገር በዘፍጥረት 36: 9-43 ያለውን የዔሣው ትውልድ ዝርዝር ያስታውቃል (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሴይር ተራራማ አገር
በሴይር ተራራ ኖረዋል ማለት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በተራራማው በሴይር አገር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ኤልፋዝ ... ራጉኤል
እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓዳ ... ቤሴሞት
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:2-3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማን ... ኦማር... ስፎ... ጎቶም... ቄኔዝ
እነዚህ የኤልፋዝ መንዶች ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ትምናዕ
የኤልፋዝ ቁባት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:13

ራጉኤል ... ጽብዖን ... የዑስ ... የዕላም ... ቆሬ
እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4-5 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ናሖት ዛራ ሣማ ሚዛህ
እነዚህ የራጉኤል ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና ... ጽብዮን
የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በሴሞት ... አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36 2 3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:15

ኤልፋዝ
ይህ ከዔሣው ወንዶች ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 36: 4 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማን ... ኦማር ... ስፎ ... ቄኔዝ ... ቆሬ ... ጎቶም ... አማሌቅ
የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓዳ
ከዔሣው ሚስቶች የአንዷ ስም ነው በዘፍጥረት 36: 2-3 ስምዋን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:17

ራጉኤል ... የዑስ ... የዕላም ... ቆሬ
እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4-5 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ናሖት ዛራ ሣማ ሚዛህ
እነዚህ የራጉኤል ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:13 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በኤዶም ምድር
ይህም በኤዶም ምድር ኖረዋል ማለት ነው:: አት: “በኤዶም ምድር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሴሞት ... አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36 :2-3 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 36:2 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:20

ሴይር
ሴይር የሚለው ቃል የአንድ ወንድ ሰውና የአንድ አገር ስም ነው

ሖሪውያን
“ሖሪውያን” የሚለው ቃል የአንድ ሕዝብ ቡድን ስም ነው:: በዘፍረት 14:6 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በምድሪቱ ነዋሪዎች
ኤዶም በተባለው በሴይር የሚኖሩ

ሎጣን ሶባል ጽብዖን ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን
እነዚህ የወንዶች ሰዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቲምናዕ
ይህ የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:23

ሶባል... ጽብዖን
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: በዘፍረት 36:20 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓልዋን ...ማኔሐት... ዔባል... ስፎና አውናም ... አያና ዓና
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:25

ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: በዘፍረት 36: 20-21 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አለህባማ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሔምዳን ኤስባን ይትራንና ክራን ቢልሐን ዛዕዋንና ዓቃን
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:29

ሖሪውያን
የአንድ ሕዝበ ወገን ስም ነው:: በዘፍጥረት 14:6 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሎጣን ሶባል ጽብዖን ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን
እነዚህ የወንድ ስዎች ስሞች ናቸው በዘፍረት 36:20-21 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በሴይር ምድር
ይህም በሴይር ምድር ኖረዋል ማለት ነው:: አት "በሴይር ምድር የኖሩ" (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 36:31

ቢዖር ባላቅ ኢዮባብ ዛራ
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማውም ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: "እርሱ የኖረበት ከተማ ስም" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዲንሃባ ባሶራ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:34

ኢዮባብ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 36 33 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሐሳም ሃዳድ ባዳድ ሠምላ
እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የቴማኒው ምድር ሐሳም
ይህም ሐሳም በቴማኒ ምድር ኖሮአል ማለት ነው:: አት "በቴማኒ ምድር የኖረ ሐሳም" (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ዓዊት ምሥሬቃ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማኒው
ቴማኒ የተባለው ሰው ትውልድ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማው ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: "እርሱ የኖረበት ከተማ ስም" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የመሥሬቃው ሠምላ
ከመሥሬቃ የሆነው ሠምላ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:37

ሠምላ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 36:36 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በወንዙ አጠገብ ያለው የርሆቦቱ ሳኡል በምትኩ ነገሠ
ሳኡል በርሆቦት ይኖር ነበር:: ርሆቦት በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ነው:: ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: "ከዚያም ሳኡል በምትኩ ነገሠ:: እርሱም ከኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ከነበረችው ከርሆቦት ነው (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ርሆቦት ፋዑ
የቦታዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማው ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: "እርሱ የኖረበት ከተማ ስም" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የሜዛሃብ ልጅ መጥሬድ የወለደቻት
እርሷም የሜዛሃብ ልጅ መጥሬት የወለደቻት ነበረች

መሄጣብኤል
የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:40

የነገድ አለቆች
የነገድ መሪዎች

እንደየስማቸው እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው
ነገዳቸውና አገራቸው በአለቆቻው ወይም በመሪዎቻቸው ስም ተሰይሞአል:: አት: "የነገዶቻቸውና የሚኖሩባቸው አገራቸው በመሪዎቻቸው ስም ተሠይሞአል" የእነርሱ ስሞች እነሆ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ቲምናዕ ዓልዋ የቴት አህሊባማ ኤላ ፋኖን ቄኔዝ ቴማን ሚብሳር መግዲኤልና ዒራም
እነዚህ የህዝብ ወገኖች ወይም የነገዶች ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በግዛታቸው ወይም በሠፈሩባቸው ምድር
"በሚኖሩባቸው ቦታዎች" ወይም "በኖሩባቸው ቦታዎች"

ይህም ዔሣው ነው
ይህ የስም ዝርዝር ዔሣው ነው የተባለው ይህ የትውልዱ አጠቃላይ ዝርዝር ነው ማለት ነው:: አት: "ይህ የዔሣው ትውልድ ዝርዝር ነው" (ተዛማጅ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Chapter 37

1 የዕቆብ አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር ተቀመጠ። 2 የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው። ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ፣ ከአባቱ ሚስቶች
ከባላቅና ከዘለፋ ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጎችና ፍየሎች ይጠብቅ ነበር። እርሱም ስለወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ ይዞለት መጣ። 3
እስራኤል ዮሴፍን በስተርጅናው ስለወለደው፣ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር፣ በኅብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብም ሰፋለት። 4 ወንድሞቹም አባታቸው
ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው መሆኑን ሲያዩ ዮሴፍን ጠሉት፤ በቅን አንደበት ሊያናግሩት አልቻሉም። 5 ዮሴፍ ሕልም አለመ፤ ሕልሙንም ለወንድሞቹ
ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት፤ 6 እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ያየሁትን ሕልም ልንገራችሁ አድምጡኝ" 7 'እኛ ሁላችን በእርሻ ውስጥ ነዶ እናስር ነበር፤ የእኔ ነዶ
ተነሣና ቀጥ ብሎ ቆመ፤ የእናንተ ነዶዎች ዙሪያውን ተሰብስበው ለእኔ ነዶ ሰገዱለት'" 8 ወንድሞቹም፣ "ታዲያ በእኛ ላይ ንጉሥ ሆነህ ልትገዛን ታስባለህን?"
ብለው ጠየቁት። ስለ ሕልሙና ስለተናገረው ቃል ከፊት ይልቅ ጠሉት። 9 እንደ ገናም ሌላ ሕልም አለመ፤ ለወንድሞቹም እነሆ፣ ሌላ ሕልም አለምሁ፣ ፀሐይና
ጨረቃ፣ ዐሥራ አንድ ክዋክብትም ሲሰግዱልኝ ዐየሁ" ብሎ ነገራቸው። 10 ይህንኑ ለወንድሞቹ የነገራቸውን ሕልም ለአባቱም በነገረው ጊዜ፣ አባቱ፣ "ይህ ምን
ዐይነት ሕልም ነው? እኔና እናትህ ወንድሞችህም በፊትህ ወደ ምድር ተጎንብሰን በርግጥ ልንሰግድልህ ነው?" ሲል ገሠጸው። 11 ወንድሞቹ ቀኑበት፤ አባቱ ግን
ነገሩን በልቡ ያዘው። 12 አንድ ቀን የዮሴፍ ወንድሞች የአባታቸውን መንጋዎች ይዘው ወደ ሴኬም ተሰማሩ፤ 13 እስራኤልም ዮሴፍን፣ "እንደምታውቀው
ወንድሞችህ መንጎቹን በሴኬም አካባቢ አሰማርተዋል፤ በል ተነሥ፣ ወደ እነርሱ ልላክህ" አለው። ዮሴፍም፣ "እሺ እሄዳለሁ" አለ። 14 አባቱም፣ "በል
እንግዲህ ሄድና የወንድሞችህንና የመንጋዎቹን ደኅንነት አይተህ ንገረኝ" አለው። በዚህ ዓይነት እስራኤል ዮሴፍን ከኬብሮን ሸለቆ ላከው። ዮሴፍም ሴኬም
በደረሰ ጊዜ፣ 15 ሜዳ ላይ ወዲያ ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው አግኝቶት፣ "ምን እየፈለግህ ነው?" ሲል ጠየቀው። 16 ዮሴፍም፣ "ወንድሞቼን እየፈለግኋቸው
ነው፤ መንጎቻቸውን የት እንዳሰማሩ ልትነግረኝ ትችላለህ?" አለው። 17 ሰውዬውም፣ "ከዚህ ሄደዋል፤ ደግሞም 'ወደ ዶታይን እንሂድ' ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ"
አለው። ከዚያም ዮሴፍ ወንድሞቹን ፍለጋ ሄደ፣ በዶታይን አቅራቢያም አገኛቸው። 18 ወንድሞቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቅ ዐዩት፣ ወደ ነበሩበትም
ስፍራ ከመድረሱ በፊት ሊገድሉት ተማከሩ። 19 እነርሱ እንዲህ ተባባሉ፦ "ያ ሕልም አላሚ መጣ፤ 20 ኑ እንግደለውና ከጉድጓዶቹ በአንዱ ውስጥ እንጣለው፤
ከዚያም፣ 'ክፉ አውሬ ነጥቆ በላው' እንላለን፤ እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን።" 21 ሮቤል ግን ይህን ምክር ሲሰማ ከእጃቸው ሊያድነው ፈለገ እንዲህም
አለ፤ "አንግደለው፤ 22 የሰው ደም አታፍስሱ፣ ከምትገድሉት ይልቅ በዚህ በበረሃ ባለው ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት" አላቸው። ሮቤል ይህን ያለው ሕይወቱን
ከእጃቸው አትርፎ ወደ አባቱ ሊመልሰው ዐስቦ ነበር። 23 ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ እንደደረሰ፣ የለበሳትን በኅብረ ቀለማት የጌጠች እጀ ጠባቡን ገፈፉት፤ 24
ይዘውም ወደ ጉድጓድ ጣሉት፤ ጉድጓዱም ውሃ የሌለበት ደረቅ ነበር። 25 ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ፤ አሻግረው ሲመለከቱም ከገለዓድ የሚመጡ
እስማኤላውያን ነጋዴዎች ጓዛቸውን በግመሎች ላይ ጭነው ተመለከቱ። ነጋዴዎቹ ሽቶ፣ በለሳን፣ ከርቤ በግመሎቻቸው ጭነው ወደ ግብፅ የሚወርዱ ነበሩ። 26
ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ "ወንድማችንን መግደልና አሟሟቱን መደበቅ ምን ይጠቅመናል? 27 ከዚህ ይልቅ ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች
እንሽጠው፤ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ አናንሳ። ምንም ቢሆን የሥጋ ወንድማችን ነው" ወንድሞቹም በሃሳቡ ተስማሙ። 28 የምድያም ነጋዴዎች የሆኑ
እስማሴላውያን በዚያ በኩል ያልፉ ነበር፤ ስለዚህ ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጉድጓድ ጎትተው በማውጣት ለእነዚህ እስማኤላውያን በሃያ ብር ሸጡላቸው፣ እነርሱም
ወደ ግብፅ ይዘውት ሄዱ። 29 ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ሲያይ፣ ዮሴፍን በማጣቱ ልብሱን በሐዘን ቀደደ። 30 ወደ ወንድሞቹም ተመልሶ፣ "እነሆ፣ ልጁ
እዚያ የለም! እንግዲህ እኔ ወዴት ብሄድ ይሻለኛል?" አለ። 31 ከዚህ በኋላ አንድ ፍየል አረዱና የዮሴፍን ልብስ በደም ነከሩት። 32 በኅብረ ቀለማት
ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ወደ አባታቸው ወስደው፣ "ይህን ወድቆ አገኘነው፤ የልጅህ እጀ ጠባብ መሆን አለመሆኑን እስቲ እየው" አሉት። 33 እርሱ የልጁ ልብስ
መሆኑን ተረድቶ፣ "ይህማ የልጄ እጀ ጠባብ ነው! ፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፣ በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቆአል" አለ። 34 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ፤
ማቅም ለብሶ ስለ ልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ፤ 35 ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት መጡ፤ እርሱ ግን ሊጽናና አልቻለም፣ "በሐዘን እንደተኮራመትሁ ልጄ
ወዳለበት መቃብር እወርዳለሁ" አለ። ስለ ልጁም አለቀሰ። 36 በዚህ ጊዜ የምድያም ነጋዴዎች ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወስደው፣ ከፈርዖን ሹማምንት አንዱ
ለነበረው ለዘበኞች አለቃ፣ ለጲጥፋራ ሸጡት።

Genesis 37:1

አባቱ በቆየበት አገር በከነዓን ምድር ተቀመጠ

አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር ተቀመጠ

የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው

ይህ ዐረፍተ ነገር በዘፍጥረት 37: 1-50:26 ያለውን የያዕቆብን ትውልድ ያስታውቃል። እዚህ ያዕቆብ መላው በተሰቡን ይወክላል። አት "ይህ የያዕቆብ ቤተሰብ ታሪክ ነው" (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

አሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ

17 ዓመት ዕድሜ

ባላ

ይህ የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29: 29 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዘለፋ

ይህ የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29: 24 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሚስቶች

እነዚህ ሴቶች ልጅ እንዲወልዱ ዘንድ ለያዕቆብ የተሰጡ የልያና የራሔል አገልጋዮች ናቸው

ስለእነርሱ መጥፎ ወሬ

ስለወንድሞቹ መጥፎ ወሬ

Genesis 37:3

አሁንም

ይህ ቃል ታሪኩ ስለ እስራኤልና ዮሴፍ ዳራ መረጃ መቀየሩን የሚያመለክት ነው (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ስለወደደው
ይህ ወንድማማች ፍቅር ወይም ጓደኛ ፍቅር ወይም ቤተሰብ ፍቅር ያመለክታል ይህ በጓደኞችና በቤተሰብ መካከል የሚገለጽ ተፈጥሮአዊ የሰው ልጅ ፍቅር ነው

በስተርጅናው
እስራኤል በአረጀ ጊዜ ዮሴፍን ወልዶአል ማለት ነው:: አት: “እስራኤል በአረጀ ጊዜ የተወለደው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እርሱ ለእርሱ ......አደረገለት
እስራኤል ለዮሴፍ ..አደረገለት

በኅብረቀለማት ያገጤ እጁ ጠባብ
እጅግ የሚያምር እጁ ጠባብ

በቅን እንደበት ሊያናግሩት አልቻሉም
በሰላም ሊያናግሩት ዘንድ አልቻሉም

Genesis 37:5

ዮሴፍም ሕልምን አለመ ሕልሙንም ለወንድሞቹ ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት
ይህ በዘፍጥረት 37:6-11 የተቀመጠው ታሪክ ማጠቃለያ ሀሳብ ነው::

የበለጠውኑ ጠሉት
የዮሴፍ ወንድሞች ከዚህ በፊት ከሚጠሉት በላይ ጠሉት

ያየሁትን ይህን ሕልም ልንገራችሁ አድምጡኝ
ሕልሜን ልንገራችሁ አድምጡኝ

Genesis 37:7

አጠቃላይ መረጃ
ስለሕልሙ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ይናገራል

እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስደናቂ ሃሳብ ትኩረት እንዲሰጠው ያነቃል

እኛ ሁላችን
“እኛ” የሚለው ቃል ዮሴፍና ወንድሞቹን ሁሉ ያጠቃልላል (ሁሉን ያቀፈ እኛ ይመልከቱ)

ነዶ እናሥር ነበር
እህል ከታጨደ በኋላ ፍሬው ከገለባው እስኪበጠር ድረስ በየነዶው ታሥሮና ተከምሮ ይጠበቃል

እንሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል ዮሴፍ ባየው እንደተደነቀ ይገልጻል

የእኔ ነዶ በድንገት ተነሥታ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተ ነዶዎች ዙሪያዋን ከበው ለእኔ ነዶ ሰገዱላት
እዚህ እንደሰው ነዶዎች ሲቆሙና ሲሰግዱ ይታያል እነዚህ ነዶዎች ዮሴፍንና ወንድሞቹን ይወክላሉ (በሰውኛ መንገድ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በላያችን ልትነግሥብን ይሆን? ልትገዛ ይሆን?
እነዚህ ሁለቱም ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የዮሴፍ ወንድሞች ጥያቄዎችን በመጠቀም ዮሴፍን ማላገድ ጀመሩ እነዚህ በዐረፍተ ነገሮች መልክ ሊገለጹ ይችላሉ አት ንጉሣችን አትሆንም እኛም ለአንተ እንሠግድም (አግናኝ ጥያቄዎችንና ተዛማጅ ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)

እኛን ልትገዛ
እኛ የሚለው ቃል ዮሴፍን ሳይሆን ወንድሞቹን ያመለክታል (ሁሉን አቀፍና ሁሉን የማያቅፍ “እኛ” ይመልከቱ)

ለሕልሙና ለተናገረው ቃል
ስለ ሕልሙና ልሰተናገረው ቃል

Genesis 37:9

ሌላ ሕልም አለመ
ዮሴፍ ሌላ ሕልም አለመ

አሥራ አንድ ከዋክብት
11 ከዋክብት ቁጥሮች ይመልከቱ

አባቱ ገሠጸው እንዲህም አለው
እስራኤልም ገሠጸው አለውም

ይህ ያየሄው ሕልም ምንድን ነው? እኔና እናትህ ወደ ምድር ተጐንብሰን ልንሰግድል ነው?
እስራኤል ዮሴፍን ለማረም ጥያቄዎችን ይጠቀማል:: ይህ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል:: አት: “ይህ ያየሄው ሕልም ትክክል አይደለም:: እኔ እናትህና ወንድሞችህ በፊትህ አንሰግድልህም!” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ቀኑበት
አንድ ሰው ስኬታማና እጅግ ታዋቂ ከመሆኑ የተነሣ በቁጣ መሞላት ማለት ነው

ነገሩን በልቡ ያዘው
ስለዮሴፍ ሕልም ትርጉም ማሰቡን ቀጠለ ማለት ነው:: አት: “የሕልሙ ትርጉም ምን እንደሆን ማሰቡን ቀጠለ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 37:12

ወንድሞችህ በሰኬም በጎችን ይጠብቁ አይደለምን?
እስራኤል በንግግሩ ውስጥ ጥያቄ ይጠቀማል:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወንድሞችህ በሰኬም በጎችን ይጠብቃሉ” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ና
ለመሄድና ወንድሞቹን ለማየት ዮሴፍ እንዲዘጋጅ እስራኤል መጠየቁን የሚገልጽ ነው:: አት “ተዘጋጅ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እነሆኝ
ለመሄድ ተዘጅቸአለሁ(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እርሱም እርሱን አለው
እስራኤል ዮሴፍን አለው

ወሬያቸውን አምጣልኝ
ወንድሞቹና በጎቹ እንዴት እንደሆኑ ዮሴፍ ተመልሶ እንዲነግረው እስራኤል ይፈልጋል አት ተመልሰው ያገኘሄውን ንገረኝ ወይም ርፖርት አቅርብልኝ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በሸለቆው
ከሸለቆው

Genesis 37:15

እነሆ ዮሴፍ ሜዳ ላይ ወዲያና ወዲህ ሲባዝን ነበር አንድ ሰውም ዮሴፍን አገኘው
ዮሴፍ ወዲያና ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው ዮሴፍን አገኘው

እነሆ
በትልቁ ታሪክ ስለሌላ ክስተት መጀመሩን የሚያመለክት ነው በቀደሙ ክስተቶች ከነበሩ ሌሎች ሰዎች የሚያሳትፍ ነው በእርስዎ ቋንቋ ይህ የሚገለጽበት መንገድ ሊኖር ይችላል

ምን እያየህ ነው ?
ምን እየፈለግህ ነው?

ወዴት ነው እባክህ ንገረኝ
ወዴት እንደሆነ እባክህ ንገረኝ

ዶታይን
ከሰኬም 22 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ያለ ቦታ ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 37:18

በሩቅ አዩት
በሩቅ እያለ የዮሴፍ ወንድሞች አዩት

ይገድሉት ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ
እርሱን ለመግደል አቀዱ

ያ ሕልም ዐላሚ መጣ
ያ ባለ ሕልም ይሄው መጣ

ስለዚህ አሁንም ኑ
ይህ አባባል ወንድሞቹ ዕቅዳቸውን መተግበር መጀመራቸውን ያሳያል:: አት: (ስለዚህ አሁን ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ክፉ አውሬ
አደገኛ አውሬ ወይም ሰው ጨካኝ አውሬ

ቦጫጭቆ በላው
ንጥቆ በላው

ከሕልሞቹም የሚሆነውን እናያለን
ወንድሞቹ ሊገድሉት አቅደዋልና ስለዚህ እስከሞተ ድረስ ሕልሞቹ ይፈጸሙ እንደሆን መናገራቸው አሽሙራዊ/ሽሙጣዊ አባባል ነው:: አት "እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን" (በአሽሙር/ሽሙጥ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 37:21

ይህን ሰማ
እነርሱ የመከሩትን ሰማ

ከእጃቸው
ከእጃቸው የሚለው አባባል ሊገድሉት ያቀዱትን የወንድሞቹን እቅድ ያመለክታል:: አት "ከእነርሱ" ወይም "ከእቅዳቸው" (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሕይወቱን አናጥፋ
ሕይወት ማጥፋት የሚለው ሀረግ አንድን ሰው ስለመግደል በንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ነው። አት: "ዮሴፍን አንግደለው" (ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋራ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ደም አታፍስሱ
በግሡ አሉታዊነት ተጨምሮበታል ደግሞም ደምን ማፍሰስ አንድን ሰው ስለመግደል በንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ነው። አት የማንኛውንም ሰው ደም አታፍስሱ ወይም አትግደሉት (በአሉታዊነት አዎንታዊነትን የመግለጽ ዘይቤና ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋራ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እጃችሁን አታንሡበት
አታቆስሉት ወይም አትጉዱት ማለት ነው አት አትጉዱት (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከእጃቸው ሊያተርፈው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "ሮቤል ይህ ያለው ዮሴፍን ሊታርፈው ዘንድ ነው"

ከእጃቸው
ከእጃቸው የሚለው አባባል ሊገድሉት ያቀዱትን የወንድሞቹን እቅድ ያመለክታል:: አት "ከእነርሱ" ወይም "ከእቅዳቸው" (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ሊመልሰው
እናም ሊመልሰው

Genesis 37:23

እንደ ደረሰ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ተፈላጊ ክስተት ለመጠቆም ተጠቅሞአል በቋንቋህ እንዲህ ዓይነት ካለ በዚህ ቦታ ሊጠቀሙ ይችላሉ

በኅብረ ቀለማት ያገጠች እጀ ጠባቡን ገፈፉት
በኅብረ ቀለማት ያገጠች እጀ ጠባቡን ከላዩ ላይ ቀደዱት

ያገጠች ልብስ
ያገጠች እጀ ጠባብ፤ በዘፍጥረት 37:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

Genesis 37:25

እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ
እንጀራ በአጠቃላይ መግብን ያመለክታል አት ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ ወይም የያዕቆብ ወንድሞች ምግባቸውን ሊበሉ ተቀመጡ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ዐይኖቻቸውንም አንስተው አዩ እነሆም... የግመል ጓዝ
እዚህ አንስተው አዩ አንድሰው በውኑ አይኑን እንሰቶ እንደሚያይ ተደርጐ ተነግሮአል ደግሞም እነሆ የሚለው ቃል ሰዎች ላዩት ትኩረት ለመስጠት ተጠቅሞአል:: አት: "አይኖቻቸውን አነሡ እናም ወዲያውም የግመል ጓዝ አዩ" (ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

ተሸክመው
ጭነው

ኬርቤ
ቅመማቅመም

በለሳን
የቆዳ ቁስለትን የሚፈውስና የሚከለክል ጣፋጭ ጣዕም ያለው ቅባታማ ነገር "መድኃኒት"

ጭነው ወደ ግብጽ የሚወርዱ
ወደ ግብጽ የሚያመጡ ይህ ግለጽ ሊደረግ ይችላል አት ለመሸጥ ወደ ግብጽ የሚወርዱ ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ

ወንድማችንን መግደልና ደሙን መሸሸግ ምን ይጠቅማናል?
ይህ እንደዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወንድማችንን በመግደልና አሟሟቱን በመደበቅ እንጠቀምም” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ደሙን መሸሸግ
የዮሴፍን ሞት በደበቅን የሚገልጽ ምሳሌዊ አነጋገር ነው:: አት “አሟሟቱን መደበቅ” (ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)

Genesis 37:27

ለእስማኤላዊያን
የእስማኤል ዘር ለሆኑ ለእነዚህ ሰዎች

እጃችንን በእርሱ ላይ አናንሳ
ይህም “አናቆስለው” ወይም “አንጉዳው” ማለት ነው አት: “አንጉዳው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ወንድማችን ሥጋችን ነው
ሥጋ የሚለው ዘመድ ለሚለው ቃለ የሚቆም ምትክ ቃል ነው:: አት: “እርሱ የሥጋ ዘመዳችን ነው” (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ወንድሞቹም የእርሱን ነገር ሰሙት
የይሁዳ ወንድሞች ሰሙት ወይም የይሁዳ ወንድሞች በሐሳቡ ተስማሙ

ምድያማዊያን ..... እስማኤላዊያን
ሁለቱም ስሞች የዮሴፍ ወንድሞች ያገኙአቸው ተመሣሣይ ነጋዴዎችን ያመለክታል

ለሃያ ጥሬ ብር
ለሃያ ጥሬ ብር ዋጋ (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ዮሴፍን ወደ ግብጽ የዘውት ሄዱ
ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት

Genesis 37:29

ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ሲያይ ዮሴፍን በማጣቱ
ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ዮሴፍን በማጣቱ እነሆ ተገረመ:: “እነሆ” የሚለው ቃል ሮቤል ዮሴፍ በሄዱን ባወቀ ጊዜ መገረሙን ያሳያል::

ልብሱን ቀደደ
ይህ የጥልቅ ጭንቀትና ሀዘን ምልክት ነው:: ይህ በግልጽ ሊገለጽ ይችላል:: አት: እጅግም ስላዘነ ልብሱን ቀደደ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ብላቴናው የለም እንግዲህ እኔ ወዴት እሄዳለሁ?
የዮሴፍ መጥፋቱን ችግር ትኩረት ለመስጠት ሮቤል ጥያቄ ይጠቀማል:: አት: “ብላቴናው ሄዶአል እንግዲህ ወደ ቤት መመለስ አልችልም” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 37:31

የዮሴፍ እጀ ጠባብ
አባቱ ያዘጋጀለት ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ያመለክታል

ደም
የፍዬል ደም

አምጥተው
እጀ በባቡን አምጥተው

ቦጫጭቆ በልቶታል
በልቶታል

በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቆአል
ያዕቆብ የዮሴፍን አካል ክፉ አውሬ እንደገነጣጠለ አሰበ:: አት: “በእርግጥም ዮሴፍን ቦጫጭቆታል” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)

Genesis 37:34

ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ
ይህ ጥልቅ መጨነቅንና ሀዘንን የሚያመለክት ነው ይህ በግልጽ ሊገለጽ ይችላል አት ያዕቆብ እጅግ ስላዘነ ልብሱን ቀደደ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በወገቡም ማቅ ታጥቆ
ወገብ የሰውነት መሀከለኛው አካል ነው አት ማቅ ለብሶ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ተነሡ
እዚህ አባታቸውን ለማጽናናት የልጆች መጥጣት እንደ መነሣት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት: “ወደ እርሱ መጡ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እርሱ ግን ሊጽናና ባለመቻሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ነገር ግን እንዲያጽናኑት አልፈቀደም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ወደ ሙታን ሥፍራ እያዘንሁ እወርዳለሁ
ከዛሬ ጀምሮ እስከሚሞት ድረስ እንደሚያዝን ይገልጻል:: አት: “በሚሞትበትና ወደ ሙትን ሥፍራ በሚወርድበትም ጊዜም በእርግጥ እያዘንኩ ይሆናል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ምድያማዊያን ሸጡት
ምድያማዊያን ዮሴፍን ሸጡት

ለዘበኞች አለቃ
ንጉሡን ለሚጠብቁ ዘበኞች መሪ

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 38

1 በዚያም ወራት ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ ሒራ ወደተባለ ዐዱላማዊ ሰው ዘንድ ሄደ፣ መኖሪያውንም 2 እዚያም ሳለ፣ ይሁዳ የከነዓናዊውን የሴዋን ሴት ልጅ
ዐየ፤ እርሷንም አግብቶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመ። 3 እርሷም አርግዛ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም ዔር ብላ ጠራችው። 4 እንደገናም አረገዘችና ወንድ
ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም አውናን አለችው። 5 አሁንም ደግማ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሴሎም ብላ ጠራችው፣ እርሱንም የወለደችው ክዚብ በተባለ ቦታ
ነበር። 6 ይሁዳ የመጀመሪያ ልጁን ዔርን ትዕማር ከምትባል ልጃገረድ ጋር አጋባው። 7 የይሁዳ የበኩር ልጅ ዔር ግን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር፤
እግዚአብሔርም ቀሠፈው። 8 ይሁዳ አውናንን፣ “ዋርሳዋ እንደመሆንህ ከወንድምህ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም የወንድምህን ስም
የሚያስጠራለት ዘር ተካለት አለው። 9 አውናን ግን የሚወለደው ልጅ የእርሱን ስም የሚያስጠራ እንደማይሆን ስላወቀ፣ ከወንድሙ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ
ግንኙነት በፈጸመ ቁጥር የወንድሙን ስም የሚያስጠራ ልጅ እንዳይወለድ ዘሩን በምድር ላይ ያፈስ ነበር። 10 ይህም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆኖ ስለተገኘ፣
እርሱንም እግዚአብሔር በሞት ቀሠፈው። 11 ከዚያም ይሁዳ ምራቱን ትዕማርን፣ “ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ ወደ አባትሽ ቤት ሄደሽ መበለት
ሆነሽ ብትኖሪ ይሻላል” አላት፤ ይህን ያለውም፤ ሴሎም እንደወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለፈራ ነበር። ትዕማርም እንዳላት ሄደች፤ በአባቷም ቤት
ተቀመጠች። 12 ከብዙ ጊዜ በኋላ የሹዓ ልጅ፣ የይሁዳ ሚስት ሞተች። ይሁዳ ከሐዘኑ ከተጽናና በኋላ ከዓዶላማዊው ከሒራ ጋር የበጎቹን ጠጉር የሚሸልቱ
ሰዎች ወዳሉበት ወደተምና ሄደ። 13 ሰዎቹም ለትዕማር፣ “አማትሽ የበጎቹን ጠጉር ወደሚሸልቱ ሰዎች ዘንድ ወደተምና እየሄዱ ነው” አሏት። ይህን እንድሰማች
14 የመበለትነት ልብሷን አውልቃ፣ ማንነቷ እንዳይታወቅ ፊቷን በሻሽ ተከናንባ ወደ ተምና በሚወስደው መንገድ ዳር ባለች ኤናይም በተባለች ከተማ መግቢያ
በር ላይ ተቀመጠች፤ ይህን ያደረገችው፣ ሴሎም ለአካለ መጠን ቢደርስም፣ እርሷን እንዲያገባ አባቱ አለመፈለጉን ስላወቀች ነው። 15 ፊቷ በሻሽ ተሸፋፍኖ
ሲያያት፣ ይሁዳ ዝሙት አዳሪ መሰለችው። 16 ምራቱ መሆኗን ባለማወቁ፣ እርሷ ወዳለችበት ወደ መንደሩ ዳር ጠጋ ብሎ፣ “እባክሽን አብሬሽ ልተኛ” አላት።
እርሷም፣ “አብሬህ ብተኛ ምን ትሰጠኛለህ?” ብላ ጠየቀችው። 17 “ከመንጋዬ መካከል አንድ የፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ” አላት። እርሷም “ጠቦቱን
እስክትልክልኝ ድረስ ምን መያዣ ትሰጠኛለህ?” ብላ ጠየቀችው። 18 “ታዲያ ምን መያዣ ልስጥሽ?” አላት። እርሷም፣ “የማኅተም ቀለበትህን ከነማሰሪያው፣
እንደዚሁም ይህን በትርህን ስጠኝ” አለችው። የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣትና አብሯት ተኛ፤ እርሷም አረገዘችለት። 19 ከዚያም ወደ መኖሪያዋ ተመልሳ፣ ሻሽዋን
አውልቃ እንደወትሮዋ የመበለት ለብሷን ለበሰች። 20 ይሁዳ በመያዣ ስም የሰጣትን ዕቃዎች ለማስመለስ የፍየሉን ጠቦት በዓዶሎማዊ ወዳጁ እጅ ላከላት፣
እርሱ ግን ሊያገኛት አልቻለም። 21 “በኤናይም ከተማ መግቢያ ከመንገዱ ዳር የነበረች ያቺ ዝሙት አዳሪ የት ደረሰች?” ብሎ ዓዶሎማዊው ሰውዬ ጠየቀ።
ሰዎቹም፣ “በዚህ አካባቢ እንደዚህ ያለች ዝሙት አዳሪ የለችም” አሉት። 22 ስለዚህ ወደ ይሁዳ ተመልሶ ሄደና፣ “ላገኛት አልቻልሁም፤ በዚያ የሚኖሩትም
ሰዎች፥ ‘እንደዚህ ያለች ዝሙት አዳሪ እዚህ የለችም’ አሉኝ” ብሎ ነገረው። 23 ይሁዳም፣ “እንግዲህ መያዣውን እንደያዘች ትቅር አለዚያ መሳቂያ እንሆናለን።
ለነገሩማ ይህን ፍየል ላክሁ፣ አንተም ፈልገህ አላገኘሃትም” አለ። 24 ከሦስት ወር ያህል በኋላ፣ “ምራትህ ትዕማር ዘማዊ ሆናለች፤ ከዚህም የተነሣ አርግዛለች”
ተብሎ ለይሁዳ ተነገረው። ይሁዳም፣ “አውጧትና በእሳት ተቃጥላ ትሙት” አለ። 25 እርሷም ተይዛ በምትወሰድበት ጊዜ ለአማትዋ፣ “እኔ ያረገዝሁት የእነዚህ
ዕቃዎች ባለቤት ከሆነ ሰው ነው” ስትል ላከችበት፤ ደግሞም፣ “የማኅተሙ ቀለበት ከነማንጠልጠያውና በትሩ የማን እንደሆነ እስቲ ተመልከት” አለችው። 26
ይሁዳም ዕቃዎቹን አውቆ፣ “ልጄ ሴሎም እንዲያገባት ባለማድረጌ፣ እርሷ ከእኔ ይልቅ ትክክል ናት” አለ። ከዚያም በኋላ ከእርሷ ጋር አልተኛም። 27
የመውለጃዋ ጊዜ እንደደረሰም ፅንሷ መንታ መሆኑ ታወቀ። 28 በምትወልድበትም ጊዜ አንደኛው እጁን አወጣ፤ አዋላጇቱም፣ “ይህኛው መጀመሪያ ወጣ”
ስትል በእጁ ላይ ቀይ ክር አሰረችለት፤ 29 ነገር ግን፣ እጁን መልሶ ሲያስገባ ወንድሙ ተወለደ። አዋላጇቱም፣ “አንተ እንዴት ጥሰህ ወጣህ!” አለች፣ ከዚያም
ስሙ ፋሬስ ተባለ። 30 ከዚያ በኋላ እጁ ላይ ቀይ ክር የታሰረለት ወንድሙ ተወለደ፣ ስሙም ዛራ ተባለ።

Genesis 38:1

በዚያም ወራት ይሁዳ
ይህ ስለ ይሁዳ የሚናገረውን አድስ የታሪኩን ክፍል ያስታውቃል (አድስ ክስተት መጀመር ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ኤራስ ወደተባለ ዓዶሎማዊ
ኤራስ በዓዶሎም የሚኖር ወንድ ሰው ስም ነው (ስሞችን ስለመተረጎም ይመልከቱ)

ሴዋ
ሴዋ ይሁዳን ያገባች ከነዓናዊ ሴት ነች (ስሞችን ስለመተረጎም ይመልከቱ)

Genesis 38:3

እርስዋም ጸንሣ
የይሁዳ ሚስት ጸንሣ

ዔር ተብሎ ተሠየመ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “አባቱ ዔር ብሎ ሰየመው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ስሙንም ... ጠራው
ሰየመው

ክዚብ
የቦታ ወይም የሀገር ስም ነው (ስሞችን ስለመተረጎም ይመልከቱ)

Genesis 38:6

ዔር
ይህ የይሁዳ ወንድ ልጅ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38:3 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጎም ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር
በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር የዔርን ክፋት እንደአየው ያመለክታል:: አት: “ክፉ ነበርና እግዚአብሔር አየው” (ፈሊጣው አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ቀሠፈው
ክፉ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ቀሠፈው:: ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ስለዚህ እግዚአብሔር ቀሠፈው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 38:8

አውናን
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 38:4 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ወደ ወንድምህ ሚስት ግባ
ይህ ታላቅ ወንድም አግብቶ ሳለ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ተከታይ ወንድሙ ወደ መበለትዋ በመግባት ሩካቤ ሥጋ በመፈጸም ዘርን የማስቀጠል ባህል እንደሆነ ያመለክታል መበለትዋ የመጀመሪያ ወንድ ከወለደች ያ ወንድ ልጅ የሞተው ወንድም ልጅ እንደሆነ በመቆጠር የሟቹን ሀብት ይወርሳል::

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር
በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር የአውናን ክፋት እንደአየው ያመለክታል:: አት: “ክፉ ነበርና እግዚአብሔር አየው” (ፈሊጣው አነጋገር ይመልከቱ)

እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ቀሠፈው
ያደረገው ነገር ክፉ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ቀሠፈው:: ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ስለዚህ እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር ቀሠፈው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 38:11

ምራቱ
የታላቅ ወንድ ልጁ ሚስት

ወደ አባትሽ ቤት
ይህም ማለት በዚህ በአባትዋ ቤት እንዲትኖር ነው:: አት “እናም በአባትሽ ቤት… ቢትኖሪ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ
ይሁዳ ትዕማር ሴሎም ለአካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንዲታገባው ያስባል። አት “ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን በደረሰ ጊዜ ሊያገባሽ ይችላል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሴሎም
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 38:5 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለ ሠጋ
ሴሎም ትዕማርን ቢያገባ እንደ ወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎ ይሁዳ ሠግቶአል:: አት “እርሱ እርስዋን ካገባ እንደወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎ ስለሠጋ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 38:12

ሹዓ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 38:2 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

ይሁዳ ከሀዘኑ ተጽናና
ይሁዳም ሀዘኑን ባቆመ ጊዜ

የበጎቹን ጸጉር ወደሚሸልቱት ሰዎች ወደ ተምና
ተምና የበጎቹንነ ጸጉም የሚሸልቱ ስዎች ወዳሉበት ሥፍራ

ተምና ... ኤናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

እርሱና የእርሱ ጓደኛ ዓዶላማዊው ሒራ
ከዓዶላም ጓደኛው ሒራ አብሮት ሄደ

ሒራ ዓዶላማዊው
ሒራ የወንድ ሰው ስም ነው እናም ዓዶላም እርሱ የሚኖርበት ቀበሌ ስም ነው። በዘፍረት 38:1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ትዕማር ተነገራት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለትዕማር ነገራት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እይው አማትሽ
ስሚ ፤ እዚህ “እይው” የሚለው ቃል የትዕማርን ትኩረት ለመሳብ ተጠቅሞአል።

አማትሽ
የባልሽ አባት

የመበለትነት ልብስ
መበለቶች የሚለብሱት ልብስ

ሻሽ
ሴቶች ፊታቸውንና ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት ከስስ ጨርስ የተሰራ ልብስ

ራስዋን ተከናንባ
ይህም ሰዎች እንዳያውቃት ራስዋን በልብስ በመከናነብ ሸፈነች ማለት ነው ሴቶች ራሳቸውን መከናነብ የሚያስችላቸው ሰፋፊ ልብሶች በባህሉ የተለመዱ ናቸው አት ሰዎች እንዳያውቃት በሰፋፊ ልብሶች ተከናነበች (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

መንገድ ዳር
በመንገድ ዳር ወይም በመንገድ

ለእርሱ ሚስት ሆና አልተሰጠችም ነበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ይሁዳ ለሴሎም ሚስት አድርጐ አልሰጣትም ነበር” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 38:15

ፊትዋን ስለሸፈነች
ይሁዳ እንደ ጋለሞታ ያሰባት ፊትዋን ስለሸፈነች ብቻ ሳይሆን በከተማው መግቢያም ስለተቀመጠች ነው አት ጭንቅላትዋን ስለሸፈነችና ጋለሞቶች በሚቀመጡበት ቦታ ስለተቀመጠች ነበር (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ወደ እርስዋም አዘነበለ
ትዕማር በመንገዱ ዳር ነበረች አት እርስዋም ወደተቀመጠችበት ወደ መንገዱ ዳር ሄደ ወይም አዘነበለ(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እባክሽ ነዪ
እባክሽ ወደ እኔ ነዪ ወይም እባክሽ አሁነ ነዪ

ምራቱ
የልጁ ሚስት

Genesis 38:17

ከመንጋዬ
ከፍዬሎች መንጋዬ

ማኅተም ቀለበት ከነማሰሪያው .... በትር
ማኅተም ብር መሣይ በላዩ ላይ ቅርጽ የተቀረጸበት የቀለጠ ሰም ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ነው ቀለበት ማኅተም ያለበትና ባለቤቱ በአንገት የሚያደረገው ነው በትር ከረጅም እንጨት የተሠራና በአዳጋች በመንገድ የሚጠቀሙበት ነው

ለእርሱም ጸነሰች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “እርሱም እርሷን አስረገዛት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 38:19

ሻሽ
ሴቶች ፊታቸውንና ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት ከስስ ጨርስ የተሰራ ልብስ ነበር:: በዘፍጥረት 38: 14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

የመበለት ልብሰዋን ለበሰች
መበለቶች የሚለብሱትን ልብስ ለበሰች:: በዘፍጥረት 38: 14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አዶሎማዊ
በአዶሎም ቀበለ የሚኖር ሰው በዘፍጥረት 38፡ 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

መያዣ የሰጣትን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “መያዣውን ለማስመለስ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከሴቲቱ እጅ
እዚህ እጅ የሚለው ቃል በእርስዋ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ አበክሮት ይሰጣል:: የሴቲቱ እጅ ሴቲቱን ይወክላል:: አት “ከሴቲቱ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 38:21

አዶሎማዊ
በአዶሎም ቀበለ የሚኖር ሰው በዘፍጥረት 38 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የአገሩ ሰዎች
በዚያ ከሚኖሩ ሰዎች እንዳንዶች

ቤተ ጣዖት ዝሙት አደሪዋ
በቤተ ጣዖት የሚታገለግል ዝሙት አዳሪ

ኤናይም
ይህ የቦታ ስም ነው በዘፍጥረት 38፡14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

አለዚያ መሳቂያ እንሆናለን
የሆነውን ነገር ሰዎች ከሰሙ በይሁዳ ይስቁበታል ይሣለቁበታል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወይም ደግሞ የሆነውን ሰዎች ካወቁ ይስቁብናል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ እና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 38:24

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩን አድስ አካል ጅማሬ ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ለይሁዳ ተነገረው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለይሁዳ ነገረው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ምራትህ ትዕማር
ትዕማር የታላቅ ልጅህ ሚስት

ከዚህም የተነሣ ጸነሰች
ከዚህ የሚለው ቃል ከዝሙት ከፈጸመችው ዝሙት ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚህም አረገዘች” ወይም “አረገዘች” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አምጡአት
አውጡአት

በእሳት ትቃጠል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እንዲትሞት እናቃጥላታለን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እርስዋም ባወጡአት ጊዜ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እነርሱ ባወጡአት ጊዜ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አማትዋ
የባልዋ አባት

ማኅተም ቀለበት ከነማሰሪያው .... በትር
ማኅተም ብር መሣይ በላዩ ላይ ቅርጽ የተቀረጸበት የቀለጠ ሰም ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ነው:: ቀለበት ማኅተም ያለበትና ባለቤቱ በአንገት የሚያደረገው ነው በትር ከረጅም እንጨት የተሠራና በአዳጋች በመንገድ የሚጠቀሙበት ነው:: (በዘፍጥረት 38: 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ)

ሴሎም
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38፡5 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 38:27

በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

እነሆ
እነሆ የሚለው ከዚህ በፊት ያልታወቀው ትዕማር መንታ ልጆችን እንደተሸከመች እንድንገረም ለማድረግ ተጠቅሞአል

ስትወልድም እንዲህ ሆነ
እንዲህ ሆነ የሚለው ሀረግ በታሪኩ ዋና ክስተት ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የመሰለውን የመግለጽ አባባል ካለ ይጠቀሙ

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

አንደኛው እጁን አወጣ
ከሕጻኖች አንደኛው እጁን አወጣ

አዋላጅ
አንድ ሴት በሚትወልድበት ጊዜ የሚረዳት ሰው ነው በዘፍረት 35:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ቀይ ክር
ደማቅ ቀይ ክር

በእጁ
በአምባሩ ዙሪያ

Genesis 38:29

እነሆ
እነሆ የሚለው ቃል ለሚከተለው የሚያስገርም መረጃ ትኩረት እንድንሰጠው ነው

እንዴት ጥሰህ መጣህ!
ይህ ሁለተኛው ሕጻን ቀድም ሲወጣ አዋላጅዋ በማየት የተደነቀችውን የሚያሳይ ነው:: አት “እንዴት የራስህን መንገድ ጥሰህ ወጣህ!” ወይም “ሰንጥቀህ ቀድመህ ወጣህ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመለከቱ)

ስም ተሰጠው ወይም ተሰየመ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት “እርስዋ ስም ሰጠችው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ፋሬስ
የወንድ ልጅ ስም ነው ተርጓሚዎች እንደሚከተለው የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: ፋሬስ የሚለው ስም ጥሶ መውጣት ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዛራ
ይህ የወንድ ልጅ ስም ነው ተርጓሚዎች እንደሚከተለው የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: ዛራ የሚለው ስም ቀይ ክር ወይም ደማቅ ቀይ ክር ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 39

1 ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተወስዶ ነበር፤ ከፈርዖንም ሹማምንት አንዱ የነበረውም የዘበኞች አለቃ፣ ግብፃዊው ጴጥፋራ ወደዚያ ከወሰዱት ከእስማኤላውያን
ነጋዴዎች እጅ ገዛው። 2 እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበረ ኑሮው ተቃናለት፤ እርሱም በግብፃዊው አሳዳሪው ቤት ኖረ። 3 አሳዳሪው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
እንዳለና ሥራውንም ሁሉ እንዳከናወነለት ባየ ጊዜ፣ 4 ዮሴፍ በእርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ፣ የቅርብ አገልጋዩም ሆነ። ጲጥፋራ በቤቱ ላይ ሾመው፣ ያለውንም ሀብት
ሁሉ በኃፊነት ሰጠው። 5 ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብፅዊውን ቤት ባረከ፣ የእግዚአብሔርም
በረከት በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ ላይ ሆነ። 6 ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠው፣ የቀረበለትንም ከመመገብ
በስተቀር፣ ማናቸውንም ጉዳይ በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር። ዮሴፍ ጥሩ ቁመና ያለውና መልከ-መልካም ነበር፤ 7 ከጊዜ በኋላ የጌታው ሚስት ዮሴፍን ተመልክታ
ስላፈቀረችው፣ “ና ከእኔ ጋር አብረን እንተኛ” አለችው። 8 እርሱ ግን ይህን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆነም፤ እንዲህም አላት፤ “ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኃላፊነት
ስለሰጠኝ፣ በቤቱ ውስጥ ስላልው ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። 9 በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኃላፊነት ያለው ማንም የለም፣ ከአንቺ በቀር በእኔ
ቁጥጥር ሥር ያላደረገው ምንም ነገር የለም፤ ይኸውም ሚስቱ ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እፈጽማለሁ?” 10
ይህንም ነገር በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር፤ እርሱም ከእርሷ ጋር ይተኛ ዘንድ ከእርስዋም ጋር ይሆን ዘንድ አልሰማትም። 11 አንድ ቀን ዮሴፍ ለሥራ ጉዳይ
ወደ ቤት ሲገባ በቤት ውስጥ አንድም ሠራተኛ አልነበረም፤ 12 እርሷም ልብሱን ጨምድዳ ይዛ፣ “በል አብረኸኝ ተኛ” አለችው። እርሱ ግን ልብሱን እጅዋ ላይ
ትቶላት ከቤት ሸሽቶ ወጣ። 13 እርሷም ልብሱን በእጅዋ ላይ ትቶ ከቤት ሸሽቶ መውጣቱን በተመለከተች ጊዜ፣ 14 አገልጋዮችዋን ጠርታ እንዲህ አለቻቸው፣
“እነሆ፣ ባለቤቴ ያመጣው ይህ ዕብራዊ ሊያዋርደኝ ነበር፤ ወዳለሁበት ክፍል ገብቶ ሊደፍረኝ ሞከረ፤ እኔ ግን ድምፄን ከፍ አድርጌ ጮኽሁ። 15 ዕርዳታ
ለማግኘትም መጮኼን በሰማ ጊዜ ልብሱን በአጠገቤ ትቶ ከቤት ሸሽቶ ወጣ።” 16 የዮሴፍ አሳዳሪ እስኪመጣ ድረስ ልብሱን በእርስዋ ዘንድ አቆየችው። 17
በመጣም ጊዜ የሆነውን ታሪክ እንዲህ ስትል ዘርዝራ ነገረችው፤ “አንተ ወደዚህ የመጣኸው ዕብራዊ አገልጋይ ወዳለሁበት ክፍል ገብቶ ሊያዋርደኝ ነበር። 18
ነገር ግን ድምፄን ከፍ አድርጌ በጮኽሁ ጊዜ ልብሱን በአጠገቤ ትቶ ከቤት ሸሽቶ ወጣ።” 19 “የአንተ አገልጋይ እንዲህ አደረገኝ” ብላ የነገረችውን ታሪክ
በሰማ ጊዜ የዮሴፍ አሳዳሪ እጅግ ተቆጣ። 20 ዮሴፍንም ወስዶ፣ የንጉሥ እስረኞች ወደታሠሩበት እስር ቤት አስገባው። 21 እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅሩን
ዐሳየው፣ በእስር ቤት አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው። 22 ስለዚህ የእስር ቤቱ አዛዥ ዮሴፍን የእስረኞች ሁሉ አለቃ አደረገው፤ በእስር ቤት ላለውም ነገር ሁሉ
ኃላፊ ሆነ። 23 እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ሆኖ የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንዲቃናለት ስላደረገ የእስር ቤት አዛዡ በዮሴፍ ቁጥጥር ሥር በነበረው ነገር ምንም
ዐሳብ አልነበረበትም።

Genesis 39:1

ዮሴፍ ወደ ግብጽ ወርዶ ነበር

ወደ ግብጽ መጓዝ ወደ ላይ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመጓዝ ተጻራሪ ወደ ታች መውረድ ተደርጐ ይቆጠራል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እስማኤላዊያን ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት” (ፈሊጣዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ እና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የዮሴፍ ጋር ነበረ

ይህ እግዚአብሔር ዮሴፍን ረድቶታል ሁልጊዜም ከእርሱ ጋር ነበር ማለት ነው:: አት “እግዚአብሔር ዮሴፍን መራው አገዘውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አሳዳሪው ቤት ኖረ

እዚህ ጸሓፊው በአሳዳሪው ቤት መሥራቱን በአሳዳሪው ቤት እንደመኖር ይናገራል:: በአሳዳሪዎቻቸው ቤት መሥራት የሚችሉት በጣም ታማኝ የሆኑ ሎሌዎች ብቻ ናቸው። አት እርሱም በቤት ውስጥ ይሠራ ነበር (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 39:3

አሳዳሪው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ አየ

አሳዳሪው እግዚአብሔር እርሱን እየረዳ እንደሆነ አየ ማለት ነው አት እግዚአብሔር እየረዳው እንደሆነ አሳዳሪው አየ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ እንዳከናወነለት

እግዚአብሔር ዮሴፍ የሚሠራው ሁሉ መከናወንለት አደረገ

ዮሴፍ በእርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ

ሞገስ ማግኘት በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማስረገጥ ማለት ነው በእርሱ ዘንድ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል በሰውዬው አመለካከት እንደሆነ ያመለክታል:: ተገቢ ትርጉሞች እነሆ 1) ጲጥፋራ በዮሴፍ ተደስቶአል 2) እግዚአብሔር በዮሴፍ ተደስቶአል (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

ጲጥፋራን አገለገለ

የጲጥፋራ የግል ሎሌው ነበር ማለት ነው

ጲጥፋራ ዮሴፍን በቤቱ ላይ ሾመው ያለውን ሀብት ሁሉ በኃላፊነት ሰጠው

ጲጥፋራ በቤቱና የጲጥፋራ በሆነው ሁሉ ላይ ለዮሴፍ በኃላፊነት ሰጠው

በእርሱ ኃላፊነት ሥር አደረገ

አንድ ነገር በአንድ ሰው ኃላፊነት ሥር ሲሆን ያ ሰው ያንን ነገር ለመንከባከብና ደኅንነቱን ለመጠበቅ ኃላፊነት አለው ማለት ነው:: አት “ዮሴፍ እንዲንከባከብ ሰጠው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 39:5

ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብጻዊውን ቤት ባረከ

ተውላጤ ስሞችን ከመጠቀምዎ በፊት “ዮሴፍ” እና “ግብጻዊው” የሚሉ ቃላትን መጠቀም ይችላሉ:: ግብጻዊው ዮሴፍን በቤቱና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ኃላፊነት ሰጠው እናም ከጊዜ ወደ ጊዜ በዮሴፍ ምክንያት እግዚአብሔር የግብጻዊውን ቤት ባረከ::

እንዲህም ሆነ

እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች ለሚቀጥለው ክስተት ዳራ መረጃ እንደሆኑ ለአንባቢያን ለመናገር ይህ ሀረግ ተጠቅሞአል

እርሱም እርሱን በቤቱና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ሾመው

ጲጥፋራ ዮሴፍን በቤቱና ባለው ተብት ሁሉ ላይ ሾመው

ባረከው

በሚባረከው ነገር ወይም ሰው መልካም ወይም ጠቃሚ ነገር እንዲደረግ ምክንያት መሆን ማለት ነው

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

የእግዚአብሔር በረከት ሆነ

እዚህ ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት በአንድ ነገር ላይ እንደተቀመጠ መሸፈኛ አድርጐ ይናገራል:: አት: “እግዚአብሔር ባረከ” ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ

በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ

ይህ ቤት እረሻውንና ከብቶችን ያለመክታል የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “በጲጥፋራ ቤትና በከብቶችና እርሻው ሁሉ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

ጲጥፋራ ማንኛውንም ጉዳይ በዮሴፍ ቁጥጥር ሥር አድርጐ/በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር

አንድ ነገር በአንድ ሰው ቁጥጥር ሥር ሲሆን ያ ሰው ሊጠብቀውና ሊንከባከበው ኃላፊነት አለው ማለት ነው አት: “ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ ለዮሴፍ ስልጣን ሰጠው”

ከሚበላው እንጀራ በቀም ምንም የሚያውቀው አልነበረም

ምን ምግብ መመገብ እንዳለበት ከመወሰን በቀር በቤቱ ስላለው ማንኛውም ነገር አይጨነቅም ነበር ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት ጲጥፋራ ምን መመገብ እንደሚፈልግ ብቻ ማሰብ ነበረበት በቤቱ ስላለው ማንኛውም ነገር መጨነቅ የለበትም (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

አሁንም

“አሁንም” የሚለው ቃል ስለ ዮሴፍ ዳራ መረጃ ለመስጠት በታሪኩ መስመር ውስጥ ጣልቃ ማስገባቱን ያመለክታል (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ዮሴፍ መልከ መልካምና ውብ ነበር

ሁለቱም ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ዮሴፍ የሚያስደስት ቁመና እንዳለው ያመለክታሉ:: ጠንካራና ጥሩ ቁመና ነበረው:: አት: “ጠንካራና መልከመልካም ነበር”

Genesis 39:7

ከዚህ በኋላ እንደዚህ ሆነ

እናም ደግሞ ይህ ሀረግ አድስ ክስተት መጀመሩን ሊያመለክት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ማታወቅ ይመልከቱ)

እይው

ስሚው ዮሴፍ የጲጥፋራን ሚስት መስብ/ትኩረት ለማግኘት ይህን ቃል ተጠቅሞአል

ጌታዬ በቤቱ ውስጥ ስላለው ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም

“ጌታዬ በኃላፊነቴ ሥር ስላለው ስለቤቱ ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም”:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ጌታዬ ስለቤቱ ያምነኛል” (ድርብ አሉታዊነት ይመልከቱ)

ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ለእኔ ስለሰጠኝ

አንድ ነገር “በአንድ ሰው ኃላፊነት ሥር” ሲሆን ያ ሰው እንዲንከባከበውና እንዲጠብቀው ኃላፊነት አለው ማለት ነው:: አት፡ “ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ስለሰጠኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም

እዚህ ጸሓፊው ኃላፊነትን እንደ ትልቅነት ይናገራል አት: “ከማንም ሰው የበለጠ ለዚህ ቤት ኃላፊነት አለኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከአንቺ በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም

ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “እርሱ ያለሰጠኝ ነገር ቢኖር አንቺን ብቻ ነው” (አሉታዊነትን በአዎንታዊነት የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዴት ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እሠራለሁ

ዮሴፍ ትኩረት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማል ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት አልሠራም (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 39:10

በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር

ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ በተደጋጋሚ ትጠይቀው ነበር ማለት ነው:: የዚህ ጥቅስ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ ትጐተጉተው ነበር” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከእርስዋም ጋር እንዲሆን

እንዲቀርባት

እንዲህም ሆነ

“እንዲሁም ደግሞ” የሚለው ሀረግ በታሪኩ አድስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

ከቤቱ አገልጋዮችም አንድም ሰው

በቤቱ ከሚያገለግሉ ሰዎች ማንም

ሸሽቶ ከቤት ወጣ

“እናም ወዲያው ሮጦ ወደ ውጪ ወጣ” ወይም “እናም ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ”

Genesis 39:13

እንዲህም ሆነ **....** ጠራች

ከዚያም .... ጠራች እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ በታሪኩ ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ሸሽቶ ወደ ውጭ ወጣ

ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ

የቤትዋን ሰዎች

በቤትዋ የሚሠሩ ሰዎች

አያችሁ

“ተመልከቱ” ወይም “ሰማችሁ” ወይም “ስለሚናገረው ነገር ትኩረት አድርጉ”

ከእኔ ጋር ሊተኛ ወደ እኔ ገባ

እዚህ የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍ ሊይዛትና ከእርስዋ ጋር ሊተኛ እንደሞከረ ትከሳለች

እንዲህም ሆነ መጮሄን ሲሰማ

ድምጼን ከፍ አድርጌ መጮሄን ሲሰማ እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

Genesis 39:16

ጌታውም

የዮሴፍ ጌታ ይህ ጲጥፋራን ያመለክታል::

እንዲህ ስትል ነገረችው

ይህን ነገር እንዲህ ብላ ነገረችው

ወደ እኛ ያመጣሄው
“እኛ” የሚለው ቃል ጲጥፋራን ሚስቱንና ሌሎች በቤት ውስጥ ያሉትን ጠቃልላል (ሁሉ አቀፍ እኛን ይመልከቱ)

መሣለቂያ ሊያደርገኝ ወደ እኔ ገባ
መሣቂያ ሊያደርገኝ ወደ እኔ ገባ መሣለቂያ የሚለው ቃል ሊይዘኝና ከእኔ ጋር ሊተኛ የሚለውን አባባል በንጎብነት ወይም አንድን ነገር ለዘብ ባለ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ ነው:: አት “ወዳለሁበት ገባ አስገድዶ ከእኔ ጋር ሊተኛ ሞከረ” (ንጎብነት ወይም አንድን ነገር ለዘብ ባለ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
“ከዚያም” የጲጥፋራ ሚስት ይህን ሀረግ የተጠቀመችው ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር ለመተኛት መሞከሩን ለእርሱ የሚትነግረውን የታሪኩን ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ነው::(አዲስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

ሸሽቶ ወደ ውጭ ወጣ
ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ

Genesis 39:19

እንዲህም ሆነ
“እንዲህም ሆነ” የሚለው ሀረግ በታሪኩ አዲስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ጌታውም
የዮሴፍ ጌታ ይህ ጲጥፋራን ያመለክታል ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት የዮሴፍ ጌታ ጲጥፋራ

እጅግ ተቈጣ
ጲጥፋራ እጅግ ተቈጣ

የንጉሡ እስረኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አተ ንጉሡ እስረኞችን ያኖረበት ቦታ ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ

በዚያ ነበረ
ዮሴፍ በዚያ ቆየ

Genesis 39:21

ነገር ግን እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ
እግዚአብሔር ለዮሴፍ ተጠነቀቀለት እናም ቸር ነበረ:: “ነገር ግን እግዚአብሔር ለዮሴፍ ቸር ነበር” ወይም “እግዚአብሔር ዮሴፍን ተንከባከበ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ገለጸለት
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም “ታማኝ” ወይም “በታማኝነት” ሊገለጽ ይችላል:: አት ከእርሱ ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነበር ወይም በታማኝነት ወደደው (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

በወህኒ ቤት አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው
ይህም እግዚአብሔር የወህኒ ቤት አዛዥ ዮሴፍን እንዲቀበለውና እንዲንከባከበው አደረገው አት እግዚአብሔር የእስር ቤቱ አዛዥ በዮሴፍ እንዲደሰት አደረገው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የእስር ቤቱ አዛዥ
“የእስረኞች አስተዳደር” ወይም “በእስር ቤቱ ኃላፊነት የተሰጠው”

በዮሴፍ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” የሚለው የዮሴፍን ኃይል/አቅም ወይም ታማኝ ኃላፊነት ይወክላል”” አት “ዮሴፍን አለቃ አደረገው” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በዚያ ለሚደረገው ማንኛውም ነገር ዮሴፍ ኃላፊ ነበር
“ዮሴፍ በዚያ ለሚደረገው ነገር ሁሉ ኃላፊ ነበር”

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ
ይህ እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳውና እንደመራው የሚያመለክት ነው። አት “እግዚአብሔር ዮሴፍን ስለመራው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር
ዮሴፍ የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር

Chapter 40

1 ከዚህም በኋላ የግብፅ ንጉሥ የመጠጥ አሳላፊውና የእንጀራ ቤት ኃላፊው ንጉሡን የሚያሳዝን በደል ፈጸሙ። 2 ፈርዖንም በመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃና
በእንጀራ ቤቱ አዛዡ፣ በሁለቱም ሹማምንቱ ላይ እጅግ ተቆጣ፤ 3 በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው ዮሴፍ ወደታሠረበት እስር ቤት አስገባቸው። 4 የዘበኞቹም
አለቃ እስረኞቹን ለዮሴፍ አስረከባቸው፤ በእስር ቤትም ለጥቂት ጊዜ ቆዩ። 5 ታስረው የነበሩት የግብፅ ንጉሥ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ ቤቱ
አዛዥ፣ በአንድ ሌሊት የየራሳቸውን ሕልም ዐዩ፤ የሁለቱም ሕልም ለየራሱ የተለየ ፍቺ ነበረው። 6 በማግስቱ ጥዋት ዮሴፍ እነርሱ ወዳሉበት ክፍል በገባ ጊዜ
ተክዘው አገኛቸውና፤ 7 “ዛሬ በፊታችሁ ላይ ሐዘን የሚታየው ለምንድን ነው?” አላቸው። 8 እነርሱም፣ “ሁለታችንም ሕልም ዐየን፤ ነገር ግን የሚተረጉምልን ሰው
አጣን” ሲሉ መለሱለት። ዮሴፍም፣ “ሕልም የመተርጎም ችሎታ የሚሰጥ እግዝአብሔር ነው፣ ስለዚህ የእያንዳንዳችሁን ሕልም ንገሩኝ” አላቸው። 9 ስለዚህ
የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ እንዲህ ሲል ሕልሙን ለዮሴፍ ነገረው፤ “ከፊት ለፊቴ አንዲት የወይን ተክል ዐየሁ፤ 10 ተክሏም ሦስት ሐረጎች ነበሯት፤ ወዲያው
እቆጥቁጣ አበበች፤ የወይን ዘለላውም ወዲያው በሰለ። 11 የፈርዖንንም ጽዋ ይዤ ነበር፣ የወይኑን ፍሬ ለቅሜ በጽዋው ውስጥ ጨምቄ ጽዋውን በእጁ
ሰጠሁት።” 12 ዮሴፍም እንዲህ አለው፤ “እንግዲህ የሕልሙ ትርጓሜ ይህ ነው፤ ሦስቱ ሐረግ ሦስት ቀን ነው፤ 13 በሦስት ቀን ውስጥ ፈርዖን ከእስር ቤት
ያወጣሃል፣ ወደ ቀድሞ ሹመትህም ይመልስሃል፤ በፊት የመጠጥ አሳላፊ በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበረው ኡሉ የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰጠዋለህ። 14
እንግዲህ፣ በጎ ነገር በገጠመህ ጊዜ፣ እኔን አስበህ ቸርነት አድርግልኝ፣ ስለ እኔም ለፈርዖን ንገርልኝ፤ ከዚህም እስር ቤት አስወጣኝ፤ 15 ከዕብራውያን ምድር
ወደዚህ የመጣሁት በአፈና ነው፤ አሁንም ቢሆን እዚህ እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች ጥፋት ኖሮብኝ አይደለም።” 16 የእንጀራ ቤት አዛዡም፣ ለመጠጥ
አሳላፊዎቹ አለቃ ሕልም የተሰጠው ፍቺ ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ሲሰማ፣ የራሱን ሕልም ለዮሴፍ እንዲህ ሲል ነገረው፤ “እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ፣ ሦስት
መሶቦች በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር፤ 17 በላይኛው መሶብ ውስጥ ለፈርዖን የተዘጋጀ የተለያየ ምግብ ነበረበት፣ ነገር ግን ወፎች ምግቡን ከመሶቡ እያነሱ የበሉት
ነበር።” 18 ዮሴፍም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “የሕልሙ ፍቺ ይህ ነው፤ ሦስቱ መሶብ ሦስት ቀን ነው፤ 19 በሦስት ቀን ውስጥ ፈርዖን ራስህን ካስቆረጠ በኋላ
በእንጨት ላይ ይሰቅልሃል፤ ወፎችም ሥጋህን የበሉታል።” 20 በሦስተኛው ቀን የፈርዖን ልደት በዓል ስለነበር ለመኳንንቱ ሁሉ ግብዣ አደረገ፤ በዚያኑ ዕለትም
የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዡን ሹማምንቱ ካሉበት ከእስር ቤት አወጣቸው። 21 የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ ሹመቱ
መለሰው፤ እርሱም እንደ ቀድሞው ጽዋውን ለፈርዖን በእጁ ይሰጠው ጀመር፤ 22 የእንጀራ ቤት አዛዡን ግን ልክ ዮሴፍ እንደተረጎመላቸው ሰቀለው። 23 የሆነው
ሆኖ፣ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ ዮሴፍን አላስታወሰውም፤ ረሳው።

Genesis 40:1

ከዚህም በኋላ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ አዲስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ነው። (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

የመጠጥ አሳላፊ
ይህ ለንጉሡ መጠጥ የሚያቀርብ ሰው ነው

እንጀራ ቤቱ
ይህ ለንጉሡ ምግብ የሚያዘጋጅ ሰው ነው

ጌታቸውን በደሉት
ጌታቸውን አስቆጡት

የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃና የእንጀራ ቤቱ አዛዥ
ዋና የመጠጥ አሳላፊና ዋና እንጀራ እቅራቢ

በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው እስር ቤት አስገባቸው
በዘበኞቹ አለቃ በሚተዳደረው የቤት ውስጥ እስር ቤት አስገባቸው

አስገባቸው
ንጉሡ ወደ እሥር ቤት አላስገባቸውም ነገር ግን እንዲታሠሩ አዘዛቸው። አት “እነርሱ እንዲያስገቡ አደረጋቸው” ወይም “ዘበኛው እንዲያስገባቸው አዘዘ” (ተዛማጅ ምትክ አባባሎችን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ዮሴፍ ወደጋዘበት እስር ቤት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ይህ ዮሴፍ የነበረበት ተመሣሣይ እስር ቤት ነው ወይም ይህ ጲጥፋራ ዮሴፍን ያስገባበት ተመሣሣይ እስር ቤት ነው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 40:4

በእስር ቤት ጥቂት ጊዜ ቆዩ
በእስር ቤት አያለ ጊዜያት ቀን ተቀመጡ

Genesis 40:6

ዮሴፍ ወደእነርሱ ገባ
ዮሴፍ ወደ መጠጥ አሳላፊውና እንጀራ አቅራቢው ገባ

እነሆም አዝነው አያቸው
እነሆም የሚለው ቃል ባየው ነገር ዮሴፍ እንዴት እንደተገረመ የሚያሳይ ነው:: አት “እነርሱን አዝነው በማየቱ ተገረመ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አብረውት የነበሩ የፈርዖን ሹማምንት
ይህ የጠጅ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ አቅራቢዎች አዛዥ ያመለክታል

በጌታው ግቢ በግዞት
በጌታው ግቢ በእስር ቤት፤ ጌታው የዮሴፍ ጌታ፤ የዘበኞች አለቃ የሚያመለክት ነው

ትርጓሜ ከእግዚአብሔር የማገኝ አይደለምን?
አጽንዖት ለመስጠት ዮሴፍ ጥያቄ ይመለከታል:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ትርጓሜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው! ወይም ለሕልሞች ትርጉምን መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ነው” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እስቲ ንገሩኝ
ሕልማቸውን እንዲነግሩት ዮሴፍ ይጠይቃቸዋል:: አት “ሕልሞቻችሁን እባካችሁ ንገሩኝ”

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 40:9

የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ
ለንጉሡ መጠጦችን የሚያቀርብ ዋና ሰው ነው”” በዘፍጥረት 40: 2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

በሕልሜ እንሆ የወይን ዛፍ በፊቴ ሆና አየሁ
“በሕልሜ የወይን ጣፍ በፋቴ ሆና አየሁ!” የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ባየው ነገር እንደተደነቀና ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ለማሳየት “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል::

ዘለላዎችዋም በሰሉ
ዘለላዎችዋም ተንዠርግገው በሰሉ

ጨመቅሁአቸው
ከእነዚያ የጁስ ጭማቂ አወጣሁ ማለት ነው አት ከእነዚያ ጁስ ጨምቄ አወጣሁ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 40:12

የዚህ ትርጓሜ ይህ ነው
የሕልሙ ትርጓሜ ይህ ነው

ሶስቱ ሐረግ ሶስት ቀን ነው
ሶስት ሐረጐች ሶስት ቀኖች ያመለክታሉ

በሶስት ቀኖች ውስጥ
እስከ ሶስት ቀኖች

ራስህን ከፍ ከፍ ያደርጋል
እዚህ ፊርዖን ከእስር ቤት የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ የሚያወጣው ፈርዖን ከፍ ከፍ እንደሚያደርገው ተደርጐ ተነግሮአል:: አት “ከእስር ቤት ያወጣሃል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ወደ ቀድሞ ሹመትህ ይመልስሃል
ወደ ሥራህ ይመልስሃል

በነበርህበት ጊዜ
በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበረው

Genesis 40:14

ቸርነት አድርግልኝ
ቸር ሁንልኝ

ስለእኔም ለፈርዖን ንገርልኝና ከዚህም እስር ቤት አስወጣኝ
ዮሴፍም የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ስለእርሱ ለፈርዖን እንዲነግረው ከዚህም የተነሣ ፈርዖን ከእስር ቤት እንዲያስወጣው ማለት ነው:: አት: “ስለእኔ ለፈርዖን በመንገር ከእስር ቤት እንዲወጣ እርዳኝ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በእርግጥ በአፈና ውስጥ ነኝ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በሃዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በእርግጥ ሰዎች አፍነው እምጥተውኛል” ወይም “በእርግጥ እስማኤላዊያን ይዘው አምጥተውኛል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የሃዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ከዕብራዊያን ምድር
ዕብራዊ ሰዎች ከሚኖሩበት ምድር

አሁንም ቢሆን እዚህ እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች ጥፋት ኖሮብኝ አይደለም
እናም ደግሞ እዚህ በግብጽ በሚርበት ጊዜ በእስር ቤት እንዲጣል የሚያደርገኝን ምንም ነገር አላደረግሁም

Genesis 40:16

የእንጀራ ቤት አዛዡም
ይህ ለንጉሡ ምግብ የሚያቀርብ መሪ ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: በዘፍጥረት 40:2 ይህ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::

እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ እናም
እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ እናም በሕልሜ

እነሆም ሶስት መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር
ሶስተ መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር! እዚህ የእንጀራ ቤቱ አዛዡ “እነሆ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ባየው ሕልም መገረሙንና ዮሴፍም ትኩረት እንዲሰጠው ለማሳየት ነው::

ለፈርዖን ከተዘጋጀው እንጀራ
ለፈርዖን ከተዘጋጀው ምግብ

Genesis 40:18

ፍቺው ይህ ነው
የሕልሙ ትርጉም ይህ ነው

ሶስቱ መሶቦች ሶስት ቀኖች ናቸው
ሶስት መሶቦች ሶስት ቀኖችን ይወክላሉ

ራስህን ከፍ ያደርጋል
ዮሴፍ በዘፍረት 40:13 ለመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ በሚናገርበት ጊዜ ደግሞ ራስህን ከፍ ያደርጋል የሚለውን ሀረግ ተጠቅሞአል እዚህ ግን የተለየ ትርጉም አለው አማራጭ ተገቢ ትርጉሞች: (1) በአንገትህ ገመድ በማሠር ራስህን ከፍ ያደርጋል ወይም (2) ራስህን በመቁረጥ ከፍ ያደርግሃል::

ሥጋ
የ “ሥጋ” ቀጥታ ትርጉሙ የአንድ ሰው አካል ክፍል ማለት ነው

Genesis 40:20

እንዲህም ሆነ በሶስተኛውም ቀን
ከዚያም በኋላ በሶስተኛውም ቀን እዚህ እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ የተጠቀመው አዲስ ክስተትን ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ግብር አበላ
ግብዣ ነበረው

የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ
ይህ ለንጉሡ መጠጥን የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ መሪ ሰው ነበር። በዘፍጥረት 40፡2 እነዚህ ቃላት እንዴት እንደተተረጐሙ ይመልከቱ፡

የእንጀራ ቤት አዛዡን
ይህ ለንጉሡ ምግብን የሚያዘጋጅ መሪ ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: በዘፍጥረት 40:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ ሹመቱ መለሰው
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሹመት ወይም ኃላፊነት እንደመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሥራው እንደሆነ ያመለክታል አት ለመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሥራውን መልሶ ሰጠው (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ነገር ግን የእንጀራ ቤት አዛዡን ሰቀለው
ፈርዖን ራሱ አልሰቀለውም ይሁን እንጂ እንዲሰቀል አዘዘ አት የእንጀራ ቤት አዛዡ እንዲሰቀል አዘዘ ወይም ዘበኞቹ ወይም ጥበቃዎቹ የእንጀራ ቤት አዛዡን እንዲሰቅሉ አዘዘ (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ልክ ዮሴፍ እንደተረጐመላቸው
ይህ ዮሴፍ ሕልማቸውን እንደተረጐመላቸው የሚለውን ያመለክታል አት የሁለቱን ሰዎች ሕልም ዮሴፍ እንደተረጐመላቸው እንዲሁ ሆነ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Chapter 41

1 ድፍን ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ፈርዖን ሕልም ዐለም፤ ሕልሙም በዓባይ ወንዝ ዳር ቆሞ ነበር፤ 2 እነሆ፣ መልካቸው ያማረ፣ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች
ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ይበሉ ጀመር። 3 ቀጥሎም መልካቸው የከፋ አጥንታቸው የወጣ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው
አስቀድመው ከወጡት ላሞች አጠገብ ቆሙ። 4 እነዚህ መልካቸው የከፋና አጥንታቸው የወጣ ላሞች፥ እነዚያን ያማሩና የወፈሩ ላሞች ሲውጡአቸው ዐየ፤
ከዚያም ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ። 5 ፈርዖንም እንደገና እንቅልፍ ወስዶት ሳለ ሌላ ሕልም ዐየ። በሕልሙም በአንድ የእህል አገዳ ላይ ሰባት የዳበሩና ያማሩ የእሸት
ዛላዎች ዐየ፤ 6 ቀጥሎም የቀጨጩና ከበረሐ በተነሣ የምሥራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁ ሰባት የእሸት ዛላዎች ወጡ። 7 የቀጨጩት የእሸት ዛላዎች፤ ሰባቱን
የዳበሩና ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዋጡአቸው፤ በዚህ ጊዜ ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ፣ ነገሩ ሕልም ነበር። 8 በነጋታውም ፈርዖን መንፈሱ ታወከበት፣ ስለዚህ በግብፅ
አገር ያሉትን አስማተኞችና ጥበበኞች በሙሉ አስጠርቶ ሕልሞቹን ነገራቸው፣ ይሁን እንጂ፣ ሕልሞቹን ሊተረጉምለት የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም። 9 በዚያን
ጊዜ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ “የሠራሁት በደል ዛሬ ታወሰኝ። 10 ፈርዖን ሆይ! አንተ በእኔና በእንጀራ ቤት ኀላፊው ላይ ተቆጥተህ
በዘበኞች አለቃ ቤት እንድንታሰር አድርገህ ነበር፤ 11 በዚያ ሳለን በአንድ ሌሊት ሁለታችንም የተለያየ ሕልም ዐየን፤ የእያንዳንዳችንም ሕልም የተለያየ ትርጒም
ነበረው። 12 በዚያን ጊዜ የዘበኞች አለቃ አገልጋይ የሆነ አንድ ዕብራዊ ወጣት ከእኛ ጋር እስር ቤት ነበር። ሕልማችንን በነገርነው ጊዜ፣ ፍቺውን ነገረን፤
ለእያንዳንዳችንም እንደ ሕልማችን ተረጐመልን፤ 13 ነገሩም ልክ እርሱ እንደተረጐመልን፤ እኔ ወደ ቀድሞ ሹመቴ ተመለስሁ፤ የእንጀራ ቤት አዛዡም ተሰቀለ። 14
ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ትእዛዝ ሰጠ፤ ከእስር ቤትም በጥድፊያ ይዘውት መጡ፤ ጠጕሩንም ከተላጨና ልብሱን ከለወጠ በኋላ ፈርዖን ፊት ቀረበ 15
ፈርዖንም ዮሴፍን፣ “ሕልም ዐይቼ ነበር፣ ሕልሜን ሊተረጉምልኝ የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም፣ አንተ ግን ሕልም ሲነገርህ የመተርጐም ችሎታ እንዳለህ ሰማሁ”
አለው። 16 ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ ብሎ መለሰ፦ “ይህ በእኔ አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን ለፈርዖን በበጎነት ይመልስለታል” 17 ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ
አለው፤ “ሕልሜ በዓባይ ወንዝ ዳር ቆሜ ነበር። 18 ሥጋቸው የወፈረና መልካቸው የማረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ሲበሉ
ዐየሁ። 19 ከእነርሱም በኋላ ዐቅመ ደካማ፣ መልካቸው እጅግ የከፋና አጥንታቸው የወጣ ሌሎች ሰባት ላሞች ወጡ፤ እነዚያን የመሰሉ የሚያስከፋ መልክ
ያላቸው ላሞች በግብፅ ምድር ከቶ ዐይቼ አላውቅም። 20 አጥንታቸው የወጣና አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች መጀመሪያ የወጡትን፣ ሥጋቸው የወፈረውን
ሰባቱን ላሞች ዋጧቸው። 21 ከዋጧቸውም በኋላ፣ ያው የበፊቱ መልካቸው ስላልተለወጠ እንደዋጧቸው ማንም ሊያውቅ አይችልም ነበር፤ ከዚያም ከእንቅልፌ
ነቃሁ 22 ደግሞም በአንድ የእህል አገዳ ላይ ሰባት የዳበሩና ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዐየሁ፤ 23 ቀጥሎም የቀጨጩና የደረቁ ሌሎች ሰባት ዛላዎች ወጡ። 24
የቀጨጩት የእሸት ዛላዎችም ሰባቱን ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዋጧቸው፤ ያየኋቸውንም ሕልሞች ለአስማተኞች ነገርሁ፣ ነገር ግን ሕልሞቹን ማንም ሊተረጉምልኝ
አልቻለም።” 25 ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ አለው፤ “ሁለቱም የፈርዖን ሕልሞች ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ናቸው፤ እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን ለፈርዖን
ገልጦለታል። 26 ሰባቱ የሚያምሩ ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው፣ ሰባቱም የሚያማምሩ የእሸት ዛላዎች ሰባት ዓመታት ናቸው፤ ሕልሙም አንድና ተመሳሳይ ነው።
27 ከእነርሱም በኋላ አጥንታቸው የወጣ አስከፊ መልክ ያላቸው ሰባት ላሞች፣ ሰባት ዓመታት ናቸው፤ እንደዚሁም ፍሬ አልባ የሆኑትና በምሥራቅ ነፋስ
ተመትተው የደረቁት ሰባት የእሸት ዛላዎች ሰባት የራብ ዓመታት ናቸው። 28 አስቀድሜ ለፈርዖን እንደተናገርሁት እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን ነገር
ለፈርዖን ገልጦለታል። 29 በመላው የግብፅ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ። 30 በዚህ በኋላ ግን በተከታታይ ሰባት
የራብ ዓመታት ይሆናሉ። የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለሚጎዳት በግብፅ የነበረው ያለፈው የጥጋብ ዘመን ሁሉ ጨርሶ አይታወስም። 31 ከጥጋብ ዓመታት
በኋላ የሚመጣው የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ፣ ቀደም ሲል የነበረው የጥጋብ ዘመን ፈጽሞ ይረሳል። 32 ሕልሙ ለፈርዖን በድጋሚ መታየቱ፣ ነገሩ
ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ ስለሆነ ነው፤ ይህንንም እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ይፈጽመዋል፤ 33 እንግዲህ ፈርዖን ብልኅና አስተዋይ ሰው ፈልጎ፣ በመላው
የግብፅ ምድር ላይ አሁኑኑ ይሹም። 34 እንደዚሁም በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት፣ አንድ አምስተኛው እንዲሰበሰብ የሚያደርጉ ኀላፊዎችን
ይሹም። 35 እነርሱም በሚመጡት የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት ሁሉ ይሰብስቡ፤ በፈርዖንም ሥልጣን ሥር ያከማቹ፤ ለምግብ እንዲሆኑም በየከተማው
ይጠበቁ። 36 የሚከማቸው እህል፣ ወደፊት በግብፅ አገር ላይ ለሚመጣው የሰባት ዓመት ራብ መጠባበቂያ ይሁን፤ በዚህም ሁኔታ አገሪቱ በራብ አትጠፋም።
37 ዕቅዱም ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ መልካም ሆኖ አገኙት። 38 ፈርዖንም፣ “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት እንደዚህ ያለ ሰው ልናገኝ እንችላለን?” ብሎ
ጠየቃቸው። 39 ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፣ “እግዚአብሔር ይህን ሁል ገለጠለህ እንዳንተ ያለ አስተዋይና ብልህ ሰው የለም። 40 አንተ በቤተ መንግሥቴ
የበላይ ትሆናለህ፤ ሕዝቤም ሁሉ ለሥልጣንህ ይገዛል፤ እኔ ከአንተ የምበልጠው በዙፋኑ ብቻ ይሆናል።” 41 ከዚያም፣ ፈርዖን ዮሴፍን፣ “በመላይቱ የግብፅ
ምድር ላይ ኀላፊ አድርጌሃለሁ” አለው። 42 ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት ከጣቱ አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገው፤ እንዲሁም ከጥሩ የተልባ እግር
የተሠራ ልብስ አለበሰው፤ በአንገቱም የወርቅ ሐብል አጠለቀለት። 43 በማዕረግ ከእርሱ ሁለተኛ ሰው አድርጎ በሠረገላ ላይ አስቀመጠው። ሰዎችም በፊቱ፣
“እጅ ንሡ” እያሉ ይጮኹ ነበር፤ በዚህ ሁኔታም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾመው። 44 ከዝህ በኋላ ፈርዖን ዮሴፍን፣ “እኔ ፈርዖን ነኝ፤ ሆኖም በመላይቱ ግብፅ
ያለ አንተ ፈቃድ ማንም ሰው እጁን ወይም እግሩን ማንቀሳቀስ አይችልም” አለው። 45 ፈርዖን ዮሴፍን ጸፍናት ፐዕናህ ብሎ ስም አወጣለት። እንዲሁም አስናት
ተብላ የምትጠራውን ኦን ተብሎ የሚጠራው ከተማ ካህን የጶጢፌራን ልጅ በሚስትነት ሰጠው። 46 ዮሴፍ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንን ማገልገል ሲጀምር፣
ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር። ዮሴፍም ከፈርዖን ፊት ወጥቶ የግብፅን ምድር በሙሉ ዞረ። 47 በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ምድሪቱ የተትረፈረፈ ሰብል ሰጠች።
48 በእነዚያ ሰባት የጥጋብ ዓመታት፣ ዮሴፍ በግብፅ አገር የተገኘውን ምርት ሰብስቦ በየከተሞቹ አከማቸ፣ በእያንዳንዱ ከተማ ከየአቅራቢያው የተመረተውን
እህል እንዲከማች አደረገ። 49 ዮሴፍ ብዛቱ እንደ ባሕር አሸዋ የሚሆን የእህል ሰብል አከማቸ፤ ሰብሉ እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ ልኩን መስፈርና መመዝገብ
አልቻለም ነበር። 50 ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመምጣታቸው በፊት የኦን ከተማ ካህን የጶጢፌራ ልጅ አስናት ለዮሴፍ ሁለት ወንድ ልጆች ወለደችለት። 51
ዮሴፍም፣ “እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአባቴንም ቤት እንድረሳ አድርጎኛል” በማለት የመጀመሪያ ልጁን ስም ምናሴ አለው። 52 እንደዚሁም “መከራ
በተቀበልሁበት ምድር እግዚአብሔር ፍሬያማ አደረገኝ” ሲል ሁለተኛ ልጁን ኤፍሬም አለው። 53 በግብፅ ምድር የነበረው ሰባቱ የጥጋብ ዘመን አለፈና 54
ዮሴፍ አስቀድሞ እንደተናገረው የሰባቱ ዓመት የራብ ዘመን ጀመረ። ሌሎች አገሮች ሁሉ ሲራቡ፣ በመላው የግብፅ ምድር መስፋፋት ሲጀመር፣ 55 ሕዝቡ ምግብ
ይሰጠን በማለት ወደ ፈርዖን ጮኹ። ፍርዖንም ግብፃውያኑን፣ “ወደ ዮሴፍ ሂዱና የሚላችሁን አድርጉ” አላቸው። 56 ራቡ በአገሩ ላይ እየተስፋፋ ስለሄደ፣ ዮሴፍ
ጎተራዎቹን ከፍቶ እህሉ ለግብፃውያን እንዲሸጥ አደረገ፤ ምክንያቱም ራቡ በመላይቱ ግብፅ ጽንቶ ነበር። 57 ራቡ በመላው ዓለም ጽንቶ ስለነበር፣ የየአገሩ ሰዎች
ሁሉ ከዮሴፍ ዘንድ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ምድር መጡ።

Genesis 41:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ያን ሊጠቀሙ ይችላሉ (አዲስ ክስተትን ማስታወቅ ይመልከቱ)

ድፍን ሁለት ዓመታት ካለፈ በኋላ
በእስር ቤት ከዮሴፍ አብረውት ስለነበሩት የፈርዖን መጠጥ አሳላፊዎች አለቃና እንጀራ ቤት አዛዥ ሕልሞችን ዮሴፍ ከተረጐመላቸው ሁለት ዓመታት ካለፉ በኋላ

እነሆም ቆሞ ነበር
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል በሰፊው ታሪክ ሌላ ክስተት መጀመሩን ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ሊኖር ይችላል። አት "ቆሞ በመገኘቱ ገርሞት ነበር"

ቆሞ ነበር
ፈርዖ ቆሞ ነበር

መልካምና የወፈሩ
ጤናማና የወፈሩ

በውሃውም ዳር ባለው ቀጠማ ተሰማርተው ነበር
በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ይበሉ ነበር

ቀጤማ
በረግረጋማ ቦታ የሚበቅል ቀጭንና ረጅም ሣር ነው

እነሆ ሌሎች ሰባት ላሞች
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈረዖን እንደገና ባየው ነገር እንደተገረመ ያሳያል

የከፉና የከሱ
ታማሚና የከሱ

ወንዝ ዳር
"በወንዝ ዳር" ወይም "ወንዝ ዳረቻ ላይ" ይህ በአንድ ወንዝ ዳር ጠርዝ የሚገኝ ከፍታ ያለው መሬት ማለት ነው::

Genesis 41:4

የከፉና የከሱ
"ደካማና የከሱ" በዘፍጥረት 41:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

መልካምና የወፈሩ
"ጤናማና የደለቡ ወይም በደንብ የበሉ" በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ነቃ
ከእንቅልፉ ነቃ

ሁለተኛ ጊዜ
"ሁለት" የሚለው ቃል ተራ ቁጥር ሁለት ነው:: አት "እንደገና" (ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

እነሆ ዛላዎች
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈርዖን ባየው ነገር እንደተገረመ የሚያሳይ ነው

የእሸት ዛላዎች
ዛላዎች ፍሬዎች የሚንዠረግጉበት የበቆሎ ተክል አካል ነው

በአንድ የእህል አገዳ ላይ
"በአንድ አገዳ ላይ ያፌራውን ወይም የተንዠረገገውን" አገዳ ወፍራምና ረጅም የተክል ክፍል ነው::

በአንዱ አገዳ ላይ የተንዠረገገና ያማረ
በአንድ አገዳ ጤናማና ያማረ

የቀጨጨና በምሥራቅ ንፋስ የተመቱ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: "ያም ከምሥራቅ ደረቅ አየር የትነሳ የቀጨጨና በዋግ የተመቱ" (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የምሥራቅ ንፋስ
የምሥራቅ ንፋስ ከረሃማ ተነሥቶ የሚነፍስ ነው። የምስራቅ ንፋስ ሙቀት እጅግ ጐጂ ነው።

ዛላዎች ወጡ
ዛላዎች አደጉ ወይም ተንዠረገጉ

Genesis 41:7

የቀጨጩ የእሸት ወይም የእህል ዛላዎች
እህል የተባለው ቃል የታወቀ ነው:: አት "የቀጨጩ የእህል ዛላዎች" (የተደበቁ ቃላትን የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ዋጡአቸው
በሉአቸው ሰው ምግብን እንደሚበላ የቀጨጩ የእሸት ዛላዎች ጤናማ የእሸት ዛላዎች ሲውጡ ፈርዖን በሕልሙ አየ

ሙሉና ፍሬያቸው የተንዠረገገውን የእሸት ዛላዎች
ጤናማና መልካም የእሸት ዛላዎች

በዘፍጥረት **41:5** የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ነቃ
ከእንቅልፉ ነቃ

እነሆ
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈርዖ ባየው ነገር እንደተገረመ ያሳያል

ሕልም ነበር
ሕልም ሲያልም ነበር

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው:: በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ:: (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይጠቀሙ)

መንፈሱ ታወከበት
እዚህ መንፈሱ የሚለው ቃለ የውስጥ ማንነቱን ወይም ስሜቱን ያመለክታል አት "በውስጥ ማንነቱ ታወከ" ወይም "ታወከ" (ተመሣሣይ ምትክ ቃል ስለመጠቀም ይመልከቱ)

ልኮና አስጠርቶ
አገልጋዮቹን እንደላካቸው መረዳት ይቻላል:: አት "እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላካቸው ወይም አገልጋዮቹ እንደጠሩ አዘዛቸው" (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የግብጽ አስማተኞችንና ጥበበኞች
የጥንት ነገሥታት አስማተኞችንና ጥበበኞችን እንደአማካሪዎች ይጠቀሙ ነበር

Genesis 41:9

የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ
ይህ ለንጉሡ መጠጥን የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ መሪ ሰው ነበር። በዘፍጥረት 40፡2 እነዚህ ቃላት እንዴት እንደተተረጐሙ ይመልከቱ፡

የሠራሁት በደል ዛሬ ታወሰኝ
ዛሬ የሚለው ቃል የተጠቀመው አስንዎት ለመስጠት ነው በደሉ ቀደም ብሎ ለፈርዖን መናገር የነበረበት አንድ ነገር ነገር ግን ያልተናገረበት ነው:: አት “ለአንተ መናገር የረሳሁትን አሁን አስታወስኩ”

ፈረዖን ተቆጥቶ ነበር
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ፈርዖንን አንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ያመለክታል ይህም አነስተኛ ኃላፊነት ያለው ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው የሚያስቀምጥበት የተለመደ መንገድ ነው እርስዎ ፈርዖን ተቆጥተው ነበር (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ከእርሱ አገልጋዮች ጋር
እዚህ እርሱ ፈርዖንን ያመለክታል አገልጋዮች የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዥ ያመለክታል:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን በዘበኞች አለቃ ግቢ አስሮን ነበር
እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን በዘበኞች አለቃ ኃላፊነት በተሰጠው እስር ቤት እስሮን ነበር:: እዚህ “ቤት” እስር ቤትን ያመለክታል::

የዘበኞች አለቃ
ንጉሡ ጠባቂዎች ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ወታደር ነው በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የእንጀራ ቤት አዛዥ
ለንጉሡ ምንብን የሚያዘጋጅ ዋና አስፈላጊ ሰው ነው። በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እርሱና እኔ በአንዲት ሌሊት ሕልም አየን
“እኛ ሁለታችን በአንድ ሌሊት ሕልም አለምን” እዚህ እኛ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃንና እንጀራ ቤት አዛዡን ያመለክታል (ነጠላና ብዙ እኛ ይመልከቱ)

የእያንዳንዳችን ሕልም የራሱ የሆነ ትርጉም ነበረው
ሕልሞቻችን የተለያየ ትርጉም ነበራቸው

Genesis 41:12

አጠቃላይ መረጃ
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ለፈርዖ መናገሩን ቀጠለ

ከእኛ ጋር ነበር
በእስር ቤት ከእንጀራ ቤት አዛዥና ከእኔ ጋር ነበር

የዘበኞች አለቃ
ንጉሡ ጠባቂዎች ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ወታደር ነው በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ሕልሞቻችንን በነገርነው ጊዜ ፊቺውን ነገረን
ሕልሞቻችንን ነገርነው እናም እርሱ ትርጉምቻቸውን ነገረን

ለእያንዳንዳችን እንደሕልማችን ተረጐመልን
እዚህ እርሱ ወይም እያንዳንዱ የሕልሙ ተርጓሚውን ሳይሆን የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃንና የእንጀራ ቤት አዛዥ በግል የሚያመለክት ነው አት ለእያንዳንዳችን ምን ሊሆን እንዳለ አስረዳን (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አጠቃቀም ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የሚችሉበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ

እርሱ እንደተረጐመልን ሆነ
ስለሕልሞቻችን እንደነገረን ሆነ

ፈርዖን ወደ ሹሜቴ መለሰኝ
እዚህ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ማከበሩን ለመግለጽ የፈርዖን የማዕረግ ስም ይጠቀማል:: አት ወደ ሥራዬ እንዲመለስ ፈቀድክልኝ (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እርሱን ወይም ሌላኛውን
የእንጀራ ቤት አዛዡን

እርሱ ሰቀለው
እዚህ እርሱ ፈርዖንን ያመለክታል እና ይህም የእንጀራ ቤት አዛዡን እንዲሰቅሉት ፈርዖን ወታደሮቹን ማዘዙን ይወክላል አት እንዲሰቀል እርስዎ ወታደሮችዎን አዝዘዋል:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽና ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ

Genesis 41:14

ፈርዖንም ሊኮ አስጠራ
ፈርዖን አገልጋዮቹን እንደላከ ይታወቃል አት ዮሴፍን እንዲያመጡት አገልጋዮችን ላከ (የተደበቁ ቃሎችን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ከግዞት ቤት
“ከእስር ቤት” ወይም “ከወህኒ”

ጸጉሩን ከተላጨ
በፈርዖን ፊት ለመቅረብ በመዘጋጀት ጊዜ የፊትና የራስ ጸጉርን መላጨት የተለመደ ተግባር ነበር

ፈርዖን ፊት መጣ
እዚህ መጣ የሚለው ገባ በሚለው ሊገለጽ ይችላል አት ፈርዖን ፊት ገባ (መጣ እና ገባ ይመልከቱ)

የሚተረጉመውም አልተገኘም
ሊተረጉምልኝ የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም

አንተ የመተርጐም ችሎታ አለህ
አንተ ትርጉሙን ሊትነግረኝ ትችላለህ

ይህ በእኔ አይደለም
እኔ የመተርጐም ችሎታ የለኝም

እግዚአብሔር በደኅንነት ለፈርዖን ይመልስለታል
እግዚአብሔር ለፈርዖን የሚሻውን ትርጉም ይሰጠዋል

Genesis 41:17

እነሆ ቆሜ ነበር
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

በዐባይ ወንዝ ዳር
በዐባይ ወንዝ ዳርቻ የለውን ከፍታ የለውን መሬት ያመለክታል:: በዘፍጥረት 41:3 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት "በዐባይ ወንዝ ዳር"

እነሆ ሰባት ላሞች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን "እነሆ" የሚለውን ቃል ይጠቀማል

የወፈሩና ያማሩ
"የተቀለቡ/የደለቡና ጤናማ" በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

በቀጠማዎች ውስጥ ወይም በመስኩ ይሰማሩ ነበር
በወንዙም ዳር ያለውን ሣር ይመገቡ ነበር:: በዘፍጥረት 41:2 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።

Genesis 41:19

እነሆ ሰባት ሌሎች ላሞች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን "እነሆ" የሚለውን ቃል ይጠቀማል

የከፉና የከሱ
አቅሜ ደካሞችና የከሱ ወይም የቀጨጩ በዘፍጥረት 41:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

እንደዚህ የሚያስከፉ
"አስከፊ" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጐም ይችላል:: አት "የሚያስከፉ ላሞች" ወይም "የማይጠቅሙ የሚመስሉ ላሞች" (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

የወፈሩ ላሞች
"የደለቡ ወይም የተቀለቡ ላሞች" በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እንደዋጧቸው ምንም ሊታወቅ አይችልም ነበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "የከሱ ላሞች የወፈሩትን መዋጣቸውን ማንም ሊነግረው እስከማይችል ነበር:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 41:22

አጠቃላይ መረጃ
ፈርዖን ሕልሙን ለዮሴፍ መናገሩን ቀጠለ

በሕልሜ አየሁ
ይህ ፈርዖን ከነቃና ተመልሶ ከተኛ በኋላ ያየውን ሕልም ይጀምራል። አት "እንደገናም ሕልም አለምሁ" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እነሆ ሰባት የእሸት ዛላዎች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን "እነሆ" የሚለውን ቃል ይጠቀማል::

ሰባት የእሸት ዛላዎች
የእሸት ወይም የእህል የሚለው አባባል የታወቀ ነው:: አት "ሰባት የእህል ዛላዎች" (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

በአንድ አገዳ ሲወጡ
"በአንድ አገዳ ሲንዠረግጉ" አገዳ ወፍራምና ረጅም የተክል አካል ነው:: በዘፍጥረት 41:5 ይህን ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

እነሆ ሰባት ሌሎች የእሸት ዛላዎች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን "እነሆ" የሚለውን ቃል ይጠቀማል::

የጠወለጉ
የደረቁና ፍሬ አልባ የሆኑ

በምሥራቅ ነፋስ
"ከበረሃማ ቦታ የሚነፍሰው የምሥራቅ ንፋስ" የምሥራቁ ንፋስ ሙቄት አብዛኛውን ጊዜ ለእህሎች እጅግ አደገኛ ነበር::

ተንዠረገገ
አደገ ወይም ፍሬ ሰጠ

የቀጨጩ የእሸት ወይም የእህል ዛላዎች
የእህል የሚለው ቃል የታወቀ ነው በዘፍጥረት 41:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ አት የቀጨጩ የእህል ዛላዎች (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ዋጧቸው
"በሉ" ፈርዖን ያለመው ሕልም ሰው ምግብን እንደሚበላ ጤናማ ያልሆኑ የበቀሉ እህሎች ጤናማ ያልሆኑትን እንደበሉ ነው:: በዘፍጥረት 41:7 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

የሚችል ማንም አልተገኘም
የሚችል አንድም አልተገኘም ወይም ማንም አልቻለም

Genesis 41:25

የፈርዖን ሕልሞች ተመሣሣይ ናቸው
ትርጉሞችም ተመሣሣይ ናቸው የሚል አንድምታ አለው:: አት "ሁለቱም ሕልሞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ለፈርዖን አስታወቀው
ዮሴፍ ፈርዖንን እንደሳስተኛ ወገን ሰው ያናግረዋል ይህ አክብሮትን መግለጫ መንገድ ነው:: እንደ ሁለተኛ ወገን ሰው መግለጽ ይቻላል:: አት "ቶሎ ሊያደርግ ያለውን እያሳየህ ነው" (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 41:27

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም መተርጐም ይቀጥላል።

የከሱና አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች
የቀጨጩና ዐቅሜ ደካማ ላሞች በዘፍጥረት 41:3 የዚህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

በምሥራቅ ነፋስ የተመቱ ሰባት የቀጨጩ የእሸት ዛላዎች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "ከምሥራቁ ሙቀት አዘል ነፋስ የተነሣ የቀጨጩ ሰባት የእህል ዛላዎች" (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይህን ለፈርዖን የተናገርኩትን ... ለፈርዖን ገልጦለታል
ዮሴፍ ፈርዖንን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ያናግረዋል ይህም አክብሮች መግለጫ መንገድ ነው:: በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ልገለጽ ይችላል:: "እንደተናገርኩህ እነዚህ ይደረጋሉ...... ፈርዖን ለአንተ ገልጦልሃል" (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እይ ሰባት
“እኔ የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነውና ትኩረት ስጥ፤ ሰባት”

በመላው የግብጸ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ
ጊዜ እንደሚመጣና በወቅቱ በአንድ ቦታ እንደሚሆን ይህ ስለጥጋብ ዓመታት ይናገራል:: አት “የተትረፈረፈ ምግብ በግብጽ በመላው የግብጽ ምድር የሚሆንበት ሰባት ዓመታት ይመጣሉ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 41:30

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልሞች መተርጐም ቀጠለ

ከዚህ በኃላ ሰባት የራብ ዓመታት ይሆናሉ
ወደ አንድ ቦታው ተንቀሳቅሶ እንደሚመጣ ነገር ተደርጐ ስለ ሰባት ዓመታት ራስ ተነግሮአል አት ከዚም በኋላ እጅግ ጥቂት ምግብ የሚሆንበት ሰባት ዓመታት ይሆናሉ (ዘይቤይዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለሚጐዳት ... የጥጋቡ ዘመን ሁለ ጨርሶ አይታወስም::
....የሚመጣው የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ የጥጋብ ዘመን ፈጽም ይረሳል:: ዮሴፍ ለጉዳዩ አጽንዖት ለመስጠት አንድን ሀሳብ በሁለት መንገድ ይገልጻል (ተመሣሣይ ተጓዳኝ አባባሎችን ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር የጥጋብ ዘመን ሁሉ ይረሳል
ምድር ሰዎችን ያመለክታል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የግብጽ ሰዎች የተትረፈረፈ ምግብ የነበረበትን ዓመታት ሁሉ ይረሳሉ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤና ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አገሪቱን ይጐዳሉ
አገር የሚለው የአገሪቷን መሬት ሰዎችና መላውን የአገሪቷን አካል ያመለክታል (ምትክ ቃላትን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ከሚመጣው ራብ የተነሣ
ይህ ተከትሎ እንደሚመጣ እንደ አንድ ነገር ስለሚመጣው ራብ ወይም ድርቅ ይናገራል። አት “ከዚያ በኋላ በሚሆነው ራብ ወይም ድርቅ የተነሣ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሕልሙ ለፈርዖን በሁለት መልክ በድጋሚ መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለሆነ ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እግዚአብሔር ሁለት ሕልሞችን የሰጠህ ነገሮች በእርግጥ እንደሚከሰቱ ለማሣየት ነው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 41:33

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ ለፈርዖን መናገሩን ቀጠለ

አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ስለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

እንግዲህ ፈርዖን ... ይፈልግ
ዮሴፍ ለፈርዖን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ይናገራል ይህ አክብሮትን የመግለጫ መንገድ ነው በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንተ ፈርዖን ፈልግ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር ላይም ይሹመው
ይሹመው ማለት ኃላፊነት ይስጠው ማለት ነው። አት “በግብጽ ግዛት ላይ ኃላፊነት ይስጠው ወይም በግብጽ ግዛት ላይ ይሹመው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የግብጽ ምድር
እዚህ ምድር በግብጽ ምድር ያሉ ሰዎችንና ሁሉን ነገር ይወክላል (ተመሣሣይ ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልቱ)

በግብጽ ምድር ከሚገኘው የእህል ምርት አንድ አምስተኛውን ይውሰዱ
አምስተኛ የሚለው ቃል ክፍልፋይ ነው:: የግብጽን ምድር እህል ምርት በአምስት መደብ ይክፈሉ፤ ከዚያም አንዱን እጅ ወይም መደብ ይውሰዱ (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ)

በሰባት የጥጋብ ዓመታት
የተትረፈረፈ ምግብ ባለባቸው ሰባት ዓመታት

Genesis 41:35

አጠቃላይ መረጃ
ፈርዖንን መምከሩን ቀጠለ

እነርሱም ይሰብስቡ
ሹማምንት ወይም ኃላፊዎች እንዲሰበስቡ ይደረግ

በእነዚህ በሚመጡት ጥጋብ ዓመታት
እነዚህ ዓመታት አንድ ነገር ተጉዞ ወደ አንድ ቦታ እንደማመጣ እንደሚመጡ ይናገራል:: አት “ቶሎ ሊመጡ ያሉ የጥጋብ ዓመታት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በፈርዖን ሥልጣን ሥር ያከማቹ
በፈርዖን ሥልጣን ሥር የሚለው ሀረግ ፈርዖን ሥልጣን ይስጣቸው ማለት ነው አት እህሉን ለመሰብሰብ የፈርዖንን ሥልጣን ይጠቀም ፈሊጣዊ አነገር ይመልከቱ

እነርሱም ይህን ይጠብቁ
እነርሱ የሚለው ቃል እህሉ እንዲጠበቅ የሚያዝዙ ሹማምንቶችንና ወታደሮች ያመለክታል አት ሹማምቶች እህሉ እንዲጠበቅ በዚያው ወታደሮችን ይመድቡ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ

እህሉ ለምድሪቱ ምግብ ይሆናል
ምድሪቱ ሰዎችን ትወክላለች አት እህሉም ለሰዎች ምግብነት ይሆናል (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)

በዚህ ሁኔታ ምድሪቱ በራብ አትጠፋም
እዚህ “ምድር” ሰዎችን ይወክላል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት “በዚህ መንገድ በራብ ጊዜ ሰዎች አይራቡም” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ወይም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 41:37

ይህ ምክር ለፈርዖንና በሎለዎቹ ፊት መልካም ሆነ
ፊት ማየትን የሚያመለክት ሲሆን ማየት ማሰብን ወይም ብያኔን ያመለክታል አት ፈርዖንና ሎሌዎቹ ይህ መልካም እቅድ ሆኖ አገኙት

ሎሌዎች
የፈርዖ ሹማምንት

እንደዚህ ያለ ሰው
ዮሴፍ የገለጸው ዓይነት ሰው

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት
የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርበት

Genesis 41:39

እንዳንተ ያለ ብልህ የለም
እንዳንተ ያለ ውሳኔ አቅራቢ የለም:: በዘፍጥረት 41:33 ብልህ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አንተ የቤተመንግሥቴ የበላይ ትሆናለህ
እዚህ "ቤት" የፈርዖን ቤተመንግሥትና በቤተመንግሥቱ ያሉ ሰዎችን ይወክላል:: የበላይ የሚለው ሀረግ ዮሴፍ የበላይ ኃላፊነት ይሰጠዋል ማለት ነው:: አት በቤተመንግሥቴ በሁሉም ላይ ሥልጣን ይሰጥሃል:: (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ዘይቤና ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሕዝቤ ሁሉ ለሥልጣኔ ይገዛል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል በሕዝቤ ላይ ገዥ ትሆናለህና አንተ የሚታዝዘውን ያደርጋሉ:: (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በዙፋኔ ብቻ
እዚህ ዙፋን ፈርዖን እንደንጉሥ ገዥ እንደሆነ ይገልጻል:: አት "በንጉሥነት ሚናዬ ብቻ"

እየው አድርጌሃለሁ
"እየው" የሚለው ቃል ፈርዖን በሚቀጥለው ለሚናገረው አጽንዖት ይሰጣል:: አት "እየው አድርጌሃለሁ"

በመላይቱ የግብጽ ምድር ላይ ኃላፊ አድርጌሃለሁ
የበላይ አድርጌሃለሁ ማለት ሥልጣን ሰጥቼሃለሁ ማለት ነው እዚህ ምድር ሰዎችን ያመለክታል አት በግብጽ ምድር ባለው በማንኛውም ላይ ኃላፊነት ሰጥቼሃለሁ (ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤና ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

Genesis 41:42

ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት አውልቆ .... የወርቅ ሐብል አጠለቀለት
እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የሚያመለክቱት ዮሴፍ ያቀደውን ሁሉ እንዲያደርግ ፈርዖን ለዮሴፍ ሥልጣን መስጠቱን ነው (ምልክታዊ ድርጊት የመልከቱ)

ባለማኅተሙ ቀለበት
ይህ ቀለበት የፈርዖን ማኅተም የተቀረጸበት ነው:: ይህም ያቀደውን እንዲያከናውን ለዮሴፍ ገንዘብና ሥልጣንን ሰጠው::

ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ልብስ
የተልባ እግር የተሠራ ልብስ ሰማያዊ አበባ ካለው የተልባ እግር የተሠራ ለስላሳ ጠንካራ ልብስ ነው::

የእርሱም በሆነው ሁለተኛው ሠረገላ ላይ አስቀመጠው
ይህ ድርጊት ለሰዎች ግልጽ የሚያደርገው የፈርዖን ሁለተኛ ሰው ዮሴፍ ብቻ መሆኑን ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ስገዱ ወይም እጅ ንሡ
ስገዱና ዮሴፍን አክብሩ እጅ መንሣትና መስገድ ክብርንና አክብሮትን የመስጠት ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ፈርዖን በምድሪቱ ባለው ማንኛውም ላይ ሾመው
ማንኛውም ላይ ሾመው የሚለው ሀረግ ሁሉ ላይ ስልጣን ሰጠው ማለት ነው:: እዚህ ምድር ሰዎችን ያመለክታል በዘፍጥረት 41:41 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት "በግብጽ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠሁ" (ፈሊጣዊ አነጋገርና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 41:44

እኔ ፈርዖን ነኝ ... ያለ አንተ
ፈርዖን የራሱን ሥልጣን አጽንቶ ይናገራል። አት "እንደ ፈርዖን እኔ የማዝዘው ያለአንተ"

ያላንተ ማንም እጁንም እግሩንም አያንሣ
እዚህ "እጅና እግር" የሰዎችን ድርጊቶች ይወክላሉ:: አት "ማንኛውም ሰው ምንም ነገር ያለፈቃድህ በግብጽ አያድርግ ወይም ማንኛውም ሰው ምንም ነገር በግብጽ ከማድረጉ በፊት ያንተን ፈቃድ ይጠይቅ" (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ማንም ሰው
እዚህ "ሰው" ወንድም ሆነ ሴት በአጠቃላይ ማንንም ሰው ያመለክታል:: (በወንድ ጾታ የተገለጹ ቃላት ለሴት ጾታም መሆናቸውን ይመልከቱ)

ጸፍናት ፐዕናህ
ተርጓሚዎች የሚከተውን በግርጌ ማስታወሻ ሊጠቀሱ ይችላሉ:: "ጸፍናት ፐዕናህ" የሚለው ስም "ሚስጢሮችን ገላጭ" ማለት ነው።

የሄልዮቱ ወይም ዖን ከተማ ካህን የጶጥፌራ ልጅ የሚትሆን አስናትን አጋባው
ጶጥፋራ የአስናት አባት ነው:: "ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ"

የሄልዮቱ ካህን
ዖን የጸሐይ አምላክ ራእ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና "የጸሐይ ከተማ" የነበረች እንዲሁም "ሄልዮቱ" ተብላ የሚትጠራ ከተማ ነች (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዮሴፍም በመላይቱ የግብጽ ምድር ተዘዋወረ
ሊመጣ ስላለው ያልታሰበ የድርቅ ጊዜ ዝግጅት ለማድረግ ዮሴፍ በመላይቱ የግሣብ ምድር ተዘዋወረ

Genesis 41:46

ሠላሳ ዓመት ዕድሜ
30 ዓመት ዕድሜ ቁጥሮችን ይመልከቱ

ዮሴፍም በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ
እዚህ በፊቱ መቆም ዮሴፍ ፈርዖንን ማገልገል መጀመሩን ያሳያል:: አት "ፈርዖንን ማገልገል በጀመረ ጊዜ" (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

በመላይቱ የግብጽ ምድር ተዘዋወረ
ዮሴፍ ዕቅዱን ለማከናወን ዝግጅት ሲያደርግ አገሪቱን በጥንቃቄ እንደመረመረ ነው

በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት
በሰባቱም መልካም ዓመታት

ምድሪቱ የተትረፈረፈ ሰብል ሰጠች
ምድራቱ ብዙ እህል አመረተች

Genesis 41:48

እርሱም ምርት ሰብስቦ .... አከማቸ
እዚህ "እርሱ" የዮሴፍን አገልጋዮች ያመለክታል:: አት "ዮሴፍ አገልጋዮቹ እንዲሰበስቡ አዘዘ .... አከማቹ (ከፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የሴፍ እንደ ባሕር አሸዋ እጅግ ብዙ እህል አከማቸ
የእህሉን እጅግ መብዛት በአጽንዖት ለመናገር ከባሕር አሸዋ ጋር ያነጻጽራል። አት “ዮሴፍ ያከማቸው እህል ባህር ዳር እንዳለ አሸዋ እጅግ ብዙ ነበር” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዮሴፍ አከማቸ **….** እርሱም አቆመ
እዚህ ዮሴፍ እና እርሱ የዮሴፍን አገልጋዮች ይወክላል:: አት “ዮሴፍ አገልጋዮቹ እንዲያከማቹ አደረገ … እነርሱም አቆሙ” (ከፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 41:50

የራብ ዓመታት ከመምጣታቸው በፊት
ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመምጣቱ በፊት ይህም አንድ ነገር ተጉዞ ወደ አንድ ቦታ እንደሚመጣ ተደርጐ ስለሚመጡ ዓመታት ይናገራል:: አት “ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመጀመራቸው በፊት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አስናት
የአንዲት ሴት ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የዖን ካህን
ዖን የጸሐይ አምላክ ራአ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና “የጸሐይ ከተማ” የሆነች እንዲሁም “ሄልዮቱ” ተብላ የሚትጠራ ከተማ ነች። በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ምናሴ
ተርጓሚዎች የሚከተለውን በግርጌ ማስታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: “ሚናሴ” የሚለው ስም ለመርሳት ምክንያት መሆን ማለት ነው::

የአባቴንም ቤት
ይህ የዮሴፍ አባት ያዕቆብንና ቤተሰቡን ያመለክታል

ኤፍሬም
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: “ኤፍሬም” የሚለው ስም “ፍሬያማ መሆን” ወይም “ልጆችን መውለድ” ማለት ነው::

ፍሬያማ አደረገኝ
“ፍሬያማ” መበልጸግ ወይም ልጆችን መውለድ ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በተሠቃየሁበት ምድር
“ሥቃይ” የሚለው ረቂቅ ስም “መከራ ተከበልኩ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት “መከራን በተቀበልሁት ምድር” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Genesis 41:53

በየአገሩ ሁሉ
ከግብጽ ባለፈ የከነዓንንም ምድር ጨምሮ በዙሪያው ባሉ አገሮች ሁሉ

በመላው የግብጽ ምድር ግን ምግብ ነበር
ይህም የሚያስረዳው በሰባት መልካም ዓመታት ሕዝቡ እህልን እንዲያጠራቅሙ ዮሴፍ ስላዘዛቸው ምግብ ነበራቸው (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 41:55

ራብ በመላው የግብጽ ምድር መስፋፋት ሲጀምር
እዚህ “ምድር” ሰዎችን ይወክላል:: አት “ግብጻዊያን ሁሉ በተራቡ ጊዜ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ራቡ በአገሩ ሁሉ ፊት እየተስፋፋ ስለሄደ
እዚህ ፊት የሚለው ቃል ምድር ላይ ማለትን ያመለክታል:: አት “ራቡ በየአገሩ ተስፋፋ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዮሴፍ ጐተራዎችን ሁሉ ከፍቶ እህሉ ለግብጻዊያን እንዲሸጥ አደረገ
እዚህ “ዮሴፍ” የዮሴፍን አገልጋዮች ይወክላል:: አት “ዮሴፍ አገልጋዮቹ ጐተራዎችን ሁሉ እንዲከፍቱና ለግብጻዊያን እህል እንዲሸጥ አደረገ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ከምድር ሁሉ ወደ ግብጽ ይመጡ ነበር
እዚህ ምድር ከሁሉ አገራት የሆኑ ሰዎችን ይወክላል:: አት “በዙሪያው ካሉ አገሮች ሁሉ ሰዎች ወደ ግብጽ ይመጡ ነበር” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

በምድር ሁሉ
በመላው ምድር በግብጻዊያንን የንግድ መሥመሮች የሚጠቀሙ በድርቅ የተጠቁ የተለያዩ የንግድ አጋሮችና አገሮች ሁሉ ወደ ግብጽ ይመጡ ነበር እንደማለት ነው

Chapter 42

1 በግብፅ እህል መኖሩን ሲሰማ፣ ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤ “ለምን እርስ በርስ ትተያያላችሁ?” 2 በግብፅ አገር እህል መኖሩን ሰምቻለሁ፤ በራብ ከመሞታችን
በፊት ወደዚያ ሂድና እህል ግዙልን” አላቸው። 3 ስለዚህ ዐሥሩ የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመግዛት ወደ ግብፅ ሄዱ። 4 ነገር ግን ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም
ብንያምን ክፉ ነገር ይደርስበታል በሚል ፍርሃት ከወንድሞቹ ጋር አልላከውም። 5 ራቡ በከነዓንም በመበርታቱ፣ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ከሄዱት መካከል
የእስራኤል ልጆችም ነበሩ። 6 በዚህ ጊዜ ዮሴፍ የምድሪቱ ገዢ ነበር፣ ለአገሩ ሰዎች ሁሉ እህል የሚሸጥላቸው እርሱ ነበር። የዮሴፍ ወንድሞችም እንደደረሱ
ከፊቱ ቀርበው ወደ ምድር ለጥ ብለው ሰገዱለት። 7 ዮሴፍም ወንድሞቹን ባየ ጊዜ ዐወቃቸው፣ ነገር ግን የማያውቃቸው በመምሰል በቁጣ ቃል፣ “ከየት ነው
የመጣችሁት?” ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፣ “እህል ለመሸመት ከከነዓን ምድር የመጣን ነን" ብለው መለሱለት። 8 ዮሴፍ ወንድሞቹን ቢያውቃቸውም እንኳ
እነርሱ ግን አላወቁትም። 9 በዚህ ጊዜ ስለወንድሞቹ ያየው ሕልም ትዝ አለውና፣ “ሰላዮች ናችሁ፣ የመጣችሁት አገራችን በየትኛው በኩል ለጥቃት የተጋለጠች
መሆኗን ለመሰለል ነው” አላቸው። 10 እነርሱም እንዲህ አሉት፤ “ጌታችን ሆይ፣ እንዲህስ አይደለም፤ እኛ አገልጋዮችህ የመጣነው እህል ለመሸመት ነው፤ 11
ሁላችንም የአንድ አባት ልጆች ነን፤ አገልጋዮችህም የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች አይደለንም።” 12 እርሱም መልሶ፣ “አይደለም፣ ግብፅ በየት በኩል ለጥቃት
የተጋለጠች መሆኗን ለመሰለል ነው” አላቸው። 13 እነርሱ ግን መልሰው፣ “እኛ አገልጋዮችህ በከነዓን አገር ከሚኖር ከአንድ ሰው የተወለድን ዐሥራ ሁለት
ወንድማማቾች ነን። ትንሹ ወንድማችን አባታችን ዘንድ ሲሆን አንዱ ወንድማችን ሞቷል። 14 ዮሴፍም እንዲህ አላቸው፤ “ነገርኋችሁ እኮ፤ ሰላዮች ናችሁ 15
ታናሽ ወንድማችሁ እዚህ እስካልመጣ ድረስ ከዚህ ንቅንቅ እንደማትሉ በፈርዖን ስም እምላለሁ፤ ማንነታችሁ የሚረጋገጠውም በዚህ ነው። 16 ከእናንተ አንዱ
ሄዶ ወንድማችሁን ያምጣ፤ የተናገራችሁትም እውነት መሆኑ ተረጋግጦ ነጻ እስክትለቀቁ ድረስ የቀራችሁት እዚሁ በእስት ቤት ትቆያላችሁ፤” 17 ሁሉንም ሦስት
ቀን በእስር አቆያቸው። 18 በሦስተኛውም ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው፤ “እኔ እግዚአብሔርን ስለምፈራ እንዲህ በማድረግ ሕይወታችሁን አትርፉ። 19 ታማኝ
ሰዎች ከሆናችሁ፣ ከመካከላችሁ አንዱ እዚህ እስር ቤት ሲቆይ፣ የቀራችሁት ግን ለተራቡት ቤተ ሰቦቻችሁ እህል ትወስዱላቸዋላችሁ፤ 20 ታናሽ ወንድማችሁን
ግን ይዛችሁ መምጣት አለባችሁ፤ በዚህም የተናገራችሁት ቃል እውነተኛነት ይረጋገጣል፤ እናንተም ከመሞት ትተርፋላችሁ።” እነርሱም ይህንኑ ለመፈጸም
ተስማሙ። 21 እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፤ “በእርግጥ በወንድማችን ላይ ስላደረስነው በደል ቅጣታችንን እየተቀበልን ነው። እርሱ እንደዚያ ተጨንቆ
ስለ ሕይወቱ ሲማጠነን፣ እኛ አልሰማነውም ነበር፤ ይህ መከራ የደረሰብንም በዚሁ ምክንያት ነው” ተባባሉ። 22 ሮቤልም መልሶ፣ “በዚህ ልጅ ላይ ክፉ ነገር
እንዳታደርጉ ብዬ አልነበረምን? እናንተ ግን አልሰማችሁኝም፤ ስለዚህም ደሙ ከእጃችን ይፈለጋል” አላቸው። 23 ዮሴፍ የሚያነጋግራቸው በአስተርጓሚ ስለሆነ
የሚነጋገሩትን እንደሚሰማባቸው ዐላወቁም ነበር። 24 ከፊታቸውም ዘወር ብሎ አለቀሰ፤ ከዚያም ወደእነርሱ ትመልሶ እንደገና አነጋገራቸው፤ ስምዖንንም
ከእነርሱ ለይቶ ዓይናቸው እያየ አሰረው፤ 25 ዮሴፍ ለአገልጋዮቹ በስልቻዎቻቸው እህል እንዲሞሉላቸው፤ ብሩንም በያንዳንዱ ሰው ስልቻ ውስጥ መልሰው
እንዲያስቀምጡና ለጉዞአቸው ስንቅ እንዲያሲዟቸው ትእዛዝ ሰጠ። ይህም ተደረገላቸው። 26 እነርሱም እህላቸውን በአህዮቻቸው ጭነው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። 27
በመንገድም ለአዳር ሰፍረው ሳለ፣ ከእነርሱ አንዱ ከያዘው እህል ላይ ለአህያው ለመስጠት ስልቻውን ሲፈታ፣ በስልቻው አፍ ላይ ብሩን አገኘ። 28 እርሱም
ወንድሞቹን፣ “ኧረ ብሬ ተመልሶልኛል፤ ይኸው ስልቻዬ ውስጥ አገኘሁት” አላቸው። ሁሉም ልባቸው በድንጋጤ ተሞልቶ እየተንቀጠቀጡ በመተያየት፣
“እግዚአብሔር ምን ሊያመጣብን ይሆን?” አሉ። 29 በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ ከደረሱ በኋላ ያጋጠማቸውን ሁሉ እንዲህ ብለው
ነገሩት፤ 30 “የግብፅ አገር አስተዳዳሪ ‘አገሬን ልትሰልሉ የመጣችሁ ናችሁ’ በማለት በቁጣ ቃል ተናገረን፤ 31 እኛ ግን እንዲህ አልነው፤ “እኛ የታመንን ሰዎች
እንጂ ሰላዮች አይደለንም። 32 እኛ የአንድ አባት ልጆች የሆንን ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን፣ አንዱ የለም፣ ታናሽ ወንድማችን ግን ከአባታችን ጋር በከነዓን
ይገኛል።’ 33 ከዚህ በኋላ የአገሩ ጌታ የሆነው ሰው እንዲህ አለን፣ “ታማኝ ሰዎች መሆናችሁን የማውቀው በዚህ ነው ከእናንተ መካከል አንዱን ወንድማችሁን
እዚህ እኔ ዘንድ ትታችሁ የተቀራችሁት ለትራቡት ቤተ ሰቦቻችሁ እህል ይዛችሁላቸው ሂዱ። 34 ነገር ግን ታናሽ ወንድማችሁን ወደ እኔ አምጡት። በዚያን ጊዜም
ታማኝ ሰዎች እንጂ ሰላዮች አለመሆናችሁን ዐውቃለሁ፤ ወንድማችሁንም መልሼ እሰጣችኋለሁ፤ እናንተም በምድሪቱ እንደፈለጋችሁ እየተዘዋወራችሁ መነገድ
ትችላላችሁ። 35 እህሉንም ሲዘረግፉ በየስልቻቸው ውስጥ ብራቸው እንደተቋጠረ ተገኘ፤ የእያንዳንዳቸውን የተቋጠረ ብር ሲያዩም፣ እነርሱም ሆኑ አባታቸው
ደነገጡ። 36 አባታቸው ያዕቆብም፣ “ያለ ልጅ እኮ አስቀራችሁኝ፣ ዮሴፍ የለም፣ ስምዖንም የለም፤ አሁን ደግሞ ብንያምን ልትወስዱ ትፈልጋላችሁ፤ በዚህ ሁሉ
መከራ የምሠቃየው እኔ ነኝ” አለ። 37 በዚህን ጊዜ ሮቤል አባቱን፣ “ብንያምን ወደ አንተ መልሼ ባላመጣው ሁለቱን ወንዶች ልጆቼን ወስደህ ግደላቸው፣
ስለዚህ በእኔ ኃላፊነት ላከው፤ እኔም መልሼ አመጣዋለሁ” አለው። 38 ያዕቆብም “ምንም ቢሆን ከእናንተ ጋር አይሄድም፤ ወንድሙ ሞቶአል፣ የቀረው እርሱ
ብቻ ነው፤ በመንገድ አንድ ጉዳት ቢደርስበት በእርጅናዬ ዘመን በመሪር ሐዘን ወደ መቃብር እንድወርድ ታደርጉኛላችሁ” አላቸው።

Genesis 42:1

አሁንም ያዕቆብ ....እንዲህ አላቸው

አሁንም የሚለው ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ለምን እርስበርስ ትተያያላችሁ?

ስለ እህል ምንም ባለማድረጋቸው ልጆቹን ለመቆጣት ያዕቆብ ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “እዚሁ ዝም ብላችሁ አትቀመጡ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደዚያ ይውረዱ .... ወረዱ

ከከነዓን ወደ ግብጽ መሄድ ወደ ታች እንደመውረድ መናገር የተለመደ ነበር

ከግብጽ

እዚህ “ግብጽ” ሰዎች እህልን የሚሸጡበት ያመለክታል:: አት “በግብጽ እህልን ከሚሸጡ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም ብንያምን ... አልላከውም

ብንያምና ዮሴፍ አንድ አባትና እናት ነበራቸው የዕቆብ የራሔል መጨረሻ ልጅዋ እንዲጐዳ ወይም ክፉ ነገር እንዲደርስበት አልፈለገም ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ

Genesis 42:5

የእስራኤል ልጆች ለእህል ሽመታ ከመጡበት ጋር

“መጡ” የሚለው ቃል “ሄዱ” በሚለው ሊተረጐም ይችላል:: እንዲሁም እህል እና ግብጽ የተባሉ ቃላት የታወቁ ናቸው:: አት “የእስራኤል ልጆች እህል ለመሸመት ከሌሎች ሰዎች ጋር ወደ ግብጽ ሄዱ” (ሄደ እና መጣ አጠቃቀምና ድብቅ ቃላት የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

በዚህን ጊዜ ዮሴፍ
“በዚህን ጊዜ” ታሪኩ ወደ ዮሴፍ ሕይወት መረጃ መቀየሩን ያመለክታል:: (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

በምድሪቱ ላይ
ምድር ግብጽን ያመለክታል:: አት “በግብጽ ላይ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ለአገሩ ሰዎች ሁሉ
እዚህ አገር ግብጽንና ዙሪያው ያሉ አገሮችን ያጠቃልላል አት እህል ለመሸመት ከተለያዩ አገሮች ለመጡ ሰዎች ሁሉ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የዮሴፍም ወንድሞች መጡ
“መጡ” እንደ “ሄዱ” ሊተረጐም ይችላል:: (መጣ እና ሄደ አጠቃቀም ይመልከቱ)

በግምባራቸው ወደ ምድር ጐንበስ ብለው ሰገዱለት
ይህ አክብሮትን የመስጠት ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 42:7

ዮሴፍም ወንድሞቹን አይቶ አወቃቸው
ዮሴፍም ወንድዋቹን ባያቸው ጊዜ አወቃቸው

እንደማያውቃቸው ሆነ
“የእነርሱ ወንድም እንዳልሆነ ታየ” ወይም “ወንድማቸው እንደሆነ እንዲያውቁት አልፈለገም”

ከየት የመጣችሁ ናችሁ?
ዮሴፍ መልሱን ቢያውቅም ይህ አግናኝ ጥያቄ አልነበረም የራሱን ማንነት ለወንድሞቹ ላለመግለጽ የመረጠው መንገድ ነበር

Genesis 42:9

ሰላዮች ናችሁ
ሰላዮች ሌላ አገርን ለመጥቅ በስውር ስለአንድ አገር መረጃ ለማግኘት የሚጥሩ ሰዎች ናቸው::

ምድሪቱ በየትኛ በኩል የተጋለጠች እንደሆነች ሊታዩ መጥታችኋል
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት አገራችን በየትኛው በኩል እንደተጋለጠች ለማየትና ከዚያም ሊታጠቁን ለማየት መጥታችኋል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ጌታችን ሆይ
አንድን ሰው ለማክበር የሚጠቀሙበት አባባል ነው

ባሪያዎችህ
ወንድሞቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች አድርገው ያቀርባሉ። ይህም ከፍተኛ ሥልጣን ላለው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው።አት “እኛ ባሪያዎችህ” ወይም “እኛ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 42:12

እርሱ ለእነርሱ አላቸው
ዮሴፍ ለወንድሞቹ አላቸው

አይደለም በየት በኩል ምድራችን ጥቃት የተጋለጠች መሆንዋን ለማየት ነው
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “አይደለም በየት በኩል ምድራችን ለጥቃት የተጋለጠች መሆንዋን ለመሰለልና ከዚያም ሊታጠቁን ነው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አሥራ ሁለቱ ወንድሞች
12ቱ ወንድሞች (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

እየው ትንሹ ወንድማችን
“ስማን ትንሹ ወንድማችን” “እየው” የሚለው ቃል ቀጥለው ለምነግሩት ነገር ትኩረት እንዲሰጥ ተጠቅሞአል::

ትንሹ ወንድማችን አባታችን ዘንድ ነው
“በዚህን ጊዜ ትንሹ ወንድማችን ከአባታችን ጋር ነው”

Genesis 42:14

ነገርኋች እኮ ሰላዮች ናችሁ
“እንደነገርኋችሁ ሰላዮች ናችሁ” (በዘፍጥረት 42;9 “ሰላዮች” እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ)

በዚህ ትፈተናላችሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የሚፈትናችሁ በዚህ ነው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በፈርዖን ሕይወት
ይህ ጠንከር ወይም ኮስተር ያለ መሃላ ነው አት በፈርዖን ሕይወት እምላለሁ

ከእናንተ አንዱን ላኩና ወንድማችሁን ይዞ ይመለስ
“ከእናንተ አንዱን ምረጡና ሂዶ ወንድማችሁን ይዞ ይመለስ”

እስር ቤት ትቆያላችሁ
የቀራችሁ በእሥር ቤት ትቆያላችሁ

የተናገራችሁት ቃል እውነት መሆኑ እስኪረጋገጥ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት እውነት መናገራችሁን እንዳውቅ (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልክቱ)

በግዞት ቤት
በእስር ቤት

Genesis 42:18

በሶስተኛውም ቀን
“ሶስት” የሚለው ተራ ቁጥር ነው:: አት “ከሁለተኛው ቀን በኋላ” (መቁጠሪያ ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)

እንዲህ በማድረግ ሕይወታችሁን አትርፉ
የተቀመጠው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “የሚለውን ካደረጋችሁ በሕይወት ትተርፉ አደርጋችኋለሁ” (የተደበቁ ቃላትን ስለመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን እፈራለሁና
ይህ ከልብ እግዚአብሔርን ማክበርንና ያንን ለእርሱ በመታዘዝ መግለጽን ያመለክታል

አንዱ ወንድማችሁ በእሥር ቤት ይቆይ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ልገለጽ ይችላል:: አት “አንዱን ወንድማችሁን እዚሁ እሥር ቤት ተውት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እናንተ ግን ሂዱ
እዚህ ሂዱ ብዙ አመላካችና በእሥር ቤት የማይቆዩ ወንድሞች ሁሉን ያመለክታል (ብዙ አመላካች እናንተ ይመልከቱ)

ለተራቡት ቤተሰቦቻችሁ እህል ትወስዱላቸዋላችሁ
እዚህ ቤቶች ቤተሰቦችን ይወክላል:: አት "በዚህ ራብ ወቅት ቤተሰቦቻችሁን ለመርዳት እህል ትወስዱላቸዋላችሁ" (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

የተናገራችሁት ቃል እውነተኛነት ይረጋገጣል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት የሚትነግሩ እውነት መሆኑን አውቃለሁ (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)

ከሞት ትተርፋላችሁ
ወንድሞቹ ሰላይ መሆናቸውን ካረጋገጠ ዮሴፍ በወታደሮቹ እንደሚያስገድላቸው የሚል ትርጉም ይኖረዋል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 42:21

ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን
ነፍሱ ዮሴፍን ይወክላል አት ዮሴፍ እንደዚያ ሲጨነቅ አይተን ወይም ዮሴፍ እንደዚያ ሲሰቃይ አይተን (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ይህ ጭንቀት የደረሰብን በዚህ ምክንያት ነው
"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "መከራ" በሚለው ግሥ ሊተረጐም ይችላል:: አት "ይህ መከራ የደረሰብን በዚሁ ምክንያት ነው" (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

በዚህ ልጅ ላይ ክፉ አታድርጉ ብዬ አልነበረምን? እናንተ ግን አልሰማችሁኝም
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገልጽ ይችላል:: አት "በዚህ ልጅ ላይ ኃጢአት እንዳታደርጉ አልነገርኋችሁምን፤ነገር ግን" ወይም "ልጁ ላይ ክፉ እንዳታደርጉ ነግሬአችኋለሁ፤ ነገር ግን" (በጥቅሶች ውስጥ ጥቅሶችንና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

አሁንም እዩ
እዚህ አሁን በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም አሁን እና እዩ ሁለቱ የተጠቀሙት ለሚቀጥለው በጣም ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

ደሙ ከእጃችን ይፈለጋል
እዚህ ደም የዮሴፍን ሞት ይወክላል ወንድሞቹ ዮሴፍ እንደሞተ አስበዋል:: "ከእጃችን ይፈለጋል" የሚለው ሀረግ ስላደረጉት ነገር ይቀጣሉ ማለት ነው:: አት "ለሞቱ የሚገባውን ቅጣት እየተቀበልን ነን" ወይም "በመግደላችን መከራ እየተቀበልን ነን" (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ወይም ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 42:23

በመካከላቸው አስተርጓሚ ነበረና .... አላወቁም
አስተርጓሚ አንድ ሰው የሚናገረውን ወደ ሌላ ቋንቋ የሚተረጉም ሰው ማለት ነው ዮሴፍ የእነርሱን ቋንቋ እንደማይናገር ለማስመሰል በራሱና በእነርሱ መካከል አስተርጓሚ አድርጐ ነበር

ከእነርሱ ዘወር ብሎ አለቀሰ
ዮሴፈ ወንድሞቹ የተናገሩትን በመስማቱ ስሜቱ ስለተነካ አለቀሰ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ተናገራቸው
እስከዚህ ዮሴፍ ወንድሞቹን የሚያናግረው በተለየ ቋንቋ ስለሆነ አስተርጓሚ ይጠቀም ነበር (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ዐይናቸው እያየ አሠረው
እዚህ ለሚያዩት ነገር ትኩረት ለመስጠት ሰዎች በዐይኖች ተመስለዋል:: አት "በፊታቸው አሰረው" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

የመንገድ ስንቅ ይሰጡአቸው ዘንድ
ለጉዞአቸው ስንቅ እንዲሰጡአቸው

ይህም ተደረገላቸው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ዮሴፍ ያዘዘውን ሁሉ አገልጋዮቹ አደረጉላቸው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 42:26

ከእነርሱም አንዱ በአደረበት ሥፍራ ለአህያው ገፈራን ሊሰጥ ዘንድ ዓይበቱን ሲፈታ ብሩን አየ እነሆም በዓይበቱ አፍ ላይ ነበረች
በመንገድም አዳር ሰፍረው ሳሉ ከእነርሱ አንዱ ከያዘው እህል ላይ ለአህያው ለመስጠት ስልቻውን ሲፈታ በስልቻው አፍ ላይ ብሩን አየ

እነሆ
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስገራሚ ሃሳብ ትኩረት እንድንሰጥ ለማድረግ ነው

ብሬ ተመልሶልኛል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልከ ሊገለጽ ይችላል አት አንድ ሰው ብሬን መልሳ አስቀመጠልኝ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልክቱ)

ይሄው ወደዚህ እዩ
ይሄው በስልቻዬ እዩ

ልባቸው በድንጋጤ ተሞላ
መፍራቻው ልባቸው በድንጋጤ እንደተዋጠ እንደተሞላ ተገልጾአል እዚህ ልብ በድፍረት ተመስሎአል አት እጅግ በጣም ፈሩ

Genesis 42:29

የአገሩ ጌታ
የግብጽ ጌታ

በቁጣ ተናገረን
በክፉ ንግግር ተናገረን

ሰላዮች እንደሆንን
ሰላዮች ሌላን አገር ለመጥቀም ሰለአንድ አገር በሚስጢር መረጃ የሚሰበስቡ ሰዎች ናቸው:: በዘፍጥረት 42 9 ሰላዮች የሚለውን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::እኛም እንዲህ አልነው እኛ የታመንን ሰዎች ነን። ሰላዮች አይደለንም። እኛ የአንድ አባት ልጆች የሆንን አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን። አንዱ በሕይወት የለም .....በከነዓን ይገኛል ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ይዞአል:: ይህም እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: አት እኛ የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች አይደለንም:: እኛ የአንድ አባት ልጆች የሆንን አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን:: አንዱ በሕይወት የለም ... በከነዓን ይገኛል (በጥቅስ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

አንዱ በሕይወት የለም
"ወንድም" የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት "አንዱ ወንድማችን በሕይወት የለም" (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይጠቀሙ)

ታናሹም ....ዛሬ ከአባታችን ጋር አለ
“ወንድም” የሚለው ቃል የታወቀ ነው:: አት “ታናሽ ወንድማችን.... ዛሬ ከአባታችን ጋር አለ” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይጠቀሙ)

Genesis 42:33

የአገሩ ጌታ
የግብጽ ጌታ

ለተራቡት ቤተሰቦቻችሁ እህል ይዛችሁላችሁ ሂዱ
ቤቶች ቤተሰብን ይወክላሉ አት በራብ ወቅት ቤተሰባችሁን ለመርዳት እህል ይዛችሁላችሁ ሂዱ (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)

መንገዳችሁን ሂዱ
ወደ ቤታችሁ ሂዱ ወይም ሂዱ

እናንተም በምድሪቱ ትነግዳላችሁ
በምድሪቱ እንዲትሸጡና እንዲትገዙ እፈቅድላችኋለሁ

Genesis 42:35

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ የተጠቀመው በታሪኩ ጠቃሚ ክስተት ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የማችሉበት መንገድ ካለ በዚህ ቦታ ሊጠቀሙ ይችላሉ

እነሆ እያንዳንዳቸው
ተገረሙ ምክንያቱም እያንዳንዳቸው

ልጅ አልባ አስቀራችሁኝ
ያለ ልጅ እኮ አስቀራችሁኝ ወይም ሁለቱን ልጆች እንዳጣ አደረጋችሁኝ

ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ደረሰ
እነዚህ ሁሉ ጎዱኝ

Genesis 42:37

እርሱን በእጄ ስጠኝ
ይህ አብሮ እንዲሄድ ብንያምን እንዲሰጠውና በጉዞው እንደሚጠነቀቅለት ሮቤል የጠየቀው ጥያቄ ነው አት ለእርሱ ኃላፊነት ስጠኝ ወይም ለእርሱ እኔ ሊጠነቀቅለት ዘይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ

ልጄ ወደዚያው አብሮአችሁ አይወርድም
ከከነዓን ወደ ግብጽ ጉዞ ስታሰብ እዚህ የተጠቀመው ወደታች መውረድ የሚለው አባባል የተለመደ ነው አት ልጄ ብንያምን አብሮአችሁ ወደ ግብጽ አይሄድም

ከእናንተ ጋር
እዚህ እናንተ ብዙን የሚያመለክትና የያዕቆብን ልጆች የሚገልጽ ነው(“እናንተ” አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወንድሙ እንደሆነ ሞቶአል የቀረው እርሱ ብቻ ነው
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ባለቤቴ ራሔል ሁለትልጆች ነበራት ዮሴፍ ሞቶአልና ብንያም ብቻውን ቀርቶአል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ስትሄዱ በመንገድ ላይ
“ወደ ግብጽ ስትሄዱና ስትመለሱ” ወይም “ርቃችሁ ስትሄዱ” እዚህ “መንገድ” “ጉዞን” ያመለክታል

ሽበቴን በመሪር ሐዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ
ወደ መቃብር ታወርዱታለችሁ እንዲሞትና ወደ መቃብር እንዲወርድ ታደርጉታላችሁ የሚል አባባል ነው:: መቃብር በተለምዶ እንደሚታመነው ከምድር በታች ስለሆነ ታወርዱታላችሁ የሚለውን ቃል ይጠቀማል:: አት “እኔን ሽማግሌውን በሐዘን እንድሞት ታደርጉታላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሽበቴን
ይህ ያዕቆብን የሚያመለክትና ሽምግልና ዕድሜውን የሚገልጽ ነው አት “እኔ ሽማግሌ ሰው” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Chapter 43

1 አሁንም በምድሪቱ ላይ እንደጸና ነበር፤ 2 ከግብፅ ያመጡትንም እህል በልተው ከጨረሱ በኋላ፣ አባታቸው፣ “እስቲ እንደገና ወርዳችሁ፣ ጥቂት እህል
ሸምቱልን” አላቸው። 3 ይሁዳ ግን እንዲህ አለው፤ “ ያ ሰው ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ ፊቴን ዐታዩም ብሎ በጥብቅ አስጠንቅቆናል፤ 4
ወንድማችን ከእኛ ጋር እንዲወርድ ከፈቀድህ ወደዚያ ሄደን እህል እንሸምትልሃለን፤ 5 እርሱን የማትልከው ከሆነ ግን እኛም ወደዚያ አንወርድም፤ ያም ሰው፣
‘ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ ፊቴን ዐታዩም’ ብሎናል።” 6 እስራኤልም፣ “ሌላ ወንድም አለን ብላችሁ ለዚያ ሰው በመንገር ለምን ይህን
ችግር እንዲደርስብኝ አደረጋችሁ?” ሲል ጠየቃቸው። 7 እነርሱም፣ “ሰውዬው ስለ ራሳችንና ስለ ቤተ ሰባችን አጥብቆ ጠየቀን፤ እንደገናም ‘አባታችሁ አሁንም
በሕይወት አለ? ሌላስ ወንድም አላችሁ?’ ሲል ጠየቀን። እኛም ለጥያቄው መልስ ሰጠነው። ታዲያ፣ ‘ወንድማችሁን ይዛችሁ ወደዚህ እንድትመጡ’ እንደሚል
እንዴት ማወቅ እንችል ነበር?” ብለው መለሱለት። 8 ይሁዳም አባቱን እስራኤልን እንዲህ አለው፣ “ልጁን ከእኔ ጋር ስደደው፤ እኛም በቶሎ እንሂድ፣ ይህ ከሆነ
አንተም፣ እኛም፣ ልጆቻችንም አንሞትም፣ እንተርፋለን። 9 ስለ ልጁ ደኅንነት እኔ ራሴ ኃላፊ ነኝ፤ ስለ እርሱም በግል ተጠያቂ እሆናለሁ፤ እርሱንም በደኅና መልሼ
ባላመጣውና እዚህ በፊትህ ባላቆመው ለዘላለም በደለኛ እኔ ልሁን። 10 ይህን ያህል ባንዘገይ ኖሮ፣ እስካሁን ሁለት ጊዜ ደርሰን መመለስ በቻልን ነበር።” 11
ከዚህ በኋላ አባታቸው እስራኤል እንዲህ አላቸው፤ “ነገሩ እንዲህ ከሆነስ ይህን አድርጉ፣ ምድሪቱ ከምታፈራቸው ምርጥ ነገሮች ጥቂት በለሳን፣ ጥቂት ማር፣
ሽቱ፣ ከርቤ፣ ተምርና ለውዝ በየስልቻችሁ ይዛችሁ ለዚያ ሰው ስጦታ ውሰዱለት። 12 በየስልቾቻችሁ አፍ ላይ የተገኘውን ብር መመለስ ስላለባችሁ፣ ዕጥፍ
ገንዘብ ያዙ፤ ያ በየስልቾቻችሁ ውስጥ የተገኘው ብር ምናልባት በስሕተት የመጣ ሊሆን ይችላል። 13 ወንድማችሁንም ይዛችሁ ወደ ሰውዬው በቶሎ ሂዱ። 14
ሌላውን ወንድማችሁንና ብንያምን ይዛችሁ ለመመለስ እንድትችሉ ሁሉን የሚችል አምላክ በምሕረቱ የዚያን ሰው ልብ ያራራላችሁ። እኔ በበኩሌ ልጆቼን ካጣሁ፣
ባዶ እጄን መቅረቴ ነው።” 15 ስለዚህ ወንድማማቾቹ ገጸ በረከቱንና ዕጥፍ ገንዘብ ይዘው ከብንያም ጋር ወደ ግብፅ ለመሄድ ጉዞ ጀመሩ፤ እዚያም በደረሱ ጊዜ
ዮሴፍ ፊት ቀረቡ። 16 ዮሴፍ ብንያምን ከወንድሞቹ ጋር ባየው ጊዜ የቤቱን አዛዥ፣ “እነዚህን ሰዎች ወደ ቤት ይዘሃቸው ሂድ፣ ዛሬ ቀትር ላይ አብረውኝ ስለሚበሉ
አንድ ከብት እረድና አዘጋጅ” አለው። 17 አዛዡም ዮሴፍ የነገረውን አደረገ፣ ሰዎቹንም ወደ ዮሴፍ ቤት ወሰዳቸው። 18 ሰዎቹም ወደ ዮሴፍ ቤት በመወሰዳቸው
ፈሩ፤ እነርሱም፣ “ወደዚህ የመጣነው ቀደም ሲል እዚህ መጥተን ስንመለስ በየስልቾቻችን ውስጥ ተመልሶ በተጨመረው ብር ሰበብ ነው። ሰውዬው ሊያስረንና
ባሪያዎች ሊያደርገን አህዮቻችንንም ሊወስድ ይችላል።” 19 ወደ ዮሴፍ ቤት አዛዥ ቀርበው፣ በቤቱ መግቢያ ላይ አነጋገሩት፤ 20 እንዲህም አሉት፤
“ለመጀመሪያ ጊዜ እህል ለመሸመት ወደዚህ መጥተን ነበር፤ 21 ነገር ግን ለአዳር በሰፈርንበት ቦታ የየስልቾቻችንን አፍ ስንከፍት እያንዳንዳችን በስልቾቻችን
አፍ ላይ ብራችንን ሙሉውን አገኘነው። ገንዘቡንም ይኸው መልሰን ይዘን መጥተናል። 22 አሁንም እህል መሸመት የሚሆነን ተጨማሪ ብር ይዘን መጥተናል፤
በዚያን ጊዜ ገንዘቡን በየስልቾቻችን ውስጥ ማን መልሶ እንዳስቀመጠው ግን አናውቅም” አሉት። 23 የቤቱ አዛዡም፣ “አይዞአችሁ አትፍሩ፣ በየስልቾቻችሁ
ውስጥ ያገኛችሁትን ገንዘብ የሰጣችሁ የእናንተም የአባቶቻችሁም አምላክ ነው፤ እኔ እንደሆንሁ ብሩን ተቀብያለሁ” አላቸው። ከዚያም ስምዖንን አውጥቶ
አገናኛቸው። 24 የቤቱ አዛዥ ሰዎቹን ወደ ዮሴፍ ቤት አስገብቶ እግራቸውን የሚታጠቡበት ውሃ አቀረበላቸው፤ ለአህዮቻቸውም የሚበሉት ገፈራ ሰጣቸው። 25
ምሳ በዚያ እንደሚበሉ ተነገሯቸው ስለነበር፣ ዮሴፍ በቀትር ከመግባቱ በፊት እጅ መንሻዎቻቸውን ለማበርከት ተዘጋጁ። 26 ዮሴፍም ወደ ቤቱ ሲገባ
የመጧቸውን ስጦታዎች አበረከቱለት፤ ወደ መሬት ዝቅ ብለውም እጅ ነሡት። 27 ዮሴፍም ስለ ደኅንነታቸው ጠየቃቸው፣ ከዚያም፣ “ሽማግሌ አባት እንዳላችሁ
ነግራችሁኝ ነበር፤ ደኅና ነው? አሁንም በሕይወት አለ?” አላቸው። 28 እነርሱም መልሰው፣ “አገልጋይህ አባታችን አሁንም በሕይወት አለ፤ ደኅና ነው” በማለት
ወደ መሬት ዝቅ ብለው እጅ ነሡት። 29 ዮሴፍ በዓይኑ ሲቃኝ የእናቱን ልጅ ብንያምን ዐየና፣ “ያ የነገራችሁኝ ታናሽ ወንድማችሁ ይህ ነው?” ብሎ ጠየቃቸው።
ብንያምንም፣ “ልጄ እግዚአብሔር ይባርክህ” አለው። 30 ዮሴፍ ወንድሙን በማየቱ ስሜቱ በጥልቅ ስለተነካ፣ ፈጥኖ ከፊታቸው ገለል አለ፤ ሰውር ያለ ቦታም
ፈልጎ፣ ዕልፍኙ ውስጥ አለቀሰ። 31 ፊቱንም ከታጠበ በኋላ ወጣ፤ ስሜቱንም በመቆጣጠር ምሳ እንዲቀርብ አዘዘ። 32 ለዮሴፍ ለብቻው ቀረበለት
ለወንድሞቹም ለብቻቸው ቀረበላቸው፤ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ለሚበሉት ግብፃውያን ደግሞ ሌላ ገበታ ቀረበላቸው፤ ምክንያቱም ግብፃውያን ከዕብራውያን ጋር
አብሮ መመገብን እንደጸያፍ ይቆጥሩት ነበር። 33 ወንድማማቾቹ ከታላቁ አንስቶ እስከታናሹ እንደየዕድሜአቸው በዮሴፍ ፊት በተርታ ተቀምጠው ነበር፤
በመገረምም እርስ በርሳቸው ተያዩ። 34 ከዮሴፍ ገበታ ላይ እየተነሣ ለእያንዳንዳቸው ምግብ ሲቀርብ የብንያም ድርሻ ከሌሎቹ አምስት ዕጥፍ ነበር። እነርሱም
እንዲህ ባለ ሁኔታ አብረውት ተደሰቱ እስኪረኩም ጠጡ።

Genesis 43:1

ራቡ በምድሪቱ ላይ እንደጸና ነበር

ከነዓን የሚለው ቃል የታወቀ ነው ይህ ሃሳብ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት በከነዓን ምድር ራቡ የጸና ነበር (ድብቅ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩን አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የሚችሉበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

በልተው ከጨረሱ በኋላ

ያዕቆብና ቤተሰቡ በልተው ከጨረሱ በኋላ

ያመጡትን

የያዕቆብ ታላቅ ልጆች ያመጡትን

ለኛ ሸምቱልን

እዚህ እኛ ያዕቆብን የያዕቆብን ልጆችና የቀሩ የቤተሰብ አባላትን ያመለክታል:: (ሁሉን አካታች “እኛ” ይመልከቱ)

Genesis 43:3

ይሁዳ እንዲህ አለው

ይሁዳ ለአባቱ ለያዕቆብ እንዲህ አለው

ያ ሰው

ይህ ዮሴፍን ነው የሚያመለክተው ነገር ግን ወንድምቹ ዮሴፍ መሆኑን አላወቁትም ነበር:: እነርሱም እርሱን ያመለከቱን እንደ “ያ ሰው” ወይም በዘፍጥረት 42:30 እንደተነገረው “ያ ሰው የምድሪቱ ጌታ” ነው::

ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ፊቴን አታዩም ብሎ አስጠንቀቆናል

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል ይህም እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ታናሽ ወንድማችንን ይዘነው ካላመጣን ፊቱን ማየት

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

እንደማንችል አስጠንቅቆናል” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

በጥብቅ አስጠንቅቆናል
እንዲህም በማለት በጥብቅ አስጠንቀቆናል

ፊቴን አታዩም
ወደ ግብጽ አገር ያለ ብንያም መመለስ እንደማይችሉ ለአባቱ ለማጽናት በዘፍጥረት 43፡ 4-5 ይሁዳ ይህን ሀረግ ሁለት ጊዜ ይጠቀማል:: ፊቴን የሚለው የዚያ ሰው የዮሴፍ ፊት ያመለክታል:: አት “ፊቴን አታዩም” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዜይቤ ይጠቀሙ)

ወንድማችን ከእኛ ጋር
ይሁዳ ራሔል ከመሞትዋ በፊት የወለደችውን የመጨረሻ ልጅ ብንያምን ያመለክታል

እኛም ወደዚያ አንወርድም
ከከነዓን ወደ ግብጽ ጉዞ በሚነገርበት ጊዜ “ወደታች መውረድ” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው

Genesis 43:6

ለምን በደላችሁኝ?
ለምን ይህ ችግር እንዲደርስብኝ አደረጋችሁ?

ሰውየው አጥብቆ ጠየቀን
ሰውየው ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቀን

ስለእኛ
እዚህ እኛ የሚለው በተለይ የሚያመለክተው ወደ ግብጽ የወረዱና ከሰውየው ጋር የተነጋገሩ ወንድሞችን ነው

አባታችሁ አሁን በሕይወት አለ? ሌላ ወንድም አላችሁ? ሲል ጠየቀን
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል አት አባታችን በሕይወት እንዳለና ሌላ ወንድም እንዳለን በቀጥታ ጠይቆናል:: (በጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እኛም ለጥያቄዎቹ መልስ ሰጠን
የጠየቀንን ጥያቄዎች መለስንለት

...ይዛችሁ እንዲትመጡ እንደሚለን እንዴት ማወቅ እንችል ነበር?
ሰውየው ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚነግር ልጆቹ አለማወቃቸውን አጽንተው ለመንገር ጥያቄ ይጠቀማሉ ይህ አግናኝ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል አት እንደዚህ … እንደሚለን አላወቅንም ነበር (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ወንድማችሁን ይዛችሁ ውረዱ ወይም አምጡ እንደሚለን
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል አት ወንድማችንን የዘን ወደ ግብጽ እንድንወርድ እንደሚነግረን (በጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ወንድማችሁን ይዛችሁ ውረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ ጉዞ በሚነገርበት ጊዜ “ወደታች መውረድ” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው

Genesis 43:8

እኛና አንተ ልጆቻችንም ደግሞ እንድንድን እንዳንሞትም
እንድንድን እና እንዳንሞት የሚሉ ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: ይሁዳም በሕይወት ለመኖር ከግብጽ እህል መሸመት እንዳለባቸው በማጽናት ይናገራል:: አት “መላው ቤተሰባችን እንዲተርፍ ወደ ግብጽ ወርደን እህል መሸመት ይገባናል” (ተመሣሣይ ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)

እኛም ተነሥተን
እዚህ እኛ ወደ ግብጽ የሚጓዙ ወንድሞችን ያመለክታል:: (የሚያቅፍና የማያቅፍ እኛ ይመልከቱ)

እኛ እንተርፋለን
እዚህ “እኛ” ወንድሞች እስራኤልና መላውን ቤተሰብ ያመለክታል (የሚያቅ “እኛ” ይመልከቱ)

እኛ ሁለታችን
እዚህ እኛ ወንድማማቾችን ያመለክታል (የሚያቅፍና የማያቅፍ “እኛ” ይመልከቱ)

እኛ አንተም
እዚህ አንተ በነጠላ የተገለጸና እስራኤልን ያመለክታል (ሁለተኛ ወገን ሰው ወይም አንተ አጠቃቀም ይመልከቱ)

የእኛም ልጆች ወይም ልጆቻችን
እኛ ወንድሞችን ያመለክታል በረሀቡ ጊዜ ሊሞቱ የሚችሉ ትናንሽ ልጆችን ያመለክታል

እኔ ዋስ እሆንለታለሁ
“ዋስ” የተባለው ረቂቅ ስም እንደ “ተስፋ” የተባለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል። (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ተጠያቂ እሆናለሁ
ያዕቆብ ይሁዳን እንዴት ተጠያቂ እንደሚያደረገው በግልጽ መነገር አለበት አት በብንያም ላይ በሚደርሰው ነገር ሁሉ ምላሽ እንዲሰጥ ታደርገኛለህ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)

እኔ ራሴ ኃላፊነትን እሸከማለሁ
ይህ አንድ ሰው እንደሚሸከመው ዕቃ ተደርጐ ኃላፊነትን መሸከም ይገልጻል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ባንዘገይ ኖሮ
ይሁዳ ቀድሞ መደረግ የነበረበት ነገር ግን ያልተደረገውን ነገር ይገጻል ተጨማሪ እህል ለመሸመት ልጆቹ ወደግብጽ ሳይሄዱ በመቆየታቸው አባቱን እንስራኤልን ይሁዳ በመውቀስ ይናገረዋል (የሚገመቱ ታሳቢ ሁኔታዎችን ይመልከቱ)

እስካሁን ሁለት ጊዜ ደርሰን መመለስ በቻልን
ሁለት ጊዜ መመላለስ በቻልን

Genesis 43:11

እንዲህ ከሆነ ይህን አድርጉ
ይህ ብቸኛ ምርጫችን ከሆነ ይህን አድረጉ

ተሸክማችሁ ውረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ መውረድ የሚለውን ቃል መጠቀም የተለመደ ነበር

በለሳን
ቆዳን ለማከምና ለመከላከል የሚጠቀሙበት ጣፊጨነት ያለው ቅባታማ ፍሬ ነው:: በዘፍጥረት 37:25 ይህን ቃል እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት “መድኃኒት”

ቅመማ ቅመሞች
የተለያዩ ቅመማ ቅመሞች በዘፍጥረት 37:25 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ለውዝ
ትናንሽ አረንጓዴ ተክል ለውዞች (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ተምር
ጣፋጭ ጣዕም ያለው የዛፍ ፍሬ (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በእጃችሁ ዕጥፍ ገንዘብ ያዙ
እዚህ "እጅ" ሙሉ ሰውን ይወክላል አት ዕጥፍ ገንዘብ ውሰዱ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በየስልቾቻችሁ አፍ የተገኘውን የተመለሰውን ብር በአጠፌታ አድርጋችሁ በእጃችሁ ውሰዱ
እዚህ እጅ ሙሉ ሰውን ይወክላል በስልቼቻችሁ አፍ የተመለሰው ብር የተባለው ሀረግ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "አንድ ሰው በስልቾቻችሁ የጨመረውን ብር መልሳችሁ ወደ ግብጽ ውሰዱ" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤና ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 43:13

ወንድማችሁንም ውሰዱ
ብንያምንም ደግሞ ውሰዱ

ሂዱ
ተመለሱ

ሁሉም የሚችል አምላክ በዚያ ሰው ፊት ምሕረትን ይሰጣችሁ
ምሕረት የሚለው ረቂቅ ስም ርኅራኄ በሚለው ቅጽል ሊተረጐም ይችላል:: አት "ሁሉን የሚችል አምላክ ያ ሰው እንዲራራ ያድርግላችሁ" (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ሌላውንም ወንድማችሁንም
ስምዖንን

እኔም ልጆቼን እንዳጣሁ አጣሁ
ልጆቼን ካጣሁ ያው አጣሁ ያዕቆብ ልጆቹን ቢያጣ እንዳጣ ሊቀበል አውቆታል ማለት ነው

በእጃቸው ... ወሰዱ
እዚህ "እጅ" ሙሉ ሰውን ይወክላል:: አት እነርሱም ... ወሰዱ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ ግብጽም ወረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ "ወደዚያ ወረደ" የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር

Genesis 43:16

ከራሳቸው ጋር ብንያምን
ብንያም ከዮሴፍ ታላቅ ወንድሞች ጋር

የቤቱን አዛዥ
የቤቱ አዛዥ የዮሴፍን ቤት ተግባራትን ለማሰተዳደር ኃላፊነት ነበረው

እነዚህን ሰዎች አመጣቸው
እዚህ "አመጣቸው" እንደ "ወሰዳቸው" ሊተረጐም ይችላል:: ("መጣ" እና "ሄደ" አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደ ዮሴፍ ቤት
ወደ ዮሴፍ ቤት ውስጥ

Genesis 43:18

ሰዎቹም ፈሩ
የዮሴፍ ወንድሞች ፈሩ

ወደ ዮሴፍ ቤት ስለተወሰዱ
ይህ ተሻጋሪ ግስ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡፤ አት "ወደ ዮሴፍ ቤት ይሄዱ ነበር" ወይም "የቤቱ አዛዥ ወደ ዮሴፍ ቤት ይወስዳቸው ነበር" (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።

ቀደም ስል እዚህ መጥተን ስንመለስ በየስልቾቻችን ውስጥ ተመልሶ በተጨመረው ብር ሰበብ ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት የቤቱ አዛዥ እየወሰደን ያለው ያነ አንድ ሰው በስልቾቻችን በጨመረው ብር ሰበብ ነው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሰውዬው በዚህ አጋጣሚ ሊተነኰልብን ይሆናል ሊያሥረንም ይችላል
ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት "ሊከሰን አጋጣሚ እየጠበቀ ስላለ ሊያሰረን ይሆናል"

Genesis 43:21

አገናኝ ዐረፍተ ነገር
ወንድሞቹ ለቤቱ አዛዥ መናገር ቀጠሉ

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ በታሪኩ ዋና ክተት ለማመልከት ተጠቅሞአል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ::

ወደምናድርበት ቦታ በደረስን ጊዜ
ለአዳር በሠፈርንበት ቦታ በደረስን ጊዜ

እነሆ
እዚህ "እነሆ" የሚለው ቃል ወንድሞቹ ባዩት ነገር እንደተገረሙ ለማሳየት ተጠቅሞአል::

እያንዳንዳችን በስልቾቻችን አፍ ብራችንን ሙሉውን አገኘነው
እያንዳንዳችን በየስልቾቻችን ሙሉውን ብሮቻችንን አገኘው

መልሰን በእጃችን አመጣነው
እዚህ እጆች ሙሉውን ሰው ይወክላሉ አት ብሮቻችንን መልሰን የዘነው መጣን (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ደግሞም እህል መሸመቻ የሚሆነንን ተጨማሪ ገንዘብ ይዘን መጥተናል/ወርደናል
እዚህ እጆች ሙሉ ሰው ይወክላሉ:: አት "ደግሞም እህል መሸመቻ የሚሆነንን ብር ይዘን መጥተናል" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ይዘን ወርደናል
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ "ወደዚያ ወረደ" የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር

ሰላም ለእናንተ ይሁን
ረቂቅ ስም ሰላም እንደ ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት "ዘና በሉ ወይም ተረጋጉ" (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)

አምላካችሁና የአባታችሁ አምላክ
የቤቱ አዛዥ ሁለት የተለያዩ አምላኮችን እየተናገረ አይደለም አት "አምላካችሁ አባታችሁ የሚያመለከው"

Genesis 43:24

እግሮቻቸውን የሚታጠቡበት
ይህ ባህል ረጅም ጉዞ ተጉዘው ከመጡ በኋላ የደከሙ መንገደኞች ድካማቸው እንዲቀል የሚረዱበት ነው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ለአህዮቻቸው የሚበሉትን ገፈራ ሰጣቸው
ገፈራ ለከበቶች የሚሆን ድርቆሽ ነው

Genesis 43:26

በእጃቸው ያመጡአቸውን እጅ መንሻዎች አበረከቱለት
"እጅ" ሙሉን ሰው ይወክላል:: አት "ወንድሞች ያመጡአቸውን እጅ መንሻቸውን" (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በፊቱም ወድቀው ሰገዱለት
ይህ ክብርና አክብሮት የሚገለጽበት መንገድ ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 43:28

አገልጋይህ አባታችን
አባታቸውን እንደ "አገልጋይህ" ማመልከታቸው አክብሮታቸውን ለማሳየት ነው አት "አባታችን የሚያገለግልህ"

አጐንብሰው ሰገዱለት
እነዚህ ቃላት በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው በሰውየው ፊት ጐንበስ በማለት አክብሮታቸውን ገለጹ:: አት "በፊቱ ሰገዱለት" (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ዮሴፍም ዐይኑን ሲቃኝ
ቀና ብሎ ሲመለከት ማለት ነው ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ

የእናቱን ልጅ እናም አለ
ይህ በአድስ ዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት "የእናቱን ልጅ.. አየ:: ዮሴፍም አለ፤"

ታናሽ ወንድማችሁ ይህ ነውን?
ተገቢ አማራጭ ትርጉሞች 1 ይህ ሰው ብንያምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ዮሴፍ በውኑ ይጠይቃቸዋል ወይም 2) ይህ አግናኝ ጥያቄ ነው:: "ደግሞ ይህ ታናሽ ወንድማችሁ .... " (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ልጄ
ይህ አንድ ሰው በዝቅተኛ ደረጃ ላለ ሌላ ሰው በኅደኝነት መንገድ የሚጠራው አጠራር ነው:: አት "ወጣቱ"

Genesis 43:30

ፈጥኖ ከክፍሉ ወጣ
ተቻኩሎ ከክፍሉ ወጣ

ወንድሙን በማየቱ ስሜቱ በጥልቅ ስለተነካ
ስሜቱ በጥልቀት የሚለው ሀረግ አንድ መልካም ነገር ሲከሰት የሚሰማ ታላቅ ስሜትን ያመለክታል:: አት "ለወንድሙ የመራራት ጠንካራ ስሜት ነበረው" ወይም "ለወንድሙ ጠንካራ የናፍቆት ስሜት ነበረው" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አለ
ዮሴፍ እንደሚናገር ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት "እናም ለአገልጋዮቹ አላቸው" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ማዕድ ይቅረብ
ሰዎች እንዲመገቡ ምግብን ማቅረብ ማለት ነው።

Genesis 43:32

አገልጋዮችም ለዮሴፍ ለብቻው ለወንድሞቹም ለብቻቸው አቀረቡላቸው:: ከእርሱ ጋር ለሚበሉ ግብጻዊያን ደግሞ ለብቻቸው አቀረቡላቸው::
ይህም ዮሴፍ ወንድሞቹና ሌሎች በአንድ ክፍል በተለያየ ቦታ ተቀምጠው ይመገባሉ ማለት ነው አገልጋዮችም ለዮሴፍ ለብቻው ለመንድሞቹም ለብቻቸው እናም ከእርሱ ጋር ለሚበሉ ግብጻዊያን ደግሞ ለብቻቸው አቀረቡላቸው

ከእርሱ ጋር ለሚበሉ ግብጻዊያን ለብቻቸው
እነዚህ ምናልባት ከእርሱ ጋር የሚበሉ የግብጽ ባለሥልጣናት ይሆናሉ ነገር ግን ከዮሴፍና ከዕብራዊያን ወንድሞቹ ተለይተው ተቀምጠዋል

ግብጻዊያን ከዕብራዊያን ጋር መመገብ አይሆንላቸውም ምክንያቱም ያ ለግብጻዊያን መርከስ ነውና
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ይህንን ያደረጉበት ምክንያት ግብጻዊያን ከዕብራዊያን ጋር መመገብ ጸያፍ አድርገው ያስባሉ

አብረው እንጀራ አይበሉም
እዚህ እንጀራ ጠቅላላ ምግብ ይወክላል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወንድምቹ በእርሱ ፊት ተቀመጡ
እያንዳንዱ ወንድም የት መቀመጥ እንዳለበት ዮሴፍ እንዳዘጋጀ ሊገመት ይገልጻል የተገለጸውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ይቻላል አት የሚቀመጡበት ቦታ በተዘጋጀላቸው መሠረት በሰውየው/ዮሴፍ ፊት ወንድሞቹ ተቀመጡ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)

በፊቱም በኩሩ እንደታላቂነቱ ታናሹም እንደታናሽነቱ
"በኩር"ና "ታናሽ" የተጠቀሙት ሁሉም ወንድሞች በአንድነት እንደየዕድሜያቸው በተርታ እንደተቀመጡ ለመግለጽ ነው::(ነጠላ ነገር በብዙ የመግለጽ ዘይቤ/merism/ ይመልከቱ)

ሰዎቹም/ወንድሞቹም በአንድነት ተገረሙ
ይህን ባወቁ ጊዜ ሰዎቹ በጣም ተገረሙ

የብንያም ድርሻ ከሌሎች ወንድሞች አምስት እጥፍ ነበር
አምስት እጥፍ የሚለው ሀረግ በአጠቃላይ ብዙ በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት "ብንያም የተቀበለው ድርሻ ወንድሞቹ ከተቀበሉት በጣም ብዙ ነበር"

Chapter 44

1 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ለቤቱ አዛዥ እንዲህ ሲል መመሪያ ሰጠው፤ የሰዎቹ ስልቻ የሚይዘውን ያህል እህል በየስልቻቸው ሙላላቸው፤ የእያንዳንዱንም ገንዘብ
በየስልቻው አፍ አስቀምጠው። 2 ከዚያም የብር ዋንጫዬን በታናሹ ወንድማቸው ስልቻ አፍ ከእህሉ ዋጋ ጋር ጨምረው።” አዛዡም ዮሴፍ እንዳለው አደረገ። 3
ጠዋት በማለዳ ወንድማማቾቹ አህዮቻቸውን ይዘው እንዲሄዱ ተደረገ። 4 ከከተማውም ምንም ያህል ርቀው ሳይሄዱ፣ ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ እንዲህ አለው፤
“እነዚያን ሰዎች ቶሎ ድረስባቸውና፣ ‘በመልካም ፋንታ ክፉ የመለሳችሁት ስለ ምንድን ነው? 5 የጌታዬን የብር ዋንጫ የሰረቃችሁት ለምንድነው? ዋንጫው
ጌታዬ የሚጠጣበትና ሁሉን ነገር መርምሮ የሚያውቅበት እንደሆነ አታውቁምን? ይህ ያደረሳችሁት በደል እጅግ ከባድ ነው’ ብለህ ነገራቸው።” 6 የቤቱ
አዛዥም እንደደረሰባቸው፣ ልክ እንደተባለው ተናገራቸው። 7 እነርሱ ግን እንዲህ አሉት፤ “ጌታችን እንዲህ ያለ ነገር ለምን ይናገራል? እኛ አገልጋዮችህ እንዲህ
ያለውን ነገር አናደርገውም። 8 ከዚህ ቀደምም በየስልቾቻችን አፍ የተገኘውን ብር ከከነዓን እንኳ መልሰን አምጥተናል፤ ታዲያ አሁን ብር ወይም ወርቅ ከጌታህ
ቤት እንዴት እንሰርቃለን? 9 የጠፋው ዕቃ ከአገልጋዮችህ የተገኘበት ይሙት፤ የቀረነው የጌታችን ባሮች እንሁን።” 10 አዛዡም መልካም ነው፤ እንዳላችሁት
ይሁን፤ ጽዋው የተገኘበት ሰው ባሪያዬ ይሆናል፤ የቀራችሁት ግን ከበደል ነጻ ትሆናላችሁ” አላቸው። 11 ስለዚህ በፍጥነት ስልቻዎቻቸውን አወረዱ፤ እያንዳንዱም
የራሱን ስልቻ ከፈተ። 12 ከዚያም አዛዡ ፍተሻውን ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ቀጠለ። በመጨረሻም ጽዋው በብንያም ስልቻ ውስጥ ተገኘ። 13 በዚህ
ጊዜ ልብሶቻቸውን በሐዘን ቀደዱ፤ ሁሉም ስልቾቻቸውን በየአህዮቻቸው ጭነው ወደ ከተማይቱ ተመለሱ። 14 ይሁዳና ወንድሞቹ ወደ ዮሴፍ ቤት ሲገቡ፣ ዮሴፍ
ገና ከቤቱ አልወጣም ነበር። እነርሱም በፊቱ ተደፍተው ሰገዱ። 15 ዮሴፍም፣ “ለምን እንዲህ ያለ ነገር አደረጋችሁ? እንደ እኔ ያለ ሰው ስውር ነገርን
የሚያውቅበት ልዩ ጥበብ እንዳለው አታውቁምን?” ሲል ጠየቃቸው። 16 ይሁዳም፣ “ከእንግዲህ ለጌታችን ምን ማለት እንችላለን? ምንስ እንመልሳለን?
እንዲህ ካለው በደል ንጹሕ መሆናችንን ማስረዳትስ እንዴት ይቻለናል? ምክንያቱም እግዚአብሔር የሠራነውን በደል ገልጦታል፤ እንግዲህ ዋንጫው የተገኘበት
ሰው ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ባሪያዎችህ እንሁን” አለ። 17 ዮሴፍም፣ “ይህንስ አላደርገውም፣ ዋንጫው የተገኘበት ሰው ብቻ የእኔ ባሪያ መሆን አለበት፤
ሌሎቻችሁ በሰላም ወደ አባታችሁ መመለስ ትችላላችሁ” አለ። 18 ይሁዳም ወደ ዮሴፍ ቀረብ ብሎ፣ “ጌታዬ ሆይ፣ እኔ አገልጋይህ አንዲት ቃል ብቻ ልናገር፣
ምንም እንኳ የፈርዖን ያህል የተከበርክ ብትሆንም እባክህ አትቆጣኝ። 19 ጌታዬ፣ ‘አባት ወይም ወንድም አላችሁ?’ ብሎ አገልጋዮቹን ጠይቆ ነበር። 20 እኛም፣
‘አዎን ሽማግሌ አባት አለን፤ አባታችንም በስተርጅና የወለደው ትንሽ ልጅ አለው፣ ወንድምዬው ሞቶአል፣ ከአንድ እናት ከተወለዱት ልጆች መካከል የተረፈው
እርሱ ብቻ ነው፤ አባቱም በጣም ይወደዋል’ ብለንህ ነበር። 21 ከዚያም አንተ አገልጋዮችህን፣ ‘እንዳየው ወደ እኔ አምጡት’ አልኸን። 22 እኛም ለጌታዬ፣ ‘ልጁ
ከአባቱ ሊለይ አይችልም፤ ከተለየው ደግሞ አባትዬው ይሞታል’ አልንህ። 23 አንተ ግን እኛን አገልጋዮችህን፣ ‘ታናሽ ወንድማችሁ አብሮአችሁ ወደዚህ ካልመጣ
ዳግመኛ ፊቴን ዐታዩም’ አልኸን። 24 እኛም ወደ አገልጋይህ ወደ አባቴ በተመለስን ጊዜ አንተ ጌታዬ ያልኸንን ነገርነው። 25 ከዚያም አባታችን፣ ‘እስቲ
ተመልሳችሁ ጥቂት እህል ሸምቱልን’ ሲለን 26 ‘መሄድ አንችልም፤ መሄድ የምንችለው ታናሽ ወንድማችን አብሮን ሲሄድ ብቻ ነው። ታናሽ ወንድማችንን ይዘን
ካልሄድን በስተቀር የሰውዬውን ፊት ማየት አንችልም’ አልነው። 27 አገልጋይህ አባቴም እንዲህ አለን፤ ‘ሚስቴ ሁለት ወንዶች ልጆች እንደወለደችልኝ
ታውቃላችሁ፤ 28 አንዱ በወጣበት በመቅረቱ በእርግጥ አውሬ በልቶት ይሆናል አልሁ፣ ከዚያ በኋላ ዐላየሁትም። 29 አሁን ደግሞ ይህን ልጅ ወስዳችሁ አንዳች
ጉዳት ቢደርስበት ሽበቴን በመራር ሐዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ።’ 30 እንግዲህ አሁን ልጁን ሳንይዝ ወደ አገልጋይህ ወደ አባቴ ብመለስ ሕይወቱ ከልጁ
ሕይወት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ስለሆነ፣ 31 የልጁን ከእኛ ጋር አለመኖር ሲያይ አባቴ ይሞታል። ከዚህም የተነሣ እኛ አገልጋዮችህ የአባታችንን ሽበት በመሪር
ሐዘን ወደ መቃብር እናወርደዋለን። 32 እኔ አገልጋይህ፣ “ልጅህን መልሼ ሳላመጣ ብቀር ለዘላለም በደለኛ አድርገህ ቁጠረኝ’ በማለት ስለ ልጁ ደህንነት
በአባቴ ፊት ራሴን ዋስ አድርጌአለሁ። 33 ስለዚህ አሁን፣ አገልጋይህ በልጁ ፋንታ የአንተ የጌታዬ ባሪያ ሆኜ እዚሁ ልቅር ልጁ ግን ከወንድሞቹ ጋር ይመለስ። 34
ልጁን ሳልይዝ እንዴት ተመልሼ ወደ አባቴ እሄዳለሁ? እባክህ በአባቴ ላይ የሚደርሰውን መከራ እንዳይ አታድርገኝ።”

Genesis 44:1

አጠቃላይ መረጃ
ይህ በታሪኩ አድስ ክስተት ይጀምራል ይህ በተለይ ከግብዣው ሁለተኛው ቀን ማግሥት የተከሰተውን ያመለክታል።

የቤቱ አዛዥ
የቤቱ አዛዥ የዮሴፍ ቤት ተግባራትን ለማስተዳደር ኃላፊነት ያለው ነበር

የሁሉም ሰው ገንዘብ
የእነርሱ ገንዘብ በትንሽ ቦርሳ ውስጥ የተቀመጡ የብር ሳንቲሞች ነበሩ

በስልቻው አፍ
በስልቻው

ዋንጫየን የብሩን ዋንጫዬን... ጨምረው
የብሩን ዋንጫዬን ጨምረው

በታናሹ ወንድማቸው ስልቻ አፍ
ወንድም የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት በታናሽ ወንድማቸው ስልቻ (ድብቅ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 44:3

ጎህ ሲቀድ
የማለዳ ብርሃን ሲወጣ

ሰዎቹ ከነአህዮቻቸው ተሸኙ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ሰዎችን ከነአህዮቻቸው ሸኙአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ለበጎ ነገር ስለምን ክፉ መለሳችሁ?
ይህ ጥያቄ ወንድሞቹን ለመቆጣት ተጠቅሞአል:: አት እኛ “ለእናንተ መልካም ካደረግን በኋላ ክፉ መለሳችሁብን” (ሽንገላ አዘል/ rhetorical/ ጥያቄ ይመልከቱ)

ይህ ጌታዬ የሚጠጣበት የተሰወረ ነገርም የሚያውቅበት ጽዋ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የተጠቀመው ወንድሞቹን ለመቆጣት ነው። አት “ይህ ጽዋ ጌታዬ የሚጠጣበትና የተሰወረ ነገርንም የሚያውቅበት እንደሆነ በእርግጥ ታውቃችሁ” (ሽንገላን የያዘ ጥያቄ ይመልከቱ) ይህ ያደረጋችሁት የፈጸማችሁት ድርጊት ክፉ ነው ያደረጋችሁት የሚለውን መደጋገሙ ትኩረት ለመስጠት ነው አት የፈጸማችሁት ነገር እጅግ ክፉ ነው ተመሣሣይ ተጓዳኝ ንጽጽር ነው::

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 44:6

ይህንም ቃል ነገራቸው
ዮሴፍ የነገራቸው የነገረውን ነገራቸው

ጌታዬ እንደዚህ ያለውን ቃል ለምን ይናገራል?
“ቃል” የተናገረውን ነገር:: ይወክላል ወንድሞቹ የቤቱን አዛዥ እንደ “ጌታዬ” ያመለክታሉ:: ይህ በከፍተኛ ኃላፊነት ላሌ ሰው የሚነገር መደበኛ አባባል ነው:: አት “ጌታዬ ለምን እንደዚህ ይናገራሉ?” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤና አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ይህን ነገር ማድረግ ከባሪያዎችህ ይራቅ
አንድ ሰው አንድን ነገር የማያደርገው ያ ሰው አንድን ዕቃ ከራሱ አርቆ እንደማስቀመጥ ተደርጐ ተገልጾአል፣ (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 44:8

እነሆ...ብር
“እኛ ስለምንናገረው ነገር ያድምጡ እናም የምንናገረው ነገር እውነት እንደሆነ ያያሉ፤ ብሩ”

በየስልቻቻችን አፍ የተገኘውን ብር
“በየስልቻቻችን ያገኘነውን ብር ያውቃሉ”

ከከነዓን አገር መልሰን ወደ አንተ አምጥተናል
ከከነዓን መልሰን ወደ አንተ አምጥተናል

ታዲያ ብር ወይም ወርቅ ከጌታህ ቤት እንዴት እንሰርቃለን?
ወንድሞቹ ከግብጽ ጌታ እንዳልሠረቁ አትኩሮት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ:: አት “ስለዚህ ከጌታህ ቤት የወሰድነው ምንም ነገር የለም!” (ሽንገላ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ብር ወይም ወርቅ
እንዚህ በጣምራ ቃላት የተጠቀሙት ዋጋ ያለውን ምንም ነገር እንዳልሠረቁ ለመግለጽ ነው

ከአገልጋዮችህ ይህ የተገኘበት
ወንድምች ራሳቸውን እንደ “የአንተ አገልጋዮች” ይገልጻሉ:: ይህ ከፍተኛ ስልጣን ላለ ሰው የሚነገር መደበኛ መንገድ ነው:: እንዲሁም ይህ የተገኘበት ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክሊገለጽ ይችላል:: አት “ከእኛ አንዱ ጽዋውን/ ዋንጫውን የሠረቀ ከተገኘ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገለላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እኛ ደግሞ የጌታችን ባሮች እንሁን
እዚህ ጌታችን የቤቱን አዛዥ ያመለክታል ይህ በሁለተኛ ሰው መልክ ሲገለጽ ይችላል አት እንደባሪዎች ሊትወስደን ትችላለህ (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገለላለጽ ይመልከቱ)

አሁን እንዲሁ እንደነገራችሁ ይሁን
መልካም ነው: እንዳላችሁት አደርጋለሁ:: እዚህ “አሁን” “በዚህ ጊዜ” ማለት አይደለም ነገር ግን የሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ተጠቅሞአል::

ጽዋው የተገኘበት ባሪያዬ ይሆናል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ከስልቻቻችን በአንዱ ጽዋውን ካገኘው ያ የተገኘበት ሰው ባሪያዬ ይሆናል (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 44:11

የየራሱን ስልቻ ወደ ምድር አወረደ
የየራሱን ስልቻ አራገፌ

ከታላቁ ... እስከታናሹ
“ወንድም” የተባለው ቃል የታወቀ ነው:: “ከታላቅ ወንድም ....እስከ ታናሽ ወንድም” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ጽዋው በታናሹ በብንያም ስልቻ ተገኘ
ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገርና ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል በታናሹ ወንድም የቤቱ አዛዥ ጽዋውን በብንያምን ስልቻ አገኘ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በዚህን ጊዜ እነርሱ ልብሳቸውን ቀደዱ
እዚህ እነርሱ ወንድሞቹን ያመለክታል ልብስን መቅደድ የታላቅ ሐዘን ወይም ተካዜ ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በየአህዮቻቸው...ተመለሱ
በየአህዮቻቸው.... እናም ተመለሱ

Genesis 44:14

እርሱ ገና እዚያው ነበረ
ዮሴፍ እዚያው ነበረ

በፊቱም መሬት ላይ ተደፉ
በፊቱም መሬት ላይ ወደቁ:: ይህ ወንድሞቹ ጌታው ምሕረት እንዲያደርግላቸው የመፈለጋቸው ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

እንደ እኔ ያለ ሰው ምሥጢርን እንዲያውቅ አታውቁምን
ዮሴፍ ወንድሞቹን ለመቆጣት ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “እንደ እኔ ያለ ሰው ስውር ነገርን በጥበብ እንደሚያውቅ ታውቃላችሁ” (ሽንገላን ያዘለ ጥያቄ ይመልከቱ)

Genesis 44:16

ለጌታዬ ምን እንመልሳለን? ምንስ እንናገራለን? ወይም በመን እንነጻለን?
ሶስቱም ጥያቄዎች ሁሉ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: የተደረገውን ለመግለጽ የሚናገሩት ምንም እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማሉ። አት “ጌታዬ የምንናገረው የለንም የሚረባ ነገር መናገር አንችልም ራሳችንን ንጹህ ማድረግ አንችልም” (ተመሣሣይ ተጓዳኝ አገላለጽ እና ሽንገላ አዘል ጥያቄዎች ይመልከቱ)

ለጌታዬ ምን እንላለን .... የጌታዬ ባሪያዎች
እዚህ ጌታዬ ዮሴፍን ያመለክታል ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው በሁለተኛ ወገን ሰው መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ምን እንላለን ... ባሪያዎችህ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የአገልጋዮችን/የባሪያችህን በደል ገልጦአል
ወንድሞቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች ያቀርባሉ :: እዚህ ገለጠ የሚለው እግዚአብሔር ወንድሞቹ ያደረጉትን ገለጠ ማለት አይደለም:: ነገር ግን እነርሱ ስላደረጉት ነገር እግዚአብሔር እየቀጣቸው ነው የሚል ትርጉም አለው:: አት “እግዚአብሔር ላለፈው ኃጢአት እየቀጣቸው ነው”

የባሪያዎችህን በደል
ወንድሞቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች ያቀርባሉ:; ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: በአንደኛ ወገን ሰው መልክ

ሊገለጽ ይችላል:: አት “በደላችንን” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እንግዲህ ጽዋው በእጁ የተገኘበት
እዚህ “እጅ” ሙሉ ሰው ይወክላል:: እንዲሁም የተገኘበት የሚለው ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:; አት “ጽዋህን የወሰደው” (ምትክ ቃል አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይህን ማድረግ ከእኔ ይራቅ
አንድ ሰው የማያደርገው አንድ ነገር ያ ሰው ከራሱ አርቆ የሚያቀምጠው ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “ያን ነገር የሚያደርግ የእኔ ዓይነት አይደለም” (ዘይቤያዊ አነጋሃገር ይመልከቱ)

ጽዋው በእጁ የተገኘበት ሰው
እዚህ “እጅ” ሙሉ ሰው ይወክላል:: እንዲሁም የተገኘበት የሚለው ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:; አት “ጽዋዬን የወሰደው ሰው” (ምትክ ቃል አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 44:18

ቀረብ ብሎ
ተጠግቶ

እኔ አገልጋይህ
ይሁዳ ራሱን እንደ “አገልጋይህ ወይም ባሪያህ” ያመለክታል:: ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ በአንደኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኔ ባሪያህ ወይም አገልጋይህ”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በጌታዬ ጆሮ አንዲት ቃል እንድናገር
“ጆሮ” የሚለው ለሙሉ ሰው የሚሆን ምትክ ቃል ነው። አት “ጌታዬ ሊናገርህ” (ምትክ ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ)

በጌታዬ ጆሮ
እዚህ ጌታዬ ዮሴፍን ያመለክታል። ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ለአንተ”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እኔን አገልጋይህን ቁጣህ አያቃጥለኝ
መቆጣት እንደሚያቃጥል እሳት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “አባክህን እኔን አገልጋይህን አትቆጣኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አንተ እንደፈርዖን ነህና
ጌታው ትልቅ ሥልጣን እንዳለው ትኩረት ለመስጠት ከፈርዖን ጋር ያወዳድረዋል:: ይህም የሚገልጸው ሊቆጣውም ሊገድለውም እንደሚችል ነው አት “እንደ ፈርዖን ኃይለኛ ስለሆንህና ወታደሮችህም ሊገድሉኝ ስለሚችሉ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

ጌታዬ ባሪያዎቹን፤ “አባት አላችሁ ወይም ወንድም?”ብሎ ጠየቀ::
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ጌታዬ አባት ወይም ወንድም እንዳለን ጠየቀን” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ጌታዬ ባሪያዎቹን ጠየቀ
ይሁዳ ዮሴፍን “ጌታዬ” እና “እርሱ” በሚሉ ቃላት ያመለክተዋል:: እንዲሁም ደግሞ ወንድሞቹንና ራሱን እንደ “የእርሱ ባሪያዎች” ይገልጻል:: አት “አንተ ጌታዬ ባሪያዎችህን ጠየቅኸን ወይም አንተ ጠቀየቅኸን” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

Genesis 44:20

አጠቃላይ መረጃ
በዮሴፍ ፊት መናገሩን ይሁዳ ቀጠለ

እኛም ለጌታዬ እንዲህ አልን ‘ሽማግሌ አባት አለን .... አባቱም ይወድደዋል’
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እናም እኛ እንዲህ አልን ‘አባት አለን አባቱም ይወድደዋል’” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ለጌታዬ እንዲህ አልን
ይሁዳ ዮሴፍን እንደ “ጌታዬ” ያመለክተዋል:: ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: አት “ጌታዬ እኛም እንዲህ አልን”(አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

አባቱም ይወድደዋል
ይህ ለጓደኛ ወዳጅ ወይም ለቤተሰብ አባል ያለውን ፍቅር ይገልጻል

ከዚያም ለባሪያዎችህ ወደእኔ አምጡት እኔም አየዋለሁ አልህ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እናም አንተ ለባሪያዎችህን ታናሽ ወንድማችሁን አምጡት እኔም አየዋለሁ አልህ’” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ከዚያም ለባሪያዎችህ እንዲህ አልህ
ይሁዳ ወንድሞቹንና ራሱን እንደ እርሱ ባሪያዎች ያመለክታል:: አት “ከዚያም ለእኛ ለባሪያዎችህ እንዲህ አልህ”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

ወደ እኔ ይዛችሁ ውረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር መውረድ የሚለው ቃል የተለመደ ነው:: አት “ወደ እኔ አምጡት” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከዚያም በኋላ ጌታዬን አልነው “ብላቴናው... አይሆንለትም ...አባቱ ይሞታልና”
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “መልሰን እኛም ለጌታዬ ልጁ ....አይችልም፤ ....አባትየው ይሞታል” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

አባትዬው ይሞታል
ከማዘን የተነሣ አባታቸው እንደሚሞት ይገልጻል (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 44:23

አጠቃላይ መረጃ
ይሁዳ ታሪኩን ለዮሴፍ መናገር ቀጠለ

ከዚያም ባሪያዎችህን እንዲህ አልሄን፤ ታናሽ ወንድማችሁ ከእናንተ ጋር ጋር ካልመጣ ዳግመኛ ፊቴን አታዩም
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚያም ለባሪያዎችህ ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር ካልመጣ ፊቴን አታዩም አልሄን ” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ከዚያም ለባሪያዎችህ አልህ
ይሁዳ ራሱንና ወንድሞቹን እንደ “እርሱ ባሪያዎች” ያመለክታል። ይህ ትልቅ ባለሥልጣን ለሆነ ለአንድ ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው። (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

ይዞ መውረድ ...ወደ ታች መውረድ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር መውረድ የሚለው ቃል የተለመደ ነው::

ዳግመኛ ፊቴን አታዩም
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰውን ይወክላል:: አት እንደገና አታዩኝም (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ከዚያም እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመለከት ነው:: በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ:: (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ወደ ባሪያህ ወደ አባታችን በወጣን ጊዜ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ ሲነገር “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው

የጌታዬን ቃል ነገርነው
ይሁዳ ዮሴፍን እንደ “ጌታዬ” ያመለክታል:: አት ጌታዬ የነገርከውን ቃል ነገርነው”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)

አባታችን ‘ተመልሳችሁ ጥቂት እህል ሸምቱልን አለ’
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አባታችን እንደገና ወደ ግብጽ በመሄድ ለእኛና ለቤተሰቦቻችን እህል እንድንሸምት ተናገረን ” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እኛም አልነው ‘መሄድ አንችልም ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር...’
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚያም ለእርሱ ወደ ግብጽ መውረድ አንችልም አልን ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር … ከእኛ ጋር ” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

የሰውየውን ፊት ማየት
እዚህ ፊት ሙሉ ሰውን ይወክላል:: አት “ሰውየውን ለማየት” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 44:27

ይሁዳ ታሪኩን ለዮሴፍ መናገርን ቀጠለ
እንዲህ አለን ሚስቴ ሁለት ወንዶች ልጆችን እንደወለደችልን እናንተ ታውቃላችሁ አንዱ ከእኔ ወጣ አውሬ በላው አላችሁኝ እስከ ዛሬም አላየሁትም ይህንም ከእኔ ለይታችሁ ደግሞ ብትወስዱ ክፉም ቢያገኘው ሽበቴን በሐዘን ወደ መቃበር ታወርዱታላችሁ ይህ ሁለት ደረጃና ሶስት ደረጃ ጥቅሶችን ይዞአል እነዚህም እንደተዘዋዋሪ ጥቅሶች ሊገለጹ ይችላሉ አት እንዲህ አለን ሚስቱ ራሔል ሁለት ወንዶች ልጆችን ብቻ እንደወለደችለት እናውቃለን ከእነርሱ አንዱ ወጣና አውሬ በላው እናም እስከ ዛሬ አላየሁትም ሌላውን ልጅ ብንወስደውና ክፉ ቢያገኘው በሐዘን እንዲሞት እናደርጋለን (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)ከዚይ አለ

እኛን እንዲህ አለን
እዚህ “እኛ” ዮሴፍን አያካትትም (ነጠላና ብዙ ወይም አካታች “እኛ” ይመልከቱ)

እናንተ ታውቃላችሁ
እዚህ “እናንተ” ብዙና ወንድሞቹን ያመለክታል (“እናንተ” አጠቃቀም ዓይነት ይመልከቱ)

በአውሬ ተበላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት አውሬ በላው ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ

ጉዳት ቢደርስበት
ለአንድ ሰው አንድ ክፉ ነገር የሚደርሰበት ጉዳት ወደዚያ ሰው እንደሚመጣ ተደርጎ ተቆጥሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሽበተን በሐዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ
“ወደ መቃብር ማውረድ” እንዲሞትና ወደ መቃብር እንዲወርድ ማድረግ ማለት ነው:: “ማውረድ” የሚለውን ቃል የተጠቀመው መቃብር በመሬት ውስጥ እንደሆነ በተለምዶ የታወቀ ስለሆነ ነው:: አት “ከዚያም እኔን ሽማግሌውን በሐዘን እንዲሞት ታደርጋላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሽበቴን
ያዕቆብን የሚያመለክትና ሽምግልናውን አበክሮ የሚናገር ነው:: አት “እኔ ሽማግለው” (ምትክ ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 44:30

አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነገር ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል

እንግዲህ በምንመለስበት ጊዜ ... በሐዘን ወደ መቃብር
ይሁዳ ያለ ብንያምን ወደ አባቱ በሚመለስበት ጊዜ ምን ሊፈጠር እንደሚችል የሚገምተውን ነገር ግን እውነት የሆነውን ለዮሴፍ ይገልጻል (ግምታዊ ሁኔታዎችን ይመልከቱ)

ወደ ባሪያህ በሚመጣበት ጊዜ
እዚህ “መምጣት” “መሄድ” ወይም “መመለስ” በሚለው መተርጐም ይችላል::

ብላቴናው ከእኛ ጋር አለመኖር
ልጁ ከእኛ ጋር አለመኖር

ሕይወቱ ከልጁ ሕይወት ጋር የተሣሠረ ስለሆነ
አባታቸው ልጁ ከሞቴ እሞታለሁ ያለው አባባል የሁለቱ ሕይወት በአካል በጥብቅ የተሣሠረ እንደሆነ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “እርሱም ልጁ ካልተመለሰ እሞታለሁ ስላለ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ
ይሁዳ ወደፊት ይሆናል ብሎ ስለሚገምተው ነገር በእርግጥ እደሚደረግ አድርጐ ይናገራል (ግምታዊ ሁኔታዎች ይመልከቱ)

ባሪያዎችህ የባሪያህን የአባታችንን ሽበት በሐዘን ወደ መቃብር ያወርዳሉ
ወደ መቃብር ማውረድ እንዲሞትና ወደ መቃብር እንዲወርድ ማድረግ ማለት ነው:: “ማውረድ” የሚለውን ቃል የተጠቀመው መቃብር በመሬት ውስጥ እንደሆነ በተለምዶ የታወቀ ስለሆነ ነው:: አት “እናም ሽማግሌውን አባታችንን በሐዘን እንዲሞት እናደርጋለን” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ባሪያዎችህ ወይም አገልጋዮችህ
ይሁዳ ራሱንና ወንድሞችን “ባሪያዎችህ” ብሎ ያመለክታል:: ይህ ለአንድ ትልቅ ባለሥልጣን መደበኛ መንገድ የሚነገርለት ነው:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” ወይም “እናም እኛ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገንነ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

የባሪያህን የአባታችንን ሽበት
እዚህ “ሽበት” ያዕቆብን የሚወክልና ሽምግልናውን የሚናገር ነው:: አት “ሽማግሌው አባታችን” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ) ስለ ልጁ ደኅንነት በአባቴ ፊት ራሴን ዋስ አድርጌአለሁ ረቂቅ ስም ዋስ ተስፋ በሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል አት ልጁን በሚመለከት ለአባቴ ተስፋ ስጥቼዋለሁ ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ

ባሪያህ
ይሁዳ ራሱን “ባሪያህ” ብሎ ያመለክታል። አት “ለእኔ ለባሪያህ” ወይም “ለእኔ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በአባቴ ፊት በደሌን እሸከማለሁ
እንደበደለኛ መቆጠር በደል እንድሰው የሚሸከመው ነገር ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “አባቴ ይወቅሰኛል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 44:33

አሁን
ይህ በአሁን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል::

ባሪያህ
ይሁዳ ራሱን “ባሪያህ” ብሎ ያመለክታል። አት “እኔ ለባሪያህ” ወይም “እኔ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ልጁ... ይውጣ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ መውጣት የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር

ልጁን ሳልይዝ እንዴት ተመልሼ ወደ አባቴ እሄዳለሁ?
ብንያምን ወደ ቤት ካልተመለሰ አባቱ ሊኖረው የሚችለውን ሐዘን ለማተኮር ይሁዳ ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “ልጁ ከእኔ ጋር ካልሆነ ወደ አባቴ መመለስ እልችልም“ (አግናኝ ወይም ሽንገላ አዘል ጥያቄዎች ይመልከቱ)

በአባቶ ላይ የሚደርሰውን መከራ እንዳላይ
ከባድ መከራ የደረሰበት ሰው በዚያው ሰው ክፉ ነገር እንደመጣበት ተደርጐ ተነግሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Chapter 45

1 በዚያን ጊዜ ዮሴፍ አጠገቡ በነበሩ ሰዎች ፊት ስሜቱን ሊገታ ባለመቻሉ፣ “እዚህ ያሉትን ሰዎች በሙሉ አስወጡልኝ” ብሎ ጮኾ ተናገረ፤ ስለዚህም ዮሴፍ
ራሱን ለወንድሞቹ በገለጠበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ሌላ ማንም ሰው አልነበረም። 2 ዮሴፍም ድምፁን ከፍ አድርጎ በማልቀሱ ግብፃውያን ሰሙት፣ ወሬውም ወደ
ፈርዖን ቤተ ሰዎች ደረሰ። 3 ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ “እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ ለመሆኑ አባቴ እስካሁን በሕይወት አለ?” ሲል ጠየቃቸው። ወንድሞቹ ግን በፊቱ
ተደናግጠው ስለነበር መልስ ሊሰጡት አልቻሉም። 4 ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ “እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በሉ” አላቸው፣ ወደ እርሱም በቀረቡ ጊዜ እንዲህ አለ፤ “ወደ
ግብፅ የሸጣችሁኝ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ 5 አሁንም በመሸጣችሁ አትቆጩ፤ በራሳችሁም አትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ
እኔን ወደዚህ ልኮኛል። 6 በምድር ላይ ራብ ከገባ ይኸው ሁለት ዓመት ሆነ፣ ከዚህ በኋላም የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበሰብባቸው አምስት ዓመታት ገና
አሉ። 7 ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፋ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ። 8
ስለዚህ አሁን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር እንጂ እናንተ አይደላችሁም፣ እርሱም ለፈርዖን እንደ አባት፤ በቤት ንብረቱ ላይ ጌታ፣ እንዲሁም በግብፅ ምድር ላይ
ገዢ አደረገኝ። 9 አሁንም ‘በፍጥነት ወደ አባቴ ተመልሳችሁ እንዲህ በሉት፤ “ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ይላል፤ ‘እግዚአብሔር የመላው ግብፅ ጌታ አድርጎኛል፤
ስለዚህ ሳትዘገይ ወደ እኔ ና። 10 ልጆችህን የልጅ ልጆችህን በጎችህን፣ ፍየሎችህን ከብቶችህንና ያለህን ሁሉ ይዘህ በአቅራቢያዬ በጌሤም ትኖራለህ። 11 ገና
ወደ ፊት የሚመጣ የአምስት ዓመት ራብ ስላለ፣ በዚያ የሚያስፈልጋችሁን እኔ እሰጣችኋለሁ፤ ያለበልዚያ ግን አንተና ቤተ ስዎችህ ያንተም የሆነው ሁሉ፣ ችግር
ላይ ትወድቃላችሁ።’ 12 ፊታችሁ ሆኜ የማናግራችሁ እኔ ዮሴፍ ራሴ መሆኔን እናንተም ሆናችሁ ወንድሜ ብንያም በዓይናችሁ የምታዩት ነው። 13 በግብፅ
ስላሏኝ ክብርና ስላያችሁትም ሁሉ ለአባቴ ንገሩት፣ አባቴንም በፍጥነት ይዛችሁት ኑ። 14 ከዚያም በወንድሙ በብንያም አንገት ላይ ተጠምጥሞ አለቀሰ፤
ብንያምም እያለቀሰ ዮሴፍን አቀፈው። 15 የቀሩትምንም ወንድሞቹን አንድ በአንድ እየሳመ አለቀሰ። ከዚያም ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መጨዋወት ጀመሩ። 16
የዮሴፍ ወንድሞች መምጣት በፈርዖን ቤተ መንግሥት በተሰማ ጊዜ፣ ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ ደስ አላቸው። 17 ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “ለወድሞችህ
እንዲህ ብለህ ንገራቸው፣ ‘እንዲህ አድርጉ እህዮቻችሁን ጭናችሁ ወደ ከነዓን ምድር ተመለሱ። 18 ከዚያም አባታችሁንና ቤተ ሰባችሁን ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤
እኔም እጅግ ለም ከሆነው የግብፅ ምድር እሰጣችኋለሁ፤ በምድሪቱ በረከት ደስ ብሎአችሁ ትኖራላችሁ።’ 19 ደግሞም እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፤ ‘ይህን
አድርጉ፣ ከግብፅ ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን የምታጓጉዙባቸው ሠረገላዎች ወስዳችሁ፤ አባታችሁን ይዛችሁ ኑ። 20 ስለ ንብረታችሁ ምንም አታስቡ፣
ከግብፅ ምድር እጅግ ለም የሆነው የእናንተ ይሆናልና።’” 21 የእስራኤልም ልጆች ይህንኑ አደረጉ። ዮሴፍም ፈርዖን ባዘዘው መሠረት ሠረገላዎች አቀረበላቸው፤
የመንገድም ስንቅ አስያዛቸው። 22 ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት የክት ልብስ ሰጣቸው፤ ለብንያም ግን ሶስት መቶ ጥሬ ብርና አምስት የክት ልብስ ሰጠው። 23
ለአባቱም በግብፅ ምድር ከሚገኘው የተመረጠ ነገር በዐሥር አህዮች፣ እንደዚሁም በዐሥር እንስት አህዮች ዳቦና ሌላ ምግብ አስጭኖ ሰደደለት። 24 ከዚህ
በኋላ ወንድሞቹን አሰናበታቸው፤ ከእርሱም ሲሰናበቱ፣ መንገድ ላይ እንዳትጣሉ” አላቸው። 25 እነርሱም ከግብፅ ወጥረው በከነዓን ምድር ወደሚኖረው ወደ
አባታቸው ወደ ያዕቆብ መጡ። 26 አባታቸውንም፣ እነሆ ዮሴፍ በሕይወት አለ፤ እንዲያውም በግብፅ ምድር ሁሉ ገዥ ሆኖአል” ብለው ነገሩት። ያዕቆብ ግን
እጅግ ደነገጠ፤ ሊያምናቸውም አልቻለም። 27 ነገር ግን ዮሴፍ ያላቸውን ሁሉ በነገሩት ጊዜና እርሱን ወደ ግብፅ የሚወስዱበትን ዮሴፍ የላከለትን ሠረገላ ባየ
ጊዜ የአባታቸው የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ። 28 ከዚያም እስራኤል፣ “ልጄ ዮሴፍ በሕይወት አለ፤ ከመሞቴ በፊት ሄጄ ዐየዋለሁ” አለ።

Genesis 45:1

ራሱን ሊቆጣጠር አልቻለም
ስሜቱን ሊገታ አልቻለም ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ማልቀስ ጀምሮ ነበር”

ከጐኑ
አጠገቡ

የፈርዖን ቤት
እዚህ “ቤት” በፈርዖን ቤተመንሥት ያሉ ሰዎችን ይወክላል። አት “በፈርዖን በተመንግሥት ያለው ሁሉ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

በፊቱ ተደናግጠው
እርሱን ፈርተው

Genesis 45:4

ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት “ወደ ግብጽ ላመጡኝ ነጋዴዎች እንደ ባሪያ የሸጣችሁኝ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አትዘኑ
“አትቄጩ” ወይመ “አትጨነቁ”

ወደዚህ ስለሸጣችሁኝ
ትርጉሙም በግልጽ ሊነገር ይችላል። አት “እንደ ባሪያ ሸጣችሁኝ እናም ወደ ግብጽ ምድር ላካችሁን”

ሕይወት ለማዳን
እዚህ “ሕይወት” ዮሴፍ በረሃቡ ጊዜ ያዳናቸውን ሰዎች ይወክላል:: አት “የብዙ ሰዎችን ሕይወት እንዳድን” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበሰብባቸው አምስት ዓመታት ገና አሉ
የማይታረስባቸው ወይም ሰብል የማይሰበሰባቸው አምስት ዓመታት አሉ እዚህ የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበስብባቸው ሰብሎች ከድርቁ የተነሣ እንደማይመረቱ የሚገልጹ ናቸው:: አት “ረሃቡ ለተጨማሪ አምስት ዓመታት ይቀጥላል” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 45:7

በምድር ላይ ቅሬታን አስቀርላችሁ ዘንድ
“እናንተና ቤተሰቦቻችሁ ከምድር ላይ ፈጽማችሁ እንዳትጠፉ” ወይም “ዘራች ከምድር ላይ እንዲኖር”

ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግ
ማዳን የተባለው ረቂቅ ስም ማትረፍ በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት “በታላቅ መንገድ በማትረፍ በሕይወት እንዲትኖሩ” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

ፈርዖን አባት አድርጐኛል
ዮሴፍ ፍርዖንን ማማከሩና መርዳቱ ዮሴፍ እንደፈርዖን አባት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት "የፈርዖን መሪ ወይም አማካሪ አድርጐኛል" ወይም "የፈርዖን ዋና አማካሪ አድርጐኛል" (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በቤቱ ሁሉ ላይ
እዚህ "ቤት" በቤተመንግሥቱ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል:: አት "በቤተሰዎቹ ሁሉ ላይ" ወይም "በቤተመግሥቱ ላይ" (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር ሁሉ ላይ ገዥ
እዚህ "ምድር" ሰዎችን ይወክላል:: አት "በግብጽ ምድር ሰዎች ሁሉ ላይ ገዥ" (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ገዥ
ዮሴፍ ከግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ሁለተኛ ደረጃ ገዥ ነው ማለት ነው:: ይህ የተነገረው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 45:9

ወደ አባቴ ውጡ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ ሲነገር ወደ ላይ መውጣት የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር:: አት "ወደ አባቴ ሂዱ"

እንዲህም በሉት ልጅህ ዮሴፍ እዲህ ይላል "እግዚአብሔር ... ያለህን ሁሉ"
ይህ ሶስት ደረጃ ያለው ጥቅስ ነው በሁለት ደረጃዎች ቀለል ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት "እኔ የምለውን ንገሩት እግዚአብሔር ያለህን ሁሉ" (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

ወደ እኔ ና/ውረድ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር ወደ ታች መውረድ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር:: አት "ወደዚህ ወደ እኔ ና"

ወደ ችግር ና
ችግርን እንደ መድረሻ አድርጐ ይናገራል:: አት "ማጣት" ወይም "ረሀብ" (ዘይቤያዊ አነገር ይመልከቱ)

Genesis 45:12

የእናንተ ዐይኖች አይተዋል እናም የወንድማችሁ የብንያምም ዐይኖች አይተዋል
እዚህ "ዐይኖች" ሙሉ ሰው ይወክላሉ:: አት "እናንተ ሁላችሁና ብንያም ታያላችሁ" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ለእናንተ የተናገረቻችሁ የእኔ አፍ እንደሆነች
እዚህ አፍ ሙሉ ሰውን ይወክላል። አት "እኔ ዮሴፍ እነግራችኋለሁ" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በግብጽ ስላለኝ ክብር ሁሉ
የግብጽ ሰዎች በታላቅነት እንዴት እንደሚያከብሩኝ

አባቴን ወደ ታች ወደዚህ አምጡት
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር ወደ ታች መውረድ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር:: አት "አባቴን ወደዚህ አምጡት"

Genesis 45:14

የወንድሙን የብንያምንም አንገት አቀፎ አለቀሰ ብንያምም በአንገቱ ላይ አለቀሰ
ዮሴፍ ወንድሙን ብንያምን አቀፈውና ሁለቱም አለቀሱ

ወንድሞቹን ሁሉ ሳማቸው
በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ ዘመድን በመሳም ሰላምታ መስጠት የተለመደ ነበር:: በቋንቋዎ እንዲህ የመሰለ ስሜት ገላጭ ሰላምታ አሰጣጥ ካለ ያን ይጠቀሙ:: ከሌለ ግን ተገቢ የሆነውን ቃል ይጠቀሙ::

እየሳማቸው አለቀሰ
ይህም ዮሴፍ በሳማቸው ጊዜ እያለቀሰ ነበር ማለት ነው

ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መነጋገር ጀመሩ
አስቀድመው ሊነጋገሩ ፈርተው ነበር:: አሁን ግን በነጻነት መነጋገር እንደሚችሉ ተሰማቸው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት "ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር በነጻነት መነጋገር ጀመሩ" (ግምታም እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 45:16

በፈርዖን ቤት የዮሴፍ ወንድሞች መጡ ተብሎ ወሬ ተሰማ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: እንዲሁም ደግሞ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "የዮሴፍ ወንድሞች እንደመጡ በፈርዖን ቤተመንግሥት ያለው ማንኛውም ሰው ሰማ" (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅስ እናም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የፈርዖን ቤት
የፈርዖንን ቤተመንሥት ይወክላል

ለወንድሞችህ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ይህን አድርጉ አህዮቻችሁን ጭናችሁ ወደ ከነዓን ምድር ሂዱ፤ አባታችሁንና ቤተሰባችሁን ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም እጅግ ለም ከሆነው የግብጽ ምድር እሰጣችኋለሁ፤ የምድርቱንም ስብ/በረከት ትበላላችሁ።
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: አት "አህዮቻቸውን እንዲጭኑና ወደ አባታቸውና ቤተሰቦቻውው ወደ ከነዓን እንዲሄዱ ለወንድሞችህ ንገራቸው፤ ወደዚህ እንዲመጡና እኔም እጅግ ለም ከሆነው የግብጽ ምድር እንደሚጣቸው፤ የምንሰጠውን በረከት እንደሚመገቡ ደግሞም ንገራቸው" (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅስ ይመልከቱ)

እኔም መልካም ከሆነው የግብጽ ምድር እሰጣችኋለሁ፤
እኔም እጅግ ለም የሆነውን የግብጽ ምድር እሰጣችኋለሁ

የምድርቱንም ስብ ትበላላችሁ
ምድርቱ የሚትሰጠው መልካም እህል እንደ ምድሪቱ ስብ ተደርጐ ተቆጥሮአል:: አት "የምድሪቱንም እህል ትመገባላችሁ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 45:19

አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ ለወንድሞቹ ምን መናገር እንዳለበት ፈርዖን መናገሩን ቀጠለ

አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ/ቁም ነገር ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል

እንዲህ ብለህ እዘዛቸው ይህን አድርጉ ከግብጽ ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን የምታጓጉዙበት ሠረገላዎች ውሰዱ አባታችሁንም ይዛችሁ ኑ ስለንብረታችሁ ምንም አታስቡ ከግብጽ ምድር እጅግ ለም የሆነው የእናንተ ነውና
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: አት "ደግሞም ከግብጽ ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን እናም አባታችሁንም ይዘው እንዲመጡ የሚያጓጉዙበትን ሠረገላዎች እንዲወስዱ ንገራቸው እኔም በግብጽ መልካም የሆነውን ስለሚሰጣቸው ንብረታችሁን ይዘው ለመምጣት ምንም አይጨነቁ (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅስ ይመልከቱ)

ታዝዛሃል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት “ደግሞም እንትነግራቸው አዝሃለሁ ወይም ደግሞም ንገራቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ሠረገላዎችን ይውሰዱ
ሠረገላዎች ሁለት ወይም አራት ጐማ ያላቸው የጭነት ሠረገላዎች ናቸው እንስሳት ተሳቢውን ይገትቱታል

Genesis 45:21

ለመንገድ ስንቅ ሰጣቸው
ለጉዞአቸው የሚያስፈልጋቸውን ሰጣቸው

ለሁሉም ሁለት ሁለት መለወጫ ልብስ ሰጣቸው
አምስት መለወጫ ልብስ ከተሰጠው ከብንያምን በስተቀር ሌሎች አያንዳንዳቸው ሁለት መለወጫ ልብስ ተቀብለዋል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ሶስት መቶ ጥሬ ብር
300 ጥሬ ብር (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

አሥር አህዮች ... አሥር እንስት አህዮች
አህዮቹ በሥጦታው ተካትተዋል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 45:24

አትጣሉ
ተገቢ ትርጉሞች የሚያጠቃልሉት 1) አትከራከሩ 2) አትኮራረፉ

ከግብጽ ወጥተው ወደ ላይ ወጡ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደላይ” የሚለው ቃለ መጠቀም የተለመደ ነው

በግብጽ ምድር ሁሉ ገዥ ሆኖአል
እዚህ “የግብጽ ምድር” የግብጽ ሰዎችን ይወክላል አት በግብጽ ሰዎች ሁሉ ላይ ገዥ ሆኖአል:: (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ልቡ ደነገጠ
እነርሱ የተናገሩትን እንደ እውነት መቀበል አቃተው

Genesis 45:27

ነገሩት
ለያዕቆብ ነገሩት

ዮሴፍ የነገራቸውን ነገር ሁሉ
ዮሴፍ የነገራቸውን ማንኛውንም ነገር

የአባታቸው የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ
እዚህ መንፈስ ሙሉ ሰው ይወክላል፡፡ አት “አባታቸው ያዕቆብ ከጭንቀቱ/ ከሐዘኑ ተሻለው” ወይም “አባታቸው ያዕቆብ እጅግ ደስተኛ ሆነ” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም የመልከቱ)

Chapter 46

1 እስራኤልም ጓዙን ሁሉ ጠቅልሎ ተነሣ፤ ቤርሳቤህም ሲደርስ፣ ለአባቱ ለይስሐቅ አምላክ መሥዋዕት ሠዋ። 2 እግዚአብሔርም ሌሊት በራእይ ለእስራኤል
ተገልጦ፣ “ያዕቆብ፣ ያዕቆብ” ብሎ ጠራው። እርሱም፣ “እነሆ፣ አለሁ” አለ። 3 እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ “እኔ የአባትህ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ፤ ወደ
ግብፅ ለመውረድ አትፍራ፤ በዚያ ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና፤ 4 አብሬህ ወደ ግብፅ እወርዳለሁ፣ ከዚያም መልሼ አወጣሃለሁ፣ የዮሴፍ የራሱ እጆች
በምትሞትበት ጊዜ ዓይኖችህን ይከድናል። 5 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሣ፤ የእስራኤል ወንዶች ልጆችም አባታቸውን ያዕቆብን ልጆቻቸውንና
ሚስቶቻቸውን ፈርዖን ለያዕቆብ በላከላቸው ሠረገላ ላይ አወጧቸው። 6 ከብቶቻቸውንና በከነዓን ምድር ያፈሩትን ሀብት ንብረታቸውን ይዘው፣ ያዕቆብና ዘሮቹ
በሙሉ ወደ ግብፅ ወረዱ። 7 ወደ ግብፅም የወረደው፤ ወንዶች ልጆቹንና ወንዶች የልጅ ልጆቹን፣ ሴቶች ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ማለት ዘሮቹን ሁሉ ይዞ ነው። 8
ወድ ግብፅ የወረዱት የእስራኤል ልጆች፣ የያዕቆብ ዘሮቹ እነዚህ ናቸው፦ የያዕቆብ የበኩል ልጅ ሮቤል። 9 የሮቤል ልጆች፦ ሄኖኅ፣ ፈሉሶ፣ አስሮን እና ከርሚ
ናቸው። 10 የስሞዖን ልጆች፦ ይሙኤል፣ ያሚን፣ ኦሃድ፣ ያኪን፣ ጸሐርና ከከነዓናዊቷ ሴት የተወለደው ሳኡል ናቸው። 11 ልጆች፦ ጌድሶን፣ ቀዓትና ሜራሪ ናቸው።
12 የይሁዳ ልጆች፦ ዔር አውናን፣ ሴሎም፣ ፋሬስ እና ዛራ ናቸው። ነገር ግን ዔርና አውናን በከነዓን ምድር ሞቱ። 13 የይሳኮር ልጆች፦ ቶላ፣ ፉዋ፣ ዮብና ሺምሮን
ናቸው፤ 14 የዛብሎን ልጆች፦ ሴሬድ፣ ኤሎንና ያሕልኤል ናቸው፤ 15 እነዚህ ወንዶች ልጆች ያዕቆብ በሰሜን ምዕራብ መሰጴጦምያ ሳለ፣ ልያ የወለደችለት
ናቸው። ሴቷን ዲናን ጨምሮ፣ የወንዶችና የሴቶች ልጆቹ ቁጥር ሠላሳ ሦስት ነው። 16 የጋድ ልጆች፦ ጽፎን፣ ሐጊ፣ ሹኒ፣ ኤስቦን፣ ዔሪ፣ አሮዲና አርኤሊ ናቸው፤
17 የአሴር ልጆች፦ ዩምና፣ የሱዋ፣ የሱዊና በሪዓ ናቸው፤ እኅታቸውም ሤራሕ ናት፤ የበሪዓ ልጆች፦ ሐቤርና መልኪኤል ናቸው፤ 18 እነዚህ ዐሥራ ስድስት ልጆች
ሁሉ ላባ ለልጁ ለልያ ከሰጣት ከዘለፋ ላይ ያዕቆብ የወለዳቸው ናቸው። 19 የያዕቆብ ሚስት የራሔል ልጆች፦ ዮሴፍና ብንያም ናቸው፤ 20 በግብፅም የኦን
ከተማ ካህን የጶጥፌራ ልጅ አስናት፣ ምናሴንና ኤፍሬምን ለዮሴፍ ወለደችለት። 21 የብንያም ልጆች፦ቤላ፣ ቤኬር፣ አስቤል፣ ጌራ፣ ንዕማን፥ አኪ፣ ሮስ፥
ማንፌን፣ ሑፊምና አርድ ናቸው። 22 እነዚህ ዐሥራ አራቱ፣ ራሔል ለያዕቆብ የወለደችለት ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው። 23 የዳን ልጅ፦ ሑሺም ነው፤ 24
የንፍታሌም ልጆች፦ ያሕጽኤል፣ ጉኒ፣ ዮጽርና ሺሌም ናቸው፤ 25 እነዚህ ሰባቱ ልጆች ሁሉ ላባ ለልጁ ለራሔል ከሰጣት ከባላ ላይ ያዕቆብ የወለዳቸው ናቸው።
26 ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የሄዱት የገዛ ዘሮቹ ብዛት ስድሳ ስድስት ሲሆን የልጆቹን ሚስቶች አይጨምርም። 27 ዮሴፍ በግብፅ የወለዳቸውን ሁለት ልጆች
ጨምሮ ወደ ግብፅ የወረደው የያዕቆብ ቤተ ሰብ ቁጥር ሰባ ነበር። 28 ያዕቆብም ወደ ጌሤም ለመሄድ መመሪያ ይቀበል ዘንድ፣ ይሁዳን አስቀድሞ ወደ ዮሴፍ
ላከው። እርሱም ጌሤም ሲደርሱ፣ 29 ዮሴፍ ሠረገላውን አዘጋጅቶ፤ አባቱን እስራኤልን ለመቀበል ወደ ጌሤም አመራ። ዮሴፍ አባቱ ዘንድ እንደደረሰ አንገቱ ላይ
ተጠምጥሞ ለረጅም ጊዜ አለቀሰ። 30 እስራኤልም ዮሴፍን፣ “በሕይወት መኖርህን ስላየሁ፣ ከእንግዲህ ብሞትም አይቆጨኝም” አለው። 31 ከዚህ በኋላ
ዮሴፍ ወንድሞቹንና የአባቱን ቤተ ሰዎች እንዲህ አላቸው፤ “ወደ ፈርዖን ወጥቼ እነግረዋለሁ፤ እንዲህም እለዋለሁ፣ ‘በከነዓን ምድር የሚኖሩት ወንድሞቼና የአባቴ
ቤተ ሰዎች ወደ እኔ መጥተዋል። 32 ሰዎቹ ከብት የሚጠብቁ ስለሆኑ እረኞች ናቸው፣ ሲመጡም በጎቻቸውን፣ ፍየሎቻቸውንና ከብቶቻቸውን እንዲሁም ያላቸውን
ሁሉ ይዘው መጥተዋል። 33 ፈርዖን አስጠርቶአችሁ፣ ‘ሥራችሁ ምንድን ነው?’ ብሎ ቢጠይቃችሁ፤ 34 እናንተ፣ ‘እኛ አገልጋዮችህ ሥራችን ከልጅነታችን ጀምሮ
ልክ እንደ አባቶቻችን ከብት ማርባት ነው’ ብላችሁ መልሱለት። ከብት አርቢዎች በግብፃውያን ዘንድ እንደ ጸያፍ ስለሚቆጠሩ፣ በጌሤም ምድር እንድትኖሩ
ይፈቅድላችኋል።”

Genesis 46:1

ወደ ቤርሳቤህ ሄደ

ወደ ቤርባህ መጣ

እነሆ አለው

“አዎን እየሰማሁ ነኝ”

ወደ ግብጽ ለመውረድ

ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ታች መውረድ” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው::

ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ

እዚህ አንተን የሚለው ነጠላ አገላለጽና ያዕቆብን የሚያመለክት ነው እዚህ ያዕቆብ ታላቅ የሚሆነውን የእርሱን ዘር ይወክላል አት ብዙ ትውልድ እሰጥሃለሁና እነርሱም ታላቅ ሕዝብ ይሆናሉ (አንተ የሚለውን ቃል አጠቃቀምና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደ ግብጽ ውስጥ

ወደ ግብጽ

ከዚያም ደግሞ እኔ አወጣሃለሁ

ተሰፋ የተሰጠው ለያዕቆብ ነው ነገር ግን ተስፋው የሚፈጸመው ለእስራኤል ትውልድ ሁሉ ነው አት በእርግጥ ዘርህን ከግብጽ ምድር አወጣለሁ (አንተ የሚለውን ቃል አጠቃቀምና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ደግሞም ወደ ላይ አወጣሃለሁ

ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው::

የዮሴፍ የራሱ እጆች ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል

የራሱ እጆች ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል የሚለው ሀረግ እስራኤል በሚሞትበት ጊዜ ዮሴፍ እንደሚገኝና በሞቱ ጊዜ የዮሴፍ እጆች የያዕቆብን የዐይን ሽፋሽፍቶች እንደሚዘጉ የሚናገርበት መንገድ ነው:: አት “ዮሴፍም ቢሆን በሞትህ ዕለት ይገኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል

አንድ ሰው ዐይኑን ከፍቶ በሚሞበት ጊዜ የዐይኑን ሽፋሽፍቶች መበሳብ መዝጋት የተለመደ ባህል ነበር:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 46:5

ተነሣ

ከዚያ ወጣ

በሠረገሎች

“ሠረገሎች” ሁለት ወይም አራት እግር ያላቸው የጭነት ሠረገሎች ናቸው እንስሳት ተሳቢውን ይጐትቱታል:: በዘፍትረት 45:19 ሠረገሎች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ያካበቱትን

“ያገኙትን” ወይም “ያፈሩትን”

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ከራሱ ጋር ይዞ አመጣቸው
ያዕቆብ ከራሱ ጋር ይዞአቸው መጣ

የልጆቹን ወንድ ልጆች
ወንድ የልጅ ልጆች

የልጆቹን ሴት ልጆች
ሴት የልጅ ልጆች

Genesis 46:8

ስማቸው ይህ ነበር
ይህ ጸሐፊው የሚዘረዝራቸውን የሰዎች ስሞች ያመለክታል።

የእስራኤል ልጆች
የእስራኤል ቤተሰብ አባላት ሄኖኀ ፌሉሶ አስሮንና ከርሚ…ይሙኤል ያሚን ኦሃድ ያኪን ጾሐርና ሳኡል …ጌድሶን ቀዓትና ሜራሪ፤ እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 46:12

ዔር አውናን ሴሎም
እነዚህ ይሁዳ ከሚስቱ ከሰዋ የወለዳቸው ወንዶች ልጆች ነበሩ:: በዘፍጥረት 38:3-5 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ፋሬስና ዛራ
እነዚህ ይሁዳ ከምራቱ ከታማር የወለዳቸው ወንዶች ልጆች ነበሩ:: በዘፍጥረት 38:29-30 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ኤስሮም ሐሙል … ቶላ ፋዋ ዮብ … ሺምሮን… ሴሬድ ኤሎን… ያሕልኤል
እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዲና
ይህ የልያ ሴት ልጅ ስም ነው በዘፍጥረት 30:21 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የወንዶችና የሴቶች ልጆች ቁጥር ሠላሣ ሶስት ነበር
እዚህ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች የያዕቆብ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እና የልያ የልጅ ልጆች ያመለክታል አት በአንድነት 33 ወንዶችና ሴቶች ልጆችና የልጅ ልጆች ነበረው (ቁጥሮች ይመልከቱ)

Genesis 46:16

ጽፎን… ሐጊ ሹኒ… ኤስቦን ዔሪ አሮዲና… አርኤሊ…ዩምና …የሱዋ የሱዊና… በሪዓ … ሐቤር… መልኪኤል
እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሤራሕ
ይህ የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ለያዕቆብ የወለደቻቸው እነዚህ ወንዶች ልጆች በአንድነት አሥራ ስድስት ናቸው
ይህ ከዘለፋ የተወለዱ አሥራ ስድስት ልጆች የልጅ ልጆችና የልጁ ልጅ ልጆች ናቸው (ቁጥሮች ይመልከቱ)

Genesis 46:19

አስናት
የሴት ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ጶጥፌራ
የወንድ ስው ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የኦን ካህን
ኦን የጸሐይ አምላክ ረሐ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና የጸሐይ ከተማ ደግሞም ሄልዮቱ የተባለች ከተማ ነች:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቤላ ቤኬር አስቤል ጌራ ናዕማን አኪ ሮስ ማንፌን ሑፊምና አርድ
እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በአጠቀለይ አሥራ አራት ናቸው
ራሔል የወለደቻቸው 14 ወንዶችና የልጅ ልጆች ናቸው

Genesis 46:23

ሑሺም ያሕጽኤል ጉኒ ዬጽርና ሺሌም
እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ወይም አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በአጠቃላይ ሰባት ነበሩ
ይህ ባላ የወለደቻቸው 7 ልጆችና የልጅ ልጆች እንደሆኑ ያመለክታል (ቁጥሮች ይመልከቱ)

Genesis 46:26

ስድሳ ስድስት
66 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሰባ
70 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Genesis 46:28

በፊቱ የጌሤምን መንገድ እንዲያሳየው
የጌሜምን መንገድ እንዲያሳያቸው

ዮሴፍ ሰረገላውን አዘጋጀና … ወጣ
እዚህ “ዮሴፍ” አገልጋዮቹን ወይም ባሪያዎቹን ይወክላል:: አት “የዮሴፍ አገልጋዮች ሠረገላውን አዘጋጁለትና ዮሴፍም ….ወጣ” (ምትክ ቃላት ይጠቀሙ)

እስራኤልን ሊገናኘው …..ወጣ
“ወደ ላይ ወጣ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው ዮሴፍ አባቱን ሊገናኘው ወደ ከፍታማ ሥፍራ ስለተጓዘ ነው:: አት “እስራኤልን ሊገናኘው ሄዴ”

አንገቱን አቀፈና ረጅም ጊዜ አለቀሰ
አንገቱ ላይ ተጠመጠመና ረጅም ጊዜ አለቀሰ

አሁን ቢሞት እይቆጨኝ
“አሁን ለሞት ተዘጋጅቻለሁ” ወይም “አሁን እንግዲ የሚሞተው በደስታ ነው”

አንተ ገና በሕይወት ሳለህ ፊትህን አይቻለሁና

እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰው ይወክላል”” ያዕቆብ ዮሴፍን በማየቱ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል:: አት “አንተን እንደገና በሕይወት ስላየሁህ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 46:31

የአባቱን ቤት

እዚህ ቤት ቤተሰቡን ይወክላል:: አት “የአባቱን ቤተሰብ” ወይም “የአባቱን ቤተሰዎች” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ወደ ፈርዖን ወጥቼ እናገረዋለሁ

ወደ አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ሄዶ መናገር ወደ ላይ ወጣ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር አት ለፈርዖን ለመናገር እሄዳለሁ

ለፈርዖን እነግረዋለሁ: ወንድሞቼ ... ያላቸውን ሁሉ

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወንድሞቼ …ያላቸውን ሁሉ… ለፈርዖን እነግረዋለሁ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

Genesis 46:33

እንዲህም ሆነ

ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ ስለተከሰተው ዋና ክስተት ለማመልከት ነው። በቋንቋዎ ይህንን የሚገልጹበት መንገድ ካለ የጠቀሙ

ሥራችሁ ምንደነው ብሎ ቢጠይቃችሁ

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል:: ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ምን ሥራ ታከናውናላችሁ ብሎ ቢጠይቃችሁ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እንዲህ በሉት እኛ ባሪያዎችህ.... እኛም አባቶቻችንም...

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል:: ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እንዲህ በሉት….እኛና አባቶቻችን ሁላችን…” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

የአንተ ባሪያዎች

የዮሴፍ ቤተሰቦች ለፈርዖን ሲናገሩ ራሳቸውን ባሪያዎችህ ብለው ማቅረብ አለባቸው:: ይህ ለአንድ ታላቅ ባለሥልጣን የሚነገርለት መንገድ ነው:: ይህም እንደ አንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በግ ጠባቂ ሁሉ ለግብጻዊያን ርኩስ/ ጸያፍ ነውና

“ጸያፍ” የሚለው ረቂቅ ስም “የሚያስጠላ” በሚለው ቅጽል ስም ሊተረጐም ይችላል:: አት “ግብጻዊያን የከብት ጠባቂዎችን እንደ ጸያፍ ይቆጥሩ ነበር” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Chapter 47

1 ዮሴፍም ወደ ፈርዖን ሄዶ፣ “አባቴና ወንድሞቼ በጎቻቸውን፣ ፍየሎቻቸውን እንዲሁም ያላቸውን ሁሉ ይዘው ከከነዓን አገር መጥተው በጌሤም ሰፍረዋል”
አለው። 2 ከወንድሞቹም መካከል አምስቱን መርጦ፣ ፈርዖን ፊት አቀረባቸው። 3 ፈርዖን የዮሴፍን ወንድሞች፣ “ሥራችሁን ምንድነው?” ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም ፈርዖንን፣ “እኛ አገልጋዮችህ ልክ እንደአባቶቻችን ከብት አርቢዎች ነን” አሉት። 4 ደግሞም፣ “በከነዓን ምድር ራቡ እጅግ የጸና በመሆኑ በጎችና ፍየሎች
የሚሰማሩበት በማጣታቸው፣ ለጊዜው እዚህ ለመኖር መጥተናል፤ አሁንም ባሮችህ በጌሤም ምድር እንድንኖር እንድትፈቅድልን እንለምንሃለን” አሉት። 5
ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “አባትንህና ወንድሞችህ ወደ አንተ መጥተዋል፤ 6 የግብፅ ምድር እንደሆነ በእጅህ ነው፤ አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ
በሆነው ምድር አስፍራቸው፤ በጌሤም ይኑሩ። ከመካከላቸው ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታውቅ ከሆነ፣ የከብቶቼ ኀላፊዎች አድርጋቸው።” 7 ከዚህ
በኋላ ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ቤተ መንግሥት አግብቶ በፈርዖን ፊት አቀረበው፤ ያዕቆብ ፈርዖንን ከመረቀው በኋላ 8 ፈርዖን፣ “ለመሆኑ ዕድሜህ ምን ያህል
ነው?” ሲል ያዕቆብን ጠየቀው። 9 ያዕቆብም ለፈርዖን፣ “በምድር ላይ በእንግድነት ያሳለፍሁት ዘመን 130 ዓመት ነው፤ ይህም አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት
ዘመን ጋር ሲነጻጸር አጭር ነው፤ ችግር የበዛበትም ነበር” ሲል መለሰለት። 10 ከዚያም ያዕቆብ ፈርዖንን መርቆ፣ ተሰናብቶት ወጣ። 11 ዮሴፍም አባቱንና
ወንድሞቹን በግብፅ እንዲኖሩ አደረገ፤ ፈርዖን በሰጠውም ትእዛዝ መሠረት ምርጥ ከሆነው ምድር ራምሴን በርስትነት ሰጣቸው። 12 ዮሴፍም ለአባቱ፣
ለወንድሞቹና ለመላው የአባቱ ቤተ ሰዎች በልጆቻቸው ቁጥር ልክ ቀለብ እንዲሰፈርላቸው አደረገ። 13 በመላው ምድር እህል ባለመኖሩ ራቡ እየጸና ሄደ፤ ከዚህ
የተነሣም ግብፅና ከነዓን በራብ እጅግ ተጐዱ፤ 14 ዮሴፍ የግብፅና የከነዓን ሰዎች እህል በመሸመት የከፈሉትን ገንዘብ ሁሉ ሰብስቦ ወደ ፈርዖን ቤተ መንግሥት
አስገባ። 15 የግብፅና የከነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ፣ ግብፃውያን ሁሉ ወደ ዮሴፍ ቀርበው፣ “የምንበላው እህል ስጠን፣ ገንዘባችን አልቆብናል፤
ዓይንህ እያየ እንዴት በራብ እንለቅ?” አሉት። 16 ዮሴፍም ከብቶቻችሁን አምጡ፣ ገንዘባችሁ ካለቀ በከብቶቻችህ ለውጥ እህል እሰጣችኋለሁ አለ። 17
ስለዚህ ከብቶቻቸውን ወደ ዮሴፍ አምጡ፤ እርሱም በፈረሶቻቸው፣ በበጎቻቸው፣ በፍየሎቻቸው፣ በከብቶቻቸውና በአህዮቻቸው ለውጥ እህል ሰጣቸው።
በከብቶቻቸው ልዋጭ ባገኙት ምግብ በዚያ ዓመት ሳይራቡ እንዲያልፉ አደረጋቸው። 18 ያም ዓመት ካለፈ በኋላ ሕዝቡ በሚቀጥለው ዓመት ወደ ዮሴፍ
መጥተው እንዲህ አሉት፣ “እንግዲህ ከጌታችን የምንሰውረው ምንም ነገር የለም፤ ገንዘባችን አልቆአል፤ ከብቶቻችንንም አስረክበንሃል፤ እንግዲህ ለጌታችን
የምንሰጠው፣ ከሰውነታችንና ከመሬታችን በቀር ሌላ ምንም ነገር የለንም። 19 ታዲያ እያየኸን እንዴት እንለቅ? መሬታችንም ለምን ጠፍ ሆኖ ይቅር? እኛንና
መሬታችንን ውሰድና በለውጡ እህል ስጠን፤ እኛ የፈርዓን አገልጋዮች እንሆናለን፤ መሬታችንም የእርሱ ይሁን፣ እኛም እንዳንሞት መሬታችንም ጠፍ ሆኖ
እንዳይቀር የምንዘራው ዘር ስጠን። 20 ስለዚህ ዮሴፍ የግብፅን ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛለት፤ ራቡም እጅግ ስለጸናባቸው ግብፃውያን ሁሉ መሬታቸውን ሸጡ፣
ምድሪቱም የፈርዖን ርስት ሆነች። 21 ዮሴፍ በግብፅ አገር ዳር እስከ ዳር ያሉት ሰዎች ሁሉ የንጉሡ አገልጋዮች እንዲሆኑ አደረገ። 22 ሆኖም ዮሴፍ የካህናቱን
መሬት አልገዛም፤ ምክንያቱም ካህናቱ ከፈርዖን ቋሚ አበል ስለሚያገኙ እርሱም ከሚሰጣቸው አበል ምግብ ያገኙ ስለነበረ መሬታቸውን አልሸጡም። 23 ዮሴፍ
ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፣ “እነሆ፣ ዛሬ እናንተንም መሬታችሁንም ለፈርዖን ገዝቻችኋለሁና ይህን ዘር ወስዳችሁ በመሬት ላይ ዝሩ። 24 መከሩ በሚሰበሰብበት
ጊዜ ግን ከአምስት እጅ አንዱን ለፈርዖን ታስገባላችሁ፣ ከአምስት እጅ አራቱን ደግሞ ለመሬታችሁ ዘር፣ እንዲሁም ለራሳችሁ፣ ለቤተ ሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ
ምግብ ታደርጉታላችሁ።” 25 እነርሱም፣ “እንግዲህ ሕይወታችንን አትርፈህልናል፤ በጌታችን ፊት ሞገስ ካገኘን ለፈርዖን ገባሮች እንሆናለን” አሉት። 26 ስለዚህ
ዮሴፍ የምርቱ አንድ አምስተኛ ለፈርዖን እንዲገባ የሚያዝ የመሬት ሕግ አወጣ፤ ይህም ሕግ እስከ ዛሬ ይሠራበታል። በፈርዖን እጅ ያልገባው መሬት የካህናቱ ብቻ
ነው። 27 በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በግብፅ አገር በጌሤም ይኖሩ ነበር፣ በዚያም ሀብት ንብረት አፈሩ፤ ቁጥራቸውም እጅግ እየበዛ ይሄድ ጀመር። 28 ያዕቆብ
በግብፅ ዐሥራ ሰባት ዓመት ኖረ፣ ዕድሜውም አንድ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ነበር። 29 እስራኤልም የሚሞትበት ጊዜ መቃረቡን እንደተረዳ ልጁን ዮሴፍን
አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ “በአንተ ዘንድ ሞገስ ካገኘሁ እጅህን በጭኔ ላይ አኑረህ፣ በጎነትንና ታማኝነትን ልታደርግልኝ ቃል ግባልኝ፤ በምሞትበት ጊዜ በግብፅ
አትቅበረኝ፤ 30 እኔም ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ ከግብፅ አውጥተህ እነርሱ በተቀበሩበት ቦት ቅበረኝ” ዮሴፍም፣ “እሺ፣ እንዳልኸኝ አደርጋለሁ” አለ። 31 ያዕቆብ፤
“በል ማልልኝ” አለው። ዮሴፍም ማለለት፣ እስራኤልም በአልጋው ራስጌ ላይ ሆኖ ጎንበስ አለ።

Genesis 47:1

ዮሴፍ ሄዶ ለፈርዖን ነገረው ....ከወንድምቹም አምስት ሰዎችን ወስዶ በፈርዖን ፊት አቀረባቸው

UDB ክስተቶች በቅደም ተከተል ሲያስቀምጥ ULB ጸሐፊው እንዳስቀመጠ ይዘረዝራል (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

Genesis 47:3

እኛ ባሪያዎችህ የበግ አርቢዎች ነን

ባሪያዎችህ በጎችን እናረባለን

ባሪያዎችህ

የዮሴፍ ወንድምች ራሳቸውን እንደ “ባሪያዎችህ” ያቀርቡታል:: ይህ ብዙ ኃላፊነት ላለው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህም እንደ አንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኛ ባሪያዎችህ ወይም እኛ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እንደ አባቶቻችን

“እኛና ቅድመ አባቶቻችን ሁላችን” ወይም “እኛና አባቶቻችን ሁሉ”

በዚህ ምድር ለጊዜው ለመኖር መጥተናል

በግብጽ ለጊዜው ለመኖር መጥተናል

በጎች የሚሠማሩበት ሥፍራ የለምና

በጎች የሚሠሩበት ሣር የለምና

አሁንም

ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነገር ትኩረት ለመስጠት ነው::

Genesis 47:5

የግብጽ ምድር በፊትህ ናት

“የግብጽ ምድር ለአንተ ክፍት ነው” ወይም “መላው የግብጽ ምድር በአንተ እጅ ነው”

በመልካም ምድር አባትህንና ወንድሞችህን አኑራቸው በጌሤም ምድር

አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ በሆነው በጌሤም ምድር አኑራቸው

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ከመካከላቸው ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታውቅ ከሆነ
ይህ የሚገለጸው ከብት የማርባት ችሎታ እንዳላቸው ነው:: አት "ከመካከላቸው ከብት በማርባት ትልቅ ችሎታ ያላቸውን የሚቃውቅ ከሆነ" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 47:7

ያዕቆብ ፈርዖንን ባረከው
እዚህ "ባረከው" የሚለው ለዚያ ሰው አዎንታዊና ጠቃሚ ነገሮች እንዲሆኑለት መሻቱን ገለጸ ማለት ነው

እድሜህ ምን ያህል ነው?
እድሜህ ስንት ዓመት ነው?

የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሣ ዓመት ነው
የእንግድነቴ ዘመን የሚለው ሀረግ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር በምድር ላይ ምን ያህል እንደኖረ ያመለክታል:: አት "በምድር ላይ በእንግድነት ያሳለፍኩት ዘመን 130 ዓመት ነው" (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የሕይወቴ ዘመኖች አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር ጥቂት ናቸው
ከአብርሃምና ከይስሐቅ የሕይወት ዘመን ጋር ስነጻጸር ዮሴፍ የሕይወቱ ዘመን አጭር እንደሆነ ይናገራል

ችግር የበዛበት
ያዕቆብ በሕይወቱ ብዙ ሥቃይና ችግር ተለማምዶአል

Genesis 47:11

ዮሴፍም አባቱንና ወንደሞቹን አኖረ
ከዚያም ዮሴፍ አባቱንና ወንድሙን ተንከባከባቸው በሚኖሩበት ሥፍራ እንዲመሠረቱ አደረገ

ራሚሴ ምድር
ይህ የጐሼም ምድር ሌላው ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በየልጆቻቸው ቁጥር
እዚህ "ልጆች" በቤተሰብ ጥገኝነት ያሉ ትናንሽ ልጆች ማለት ነው:: አት "በየቤተሰቡ በሚገኙ ትናንሽ ልጆች ቁጥር"

Genesis 47:13

አሁንም
ይህ ቃል ዋናው ታሪክ በመሃል የሚቋረጥበትን ለማመልከት ተጠቅሞአል:: በዚህ ጸሐፊው የታሪኩን አድስ ክፍለ መናገር ይጀምራል::

የግብጽ ምድርና የከነዓን ምድር
ይህ በእነዚህ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል አት የግብጽ ሰዎችና የከነዓን ሰዎች (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ተጐዳ
ተቀጨ ወይም ደከመ

ዮሴፍም በግብጽ ምድርና በከነዓን ምድር በእህል ሽመት የተገኘውን ገንዘብ ሰበሰበ
ዮሴፍም የግብጽና የከነዓን ሰዎች ገንዘባቸውን ሁሉ ከዮሴፍ እህል ለመሸመት አውለዋል

ዮሴፍም ሰበሰበ... ዮሴፍም አመጣ
ገንዘቡን እንዲሰበስቡና እንዲያመጡ ዮሴፍ አገልጋዮቹን እንዳዘዘ ይገመታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

Genesis 47:15

የግብጽና የከነዓን ምድር ገንዘብ ባለቀ ጊዜ
እዚህ ምድር በዚያ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት "የግብጽና የከነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ" (ምትክ ቃላት አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

የግብጽና የከነዓን ምድሮች
ከግብጽ ምድር እና ከከነዓን ምድር

ብሩ አልቆብናልና በፊትህ ስለምን እንሞታለን?
ሰዎች እህል ለመሸመት እንዴት እንደጓጉ ትኩረት ለመሰጠት ጥቃቄ ይጠቀማሉ። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል፡ አት "ገንዘባችን ስላለቀብን እባካችሁ እንድንሞት አታድርጉ!" (ሽንገላ አዘል አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እህልን መገባቸው
እህል ምግብን በአጠቃላይ ይወክላል:: አት "እህልን ሰጣቸው" ወይም "እህልን አደላቸው" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 47:18

እነርሱም ወደ እርሱ መጡ
ሰዎች ወደ ዮሴፍ መጡ

እኛ ከጌታችን አንሰውርም
ሰዎችን ዮሴፍን እንደ" ጌታችን" ያመለክታሉ ይህ ትልቅ ሥልጣን ላሌው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ እንደ ሁለተኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት" ከጌታችን የምንሰውረው የለም" ወይም "ከአንተ የምንሰውረው የለም" (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

በጌታችን ፊት አንዳች የቀረ የለም
እዚህ ፊት ዮሴፍን ያመለክታል:: አት "ለጌታችን የምንሰጠው የቀረ የለንም" (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እኛ በዐይኖችህ ፊት ስለምን እንሞታለን? ምድራችንስ ስለምን ትጠፋለች?
እዚህ ዐይኖች የዮሴፍን እይታ ያመለክታሉ ሰዎች እህልን ለመግዛት ምንኛ እንደጓጉ ለማተኮር ጥያቄ ይጠቀማሉ ይህ ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት "እኛ ስንሞት ምድራችም ስትጐዳ እባክህን እንዲሁ ዝም ብለህ አትመለከተን" (ምትክ ቃላት አጠቃቀምና ሽንገላ አዘል አግናኝ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ)

እኛ ለምን እንሞታለን እኛና ምድራችን
የተዘራበት ዘር ስለሌለባት ምድሪቱ የተጐዳችና ጥቅም የሌላት መሆንዋ ምድሪቱ እንደሚትሞት ተደርጐ ተነግሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 47:20

በዚህ መንገድ የግብጽ ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛለት
ስለዚህ ምድሪቱ የፈርዖን ሆነች

ዮሴፍ ያልገዛው የካህናቱን መሬት ብቻ ነበር
ነገር ግን የካህናቱን መሬት አልገዛም

ካህናቱ ድርጐ ያገኙ ነበር
ድርጐ በቋሚነት አንድ ሰው ለሌላ ሰው የሚሰጠው የገንዘብ ወይም የመግብ መጠን ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "ፈርዖን

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

በየዕለቱ ለካህናት የተወሰነ ምግብ ይሰጥ ነበር" (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እነርሱም ፈርዖን ከመደበላቸው ይመገቡ ነበር
ፈርዖን ከሰጣቸው ይመገቡ ነበር

Genesis 47:23

በመሬት ላይ ዝሩ
ሊትዘሩ ትችላላችሁ

በመከርም ጊዜ ፍሬውን ከአምስቱ እጅ አንዱን እጅ ለፈርዖን ስጡ አራቱም እጅ ለእናንተ ለራሳችሁ ይሆናል
አምስት እጅ የሚለው ቃል ክፍልፋይ ነው። እት "በመከር ጊዜ እህላችሁን በአምስት መደብ ትከፍላላችሁ አንዱን መደብ እንደክፍያ ለፈርዖን ትሰጡታላችሁ እናም አራቱ መደቦች ለእናንተ ይሆናሉ" (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ) ለቤተሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ምግብ ታደርጉታላችሁ (የተደበቁትን ስለመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 47:25

በዐይኖችህ ፊት ሞገስ ካገኘን
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማግኘት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ደግሞም ዐይኖች ማየትንና ማየት ሃሳብንና በየናን ይወክላል:: አት "በእኛ ከተደሰትክ" (ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር
"በግብጸ ምድር ላይ" ወይም "በመላው የግብጽ ምድር"

እስክ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ

አንድ አምስተኛ
በዘፍጥረት 47:24 አንድ እምስተኛ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

Genesis 47:27

ንብረትንም አፈሩ እጅግም በዙ
በዙ የሚለው ቃል እንዴት እንደአፈሩ ይገልጻል እነርሱም ብዙ ልጆች ነበሩአቸው (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)

ፍሬያማ ነበሩ
እዚህ ፍሬያማ መበልጸግ ወይም ብዙ ልጆች መኖር ማለት ነው

አሥራ ሰባት ዓመታት
17 ዓመታት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የያዕቆብም የሕይወቱ ዘመን አንድ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ነበር
ያዕቆብ የኖረው 147 ዓመት ነው (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Genesis 47:29

እስራኤልም የሚሞትበት ጊዜ መቃረቡን
ይህ ጊዜ እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚመጣ ይናገራል:: አት "እስራኤል የሚሞትበት ጊዜ እንደደረሰ" (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)

በዓይኖችህ ፊተ ሞገስን ካገኘሁ
እዚህ ዓይኖች የማየት ምትክ ቃል ነው እናም ማየት ሃሳብን ወይም አመለካከትን ይወክላል:: አት "በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ ወይም ካስደሰትኩህ" (ምትክ ቃላትና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

ሞገስ ማግኘት
አንድ ሰው በአንድ ሰው ተቀባይነቱን ማረጋገጥ ማለት ነው ፈሊጣሊ አነጋገር ይመልከቱ

እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ
ለጠንቃቃ ቃል መግባት የሚደረግ ምልክት ነው በዘፍጥረት 24:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በጐነትንና ታማኝነትን ሊታደርግልኝ
በጐነት እና ታማኝነት የተባሉ ረቂቅ ስሞች እንደ ቅጽል ስሞች ሊተረጐሙ ይችላሉ አት በበጐነትና በታማኝነት አድርግልኝ ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ

እባክህን በግብጽ አትቅበረኝ
እባክህን የሚለው ለዚህ ጥያቄ እጽንዖት ይሰጣል

ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ
ማንቀላፋት መሞትን ለዘብ ባለ ቃል የሚገልጽ ነውፀፀ አት "በሚሞትበትና ከዚህ ቀደም የሞቱ ቤተሰቦቼን በሚገናኝበት ጊዜ" (ንኀብነት ወይም ለዘብ ባለና በተዘዋዋሪ መንገድ አንድን ነገር የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ቃል ግባልኝ
"ተስፋ ስጠኝ" ወይም "ማልልኝ"

ማለለት
"ተስፋ ሰጠው" ወይም "ቃል ገባለት"

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 48

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላም፣ “አባትህ ታሞአል” ተብሎ ለዮሴፍ ስለተነገረው ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን ይዞ ሄደ። 2 ለያዕቆብ፣ “ልጅህ ዮሴፍ ወደ አንተ
መጥቶአል” ተብሎ በተነገረው ጊዜ፣ እስራኤል ተበረታትቶ አልጋው ላይ ተቀመጠ። 3 ያዕቆብም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “ሁሉን የሚችል አምላክ በከነዓን
ምድር ሎዛ በምትባል ቦታ ተገለጠልኝ፤ ባረከኝም፤ 4 እንዲህም አለኝ፤ ‘ፍሬያማ አደርግሃለሁ፣ ዘርያዎችህም ብዙ ሕዝቦች ይሆናሉ፣ ይህችንም ምድር
ለዝርያዎችህ ለዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣቸዋለሁ’ አለኝ።” 5 ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት በግብፅ የወለድሃቸው ሁለቱ ልጆችህ ከእንግዲህ የእኔ ልጆች ሆነው
ይቆጠራሉ፤ ሮቤልና ስምዖን ልጆቼ እንደሆኑ ሁሉ፣ ኤፍሬምና ምናሴም ልጆቼ ይሆናሉ። 6 ከእነርሱ በኋላ የሚወለዱልህ ልጆች ግን፣ የአንተ ይሁኑ፤ በርስት
ድልድላችው ግን በወንድሞቻቸው ስም ይቆጠራሉ። 7 ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ስመለስ ኤፍራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ፤ እናትህ ራሔል በከነዓን
ምድር ሞታብኝ አዘንሁ። እኔም ወደ ኤፍራታ ማለት ወደ ቤተ ልሔም በሚወስደው መንገድ ዳር ቀበርኋት።” 8 እስራኤልም የዮሴፍን ልጆች ባየ ጊዜ፣ “እነዚህ
እነማን ናቸው?” ሲል ጠየቀ፤ 9 ዮሴፍም፣ “እነዚህ እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች ናቸው” ብሎ መለሰለት፤ እስራኤልም “አቅርባቸውና ልመርቃቸው” አለ። 10
በዚህ ጊዜ እስራኤል ዓይኖቹ በእርጅና ምክንያት በመድከማቸው አጥርቶ ማየት ይሳነው ነበር፤ ስለዚህ ዮሴፍ ልጆቹን አባቱ ዘንድ አቀረባቸው፤ አባቱም ስሞ
አቀፋቸው። 11 እስራኤልም ዮሴፍን፣ “ዓይንህን እንደገና ዐያለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ልጆችህን ጭምር ለማየት አበቃኝ” አለው። 12
ዮሴፍም ልጆቹን ከእስራኤል ጉልበት ፈቀቅ በማድረግ አጎንብሶ በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ። 13 ከዚያም ዮሴፍ ሁለቱን ልጆቹን ይዞ ኤፍሬምን ከራሱ በስተቀኝ
ከእስራኤል በስተግራ፣ ምናሴን ደግሞ ከራሱ በስተግራ ከእስራኤል በስተቀኝ በኩል አቀረባቸው። 14 እስራኤል ግን ቀኝ እጁን በታናሹ በኤፍሬም ራስ ላይ
አኖረ፣ ግራ እጁንም በቀኝ እጁ ላይ አስተላልፎ በበኩሩ በምናሴ ላይ አኖረ። 15 ከዚህ በኋላ ዮሴፍን ባረከ፤ እንዲህም አለው፤ “አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ
መንገዱን በመከተል ያገለገሉትና ለእኔም እስከ ዛሬ ድረስ በዘመኔ ሁሉ እረኛ የሆነኝ አምላክ፣ 16 ከጉዳትም ሁሉ የታደገኝ ምልአክ፣ እርሱ እነዚህን ልጆች
ይባርክ፤ እነርሱም በስሜ፣ በአባቶቼ በአብርሃምና በይስሐቅ ስም ይጠሩ፣ በምድር ላይ እጅግ ይብዙ። 17 ዮሴፍ አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ማድረጉን
ሲያይ ቅር ተሰኘ፤ ከኤፍሬም ራስ ላይ አንስቶ በምናሴ ራስ ላይ ለማኖር የአባቱን እጅ ያዘ፤ 18 ዮሴፍም፣ “አባቴ ሆይ፣ እንዲህ አይደለም በኩሩ ይህኛው ስለሆነ፣
ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድርግ” አለው። 19 አባቱ ግን፣ “ዐውቃለሁ፣ ልጄ ዐውቃለሁ፣ እርሱም እኮ ሕዝብ ይሆናል፤ ታላቅም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ ታናሽ
ወንድሙ ከእርሱ ይበልጣል፤ ዘሮቹም ታላቅ ሕዝቦች ይሆናሉ” ብሎ እምቢ አለው። 20 በዚያን ዕለት ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው፤ “እስራኤላውያን
በሚመርቁበት ጊዜ የእናንተን ስም በማስታወስ፤ ‘እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደ ምናሴ ያድርጋችሁ’ ይላሉ” በዚህ ሁኔታም ኤፍሬምን ከምናሴ
አስቀደመው። 21 ከዚህ በኋላ እስራኤል ዮሴፍን እንዲህ አለው፣ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ ወደ
አባቶቻችሁም ምድር መልሶ ያገባችኋል። 22 እነሆ በሰይፌና በቀስቴ ከአሞራውያን እጅ የወሰድኋትን ምድር ከወንድሞችህ ድርሻ አብልጬ ለአንተ
ሰጥቼሃለሁ።”

Genesis 48:1

እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከቱ ተጠቅሞአል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

አንድ ሰው ለዮሴፍ ተናገረው
አደ ሰው ለዮሴፍ ነገረው

እየው፤ አባትህ
ስማ ፤አባትህ፤ እዚህ “እየው” የሚለው ቃል የዮሴፍን ትኩረት ለማግኘት ተጠቅሞአል::

ስለዚህ ይዞ
ስለዚህ ዮሴፍ ይዞ

ለያዕቆብ ... በተነገረው ጊዜ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት “አንድ ሰው ለያዕቆብ በነገረው ጊዜ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ልጅህ ዮሴፍ ልያይህ ወደ አንተ መጥቶአል
ልጅህ ዮሴፍ መጥቶአል

እስራኤል ተበረታትቶ በአልጋው ላይ ተቀመጠ
እዚህ እስራኤል ተነሥቶ በአልጋው ሊቀመጥ የታገለውን አንድ ሰው አንድን ዕቃ እንደሚሰበስብ ብርታትን እንደሰበሰበ አድርጎ ጸሐፊው ይናገራል:: አት “በአልጋው ተነሥቶ ሊቀመጥ እስራኤል ከፍተኛ ጥረት አድርጎአል ወይም በአልጋው ተነሥቶ ሊቀመጥ እስራኤል ታግሎአል” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይጠቀሙ)

Genesis 48:3

ሎዛ
ይህ የከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 28:19 የዚህን ከተማ ስም እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጎም ይመልከቱ)

በከነዓን ምድር ... ባረከኝም እንዲህም አለኝ
ይህ በሌላ ሀረግ እንደሚጀምር እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል:: “በከነዓን ምድር ባረከኝ እናም እንዲህ አለኝ”

ባረከኝ
እግዚአብሔር መደበኛ በረከትን በአንድ ሰው ላይ እንዳደረገ ያመለክታል

እንዲህም አለኝ እነሆ ፍሬያማ አደርግሃለሁ አበዛሃለሁ ለብዙ ሕዝብም ጉባዔ አደርግሃለሁ ይህችንም ምድር ከአንተ በኋላ ለዘላለም ርስት ለዘርህ እሰጣታለሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል አት ፍሬያማ እንደሚያደርገኝና እንደሚያበዛኝ ተናግሮኛል:: እናም ለብዙ ሕዝብም ጉባዔ እንደሚያደርገኝና ይህችንም ምድር ከእኔ በኋላ ለዘላለም ርስት አድርጎ ለዘሬ እንደሚሰጠኝ ነግሮኛል (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እነሆ
እዚህ ቦታ እነሆ የተጠቀመው እግዚአብሔር ሊናገር ስላለው ነገር ያዕቆብ ትኩረት እንዲሰጥ ለማንቃት ነው

ፍሬያማ አደርግሃለሁ አበዛሃለሁ
አበዛሃለሁ የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር እንዴት ያዕቆብን ፍሬያማ እንደሚያደርገው ይገልጻል:: አት “ብዙ ዘር/ትውልድ እሰጥሃለሁ” (ድርብ ቃላትና ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

አንተን ለብዙ ሕዝብ ጉባዔ አደርግሃለሁ
እዚህ አንተ ያዕቆብን ቢያመለክትም የያዕቆብን ትውልድ ይወክላል አት “ትውልድህን ብዙ ሕዝቦች አደርጋለሁ” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

የዘላለም ርስት
ቋሚ ርስት

Genesis 48:5

አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል

ኤፍሬምና ሚናሴ ለእኔ ናቸው
እንደ ዮሴፍ ወንድሞች ኤፍሬምና ሚናሴ ከምድሪቱ ክፍል የየራሳቸውን ርስት ይቀበላሉ

በርስታቸው በወንድሞቻቸው ስም ይጠራሉ
ተገቢ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው 1 እንደ ሚናሴና ኤፍሬም ነገዶች ሌሎች የዮሴፍ ልጆች ምድሪቱን ይወርሳሉ 2 ዮሴፍ ከኤፍሬምና ሚናሴ የተለየ ምድር የሰጠዋል እናም የዮሴፍ ሌሎች ልጆች ያን ምድር ይወርሳሉ አት በርስት ድልደላቸው በወንድሞቻቸው ስም ይቆጠራሉ

ኤፍራታ
ይህ የቤተልሔም ከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 35:16 የዚህን ከተማ ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

ያም ቤተልሔም ነው
ጸሐፊው የዳራ መረጃ ይሰጣል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 48:8

እነዚህ እነማን ናቸው?
እነዚህ የማን ወንዶች ልጆች ናቸው?

ባረካቸው
አባት ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን እብዛኛውን ጊዜ መደበኛ በረከት ይባርካል

በዚህን ጊዜ የእስራኤል ዐይኖች .... ማየት ተስኖአቸው
በዚህን ጊዜ የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩ ወደ እስራኤል ዳራ መረጃ እንደተቀየረ ለማመልከት ነው (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

እርሱም ሳማቸው
እስራኤል ሳማቸው

Genesis 48:11

ፊትህን እንደገና አያለሁ
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰው ይወክላል:: አት እንደገና አይሃለሁ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

በእስራኤል ጉልበቶች መካከል
ዮሴፍ ልጆቹን በእስራኤል ጭን ወይም ጉልበት ላይ ማስቀመጡ እስራኤል እንደራሱ ልጆች እንደተቀበላው የሚገልጽ ምልክት ነው:: ይህም ለልጆች የወራሽነት መብት ከያዕቆብ ያስገኛል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በግምባሩም ወደ ምድር አኈንብሶ ሰገደ
ዮሴፍ ለአባቱ ክብርን ለመስጠት ወደ ምድር አኈንበሶ ሰገደ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

ሚናሴንም በግራው በእስራኤል ቀኝ
እስራኤል ቀኝ እጁን በሚናሴ ላይ እንዲያደርግ ዮሴፍ ልጆቹን ያስቀምጣቸዋል ሚናሴ ታላቅ ወንድም ነው እናም ቀኝ እጅ ትልቅ በረከት የመቀበል ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 48:14

ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ
ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ማኖር እርሱ ትልቅ በረከት እንዲቀበል ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

እስራኤል ዮሴፍን ባረከው
ዮሴፍ ደግሞ ኤፍሬምንና ሚናሴን ይወክላል:: ዮሴፍ አባት ስለሆነ እርሱ ብቻውን ተጠቅሶአል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እግዚአብሔር
እግዚአብሔርን ማገልገል በእግዚአብሔር ፊት እንደመሄድ ተደርጐ ተነግሮአል አት አያቴ አብርሃምና አባቴ ይስሐቅ ያገለገሉት እግዚአብሔር (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እረኛ የሆነኝ
እረኛ በጐቹን እንደምንከባከብ እግዚአብሔር እስራኤልን ተንከባክቦታል አት እረኛ እንስሳትን እንደሚንከባከብ የተንከባከበኝ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

መልአክ
ተገቢ ትርጉሞች አት እግዚአብሔር ያዕቆብን ለመጠበቅ የላከውን መልአክ ያመለክታል 2 ይህ እግዚአብሔር ያዕቆብን ለመጠበቅ በመልአክ መልክ የተገለጸውን ያመለክታል

ጠበቀኝ
አዳነኝ

ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅ ስም በእነርሱ ይጠራ
እዚህ ስም ሰውን ይወክላል ስሜ በእነርሱ ይጠራ የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ከሌላ ሰው የተነሣ እንዲታወስ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከኤፍሬምና ሚናሴ የተነሣ ሰዎች አብርሃም ይስሐቅንና እኔን ያስታውሱ” (ምትክ ቃል : ፈሊጣዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በምድርም ላይ ይብዙ
እዚህ እነርሱ ኤፍሬምንና ሚናሴን ቢያመለክትም የእነርሱ ትውልድንም ይወክላል:: አት “በምድር ሁሉ ላይ የሚኖር ብዙ ትውልድ ይኑራቸው” (ምትክ ቃል እጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 48:17

ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድርግ
ቀኝ እጅ በኩር ወንድ ልጅ የሚያገኘው ትልቅ በረከት ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 48:19

እርሱ ደግሞ ሕዝብ ይሆናል ታላቅም ይሆናል
እዚህ እርሱ ሚናሴን ቢያመለክትም የእርሱን ትውልድ ይወክላል አት ታላቅ ልጅህ ብዙ ትውልድ ይኖረዋል እናም ታላቅ ሕዝብ ይሆናል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በዚያን ቀን በእነዚህ ቃላት
በዚያ ዕለት እንዲህ ብሎ

በእናንተ ስም እስራኤል እንዲህ ብሎ ይባርካል
የእስራኤልም ሰዎች ሌሎችን በሚባርኩበት ጊዜ በስማችሁ ይባርካሉ

በእናንተ ስም እንዲህ ብለው እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደሚናሴ ያድርጋችሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል ይህም እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “በእናንተ ስም እግዚአብሔር ሌሎችን ሰዎች እንደ ኤፍሬምና እንደ ሚናሴ እንዲያደርግ ይጠይቁታል” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እንደ ኤፍሬምና እንደ ሚናሴ
እስራኤል ኤፍሬምን አስቀድሞ መጥራቱ ኤፍሬም ከሚናሴ ታላቅ እንደሚሆን የሚገልጽ ነው

እስራኤል ኤፍሬምን ከሚናሴ አስቀድሞታል
ለኤፍሬም ትልቁን በረከት መስጠትና ኤፍሬም ከሚናሴ የተሻለ አድርጎ መውሰድ እስራኤል በአካል ኤፍሬምን ከሚናሴ በፊት እንዳስቀመጠው ተደርጐ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 48:21

ከእናንተ ጋር ይሆናል ወደ አባቶቻችሁም ምድር መልሶ ያገባችኋል
እዚህ “እናንተ” “የእናንተ” ብዙና የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ያመለክታል (“እናንተ” አጠቃቀም ይመልከቱ)

ከእናንተ ጋር ይሆናል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚረዳና እንደሚባረካቸው የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው አት እግዚአብሔር ይረዳችኋል ወይም እግዚአብሔር ይባርካችኋል (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ወደ አባቶቻችሁም ምድር
ወደ ዘራችሁም ወይም ትውልዳችሁም ምድር

ለአንተ ከወንድሞችህ አንድ እጅ አብልጬ ዐምባ ሰጠሁህ
ተገቢ ትርጉሞች 1 ከወንድሞቹ ይበልጥ ብዙ ክብርና ሥልጣን ለዮሴፍ መሰጠቱ እርሱ በአካል ከሌሎች የበላይ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “ለአንተ ከሌሎች ለሚትበልጠው የተራራውን ዐምባ ሰጠሁህ” ወይም 2)ያዕቆብ ለዮሴፍ ወንድሞች ከሚሰጠው መሬት በላይ ለዮሴፍ እንደሚሰጠው ይገልጻል:: አት “ለአንተ ለወንድሞችህ ከሰጠሁት በላይ ridge ሰጠሁህ የተራራውን ዐምባ ሰጠሁህ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለአንተ
እዚህ አንተ በነጠላ የተገለጸና ዮሴፍን ያመለክታል (አንተ አጠቃቀም ይመልከቱ)

በሰይፌና በቀስቴ ከአሞራዊያን እጅ የወሰድኳትን ዐምባ
እዚህ ሰይፍ እና ቀስት በጦርነት መዋጋትን ያመለክታሉ። አት “የተዋጋሁትና ከአሞራዊያን እጅ የወሰድሁት ምድር” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Chapter 49

1 ያዕቆብ ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “በአንድነት ተሰብሰቡና ወደፊት የሚገጥማችሁን ነገር ልንገራችሁ፣ 2 እናንተ የያዕቆብ ልጆች፣ በአንድነት
ተሰብስባችሁ ስሙ፣ አባታችሁ እስራኤል የሚነግራችሁንም አድምጡ። 3 ሮቤል፣ ኃይልና የጎልማሳነት ብርታት በነበረኝ ጊዜ የወለድሁህ የበኩር ልጄ ነህ።
ከልጆቼ ሁሉ በክብርና በኃይል የምትበልጥ አንተ ነህ። 4 ይሁን እንጂ እንደ ውሃ የምትዋልል ስለሆንህ የበላይ አለቅነት ለአንተ አይገባም፣ ምክያንቱም የአባትህን
መኝታ ደፍረሃል ምንጣፌንም አርክሰሃል። 5 “ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው፣ ዓመፅ ለመፈጸም የጦር መሣሪያዎቻቸውን ያነሳሉ። 6 ወደ ሸንጎአቸው
አልግባ፣ ጉባኤያቸው ውስጥ አልገኝ፣ በቁጣ ተነሣስተው ወንዶችን ገድለዋል፣ የበሬዎችንም ቋንጃ እንደፈለጉ ቆራርጠዋል። 7 እጅግ አስፈሪ የሆነ ቁጣቸው፣
ጭከና የተሞላ ንዴታቸው የተረገመ ይሁን፤ በያዕቆብ እበትናቸዋለሁ፣ በመላው እስራኤልም አሠራጫቸዋለሁ። 8 ይሁዳ ወንድሞችህ ያመሰግኑሃል፣ እጅህም
የጠላቶችህን አንገት አንቆ ይይዛል፣ የአባትህ ልጆች በፊትህ ተደፍተው ይስግዱልሃል። 9 ይሁዳ እንደ ደቦል አንበሳ ነው፣ ከዐደንህ የምትመለስ ልጄ፣ እንደ
አንበሳ ያደፍጣል በምድርም ላይ ይተኛል፤ እንደ እንስት እንበሳም ያደባል፣ ታዲያ ማን ሊቀሰቅሰው ይደፍራል? 10 በትረ መንግስሥት ከይሁዳ እጅ አይወጣም፤
የገዥነት ምርኩዝም ከእግሮቹ መካከል፣ ሕዝቦች ሁሉ የሚታዘዙለት ‘ሴሎ’ እስኪመጣ ድረስ፣ ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙለታል። 11 አህያውን በወይን ግንድ፣
ውርንጫውንም በምርጡ የወይን ሐረግ ቅርንጫፍ ላይ ያስራል፣ ልብሱን በወይን ጠጅ፣ መጎናጸፊያውንም በወይን ጭማቂ ያጥባል። 12 ዓይኖቹ ከወይን ጠጅ
የቀሉ፣ ጥርሶቹም ከወተት ይልቅ የነጡ ይሆናሉ። 13 ዛብሎን በባሕር ዳርቻ ይኖራል፣ የመርከቦቹ መጠጊያም ይሆናል፣ ወሰኑም እስከ ሲዶና ይደርሳል። 14
ይሳኮር፣ አጥንተ ብርቱ አህያ በጭነት መካከል የሚተኛ፣ ማረፊያ ቦታው መልካም፣ 15 ምድሪቱም አስደሳች መሆኗን ሲያይ፣ ትከሻውን ለሸክም ዝቅ ያደርጋል
ከባድ የጉልበት ሥራም ይሠራል። 16 ዳን ከእስራኤል ነገዶች እንደ አንዱ ሆኖ በራሱ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል። 17 ዳን የመንገድ ዳር እባብ፣ የመተላለፊያም
መንገድ እፉኝት ነው፤ ጋላቢው የኋሊት እንዲወድቅ፣ የፈረሱን ሰኮና ይነክሳል። 18 እግዚአብሔር ሆይ፣ ማዳንህን እጠባበቃለሁ። 19 ጋድን ወራሪዎች አደጋ
ይጥሉበታል፣ እርሱ ግን ዱካቸውን ተከታትሎ ብድሩን ይመልሳል። 20 አሴር ማዕደ ሰፊ ይሆናል፤ ለነገሥታትም የሚስማማ ምግብ ያቀርባል። 21 ነጻ
እንደተለቀቀች ሚዳቋ ነው፣ የሚያማምሩ ግልገሎች ይኖሩታል። 22 ዮሴፍ፤ ፍሬያማ የወይን ተክል፣ በምንጭ ዳር የተተከለ ወይን ነው። ሐረጎቹ ቅጥርን
ያለብሳሉ። 23 ቀስተኞች በብርቱ ያጠቁታል፤ በቀስታቸውም እየነደፉ ያሳድዱታል፤ 24 ነገር ግን በያዕቆብ ኃያል አምላክ ክንድ፣ እረኛም በሆነው በእስራኤል
አለት ቀስቱ ጸና ጠንካራ ክንዱም ቀልጣፋ ሆነ። 25 አንተን በሚረዳህ በአባትህ አምላክ፣ በሚባርክህ ሁሉን በሚችል አምላክ፣ ከላይ ከሰማይ በሚገኝ ረድኤት፣
ከምድር ጥልቅ በሚገኝ በረከት፣ ከማኅፀንና ከጡት በሚገኝ ምርቃት ይባርክሃል። 26 ከጥንት ተራሮች በረከት፣ ከዘላለም ኮረብቶች ምርቃት ይልቅ፣ የአባትይ
በረከት ይበልጣል፤ ይህ ሁሉ በዮሴፍ ራስ ላይ ይውረድ፤ በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነውም ግንባር ላይ ይረፍ። 27 ብንያም ነጣቂ ተኩላ ነው፤ ያደነውን
ማለዳ ይበላል፤ የማረከውን ማታ ያከፋፍላል። 28 እነዚህ ሁሉ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው። ይህም እያንዳንዳቸውን ተገቢ በሆነው በረከት አባታቸው
ሲባርካቸው የተናገረው ቃል ነው። 29 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ “እኔ የምሞትበትና ወደ ወገኖቼ የምሰበሰብበት ጊዜ ደርሶአል፤ ስለዚህ
በኬጢያዊው በኤፍሮን እርሻ ውስጥ ባለችው ዋሻ ከአባቶቼ ዘንድ ቅበሩኝ፤ 30 ይህንን በከነዓን ምድር በመምሬ አጠገብ በማክፌል እርሻ ውስጥ ያለውን ዋሻ
የመቃብር ቦታ እንዲሆን ከኬጢያዊው ኤፍሮን ላይ የገዛው አብርሃም ነው። 31 በዚያ አብርሃምና ሚስቱ ሣራ ተቀብረዋል፤ በዚያ ይስሐቅና ሚስቱ ርብቃ
ተቀብረዋል፤ እኔም ልያን የቀበርኋት እዚያው ነው፤ 32 እርሻውና ዋሻው የተገዙት ከኬጢያውያን ላይ ነው።” 33 ያዕቆብ እነዚህን ቃላት ለልጆቹ ተናግሮ እንዳበቃ
እግሮቹን በአልጋው ላይ ሰብስቦ የመጨረሻ ትንፋሹን ተንፍሶ ሞተ፣ ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ።

Genesis 49:1

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ያዕቆብ ልጆቹን የሚባርከውን መጨረሻውን በረከት የጀምራል:: ይህም እስከ ዘፍጥረት 49:27 ይቀጥላል የያዕቆብ ምርቃቶች በግጥም መልክ ተጽፈዋል (ሥነ ግጥሞችን ይመልከቱ)

እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ተሰብሰቡና ስሙ፤ አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ

ሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች ትኩረት ለመስጠት ተመሣሣይ ሃሳብ ይናገራሉ አት ወደ አባታችሁ ኑና በጥንቃቄ አድምጡ (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

እናንተ የያዕቆብ ልጆች አባታችሁን እስራኤልን አድምጡ

ያዕቆብ ራሱን እንደሶስተኛ ወገን ሰው ያቀርባል እንደአንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል አት ልጆች ሆይ እኔን አባታችሁን ስሙ (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አጠቃቀም ይመልከቱ)

Genesis 49:3

የበኩር ልጄ ኃይሌና የጉብዝናዬ መጀመሪያ

የበኩር ልጄ ኃይሌ የጉብዝናዬ መጀመሪያ የሚሉ ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ኃይል እና ጉብዝና የሚሉ ቃሎች የያዕቆብ ልጅ የመውለድ አቅሙን ያመለክታሉ በኩር እና መጀመሪያ የሚሉ ቃላት ሮቤል በኩር ልጁ እንደሆነ ይገልጻሉ (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

በክብር ትልቃለህ በኃይልም ትበልጣለህ

ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል አት በክብርና በኃይል የመጀመሪያ ትሆናለህ ወይም በክብርና በኃይል ማንኛውንም ሰው ትበልጣለህ

እንደ ውሃ የምትዋልል ነህ

ያዕቆብ ሮቤል ቁጣውን እንደማይችል ለማተኮር በከባድ ማዕበል እንደሚዋልል ውሃ አድርጐ ያቀርበዋልና እርሱ የተረጋጋ አይደለም (ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)

እልቅና አይኖርህም

በወንድሞችህ መካከል የመጀመሪያ ወይም አለቃ አትሆንም

ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና ከዚያም አርክሰሄዋል ወደ አልጋዬም ወጥተሃል

እዚህ መኝታና አልጋ የያዕቆብን ቁባት ባላን ያመለክታሉ ያዕቆብ ሮቤል ከባላ ጋር የተኛበትን ያመለክታል (ዘፍጥረት 35:22 ይመልከቱ) አት “ወደ አልጋዬ ስለወጣህና በቁባቴ ከባላ ጋር ስለተኛህ አዋርደህኛልና” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደ አባትህ አልጋ ወጥተሃል ወደ አልጋዬም ወጥተሃል

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

 generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 49:5

ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው
ይህ በትውልድ ወንድሞች መሆናቸውን አይገልጽም ያዕቆብ የሴኬም ሰዎችን ለመግደል አብረው መሥራታቸውን ለማተኮር ነው።

ሰይፎቻቸው የዐመጽ መሣሪያ ናቸው
ሰዎችን ለመጉዳትና ለመግደል ሰይፎቻቸውን ይጠቀማሉ

ነፍሴ .... ልቤ
ያዕቆብ ራሱን ለመግለጽ ነፍሴ እና ልቤ የሚሉ ቃሎችን ይጠቀማልና ክፉን ለማድረግ ከሚያቅዱት ጋር ባለመተባበሩ ሌሎች ሰዎችና እግዚአብሔርም ደግሞ እጅግ እንዳከበሩት ይናገራል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ወደ ሸንጐአቸው አልግባ
ጉባዔያቸው ውስጥ አልገኝ እነዚህ ሁለቱ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ያዕቆብ ሁለቱን በማገናኘት በክፉ እቅዳቸው እንደማይሳተፍ አበክሮ ይገልጻል አት ማንኛውንም እቅድ ለማዘጋጀት ከእነርሱ ጋር አልተባበርም (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

የቤሬዎችን ቋንጃ ቈራርጠዋል
ስምዖንና ለዊ ለዕይታ ብለው ቤሬዎችን አስነክሰዋል

ቋንጃ መቈረጥ ወይም ማስነከስ
ይህ የእንስሳትን ቋንጃ በመቁረጥ እንዳይራመዱ ማድረግ ነው

Genesis 49:7

ቁጣቸው ርጉም ይሁን ጽኑ ነበርና ንዴታቸው ጭከና የተሞላ ነበርና
እግዚአብሔር ስምዖንና ሌዊን የሚረግመው እግዚአብሔር ቁጣቸውንና ንዴታቸውን እንደሚረግም ተደርጐ የገልጾአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ቁጣቸው የተረገመ ይሁን
አብዛኛውን ጊዜ ነብይ ትንቢትን ሲናገር የሚናገረው ቃል እግዚአብሔር እንደሚናገር ይቆጠራል:: ይህም የሚናገረው ነበዩና እግዚአብሔር እንዴት እንደተቆራኙ ነው::

ንዴታቸው ጭከና የተሞላ ስለነበር
እረግማለሁ የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት ንዴታቸው ጭከናን የተሞላ ስለሆነ እረግማለሁ (የተደበቁትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እኔም በያዕቆብ እከፋፍላቸዋለሁ በእስራኤልም እበትናቸዋለሁ
“እኔ” እግዚአብሔርን ያመለክታል:: “እነርሱ” ስምዖንንና ለዊን ቢሆንም ምትክ ቃል ስለሆነ ለትውልዳቸውም ይሆናል:: “ያዕቆብ”ና “እስራኤል” ተወራራሽ ስሞችና የእስራእል ሕዝብ የሚተኩ ናቸው:: አት ትውልዳቸውን እበትናለሁ በእስራኤልም ሰዎች መካከል አሠራጫለሁ (ምትክ ቃላትና ተመሣሣይ ተነጻጻሪ አባባል ይመልከቱ)

Genesis 49:8

ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)

ያመሰግኑሃል፤ እጅህ
ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ለአንደኛው ምክንያት ነው ይህ “ስለ” ወይም “ምክንያቱም/የተነሣ” አገናኝ ቃላትን በመጠቀም ግልጽ ሊሆን ይችላል:: አት “ስለ እጅህ ያመሰግኑሃል” ወይም “ከእጅህ የተነሣ ያመሠግኑሃል” (አገናኝ ቃላት ይመልከቱ)

እጅህ በጠላቶችህ አንገት ላይ ነው
“ጠላቶችህን ታሸንፋለህ” የሚል አባባል ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ይሰግዳሉ
ለአንድ ሰው እጅ መንሣት ወይም አክብሮት በትህትና ለመግለጽ ጐንበስ ማለትን ይገልጻል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

Genesis 49:9

ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው
የአንበባ ደቦል እንደሆነ ስለ ይሁዳ ያዕቆብ ይናገራል:: ያዕቆብ የይሁዳን ጥንካሬ በአትኩሮት ይገልጻል:: አት “ይሁዳ እንደ አንበሳ ደቦል ነው” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ልጄ ሆይ ከአደንህ ወጣህ
“አንተ ልጄ ከአደንህ ተመለስህ”

እንደ እንስት አንበሳ
ያዕቆብ ይሁዳን ከእንስት አንበሳ ጋር ያነጻጽራል አት እንስት አንበሳ በአደን ቀዳማይና ቡድንዋን የሚትከላከል ነች (ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)

ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል?
ያዕቆብ ይሁዳ ለሌሎች ሰዎች ምንኛ አስፈሪ እንደሆነ ትኩረት ለመሰጠቅ ጥያቄ ይጠቀማል። አት “ማንም ሊቀሰቅሰው አይችልም” (አግናኝ ጥያቄ ይመልከቱ)

Genesis 49:10

በትሬ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል
በትርና ዘንግ ንጉሥ የሚይዛቸው ያገጡ ረጃጅም በትሮች ናቸው የሥልጣን አገዛዝ የሚተኩ ምልክቶች ናቸው እናም ይሁዳ የእርሱን ዘር ይወክላል:: አት “የአገዛዝ ሥልጣን ሁልጊዜም ለይሁዳ ዘር ይሆናል” (ምትክ ቃላትና ተመሣሣይ ተነጻጻሪ አባባል ይመልከቱ)

ገዥነት የሚገባው ወይም ሰሎ እስኪመጣ ድረስ
ተገቢ ትርጉሞች 1 ሰሎ ማለት ክብር ወይም አድናቆት ማለት ነው አት ሕዝቦች እስኪታዘዙለትና እስኪያከብሩት ድረስ ወይም 2 ሰሎ የሴሎ ከተማን ይወክላል አት ገዥ ወደ ሰሎ እስኪመጣና ሕዝቦች እስኪታዘዙለት ድረስ ብዙ ሰዎች እንደሚናገሩት ይህ ትንቢት ከዳዊት ዘር ስለሚመጣው መስህ ነው ዳዊት ከይሁዳ ዘር ነውና

ሕዝቦች ይታዘዙለታል
ሕዝቦች ሰዎችን ያመለክታሉ አት ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙለታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

Genesis 49:11

አህያውን ያስራል... በወይን ግንድ
ሁለቱም አረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የወይኑ ፍሬ ብዙ ስለሆነ አህያው ፍሬዎችን ቢበላ ጌታው እንደማይገደው ተደረጐ ተገልጾአል:: (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

የእርሱ ... እርሱ
የእርሱ ወይም እርሱ በተጠቀሱባቸው ሁሉ ተገቢ ትርጉማቸው 1 የይሁዳን ዘር ያመለክታሉ:: “የእነርሱ” “እነርሱ” ወይም 2) እነርሱ በዘፍጥረት 49:10 ምናልባት ሚናሴን የሚያመለክተውን ገዥ ያመለክታሉ::

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

ልበሱን ያጥባል... በወይን ጭማቂ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ይህም በጭማቂዎቻቸው ልብሶቻቸውን ማጠብ እንኳ የሚያስችል ብዙ ወይን ፍሬዎች ይኖራሉ ማለት ነው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አጠበ
አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት የሚፈጸሙ ትንብቶች እንደተፈጸመ ተደርጐ ይገለጻል ይህ በአትኩሮት የሚናገረው ክስተቱ በእርግጥ እንደሚፈጸም ነው አት እነርሱ ያጥባሉ ወይም እርሱ ያጥባል (ወደፊት አመላካች ኃላፊ ክስተት ይመልከቱ)

የወይን ደም ወይም ጭማቂ
የወይን ጭማቂን እንደ ወይን ደም ያቀርባል ይህም ጭማቂው ምንኛ ቀይ ቀለም እንዳለው ይገልጻል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዐይኖቹ እንደ ወይን የቀሉ
ይህ እንደ ቀይ ቀለም ወይን የሰውን ዐይን ቀለም ቅላት ያመለክታል:: ተገቢ አማራጭ ትርጉሞች እነሆ አት 1)ጥቁር ቀለም ያላቸው ዐይኖች ጤናማ ዐይኖች ናቸው ወይም 2) ብዙ የወይን ጠጅ ከመጠጣት የተነሣ የሰዎች ዐይኖች ይቀላሉ (ተመሣሣይ አባባል እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ጥርሶቹ ከወተት ይልቅ የነጡ
ይህ የሰውን ነጭ ጥርስ ከወተት ንጣት ጋር ያነጻጽራል። ይህም ወተትን የሚጠጡበት ብዙ የሚታለቡ ላሞች እንደሚኖሩ ነው (ተመሣሣይ አባባል እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 49:13

ዛብሎን በበሕር ዳር ይኖራል
ይህ የዛብሎንን ነገድ ያመለክታል:: የዛብሎት ነገድ ወይም ትውልድ በበሕር ዳር ይኖራል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እርሱም ወደብ ይሆናል
እዚህ እርሱ የዛብሎን ሰዎች የሚወርሱት ወይም የሚገነቡት የባሕር ዳር ከተሞችን ይወክላል እነዚህ የወደብ ከተሞች ለመረከበኞች መጠለያ ይሆናሉ (ምትክ ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደብ
በባህር ዳር ያለ መሬትና ለመርከቦች መቆሚያ ደኅንነት ያለው ቦታ ማለት ነው

Genesis 49:14

ይሳኮር አጥንተ ብርቱ አህያ ነው
ያዕቆብ ስለይሳኮርና ነገድ ወይም ትውልድ ሲናገር እንደ አህያ ይቆጥራቸዋል ይህም እጅግ የሚሠሩ እንደሚሆኑ በአትኩሮት ይገልጻል የይሳኮር ትውልድ እንደ አጥንተ ብርቱ አህያ ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ይሳኮርም
አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት የሚፈጸሙ ትንቢቶች እንደተፈጸመ ተደርጐ ይገለጻል ይህ በአትኩሮት የሚናገረው ክስተቱ በእርግጥ እንደሚፈጸም ነው ይህም በወደፊት ጊዜ ሊገለጽ ይችላል አት “ይሳኮር… ይሆናል” ወይም “የይሳኮር ትውልድ… ይሆናል” (ወደፊት አመላካች ኃላፊ ክስተት ይመልከቱ)

ይሳኮር ...ያያል... ይሆናል
እዚህ ይሳኮር ለነገዱ ምትክ ሆኖ የሚቆም ስም ነው አት “የይሳኮር ትውልዶች… ያያሉ …ይሆናሉ” (ምትክ ቃላት ይጠቀሙ)

በበጐች ጉሬኖ መካከል ያርፋል
ተገቢ ትርጉሞች 1 በጭነት መካከል ይተኛል ወይም 2 በሁለት በጐች አጥር መካከል ይተኛል ደግሞም በሌላ መንገድ ያዕቆብ ስለይሳኮር ልጆች እጅግ እንደሚሠሩና ከዚያም ለእረፍት እንደሚተኙ ይናገራል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

መልካም የእረፍት ቦታና የለማች ምድር
መልካም እረፍት የሚያገኙበት ቦታና የለማች ምድር

ትከሻውን ለሸክም ያመቻቻል
ትከሻውን ለሸክም ያመቻቻል ማለት ሸክምን በመሸከም እጅግ ይሠራል ማለት ነው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለሥራ ባሪያ ይሆናል
ለሌሎች እንደባሪያ ያገለግላል

Genesis 49:16

ዳን በወገኑ ይፈርዳል
እዚህ ዳን ነገዱን ይወክላል የዳን ልጆች በራሱ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ

የራሱ ሕዝብ
ተገቢ ትርጉሞች የራሱ ሕዝብ፤ 1) በዳን ሕዝብ 2) በእስራኤል ሕዝብ

ዳን የመንገድ ዳር እባብ ይሆናል
ያዕቆብ ስለዳንና የእርሱ ትውልድ እንደ እባብ አድርጐ ይናገራቸዋል እባብ ምንም ትንሽ ቢሆን መንገደኛውን ከፈረስ ላይ ማውረድ ይችላል እንዲሁ ዳን ትንሽ ነገድ ሲሆን በጠላቶቹ ላይ አደገኛ ነው አት የዳን ልጆች በመንገድ ዳር እንዳለ እባብ ናቸው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሆይ ማዳንህን እጠባበቃለሁ
ረቂቅ ስም “ማዳን” እንደ “መዳን” ሊተረጐም ይችላል። አት “እግዚአብሔር ሆይ እንዲታድነኝ እጠባብቃለሁ”

እኔ እጠባበቃለሁ
“እኔ” ያዕቆብን ያመለክታል

Genesis 49:19

ጋድ ...ይዘምቱበታል እርሱ ግን
ጋድ ትውልዱን ይወክላል:: አት “የጋድ ልጆች ..ይጠቃሉ ነገር ግን እነርሱ” (ምትክ ቃል ይጠቀሙ)

አሴር ማእደ ሰፊ ይሆናል ...እርሱም
አሴር የአሴር ልጆችን ይወክላል:: እት “የአሴር ልጆች ማእደ ሰፊ… እናም እነርሱ” ምትክ ቃል ይጠቀሙ

ንፍታሌም ...እርሱም
ንፍታሌም የንፍታሌምን ትውልድ ይወክላል:: አት “የንፍታሌም ልጆች.. እነርሱ… ይሆናሉ”

በተራሮች
ከዳን ልጆች በመሸሸ በተራራማው የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል

ምግቡ የተረከተ
እዚህ የበረከተ የሚለው ምግቡ ጣፋጭ ማለት ነው ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ

ንፍታለም ነጻ እንደተለቀቀች ሚዳቋ ነው
ያዕቆብ ስለንፍታሌም ልጆች ለመሮጥ እንደተለቀቀች እንደ እንስት ሚዳቋ እንደሆነ ይናገራል:: ይህም እነርሱ ፈጣን መልእክተኞች እንደሆኑ ነው:: አት “የንፍታሌም ዘሮች እንደተለቀቀች ሚዳቋ ይሆናሉ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

የሚያማምሩ ግልገሎች
ግልገሎች ትናንሽ የሚዳቋ ግልገሎች ናቸው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም ግልጽ አይደለም አንዳንድ ትርጉሞች መልካም ቃል ይሰጣል ወይም መልካም ነገር ይናገራል የሚለውን ተጠቅመዋል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:22

የዮሴፍ ፍሬያማ ዛፍ ነው
የዮሴፍ ትውልዱን/ዘሩን ይወክላል ያዕቆብ እነርሱን ብዙ ፍሬ እንደሚያፈራ የዛፍ ቅርንጫፍ አድርጎ ይናገራል:: አት "የዮሴፍ ዘር ፍሬያማ የዛፍ ቅርንጫፍ ነው"

የዛፍ ቅርንጫፍ
የዛፍ ዋና ቅርንጫፍ

ሐረጎቹ ቅጥርን ያለብሳሉ
ቅርንጫፎች አድገው ቅጥርን ማልበሳቸው እነዚያ በቅጥር ላይ እንደሚወጡ ተደርጎ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:24

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ዮሴፍንና ዘሩን መባረክ ይቀጥላል

ቀስቱ ጸና
ቀስቱን የያዘው ሰው መጽናቱ ቀስቱ ራሱ እንደጸና ተደርጎ ተግልጾአል ወደ ጠላቱ በሚያልምበት ጊዜ ቀስቱ እንደሚጸና ይገልጻል አት ወደ ጠላቱ በሚያልምበት ጊዜ ቀስቱን አጽንቶ ይይዛል (ምትክ ቃላት አጠቃቀም እና ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ቀስቱ....እጆቹ
እዚህ "እርሱ" ዘሩን የሚወክለውን ዮሴፍን ነው አት "ቀስቶቻቸውና እጆቻቸው" (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እጆቹ ቀልጣፋ ይሆናሉ
ቀስትን መያዝ የለመዱ እጆች ስለሆኑ ሙሉ ሰው እንደ እጆች ተገልጾአል:: (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ኃያል አምላክ እጆች
እጆች የእግዚአብሔርን ኃይል ይገልጻሉ:: አት "የሁሉን ቻይ አምላክ ኃይል" (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ከእረኛው ስም የተነሣ
እዚህ ስም ሙሉ ሰው ይወክላል አት ከእረኛው የተነሣ (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እረኛው
ያዕቆብ እግዚአብሔር እረኛ እንደሆነ ይናገራል አት ይህም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚመራና እንደሚጠብቅ ይናገራል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዐለት
ያዕቆብ እግዚአብሔር ሰዎች የሚወጡበትና ከጠላቶቻቸው የምድኑበት አለት እንደሆነ ይናገራል ይህ የሚያጐላው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚጠብቅ ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:25

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ዮሴፍንና ዘሩን መባረክ ይቀጥላል (ዘፍጥረት 49:22-23 ይመልከቱ)

አንተን በሚረዳህ ...በሚባርክህ
እዚህ "አንተ" ዘሩን የሚወክለውን ዮሴፍን ያመለክታል አት "የአንተን ዘር በሚረዳ ....በሚባርክህ" (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

በሰማይ በረከቶች
ሰማይ ተክልን ወይም ሰብልን የሚያሳድገው ዝናብን ይወክላል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

ከምድር ጥልቅ ከሚገኝ በረከት
ጥልቅ ለወንዞችና ለኩሬዎች የሚሆን ውሃ የሚወጣበትን ይወክላል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በጡትና በማህጸን በረከት
እዚህ ጡቶችና ማህጸን እናቶች የመውለድና ጡት የማጥባት አቅም ያመለክታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

Genesis 49:26

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ዮሴፍንና ልጆቹን መባረክ ይቀጥላል።

ከጥንት ተራሮች
የመሠረታዊው ቋንቋ ትርጉም ግልጽ አይደለም:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በጥንት ተራሮች ፈንታ ጥንት አባቶች ይጠቀማሉ::

እነርሱ በዮሴፍ ራስ ላይ ይሁኑ
እዚህ "እነርሱ" የአባቱ በረከቶች ናቸው::

በወንድሞች መካከል አለቃ በሆነው ራስ አናት ላይ
ያዕቆብ እነዚህ በረከቶች ልጆቹ እጅግ በበለጡት ላይ እንዲሆን ይሻል:: አት "እጅግ በበለጡ በዮሴፍ ልጆች ራስ አናት ላይ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነው
ከወንድሞቹ ዋና በሆነው

Genesis 49:27

ብንያም ነጣቂ ተኩላ ነው
ብንያም ዘሩን የሚወክል ምትክ ስም ነው:: ያዕቆብ የብያም ልጆችን እንደ ተራበ ተኩላ ይናገራል:: ይህም አጉልቶ የሚናገረው አጥቂ ተዋጊዎች እንደሆኑ ነው:: የብንያም ነገድ ሰዎች እንደተራቡ ተኩላ ናቸው:: (ምትክ ቃልና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 49:28

እነዚህ አሥራ ሁሉቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው
እነዚህም በዘፍጥረት 49: 1- 27 የተዘረዘሩትን ይመለከታል እያንዳንዱ ልጅ የነገድ አባት ሆኖአል።

በባረካቸው ጊዜ
እዚህ "ባረካቸው" የሚለው መደበኛ በረከቶችን እንደተናገረ ነው

እያንዳንዱን በተገቢ መንገድ ባረካቸው
ለእያንዳንዱ የሚገባውን በረከት ባረከ

መመሪያ ሰጣቸው
አዘዛቸው

ወደ ወገኖቼ የምሄድበት ጊዜ ደርሶአል
ይህ ለመሞት መድረሱን በትህትና የሚገለጸበት መንገድ ነው። አት “ለመሞት ቀርበአለሁ ወይም ልሞት ነኝ” (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ወደ ወገኖቼ የምሄድበት
ያዕቆብ በሚሞትበት ጊዜ የራሱ ውስጠኛው ሰው/ ነፍሱ ወደየት እንደሚሄድ ያመለክታል:: ከሞት በኋላ አብርሃምንና ይስሐቅን አንደሚገናኝ ይጠብቃል (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ኬጢያዊው ኤፍሮን
ይህ ወንድ ሰው ስም ነው። “ኬጢያዊ” የኬጥ ዘር ነው:: በዘፍጥረት 23:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ማክፌላ
የአንድ ቦታ ወይም ግዛት ስም ነው። በዘፍጥረት 23:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

መምሬ
ይህ የሔብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው:: ምናልባት መምሬ የተባለው የአብርሃም ወዳጅ ስም የተሰየመ ሳይሆን አይቀርም:: በዘፍጥረት 13:18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በዚያ የተገዛው
ግዥው ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “በዚያ አብርሃም የገዛውን” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከኬጥ ሰዎች
ከኬጢያዊያን

እነዚህን መመሪያዎች ለልጆች ተናግሮ እንዳበቃ
“ለልጆቹ መመሪያ መሰጠቱን እንዳበቃ” ወይም “ልጆቹን አዝዞ እንዳበቃ”

እግሮቹን በአልጋው ላይ ሰብስቦ
ያዕቆብ በአልጋው ላይ ተቀምጦ ነበር አሁን ግን ሊሞት መልሶ እግሮቹን በአልጋ ላይ የሰበሰባል

የመጨረሻ እስትንፋሱን ተነፈሰ/ሰጠ
ይህ አንድ ሰው መሞቱን ለዛ ባለ ቋንቋ የሚገለጽበት መንገድ ነው (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽን ይመልከቱ)

ወደ ወገኖቹ ተሰበሰበ
ያዕቆብ በሞተ ጊዜ ውስጠኛው ሰው ወይም ነፍሱ ከእርሱ በፊት የሞቱ ወገኖች ወደሄዱበት ቦታ ተሰብስቦአል (ንኀብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Genesis 49:31

አጠቃላይ መረጃ
ያዕቆብ ለልጆቹ መናገሩን ይቀጥላል

Chapter 50

1 ዮሴፍ እጅግ ከማዘኑ የተነሣ በአባቱ ፊት ተደፍቶ አለቀሰ ሳመውም። 2 ከዚያም የአባቱ የእስራኤል አስከሬን እንዳይፈርስ ባለ መድኃኒት የሆኑ አገለጋዮች
በመድኃኒት እንዲያሹት አዘዘ። ባለ መድኃኒቶቹም አስከሬኑ እንዳይፈርስ በመድኃኒት አሹት። 3 በአገሩ ልማድ መሠረት አስከሬኑ እንዳይፈርስ ማሸቱ አርባ ቀን
ወሰደባቸው፤ ገብፃውያንም ሰባ ቀን አለቀሱለት። 4 የለቅሶው ወራት በተፈጸመ ጊዜ ዮሴፍ የፈርዖንን ባለሥልጣኖች እንዲህ አላቸው፤ “መልካም ፈቃዳችሁ
ቢሆን እባካችሁ ለፈርዖን፣ 5 ‘አባቴ ለመሞት ሲቃረብ በከነዓን ምድር ባዘጋጀው መቃብር እንድቀብረው በመሐላ ቃል አስገብቶኛል፤ ስለዚህ ወደዚያ ሄጄ አባቴን
ቀብሬ እንድመለስ ይፈቀድልኝ ሲል ጠይቆአል’ ብላችሁ ንገሩልኝ” አላቸው። 6 ፈርዖንም፣ “ባስማለህ መሠረት ሄደህ አባትህን ቅበር” አለው። 7 ስለዚህ ዮሴፍ
አባቱን ለመቅበር ሄደ፣ የፈርዖን ሹማምንት በሙሉ፣ የቤተ መንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እንዲሁም የግብፅ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ሁሉ ተከተሉት። 8
እንደዚሁም የዮሴፍ ቤተ ሰቦች ወንድሞቹና ሌሎችም የአባቱ ቤተ ሰቦች ሁሉ ከዮሴር ጋር ሄዱ፣ በጌሤም የቀሩት ሕፃናት ልጆቻቸው፣ የበግ፣ የፍየልና የከብት
መንጋዎቻቸው ብቻ ነበሩ። 9 እንዲሁም ሠረገሎች፣ ፈረሰኞች አብረውት ወጡ፤ አጀቡም እጅግ ብዙ ነበር። 10 እነርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ካለው አጣድ
ከተባለው ዐውድማ ሲደርሱ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ምርር ብለው አለቀሱ፤ ዮሴፍም በዚያ ለአባቱ ሰባት ቀን ለቅሶ ተቀመጠ። 11 በዚያ የሚኖሩ ከነዓናውያን
በአጣድ ዐውድማ የተደረገውን ልቅሶ ባዩ ጊዜ፣ “ይህ ለግብፃውያን መራራ ልቅሶአቸው ነው” አሉ። በዮርዳኖስ አጠገብ ያለው የዚያ ቦታ ስም አቤል ምጽራይም
ተብሎ መጠራቱም ከዚሁ የተነሣ ነበር። 12 በዚህ ሁኔታ የያዕቆብ ልጆች አባታቸው እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ 13 አስከሬኑን ወደ ከነዓን ወስደው ከመምሬ
በስተምሥራቅ በምትገኘው በማክፌላ ዋሻ ቀበሩት፤ ይህም ዋሻ አብርሃም ለመቃብር ቦት እንዲሆን ከኬጢያዊው ከኤፍሮን በገዛው እርሻ ውስጥ የሚገኝ ነው።
14 ዮሴፍ አባቱን ከቀበረ በኋላ ከወንድሞቹና ለቀብር አጅበውት ከሄዱት ሰዎች ሁሉ ጋር ሆኖ ወደ ግብፅ ተመለሰ። 15 የዮሴፍ ወንድሞች ከአባታቸው ሞት
በኋላ፣ “ከፈጸምንበት በደል የተነሣ ዮሴፍ ቂም ይዞ በበቀልን ምን እናደርጋለን ተባባሉ። 16 ስለዚህ እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ፣ አባትህ ከመሞቱ በፊት፣
17 ‘ለዮሴፍ ወንድሞችህ በአንተ ላይ የፈጸሙትን ኃጢአትና ክፉ በደል ይቅር በላቸው’ ብላችሁ ንገሩት የሚል ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር። አሁንም የአባትህን
አምላክ አገልጋዮች ኃጢአት ይቅር በለን።” ዮሴፍ ይህን በሰማ ጊዜ አለቀሰ። 18 ከዚያም ወንድሞቹ መጡና በፊቱ ተደፍተው፣ “እኛ የአንተ አገልጋዮች ነን”
አሉት። 19 ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው፤ “አትፍሩ፣ እኔ በእግዚአብሔር ምትክ የተቀመጥሁ አይደለሁም፣ 20 እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት
ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው። 21 አሁንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻችሁ
የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላችኋለሁ” በማለት በመልካም ንግግር አረጋጋቸው። 22 ዮሴፍ ከአባቱ ቤተ ሰቦች ጋር በግብፅ ተቀመጠ፤ አንድ መቶ ዐሥር
ዓመትም ኖረ፤ 23 የኤፍሬምንም የልጅ ልጆች እስከ ሦስት ትውልድ ድረስ ዐየ። ከምናሴ የተወለደውንም የማኪርንም ልጆች በጭኑ ላይ አድርጎ አቀፋቸው። 24
ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ “እነሆ፣ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤ እናንተ ግን እግዚአብሔር በረድኤት ይጎበኛችኋል፤ ከዚህም አገር
አውጥቶ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ለመስጠት በመሐላ ቃል ወደገባላቸው ምድር ይመልሳችኋል። 25 እግዚአብሔር በሚጎበኛችሁና ወደዚያች ምድር
በሚመልሳችሁ ጊዜ ዐጽሜን ከዚህ ይዛችሁ የምትወጡ መሆናችሁን በማረጋገጥ ቃል ግቡልኝ” ብሎ አስማላቸው። 26 ዮሴፍም ዕድሜው መቶ ዐሥር ዓመት
ሲሞላው ሞተ፣ አስከሬኑንም መድኃኒት ቀብተው በሬሳ ሳጥን ካስገቡት በኋላ በግብፅ ምድር አስቀመጡት።

Genesis 50:1

በአባቱ ፊት ተደፍቶ
እዚህ ተደፍቶ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ተመስጦ ማለት ነው። አት “በአባቱ ላይ ተደፍቶ በሀዘን” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ባለመድኃኒት የሆኑ አገልጋዮቹ
አስከሬንን የሚያስተካክሉ አገልጋዮቹ

የአባቱን አስከሬን እንዲቀቡት
መቀባት ከቀብር በፊት አስከሬኑ እንዳይፈርስ የሚያቆዩበት ልዩ መንገድ ነው (ንኅብነት ወይም ለዛ ባለ መንገድ መግለጽን ይመልከቱ)

አርባ ቀን ወሰደባቸው
40 ቀናት ወሰደባቸው (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

ሰባ ቀናት
70 ቀናት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

Genesis 50:4

የሐዘኑ ጊዜ እንዳበቃ
“የማዘኑ ቀናት” ወይም “ለእርሱ የማልቀስ ቀናት”

ዮሴፍ ለፈርዖን ቤት ተናገረ
እዚህ የፈርዖን ቤት የፈርዖን ንጉሣዊ ፍርድ ቤት ወክል ባለሥልጣናት ያመለክታል ዮሴፍ ለፈርዖን ባለሥልጣናት ተናገረ (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

በፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሐረግ በአንድ ሰው ፊት ተቀባይነትን ማትረፍ የሚናገር ፈሊጣዊ አባባል ነው:: አት “በእናንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ ወይም በእኔ ደስተኞች ከሆናችሁ” (ፈሊጣዊ አባባልና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለፈርዖን እንዲህ ብላችሁ ንገሩልኝ ፤አባቴ አምሎኛል፤ እንዲህ ስል፤ እነሆ እኔ እሞታለሁ፤ በቆፈርሁትም መቃብር በከነዓን ምድር ከዚያ ቅበረኝ ። አሁንም ወጥቼ አባቴን ሊቅበርና ሊመለስ።
ይህ ሁለት ደረጃና ሶስት ደረጃ ጥቅስ ይዞአል እነዚህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጹ ይችላሉ:: አት “በከነዓን ምድር በቆፈረው መቃብር እንዲቀብረው አባቴ በሚሞትበት ጊዜ እንዳመለኝ ለፈርዖን ንገሩልኝ:: አባተን እንዲቀብረውና ከዚያም ተመልሸ እንዲመጣ ፈርዖንን ጠይቁልኝ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እኔ ልሞት ቀርበአለሁ
ሊሞት ነኝ

ልውጣ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው።

ፈርዖንም መለሰ
የመንግሥት ምክር ቤት አባላት ለፈርዖን ነገሩትና ከዚያም ፈርዖን ለዮሴፍ መለሰ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

አባትህ እንዳማለህ
ለእርሱ እንደማልህለት

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 50:7

ዮሴፍም... ወጣ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው።

የፈርዖን ሹማምንት በሙሉ የቤቱ ሽማግሌዎች/የቤተመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የግብጽ ምድር ከፍተኛ ባለሥልጣናት
የፈርዖን ከፍተኛ መሪዎች ሁሉ የቀብሩን ሥነሥርዓት ተካፈሉ (የሁኔቶች ሥርዓት ይመልከቱ)

የቤቱ ሽማግሌዎች
የፈሪዖን ቤተምንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ያመለክታል

ከግብጽ ምድር ፤የዮሴፍ ቤተ ሰዎች ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ ሰዎች
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት “የግብጽ ምድር ፤ እንዲሁም የዮሴፍ ቤተ ሰዎች ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ ሰዎች ከእርሱ ጋር አብረውት ሄዱ” (የሁኔቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

ሰረገላዎች
እዚህ በሠረገላዎች የተቀመጡ ሰዎችን ያመለክታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)

እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ
እጅግ ብዙ ሰዎች ጉባኤ ነበር

Genesis 50:10

እነርሱም በመጡ ጊዜ
“እነርሱ” የሚለው ቃል በቀብር ሥነሥርዓቱን ይካፈሉ የነበሩ ሰዎችን ያመለክታል

የአጣድ አውድማ
ተገቢ ትርጉሞች 1) “አጣድ” የሚለው ቃል እሾህ ማለት ነው፤ አናም እጅግ ብዙ እሾሆች የሚበቅሉበት መሬት ሊባል ይችላል ወይም 2) “የአውድማው ባለቤት ስም ሊሆን ሊችላል:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ከፍተኛና መራራ ለቅሶ አለቀሱ
እጅግ መራራና ከፍተኛ ልቅሶ አልቅሰው ነበር

ሰባት ቀን
7 ቀን (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

በአጣድ አውድማ
ተገቢ ትርጉሞች 1) አጣድ የተባለው ሰው አውድማ ውስጥ ወይም 2) አጣድ በተባለው አውድማ ውስጥ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ይህ ግብጻዊያን እጅግ ያዘኑበት ጊዜ ነበር
የግብጻዊያን ልቅሶ መራራ ነበር

አቤል ምጽራይም
ተርጓሚዎች የሚከተለውን እንደ ግርጌ ማስታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ አቤል ምጽራይም የሚለው ስም የግብጻዊያን ሐዘን ማለት ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 50:12

ልጆቹም
የያዕቆብ ልጆችም

ልክ እንዳዘዛቸው
ልክ መመሪያ እንደሰጣቸው

ልጆቹም ተሸክመውት
ልጆቹም አስከሬኑን ተሸክመውት

ማክፌላ
ማክፌላ የቦታ ወይም የግዛት ስም ነው በዘፍጥረት 23፡9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

መምሬ
የሒብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው በዚያ ይኖር በነበረው በአብርሃም ወዳጅ መምሬ ስም ሳትሰየም አትቀርም። በዘፍጥረት 13፡ 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ኬጢያዊው ኤፍሮን
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው ኬጢያዊ የኬጥ ዘር ነው በዘፍጥረት 23፡8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ወደ ግብጽ ዮሴፍ ተመለሰ
ዮሴፍ ወደ ግብጽ ተመለሰ

አብረውት የነበሩ ሁሉ
አብረውት የሄዱት ሁሉ

Genesis 50:15

ምናልባት ዮሴፍ ቂም ሊበቀለን ይሆናል
እዚህ ቂም ዮሴፍ በእጁ እንደምይዝ ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል አት ምናልባት ዮሴፍ የጠላን ይሆናል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ባደረግንበት ክፋት ሁሉ ብድራት ይመልስብን ይሆናል
እርሱን የበደለውን ሰው መበቀል አንድ ሰው ከሌላ ሰው የተበደረውን እንደመመለስ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “ባደረግንበት ክፋት ምናልባት ልበቀለን ይችላል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አባትህ ገና ሳይሞት እንዲህ ብሎ አዝዞአል ዮሴፍን እንዲህ በሉት እባክህ የወንድምችን በደል ኃጢአታቸውንም ይቅር በል እነርሱ በአንተ ከፍተውብሃልና
ይህ ሁለት ደረጃና ሶስት ደረጃ ጥቅስ ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስም ሊገለጹ ይችላሉ:: አት “አባትህ ከመሞቱ በፊት እኛ የበደልንህን ይቅር እንዲትለን እንድንነግርህ አዝዞናል” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

አባትህ ከመሞቱ በፊት አዝዞናል እንዲህ ስል
ያዕቆብ ለወንድማማቾች ሁሉ አባት ነው:: እዚህ ዮሴፍ አባቱ ለተናገረው ትኩረት እንዲሰጥ “አባትህ” ብለው ይናገራሉ:: አት “አባታችን ከመሞቱ በፊት”

በበደሉህ ጊዜ ያደረጉትን ኃጢአታቸውን
በአንተ ላይ ስላደረጉት ክፉ ነገሮች

አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው

የአባትህ አምላክ ባሪያዎች የበደሉህን ይቅር በል
ወንድሞቹ ራሳቸውን “የአባትህ አምላክ ባሪያዎች” ብለው ይገልጻሉ:: (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ዮሴፍ ይህን ስሉት አለቀሰ
የሴፍ ይህን መልእክት በሰማ ጊዜ አለቀሰ

generated on Mon Aug 7 15:32:41 2023

Genesis 50:18

በፊቱ ሰግደው
በፊቱ ወደ መሬት ጐንበስ በማለት ሰግደው፤ ይህ የትህትና እና ለዮሴፍ ክብርን የመስጠት ምልክት ነው። (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ ነኝን?
ዮሴፍ ወንድሞቹን ለማደፋፈር ጥያቄ ይጠቀማል:: አት "እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ አይደለሁም" ወይም "እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም" (አግናኝ ወይም ሽንገላ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

እናንተ ክፉ ነገር አስባችሁብኝ
እናንተ ክፉ ነገር አድርጋችሁብኝ

እግዚአብሔር ለመልካም አሰበው
እግዚአብሔር ለመልካም አደረገው

ስለዚህ አሁንም አተፍሩ
ስለዚህ እኔን አተፍሩ

እናንተንና ልጆቻችሁን እመግባችኋለሁ
ሁል ጊዜ እናንተና ልጆቻችሁ በቂ ምግብ እንዲኖራችሁ አረጋግጣለሁ

አጽናናቸውም ልባቸውን ደስ አሰኛቸው
እዚህ ልቦች ወንድሞቹን ያመለክታሉ:: አት "አጽናናቸውም ደስም አሰኛቸው" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

Genesis 50:22

መቶ አሥር ዓመት
110 ዓመት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)

የኤፍሬም ልጆች እስከ ሶስት ትውልድ
የኤፍሬም ልጆችና የልጅ ልጆች

ማኪር
ይህ የዮሴፍ ወንድ የልጅ ልጅ ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በዮሴፍ ጭን ላይ ተወለዱ
ይህ አባበል ዮሴፍ እነዚህን የማኪርን ልጆች የራሱ የልጅ ልጆች አድርጐ ተቀበላቸው ማለት ነው:: ይህም ዮሴፍን ለመውረስ ልዩ መብት አላቸው ማለት ነው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 50:24

በእርግጥ እናንተን ይጐበኛችኋል
በዘፍጥረት 50: 24./26 "እናንተ" የሚለው ቃል የዮሴፍን ወንድሞች ነገር ግን ደግሞ የእነርሱን ልጆች ያመለክታል፡: (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወደ ምድራችሁ ከዚህ ምድር ያወጣችኋል
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ "ወደ ላይ መውጣት" የሚለውን ቃለ መጠቀም የተለመደ ነው:: አት "ከዚህ ምድር ያወጣችኋል ወደ ምድራችሁ ይወስዳችኋል" (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)

110 ዓመታት
መቶ አሥር ዓመታት

እነርሱም በመድሃኒት ቀቡት
አንድን አስከሬን ከመቀበሩ በፊት እንዳይፈርስ ለማቆየት መድሃኒት መቀባት ልዩ የሆነ መንገድ ነበር በዘፍጥረት 50 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ኖረ ወይም ተቀመጠ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት "አኖሩት" (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በአስከሬን ሳጥን ውስጥ
"በሬሳ ሳጥን" ወይም "በሳጥን" ይህ ሳጥን የሞተ ሰው የሚቀመጥበት ነው::